**DSpace Institution**

**DSpace Repository** **http://dspace.org**

Ethiopian Languages and Literature - Amharic Thesis and Dissertations

2020-11-11

# þÿ M u ` C ª ó • ( f õ Í 5 % d ¨ « • þÿ è M « , - f “ u } u • ; -

þÿ Ø * • 5 ( 5

http://hdl.handle.net/123456789/11617

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) እና ሥነ-ጽሑፍ አማርኛ-ትምህርት ክፍል

# ፍላጎት *በቃል ኪዳን ረጅም* ልቦለድ ውስጥ፤ ከላካንያን የፍካሬ-ልቦና ትችት አንጻር

በ

ዘሪሁን አስረስ

ሐምሌ፣2012 ዓ.ም.

ባሕር ዳር

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) እና ሥነ-ጽሑፍ አማርኛ-ትምህርት ክፍል

# ፍላጎት *በቃል ኪዳን ረጅም* ልቦለድ ውስጥ፤ ከላካንያን የፍካሬ-ልቦና ትችት አንጻር

በ

ዘሪሁን አስረስ

ለአማርኛ ሥነ-ጽሑፍ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ መመረቂያ

ጥናታዊ ጽሑፍ

አማካሪ፡- አየነው ጓዱ (ዶ\ር)

ሐምሌ፣2012 ዓ.ም.

ባሕር ዳር

© ዘሪሁን አስረስ 2012 ዓ.ም.

**ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ**

**ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) እና ሥነ-ጽሑፍ አማርኛ-ትምህርት ክፍል**

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

እኛ ስማችን ከዚህ በታች የተዘረዘረው የፈተና ቦርድ አባላት ‹‹ፍላጎት *በቃል ኪዳን* ረጅም ልቦለድ ውስጥ፤ከLacanian የፍካሬ-ልቦና ትችት አንጻር›› የሚለውን መመረቂያ ጽሑፍ ፈትነን የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ መመረቂያ ጽሑፍ እንዲያሟላ የሚፈለገውን ያሟላ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ------------------------- | -------------------- | ----------------------- |
| የውጭ ፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
| ---------------------------- | ------------------------ | ------------------------- |
| የውስጥ ፈታኝ ስም | ፊርማ | ቀን |
| ---------------------------- | ------------------------ | ------------------------- |
| የፈተናው ሰብሳቢ ስም | ፊርማ | ቀን |

# ማረጋገጫ

ይህ ‹‹ፍላጎት በቃል ኪዳን ረጅም ልቦለድ ውስጥ፤ከላካንያን የፍካሬ-ልቦና ትችት አንጻር›› በሚል ርእስ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ሥነ-ጽሑፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል ለአማርኛ ሥነ-ጽሑፍ ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ መመረቂያ ጥናታዊ ጽሑፍ ሲሆን፣ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርሲቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም። ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸው መረጃዎችን በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ዘሪሁን አስረስ 17\11\2012 ዓ.ም ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ባሕር ዳር

**በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) እና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል**

**የጥናታዊ ጽሑፉ ማረጋገጫ ቅጽ**

ይህን ‹‹ፍላጎት *በቃል ኪዳን ረጅም* ልቦለድ ውስጥ፤ከ Lacanian የፍካሬ-ልቦና ትችት አንጻር›› የሚለውን የማስተርስ ዲግሪ መመረቂያ ጽሑፍ በደንቡ መሠረት እያነበብኩ መማከሬን እያረጋገጥኩ ለቃል ፈተና እንዲቀርብ ስምምነቴን እገልጻለሁ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ---------------------------------- | --------------------------- | ------------------------ |
| **የአማካሪው ስም** | **ፊርማ** | **ቀን** |
| ----------------------------- | --------------------------- | ------------------------ |
| **የትምህርት ክፍሉ ኃላፊ ስም** | **ፊርማ** | **ቀን** |

# ምስጋና

በመጀመሪያ ውጥኔ እንዲሳካ ላደረገልኝ ለልዑል እግዚኣብሔር ይክበር ይመስገን፡፡

አቀራረብዎ የጓደኛ እና የቤተሰብ ያህል ለሆነው ርእስ ከማጽደቅ ጀምሮ በጥናቱ ሒደት ከሚገባው በላይ ገንቢ የሆነ አስተያየት እና  እርማት ለሰጡኝ ለመምህሬ እና አማካሪዬ ዶ\ር አየነው ጓዱ ቅን መሆን ለራስ ነውና ቅንነትዎን ያብዛው፡፡ በእጅጉ አመሰግናለሁ፡፡ አባታዊ ምክርዎት ያልተለየኝ መምህሬ ዶ\ር አንተነህ አወቀ፣እንዲሁም ሁሉንም መምህሮቼን አመሰግናለሁ፡፡

ትምህርት ከመጀመሬ በፊት እና ትምህርት በጀመርኩ ጊዜ መጽሐፍትን እና አስፈላጊ የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶችን በሥጦታ ላበረከቱልኝ ዶ\ር ጎሩይ አብዱ፣በራስ ወጭ የሚያስፈልገኝን መጽሐፍ ለላኩልኝ እና በየጊዜው በመደወል ላተጉኝ ዶ\ር ደሳለኝ አምሳሉ፣ እንደ ልጅ ለራሴ ጉዳይ ለተላኩኝ እና ባገኙኝ ጊዜ ላበረታቱኝ ዶ\ር ያረጋል አለነ ከልብ የመነጨ ልዩ ምስጋናዬ ባላችሁበት ይድረስ፡፡

በብዙ ነገር ላገዛችሁኝ እና ከጎኔ የነበራችሁ መልካም ጓደኞቼን እጅግ አመሰግናለሁ፡፡ ለቤተሰቦቼ ምስጋናዬ ልዩ ነው፡፡ ዕድሜ እና ጤናውን አብዝቶ ይሰጥልኝ ዘንድ ልባዊ ምኞቴ ነው፡፡

# ማውጫ

*ይዘት* *ገጽ*

ምስጋና ........ i
ማውጫ ........ ii
አሕጽሮተ-ጥናት ........ iv
ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ ........ 1
1. 1. የጥናቱ ዳራ ........ 1
1. 2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ........ 3
1. 3. የምርምሩ ጥያቄዎች ........ 5
1. 4. የጥናቱ ዓላማዎች ........ 6
1. 5. የጥናቱ ፋይዳዎች ........ 6
1. 6. የጥናቱ ወሰን ........ 7
1. 7. የጥናቱ ሥነ-ዘዴዎች ........ 7
1. 7. 1. የአጠናን ዘዴዎች ........ 7
1. 7. 2. የልቦለድ የአመራረጥ መስፈርት ........ 7
1. 7. 3. የመረጃ መሠብሠቢያ ዘዴዎች ........ 8
1. 7. 4. የመረጃ አተናተን ሥልት እና ሒደት ........ 8
1. 8. የጥናቱ አደረጃጀት ........ 9
ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት ........ 10
2. 1. ንድፈ-ሐሳባዊ ክለሳ ........ 10
2. 1. 1. ሥነ-ጽሑፍ እና ፍካሬ-ልቦና ........ 10
2. 1. 2. ሥነ-ጽሑፍ እና የLacanian ፍካሬ-ልቦና (1901-1981 እ.ኤ.አ.) ........ 11
2. 1. 3. ቋንቋ እና ኢ-ንቁ ልቦና ........ 15
2. 1. 4. የLacanian የዲስኩር ብያኔ ........ 17
2. 1. 5. ፍላጎት ........ 18

2. 1. 6. የመስታወት ደረጃ (ባይተዋርነት) ........ 23
2. 1. 7. ፋለስ ........ 28
2. 1. 7. 1. ጁዊሶንስ ........ 32
2. 1. 7. 2. ፋሎ-ሴንተሪዝም ........ 33
2. 1. 7. 3. ሳይኮ-ፓቶሎጂ ........ 34
2. 2. የቀደምት ጥናቶች ክለሳ ........ 37
2. 2. 1. በአማርኛ ልቦለዶች ላይ የተሠሩ ጥናቶች ክለሳ ........ 37
2. 2. 2. በውጭ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች ላይ የተሠሩ ጥናቶች ክለሳ ........ 37
ምዕራፍ ሦስት፡- የፍላጎት ትንተና ........ 41
3. 1. ፍላጎት ........ 42
3. 2. የመስታወት ደረጃ (ባይተዋርነት) ........ 60
3. 3. ፋለስ ........ 76
ምዕራፍ አራት፡- ማጠቃለያ ........ 88
ዋቢ ጽሑፎች ........ 92
፩. ቀዳማይ ምንጮች ........ 92
፪. ካልዓይ ምንጮች ........ 92
አባሪ ፡- የልቦለዱ አጽመ-ታሪክ ........ 96

# አሕጽሮተ-ጥናት

*የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ርእስ ‹‹ፍላጎት በቃል ኪዳን ረጅም ልቦለድ ውስጥ፤ከLacanian የፍካሬ-ልቦና ትችት አንጻር›› የሚል ነው፡፡ የጥናቱ ዐብይ ዓላማ ‹‹በቃል ኪዳን›› ረጅም ልቦለድ ውስጥ የዋና ገጸ-ባህርያትን ፍላጎቶችን እና የፍላጎት ምንጮችን ማሳየት ነው፡፡ የጥናቱ ወሰን ደግሞ ‹‹በቃል-ኪዳን›› ረጅም ልቦለድ እና በLacanian, ‹‹ፍላጎት››፣ ‹‹የባይተዋርነት›› እና ‹‹ፋለስ›› የሚሉትን ጽንሰ-ሐሳቦች በመመርመር ላይ የተገደበ ነው፡፡ ይህ ጥናት የሥነ-ጽሑፋዊ ጥናት (ሂስ) ስለሆነ አይነታዊ የምርምር ዘዴን እና ቴክስታዊ የትንተና ሥልትን የተከተለ ነው፡፡ መረጃ ለመሠብሠብም ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ከመረጃ ትንተናው ዋና ዋና ግኝቶች መካከል የመጀመሪያው፣ ገጸ-ባህርያቱ ፍላጎታቸውን በሌላ እና **ሌ**ላ ሥልት ለማሟላት ሲጥሩ ታይቷል፡፡ ሁለተኛው፣የልቦለዱ ገጸ-ባህርያት ፍላጎታቸውን ለማሟላት በሚያደርጉት ጥረት የእኔ እንጂ የሌላው የሚለው ግድ ስለማይላቸው የ**ሌ**ላነት ስሜት ተንጸባርቆባቸዋል፡፡ ሦስተኛው፣የሴት ገጸ-ባህርያቶች ፍላጎት በማኅበረ-ባህላዊ ሕግ ተጽእኖ ሥር የወደቀ ነው፡፡ አራተኛው፣ የትንተና ውጤት በእውናዊ ሥርዓት ውስጥ የገጸ-ባህርያቱ ፍላጎት የተደናቀፈበትን ሁኔታ የሚያሣይ ነው፡፡ በመሆኑም ገጸ-ባህርያቱ ኢ-ንቁ ፍላጎት እጦታቸውን በጽሑፍ (ስንኝ በመቋጠር እና ደብዳቤ በመጻፍ)፣ በሕልም፣ በቅዠት፣ በቁጣ እና በስካር ለመግለጽ ሲጥሩ ይታያሉ፡፡ ቋንቋ የፍላጎት ማሟያ እና ለእጦት ምክንያት እንደሚሆን በትንተናው ታይቷል፡፡ በስድብ ቃላት ፋለስን መነጠቅ እንዳለም ትንተናው ያሣያል፡፡ የልቦለዱ ገጸ-ባህርያት የሚያሳዩት ኢ-ንቁ የሆነ የፍቅር፣የገንዘብ፣የሞት እና የበቀል ፍላጎት ለፍርሃት፣ለጭንቀት፣ለስጋት፣ለስቃይ እና ለእጦት እንደዳረጋቸው ትንተናው ያመላክታል፡፡ የተወሰኑት ዋና ዋና ገጸ-ባህርያት ለሚገጥማቸው ከባድ እጦት፣የአእምሮ ሕመም እንዲሁም ሞት ዋናው መንስኤም ሊሳኩ ያልቻሉት ኢ-ንቁ ፍላጎቶች ናቸው፡፡ ይህም የሰው ልጆች ፍላጎት በእጦት እና በስቃይ የተሞላ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡*

# ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ

በአገራችን ሥነ-ጽሑፋዊ ጥናት መቼ እንደተጀመረ በወጉ የሚያስረግጥ ማስረጃ ባይኖርም ከረጅም ዓመታት ጀምሮ በተለያዩ የውጭ እና ኢትዮጵያዊያን አጥኚዎች በተለያዩ ቋንቋዎች ተጠንቷል። ሆኖም የሥነ-ጽሑፍ ጥናት በቅርጽ፣በይዘት፣በዘመን፣በዘውግ ወ.ዘ.ተ የሚሉትን የዕድገት እርከኖች ተሻግሮ ንድፈ-ሐሳባዊ መሠረት ላይ ደርሷል።

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

በ20ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ የሥነ-ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ ዘመናዊ ቅርጽን ከያዙት የሥነ-ጽሑፋዊ የትችት አንጻሮች መካከል ፍካሬ-ልቦና በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል። የተለያዩ የዕድገት እርከኖችንም ተሻግሯል (Singh,1998,2)። Guerin,(1999)፣ደግሞ አብዛኞቹ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች የፍካሬ-ልቦናን ፈለግ ተከትለው የሚደረሱ እንደሆኑ ይገልጻሉ። ይህንም በዘመናዊ የፍካሬ-ልቦና መስክ አጉልተው በማሳየት ረገድ፣Sigmund Freud, C.G.Jung እና Jacques Lacan, በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ (ገጽ፣12)።

Barry, (2002)፣ እንደሚገልጹት፣Freud, (1856-1939)፣ ዘመናዊ ፍካሬ-ልቦናን ከሕክምና ሳይንስ ጋር በማዛመድ ለመጀመሪያ ጊዜ ግልጋሎት ላይ ያዋሉ ኦስትሪያዊ የፍካሬ-ልቦና ምሁር ናቸው። በበርካታ የፍካሬ-ልቦና ሥራቸውም የዘመናዊ ፍካሬ-ልቦና ‹‹አባት›› ለመባል በቅተዋል። ፍካሬ-ልቦናን ከጾታዊ ግንኙነት፣ከኢ-ንቁ ልቦና እና ከተጨቆኑ ፍላጎቶች እንዲሁም ከትእምርታዊነት አንጻር ይተነትናሉ (Barry,2002,96)። የአእምሮ መዋቅርን ‹‹ኢድ››፣ ‹‹ኢጎ›› እና ‹‹ሱፐር-ኢጎ›› በማለት በመከፋፈልም የመጀመሪያው ናቸው። እንዲሁም ‹‹ኢጎን ከንቁ››፣ ‹‹ሱፐር-ኢጎን ከከፊል-ንቁ››፣ ‹‹ኢድን ደግሞ ከኢ-ንቁ ልቦና›› ጋር ያዛምዳሉ። በ‹‹ሃፍረተ-ሥጋ ስለመቅናት›› (*Penis Envy*)፣(ለሴት ሕጻን) እና ‹‹ስለመኮላሸት ፍርሃት›› (ለወንድ ሕጻን) እንዲሁም ስለ *‹‹Dream work››*፣ ከ‹‹ኮንደንሴሽን›› እና ‹‹ዲስፕለስመንት›› ጋር በማያያዝ ያብራራሉ (Singh,1998,164,166-170)።

Freud, በታካሚዎቻቸው የሞከሩትን ፍካሬ-ልቦና፤ውስብስብ ከሆነው የኢ-ንቁ ልቦና መዋቅር ጋር በማስተሳሰር ሥነ-ጽሑፋዊ የትችት አንጻርን ገቢራዊ አድርገዋል። ለዚህም ምሣሌ የሚሆነው *‹‹Hamlet››* በተሰኘው የሼክስፒር ተውኔት መነሻነት ‹‹ኤዲፐስ ኮምፕሌክስን›› ከኢ-ንቁ የፍካሬ-ልቦና ትችት አንጻር ተንትነዋል (Guerin,1999,126,127)።

Jung, የፍሮይድን ‹‹Personal unconscious›› ባለመቀበል የራሱን ጽንሰ-ሐሳብ አቅርቧል፡፡ ፍካሬ-ልቡናን ከሃይማኖታዊ እና ከሚስቲካል ጋር በማዛመድ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎችን ‹‹the collective unconscious›› ጋር በማዛመድ ስለ ‹‹ኤሌክትራ ኮምፕሌክስ›› ትንታኔ ሰጥቷል (Singh, 1998,164,176,179)፡፡

Lacan, ፍካሬ-ልቡናን ከመዋቅራዊነት (Structuralism) እና ከድኅረ-መዋቅራዊነት (Post-Structuralism) ትችት ጋር በማቃየጥ ትችት ያካሄዱ ናቸው፡፡ የፍሮይድን ‹‹ኢድ››፣ ‹‹ኢጎ›› እና ‹‹ሱፐር-ኢጎን››፤‹‹ምናባዊ›› (the Imaginary)፣‹‹ትእምርታዊ›› (the Symbolic) እና ‹‹እውናዊ›› (the Real) ደረጃ\ሥርዓት እና ‹‹የመስታወት ደረጃ›› በማለት ርስ በርስ ተቆላላፊነት ባለው መልኩ ሰፊ አስተንትኖት ሰጥተዋል፡፡ የJakobson, *‹‹ሜታፈር›› እና ‹‹ሜታኖሚ››*፣ከFreud, *‹‹ኮንደንሴሽን›› እና ‹‹ዲስፕለስመንት››* ጋር በማጣመር፤እንዲሁም የSaussureን ‹‹ሲግኒፋየር እና ሲግኒፋይድ›› የተባሉ የሥነ-ልሳን መዋቅሮችን ከጥንድ ተቃርኖ፣ከመሠረታዊ ፍላጎት፣ከመጠየቅ፣ከፍላጎት እና ከእጦት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ይተነትናሉ፡፡ ስለቅድመ-ኤዲፐስ ኮምፕሌክስ፣ኤዲፐስ ኮምፕሌክስ፣ካስትሬሽን ኮምፕሌክስ እንዲሁም ስለፋለስ እና በፋለስ መቅናት የራሳቸውን ብያኔ ያቀርባሉ (Bailly,2009,11 ; Sarup,1999, 6-12)፡፡

Lacan, ‹‹ፍላጎት›› በቋንቋ እንደሚገለጽ እና ከእጦት ጋር እንደማይነጣጠሉ ያብራራሉ፡፡ ለዚህ ምሣሌ፡- እናት የልጅ ፍላጎቷን ለማሟላት ስታረግዝ ያለፈውን ሁሉ በመተው **ሌ**ላ ትሆናለች፡፡ ጽንሱ ግን እጦት በሌለበት የማሕጸን (*Womb*)፣ዓለም ውስጥ ይኖራል፡፡ እንደተወለደም የማሕጸን ኑሮ ማንነቱን ማጣት የሚጀምር ሲሆን፣በእናቱ ዘንድ ደግሞ በሕጻኑ ጾታ (ወንድ\ ሴት) መሆን ሳይቀር እጦትን ታስተናግዳለች፡፡ ሕጻኑ ቋንቋ እስከሚችል ድረስም የምታሳልፈው ስቃይ ብዙ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በሥነ-ጽሑፍ ሥራዎችም ገጸ-ባህርያት ሲቀረጹ ጀምሮ ፍላጎት እና እጦት የሚስተዋልባቸው ሲሆን፣በፍላጎታቸው መጽናት እና ቀድሞ እጦትን አምኖ መቀበል በገጸ-ባህርያቱ በራስ የመተማመን ስሜት ይወሰናል፡፡ የእጦት ግዛቱ የመስታወት ደረጃ ሲሆን፣ይህ መሠረተ ሐሳብ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ለሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች የእንደወረደ ሥልት ማደግ አስተዋጽኦ አበርክቷል (Sarup,1999,13-16; 20-22)፡፡

የLacanian, ፍካሬ-ልቡና ትችት መሠረቱ ቋንቋ ሲሆን፣ሆሄያትን በትንሹ እና በትልቁ በመጻፍ የትርጓሜ ልዩነት እንዳለ ይገልጻሉ፡፡ ለዚህም ምሣሌ፡- መሠረታዊ ፍላጎት (*need\Need*)፣

*መጠየቅ* (*demand\Demand*)፣ ፍላጎት(*desire*| *Desire*)፣እጦት(*lack*\ *Lack*)፣ **ሲግኒፋየር**፡-(ከሲግኒፋይድ ለመለየት እና በብዙ አቅጣጫ ትርጓሜ ሊሰጥ እንደሚችል ለማመላከት ነው)፣ **ሌላ****ሌላ** (*other*|*Other*) ወ.ዘተ. ተጠቃሾች ናቸው፡፡ **ሌላ** (*other*)፣ **ሌላ** (*Other*) መካከል የትርጉም እና የንባብ ልዩነት አላቸው፡፡ ‹‹**ሌላ**››፣‹‹**ሌ**›› በትንሹ ሆሄ ሲጻፍ ምናባዊ *ሥርዓትን* ይወክላል፡፡ ‹‹**ሌላ**››፣ ‹‹**ሌ**›› በትልቁ ሆሄ ሲጻፍ ደግሞ ፍጹም ሌላን (ትእምርታዊ) *ሥርዓትን* ይወክላል (Bailly,2009,11-13)፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ምናባዊ *ሥርዓትን* የሚወክለው ‹‹**ሌላ**››፣‹‹**ሌ**›› ሆሄ (በ12 ፎንት) በማድመቅ የተጻፈ ሲሆን፤ትእምርታዊ *ሥርዓትን* የሚወክለው ‹‹**ሌላ**››፣‹‹**ሌ**›› ሆሄ ደግሞ (በ14 ፎንት) በማድመቅ ተጽፎ ይገኛል፡፡

ሆኖም የLacanian, የትችት አንጻርን በአገራችን *ሥነ-ጽሑፋዊ* ጥናት በማናበቢያነት በመጠቀም ረገድ ውስንነት ይታያል፡፡ እንዲሁም *ቃል ኪዳን* የጌታቸው አያልቁ ረጅም ልቦለድ ሲሆን፣ ስድስት ጊዜ (በ1982 ‹‹3 ጊዜ››፣በ1997፣በ2002 እና በ2006 ዓ.ም) የታተመ ልቦለድ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በLacanian, የፍካሬ-ልቦና ትችት ማናበቢያነት የጌታቸው አያልቁ *(ቃል ኪዳን* [1982]፣2006 ዓ.ም.) ረጅም ልቦለድ ውስጥ የዋና ገጸ-ባህርያትን ፍላጎቶችን እና የፍላጎት ምንጮችን ለመተንተን እና ለመፈከር መሞከር ነው፡፡ ለዚህ ጥናት አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶችም ቀጥሎ ባለው ርእስ ሥር ቀርበዋል፡፡

## 1. 2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ይህን ጥናት ለመከወን ያነሳሱኝ ምክንያቶች አራት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት፡- በአማርኛ እና በውጭ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች ላይ የተሠሩ ቀደምት ጥናቶች ያላቸውን የሂስ ክፍተት ለመሙላት የራሱን ሚና ይጫወታል በሚል፤ሁለት የሁለተኛ ዲግሪ እና አንድ የሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች፣እንዲሁም አምስት በውጭ ቋንቋ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች የተካሄዱ ጥናቶች ተዳሰዋል፡፡ የመጀመሪያው፡- በቴዎድሮስ አለበል (2006 ዓ.ም.) *‹‹ልጅነት በማሕሌት እና በአለንጋና ምስር፤ሥነ-ልቦናዊ ንባብ››* በሚል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተጠና ነው፡፡ ሁለተኛው፡- በሰብለ ወልደኪዳን (2009 ዓ.ም.*) ‹‹የእኔነት ሐተታ በተመረጡ የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች››* በሚል ርእስ የተካሄደ የሦስተኛ ዲግሪ ጥናት ነው፡፡ ሦስተኛ፡- በኢዩኤል እንደሻው (2010 ዓ.ም.) *‹‹ድብቅ ባህርያት እና የተጨቆኑ ፍላጎቶች ሥነ-ልቦናዊ ንባብ በቅበላ»* በሚል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተጠና ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የቴዎድሮስ አለበል (2006) ጥናት የልጅነት ጭብጥን ከErikson, ከFreud እና ከLacan, የንድፈ-ሐሳብ ማዕቀፎች አንጻር የተነተነ ቢሆንም፡- በመፈከሪያ ሐሳብ እና ይዞት በተነሳው ዋና ዓላማ ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡ ሰብለ ወልደኪዳን (2009) የLacanian, ፍካሬ-ልቦናን በመፈከሪያነት የተጠቀመች ቢሆንም፡- በመጽሐፍ ምርጫ ይዛው በተነሳችው ዋና ዓላማ እና በሚተነተኑ ሐሳቦች ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡ የኢዩኤል (2010) ጥናት ደግሞ መፈከሪያ ንድፈ-ሐሳቡ ፍካሬ-ልቦና ቢሆንም በFreudian, የፍካሬ-ልቦና ትንታኔ ማተኮሩ እና ይዞት በተነሳው ዋና ዓላማ ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡

የLacan, et al., (1977) ጥናታዊ ጽሑፍ ትኩረቱ ‹‹*Hamlet*›› በተሰኘው የሼክስፒር ተውኔት ፍላጎት እና ፍላጎት እንዴት እንደተተረጎመ ትንታኔ ሰጥተዋል፡፡ የVanheule, and Paul, (2009) ጥናታዊ ጽሑፍ ትኩረቱ Freudian, Lacanian, እና Fonagy and Target, (*attachment theory*) ስለማንነት በሚያነሷቸው ጥያቄዎች እና በሚሰጧቸው መልሶች ዙርያ የሚያተኩር ነው፡፡ የGokariksel, and Secor, (2014) ጥናታዊ ጽሑፍ በLacan, (1972) መነሻነት በፍላጎት እና በቱርክ የአለባበስ ፋሽን እና ስታይል ዙርያ የሚያተኩር ነው፡፡ የGardiner, (2014) የማስተርስ ጥናታዊ ጽሑፍ ፍላጎት እና ፋንታዚ ከሌላ ጋር ያለውን ግንኙነት ከሲኒማ ጋር ማያያዙ ከዚህ ጥናት ይለየዋል፡፡ የKomorowski, (2017) በQuin Ann, ሥራዎች ላይ በማተኮር ተጠንቷል፡፡ ዓላማውም ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ነው፡፡ ከላይ የተገለጹት ጥናቶች ጠቅለል ተደርገው ሲወሰዱ በአንድ በኩል ስለፍላጎት ሲጠቅሱ፣በሌላ መልኩ ደግሞ የትኩረት ክፍተት እንዳለ ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከፍላጎት ላይ በማተኮር ክፍተትን ለመሙላት የራሱ የሆነ ሚና ይጫወታል ተብሎ ይታመናል፡፡

ሁለተኛው ምክንያት፡- በአማርኛ ከተገኙት መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው በLacanian, የትችት አንጻር የተጠኑ ጥናቶች ጥቂት ናቸው፡፡ ይህም የLacanian,የትችት አንጻርን በአገራችን ሥነ-ጽሑፋዊ ጥናት በማናበቢያነት በመጠቀም ረገድ ብዙ ያልተሰራበት እንደሆነ አመላካች ነው፡፡ በዚህም ሳቢያ የLacanian, ፍካሬ-ልቦና ትችት ውስብስብነቱ እንጂ ለአገራችን ሥነ-ጽሑፋዊ ትችት ያለው ፋይዳው በወጉ ታውቋል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ለዚህም በተጨማሪነት ሦስት ዓለም-አቀፋዊ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ (Bailly,2009,1)፡፡ አንደኛው፣ የLacanian,ንድፈ-ሐሳባዊ ማዕቀፎች የተዋቀሩት ንግግርን ሲያስተምሩ ከሠበሠቧቸው መረጃዎች በመነሳት ስለሆነ ወደ ንግግር ያመዘኑ መሆናቸው፤ሁለተኛው፣የLacanian, የፍካሬ-ልቦና ትችት አራማጆች ማነስ እና ጠንካራ ስሜት እና ፍላጎት አለመኖር፤ሦስተኛው፣በቃላት

ትርጓሜ ላይ በመፈላሰፍ ንድፈ-ሐሳቡን ውስብስብ እና ግልጽነት እንዲጎድለው ያደርጋሉ የሚሉት ናቸው (Bailly, 2009,1-3)።

ሦስተኛው ምክንያት፡- ‹‹ፍላጎት ከወቅታዊ፣ማህበራዊ፣ባህላዊ፣ታሪካዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ሥነ-ልቦናዊ እና ወ.ዘ.ተ ሁኔታዎች አንጻር ማህበረሰብን እና ጥቅል እንቅስቃሴን ለመረዳት የሚያስችል በመሆኑ መጠናት አለበት በሚል ሐሳብ መነሻነት፤

አራተኛው ምክንያት ደግሞ ልቦለዱን በማነብበት ጊዜ የልቦለዱ ገጸ-ባህርያት በፍላጎት የተሞሉ መሆናቸው፣ፍላጎታቸውን ከመስታወት ጋር ማያያዝ፣መገለል፣ፍርሃት፣የአእምሮ ሕመም፣ ማጣት፣በፍላጎታቸው ላይ ቋንቋ ተጽእኖ የሚያሳድርባቸው ገጸ-ባህርያት መቀረጻቸው እና ሲሰቃዩ የሚስተዋሉ መሆናቸው ነው። እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ ከLacanian, የፍካሬ-ልቦና ትችት አንጻር አንድምታ ስላላቸው፣‹‹ፍላጎት *በቃል ኪዳን* ረጅም ልቦለድ ውስጥ፤ከLacanian, የፍካሬ-ልቦና ትችት አንጻር በሚል ርእስ ለማጥናት ያነሳሱኝ ምክንያቶች ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱትን የጥናት ክፍተቶችን እና ሂሳዊ እና ንድፈ-ሐሳባዊ ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ ይህን ጥናት ለማከናወን የሚረዱ የምርምር ጥያቄዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

## 1. 3. የምርምሩ ጥያቄዎች

ምርምሩ የሚመልሰው ዐብይ ጥያቄ *ቃል ኪዳን* (2006 ዓ.ም.) በተሰኘው የጌታቸው አያልቄ ረጅም ልቦለድ ውስጥ የዋና ገጸ-ባህርያት ፍላጐቶች እና የፍላጐት ምንጮች ምንድን ናቸው? የሚል ነው። ምርምሩ የሚመልሳቸው ንኡሳን ጥያቄዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) በተመረጠው ረጅም ልቦለድ ውስጥ ገጸ-ባህርያቱ በፍላጎታቸው ምክንያት የሚደርስባቸው ፍርሃት እና ስጋት፣በደል እና ስቃዮች ምን ምን ናቸው? እንዴትስ ቀርበዋል?

ለ) በረጅም ልቦለዱ ውስጥ **ሌላ** *(other)* እና **ሌላ** *(Other)* እንዴት ባለ ሁኔታ ቀርበዋል?

ሐ) በዚሁ ረጅም ልቦለድ ውስጥ በገጸ-ባህርያቱ ፍላጎት ላይ ቋንቋ የሚያሳድረው ተጽእኖ ምንድን ነው?

መ) በገጸ-ባህርያቱ ዘንድ ምናባዊ፣ትእምርታዊ እና እውናዊ ሥርዓቶች በምን መልኩ ቀርበዋል?

ሠ) በልቦለዱ ውስጥ የገጸ-ባህርያቱ እጦቶች ምን ምን ናቸው? ምንስ ተጽእኖ አሳደሩባቸው?

## 1. 4. የጥናቱ ዓላማዎች

የጥናቱ ዋና ዓላማ *በቃል ኪዳን* ረጅም ልቦለድ ውስጥ የዋና ገጸ-ባህርያትን ፍላጐቶችን እና የፍላጐት ምንጮችን ከLacanian, ንድፈ-ሐሳብ አንጻር ማሳየት ነው፡፡ የጥናቱ ንኡሳን ዓላማዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው ፡-

ሀ) በተመረጠው ረጅም ልቦለድ ውስጥ ገጸ-ባህርያቱ በፍላጎታቸው ምክንያት የሚደርስባቸው ፍርሃት እና ስጋት፣በደል እና ስቃዮች ምን ምን እንደሆኑ መተንተን፤

ለ) *በረጅም* ልቦለዱ ውስጥ **ሌላ** *(other)* እና **ሌላ** *(Other)* እንዴት ባለ ሁኔታ እንደቀረቡ መተንተን፤

ሐ) በዚሁ ረጅም ልቦለድ ውስጥ በገጸ-ባህርያቱ ፍላጎት ላይ ቋንቋ የሚያሳድረው ተጽእኖ ምን ምን እንደሆነ መተንተን፤

መ) በገጸ-ባህርያቱ ዘንድ ምናባዊ፣ትእምርታዊ እና እውናዊ ሥርዓቶች በምን መልኩ እንደቀረቡ መተንተን፤

ሠ) በልቦለዱ ውስጥ የገጸ-ባህርያቱን እጦቶች በመለየት፣ምን ምን ተጽእኖ እንዳሳደሩባቸው መተንተን እና ፍካሬ መስጠት የሚሉት ናቸው፡፡

## 1. 5. የጥናቱ ፋይዳዎች

ይህ ጥናት ሥነ-ጽሑፋዊ እንደመሆኑ መጠን፣በዋናነት ለሥነ-ጽሑፍ ተማሪዎች ፋይዳ ያለው ሲሆን፣ለትያትር እና ለፊልም ተማሪዎችም የሚጠቅም ይሆናል፡፡ ሆኖም በአገራችን ሥነ-ጽሑፋዊ ጥናት የLacanian, የትችት አንጻርን በማናበቢያነት በመጠቀም ረገድ ውስንነት የሚስተዋል በመሆኑ በዘርፉ ያለውን ክፍተት በመሙላት ረገድ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ሥነ-ጽሑፍ የማሕበረሰብ ነጸብራቅ እንደመሆኑ መጠን የሰው ልጆች ፍላጎታቸውን ለማሟላት የሚያደርጉትን ጥረት እና የሚያጋጥሟቸውን እንቅፋቶች በሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ እንዴት እንደቀረቡ? እና በምን መልኩ የማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ሥነ-ልቦናዊ እና ወ.ዘ.ተ አካል እንደሚሆኑ የሚያስገነዝብ ይሆናል፡፡ ጥልቅ አንባቢያን የሆኑ የሥነ-ጽሑፍ ተማሪዎች ረጅም ልቦለዱን በተለያየ እይታ እንዲያነቡት ሊያግዝ ይችላል፡፡ ከዚህም ባሻገር ለማስተማሪያ በግብዓትነት ያገለግል ይሆናል፡፡ እንዲሁም ፍላጎት እና እጦት በቋንቋ እንዴት እንደሚገለጹ እና የLacanian, የፍካሬ-ልቦና ትችት ከሥነ-ጽሑፍ እና ከቋንቋ ጋር ስላለው ጥብቅ ቁርኝት

ግንዛቤ እንዲያገኙበት ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ከዚሁ ርእስ ጋር በተዛመደ ወደፊት ለሚካሄዱ ጥናቶች መንደርደሪያ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 1. 6. የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ ዐብይ ዓላማ *በቃል ኪዳን* (2006 ዓ.ም.) በተሰኘው የጌታቸው አያልቄ ረጅም ልቦለድ ውስጥ የዋና ገጸ-ባህርያትን ፍላጐቶችን እና የፍላጎት ምንጮችን ከLacanian, ንድፈ-ሐሳብ አንጻር ማሳየት ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት የሚወሰነው *‹‹በቃል ኪዳን››* ረጅም ልቦለድ እና ለፍላጎት ሰፊ አስተንትኖት በሚሰጡት የLacanian, ‹‹ፍላጎት››፣‹‹የመስታወት ደረጃ (የባይተዋርነት)›› እና ‹‹ፋለስ (ጁዊሶንስ፣ፋሎ-ሴንተሪዝም እና ሳይኮ-ፓቶሎጂ)›› የሚሉትን ጽንሰ-ሐሳቦች በመመርመር ላይ የተገደበ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት በLacanian, የፍካሬ-ልቦና ትችት ቢያተኩርም ‹‹Lacanian›› የሚለው የሌሎችም የLacan, ሂስ አራማጆች ጥቅል መጠሪያ በመሆኑ ሥነ-ጾታ እና Lacan, እንዲሁም ዲ-ኮንስትራክት፣ትችት ጋር የተቆራኙ ጉዳዮችን አይመለከትም፡፡

## 1. 7. የጥናቱ ሥነ-ዘዴ

በዚህ ንኡስ ርእስ ሥር የአጠናን ዘዴዎች፣የልቦለድ አመራረጥ መስፈርት፣የመረጃ መሠብሠቢያ ዘዴዎች እና የመረጃ መተንተኛ ዘዴ እና ሒደት ተብራርተዋል፡፡

### 1. 7. 1. የአጠናን ዘዴዎች

Lewis and Ritchie, (2003,2) እንደሚያስገነዝቡት፡- አይነታዊ የምርምር ዘዴ የሰርክ እንቅስቃሴን እና የሰው ልጆችን ተለዋዋጭ ባህርይ የሚያሣይ ነው፡፡ ስለዚህ የሥነ-ጽሑፋዊ ትችት በመሆኑ የገጸ-ባህርያት የሰርክ ተግባር የሆነውን ፍላጎት ለመተንተን እና ለመተርጎም አይነታዊ የምርምር ዘዴን ከቴክስታዊ የትንተና ሥልት ጋር በማስተሳሰር አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

### 1. 7. 2. የልቦለዱ የአመራረጥ መስፈርት

የሥነ-ጽሑፋዊ ትችት ኮርስ I ፣(የፍካሬ-ልቦና ትችት)፣ኮርስን ስማር Lacanian, ከFreudian, የፍካሬ-ልቦና ትችት ስለሚለይባቸው ምናባዊ፣ትእምርታዊ እና እውናዊ ሥርዓቶች፣ስለፍላጎት፣ ስለመስታወት ደረጃ፣ስለቋንቋ እና Lacanian, ወ.ዘ.ተ ከተሰጠው ጥቅል ማብራሪያ ያገኘሁትን

ግንዛቤ ከአላማ-ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ጋር በማገናዘብ ቀደም ሲል ያነበብኩትን *ቃል ኪዳን ረጅም* ልቦለድን የመረጥኩ ሲሆን፤*ቃል ኪዳን* ልቦለድን ለጥናት የመረጥኩበት ምክንያትም በአነሳሽ ምክንያት አራት ላይ ከተገለጸው ጋር የሚገናዘብ ነው፡፡ *በቃል ኪዳን ረጅም* ልቦለድ ውስጥ የተቀረጹ ዋና ገጸ-ባህርያት ፍላጎቶች እና የፍላጎት ምንጮች ምን ምን እንደሆኑ በLacanian,የፍካሬ-ልቦና ትችት ማናበቢያነት ማሳየትን ዓላማው ያደረገ ጥናት ነው፡፡

## 1. 7. 3. የመረጃ መሠብሠቢያ ዘዴዎች

በዚህ ጥናት ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ተዳሰዋል፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ የሚጠናው ልቦለድ ሲሆን፣ፍላጎት፣ባይተዋርነት እና ፋለስ ከተባሉ የLacanian, ጽንሰ-ሐሳቦች ጋር ተዛምዶ ያላቸውን ሐሳቦች ነቅሶ በማውጣ ይቀርባል፡፡ ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ ከመረጃ መረብ (ኢንተርኔት) እና በቤተ መጽሐፍት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ መጽሔቶች፣ መጽሐፍቶች እና ቀደምት ጥናቶች ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ሲሆኑ፣ከእነዚህም የLacanian, የፍካሬ-ልቦና ትችት ገለጻዎች ተገኝተዋል፡፡

## 1. 7. 4. የመረጃ አተናተን ሥልት እና ሒደት

የዚህ ጥናት ዓላማ ከላይ የተጠቀሱትን ዘዴዎች በመጠቀም *በቃል ኪዳን ረጅም* ልቦለድ ውስጥ የዋና ገጸ-ባህርያትን ፍላጎቶችን እና የፍላጎት ምንጮችን መተንተን ነው፡፡ በመሆኑም ለመተንተን እና ለመተርጎም ይመች ዘንድ የLacanian, የፍላጎት ትንተናዎችን በሦስት የጽንሰ-ሐሳብ አርእስት ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡ ማለትም፡- ‹‹የፍላጎት ትንተና››፣‹‹የመስታወት ደረጃ (የባይተዋርነት) ትንተና›› እና ‹‹የፋለስ ትንተና›› በሚሉ ጽንሰ-ሐሳቦች የተከፋፈለ ሲሆን ጁዊሶንስ፣ፋሎ-ሴንተሪዝም እና ሳይኮ-ፓቶሎጂ የሚሉ ጭብጦችን ደግሞ ነጣጥሎ ከማየት ይልቅ እንደ አስፈላጊነቱ በፋለስ ትንተና ውስጥ ተካተው ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በመሆኑም የተመረጡትን ዓበይት ጽንሰ-ሐሳቦች አጉልቶ ለማሳየት ይረዳ ዘንድ የሚከተሉትን የትንተና ሒደቶች ይከተላል፡፡

የጥናቱ ትንተና የሚጀምረው የዋና ገጸ-ባህርያትን ግላዊ ባህርይ፣ድርጊት(ቶች)፣ያለፈ የሕይወት ልምድ፣የልጅነት ልምድ እና ቤተሰብ፣ዝንባሌዎች፣ምኞት(ቶች)፣ የሚወዷቸውን እና የሚጠሏቸውን ነገሮች፣ሕልሞችን\ቅዠት፣የጾታዊ ግንኙነት ሁኔታ፣የቋንቋ አጠቃቀም፣ቁጣ፣ ቀልዶች፣ፍርሃት እና ስጋት ወ.ዘ.ተ. ግምት ውስጥ በማስገባት ቁልፍ የሆኑትን የገጸ-ባህርያቱ

ኢ-ንቁ ፍልጎቶችን እና እጦቶችን የሚያሳዩ ጥቅሶችን ከልቦለዱ መርጦ በመውሰድ ይተነተናሉ፡፡ ቀጥሎም ኢ-ንቁ ከሆነው የፍካሬ-ልቦና መነሻነት ጋር በማዛመድ፣በአይነታዊ የምርምር ዘዴ እና በቴክስታዊ የትንተና ሥልት በመመርኮዝ የተለዩ ያልተሟሉ ኢ-ንቁ ፍላጎቶችን በየጽንሰ-ሐሳቦቹ ርእስ ሥር ይተረጎማሉ፡፡ በመጨረሻም የማጠቃለያ ሐሳብ በመሰንዘር ጥናቱ ይደመደማል፡፡

## 1. 8. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት አራት ምዕራፎች አሉት፡፡ ምዕራፍ አንድ፡- የጥናቱ መግቢያ ሲሆን የጥናቱን ዳራ፣ የጥናቱን አነሳሽ ምክንያቶች፣የምርምር ጥያቄዎችን፣የጥናቱን ዓላማዎች፣ የጥናቱን ፋይዳዎች፣ የጥናቱን ገደብ እና የጥናቱን ሥነ-ዘዴ ያካተተ ነው፡፡

ምዕራፍ ሁለት ስለ Lacanian, የፍካሬ-ልቦና ትችት የንድፈ-ሐሳብ ክለሳ እና ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የቀደምት ጥናቶች ተከልሰዋል፡፡ ምዕራፍ ሦስት ትንተና ሲሆን፣የጥናቱ ዋና ጉዳይ ከሆነው ‹‹የፍላጎት›› ጽንሰ-ሐሳብ አንጻር ከLacanian, የትችት አንጻር ‹‹ፍላጎት››፣ ‹‹የመስታወት ደረጃ (ባይተዋርነት)›› እና ‹‹ፋለስ›› ከሚሉት ጽንሰ-ሐሳቦች አንጻር ትንተና እና ፍካሬ ተደርጓል፡፡ በምዕራፍ አራት ደግሞ የጥናቱ ማጠቃለያ\መደምደሚያ ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት

ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት የተካሄደበት ሲሆን ወደ ሁለት ንኡሳን ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ንኡስ ክፍል የንድፈ-ሐሳባዊ ጽሑፍ ክለሳ ሲሆን፣የLacanian, የፍካሬ-ልቦና ትችት ገለጻ ማለትም፡- ሥነ-ጽሑፍ እና ፍካሬ-ልቦና፣ሥነ-ጽሑፍ እና Lacanian, ቋንቋ እና ኢ-ንቁ ልቦና፣የLacanian, የዲስኩር ብያኔ፣እንዲሁም ‹‹ፍላጎት››፣ ‹‹የመስታወት ደረጃ (ባይተዋርነት)›› እና ‹‹ፋለስ (ጁዊሶንስ፣ፋሎ-ሴንተሪዝም እና ሳይኮ-ፓቶሎጂ)›› የሚሉት ርእሶች (ጭብጦች) ክለሳ የቀረበበት ነው፡፡

በሁለተኛው ንኡስ ክፍል ደግሞ ከዚሁ ጥናት ጋር ቀረቤታ ያላቸው የቀደምት ጥናቶች ክለሳ የተካሄደበት ሲሆን፣ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ‹‹በአማርኛ ረጅም ልቦለዶች ላይ የተሠሩ ጥናቶች ክለሳ እና በውጭ ቋንቋ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች ላይ የተሠሩ ጥናቶች ክለሳ›› በሚሉ ርእሶች ተከፍሎ የተካሄደ ሂሳዊ ክለሳ የቀረበበት ነው፡፡

## 2. 1. የንድፈ-ሐሳባዊ ጽሑፍ ክለሳ

### 2. 1. 1. *ሥነ-ጽሑፍ* እና ፍካሬ-ልቦና

የ*ሥነ-ጽሑፍ* እና የፍካሬ-ልቦና ቁርኝት አያሌ ዘመናትን ያስቆጠረ ነው፡፡ Aristotle, ትራጀዲያዊ የሆኑ የ*ሥነ-ጽሑፍ ሥራዎችን* በማስተዋወቅ፤አሳዛኝ ገጽታዎችን እና መጥፎ ስሜትን በመጻፍ፣በመናገር፣በማዜም ስሜትን መግለጽ መቻልን *‹‹Catharsis››* ይሉታል፡፡ ይህም *‹‹Hamlet››* በተሰኘው የሸክስፒር ድራማ (ተውኔት) በጉልህ ተስተውሏል፡፡ የገጸ-ባህርያት በመጥፎ፣ በአስጨናቂ እና በአጣብቂኝ ስሜት ውስጥ መሠንቀር የፍካሬ-ልቦና ጣጣን አመላካች ነው (Childs and Fowler, 2006,190)፡፡ ‹‹የ*ሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች* የእየ-ደራሲዎች የምናባዊ ፈጠራ ውጤት ናቸው፡፡ የራሱን ሥልት ተከትሎ በመጻፍ የገሃዱን ዓለም እና የሕይወትን ልዩ ልዩ ገጽታዎች ያሳያል፡፡ መልዕክቱን የመገንዘብ ችሎታም በአንባቢያን የፍካሬ-ልቦና የልዕልና ደረጃ የሚወሰን ይሆናል›› (Childs and Fowler, 2006,191)፡፡

ፍካሬ-ልቦና እና ሥነ-ጽሑፍ ከሰው ልጅ ሕይወት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ሲሆኑ፣የሰውን ባህርይ፣ሐሳብ እና ተነሳሽነት መግለጫ መንገዶች ናቸው፡፡ ፍካሬ-ልቦና ‹‹የሰውን ልጅ ባህርይ የሚያጠና ሳይንስ ነው›› (Kartono,1980,94)፡፡ ‹‹የፍካሬ-ልቦና ትችት ሠፊ ትርጓሜ ያለው ሲሆን፣ ውጫዊውን ዓለም ከውስጣዊው ሐሳብ እና ስሜት ጋር በማዛነቅ የሰው ልጆችን ባህርይ

ሳይንሳዊ በሆነ ዘዴ የሚያጠና ነው›› (Wortman et al.,1999, 4)፡፡ ፍካሬ-ልቦና በሰው ልጆች የኑሮ መርሆ ላይ ገቢራዊ የሚሆኑ ሁነቶችን መርምሮ ለማግኘትና ለማብራራት ይጠቅማል፡፡ የፍካሬ-ልቦና ትችት ‹‹ስሜታዊ እና ፍካሬ-ልቦናዊ እውነታን ከሥነ-ጽሑፍ ሥራው ጋር በማቃየጥ ውስብስብ በሆነ መልኩ የሚገልጽ ነው›› (Wellek and Warren,1977, 92-93)::

የድኅረ-Freudian, ፍካሬ-ልቦና ትችት ዕድገት በደመ-ነብሳዊ እና በማኅበረ-ታሪካዊ ለውጥ ላይ የሚመሠረቱ ሲሆኑ ለLacanian, የፍካሬ-ልቦና ትችት ማኅበረ-ባህላዊ ይዘት እና ቋንቋ ዋልታዎቹ ናቸው፡፡ የፍካሬ-ልቦና ሥነ-ጽሑፋዊ ትችት በየጊዜው ከተለያዩ የዕውቀት መስኮች ጋር ተቃይጧል፡፡ ከእነዚህም መካከል መዋቅራዊነት እና ድኅረ-መዋቅራዊነት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ለዚህም Lacan, ቀዳሚው ናቸው፡፡ Lacan,Levi-Strauss የተባሉት አንትሮፖሎጂስት እሳቤን ከሥነ-ልሳን እና ከሕክምና ጋር በማቀናጀት ትንታኔ ሰጥተዋል (Childs and Fowler., 2006 ,192-194)፡፡

## 2. 1. 2. ሥነ-ጽሑፍ እና Lacanian (1901-1981 እ.ኤ.አ.)

Lacan, ‹‹በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሁለተኛው አጋማሽ ብቅ ያሉ የፍካሬ-ልቦና ትችትን ከፍልስፍና፣ከሒሳብ፣ከሥነ-ልሳን፣ከሥነ-ጽሑፍ፣ከሕክምና እና *ከSur-realism,* (የLacan የሕክምና ጥናት) ጋር በማጣመር የተነተኑ የፈረንሳይ ምሁር ናቸው›› (Bailly, 2009,16-21; Bowie,1990, 101)

Lacan, የኢ-ንቁ መዋቅር እንደ ቋንቋ ነው ይላሉ፡፡ ገጸ-ባህርያት ያለፈን ዘመን ችግራቸውን ከመናገር ይቆጠባሉ፡፡ የመጽሐፍት የትረካ ፍሰት ኢ-ንቁ የሆነው እጦት በሕልም፣በትረካ፣ በምላስ ወለምታ *(slips of the tongue*)፣በቀልድ፣በአካላዊ\ገጽታ ምልክቶች እና በበሽታ ገሃድ የመውጣት ውጤት ነው›› (Rawson and Nisbet, 2008,175)፡፡

Lacan, ‹‹ልቦና ቴክስት ነው፤ቴክስትም ልቦና ነው›› *(psyche as text-text as psyche)* (Rawson and Nisbet, 2008,185)፡፡ ያልተቋጨ እና ረቂቅ ‹‹የራስ›› ትዕይንት በእኔ ሐሳብ ላይ ስቃይ የሚፈጥረው ለምንድን ነው? እንዴትስ ከዚህ ስቃይ መላቀቅ ይቻላል? ሲግኒፋይድ + ሲግኒፋየር=ሲግኒፊኬሽን ሲሆን ውጤቱም የቴክስት ‹‹እጦት›› *(Lack*) ነው (Rawson and Nisbet, 2008,186)፡፡ እንደ Lacanian,ትችት ቴክስት የፋለስ ፍላጎት እና እጦት ውጤት ሲሆን የቴክስት የመጨረሻ ውጤት ውድቀት እንደሆነም ይገልጻሉ፡፡ የፋለስ እጦት በሃይማኖታዊ አስተምህሮ የጸና እና በአባት ሥም የሚከለከል (አይነኬ) የሆነ እና አፍራሽ

ድርጊት የማይስተዋልበት ነው። የእኔነት ሐሳብ ርዕዮተ ዓለም እና ቁስ ጋር ግንኙነት አለው የሚሉት ደግሞ Althusser, ናቸው (Rawson and Nisbet, 2008,187)። ‹‹ሥነ-ጽሑፍ ከድኅረ-መዋቅራዊያን ትችት አንጻር በልቦና ውቅር ይመሠረታል። የቴክስቱን መዋቅር በወጉ ለመረዳት እና ተግባቦት ለመፍጠር ደጋግሞ ማንበብን ይጠይቃል›› (ዝኒ ከማሁ፣2008፣188)። ‹‹አንባቢያን ደጋግመው በማንበባቸው ውስብስብ የሆነውን ይገነዘባሉ። እጦትን የመሙላት ዕውቀትም ይኖራቸዋል። የLacanian, ትኩረት በትረካው መዋቅር እና በድምጾች ላይ በመሆኑ በአንባብያን እና በመጽሐፉ በኩል ጠቃሚ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል›› (Bertens, 2001 ,163)።

Tyson, (2006) የLacanian, የፍካሬ-ልቦና ትችት ከሦስቱ የልቦና ውቅሮች ጋር በማጋመድ አጠያቂ ትንታኔ ይሰጣሉ። የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች በLacan, እይታ የቴክስቱን መዋቅር ከምናባዊ፣ከትእምርታዊ እና ከእውናዊ ሥርዓቶች ጋር በማዛመድ በጥልቀት መመርመርን ይጠይቃል። የገጸ-ባህርያቱ ሁኔታ በትረካው ውስጥ ምናባዊ ሥርዓት በምን መልኩ ይሿል? ምናባዊ በሆነው ጉዳይ ውስጥ ራስን በማስገባትስ የግል ሕይወትን እና ዓለምን *በፋንታዚ* መተካት ይቻላልን? የገጸ-ባህርያቱን ባህርይ እና የትረካውን ፍሰት ከማሕበረሰቡ እሴት፣ባህል፣ ርዕዮተ-ዓለም ጋር በማስተሳሰር እንዴት መቆጣጠር ይቻላል? ቴክስቱ እንዴት እውነታን ይወክላል? በማለት ታጠይቅ እና አስተንትኖት ትሰጣለች (ገጽ፣33)።

Lacan, የጾታዊ ልዩነትን ለማመላከት የሳሏቸው ሁለቱ በሮች የሕጻኑ ወደ ትእምርታዊ ግዛት መሸጋገርን አመላካች ናቸው። በመግቢያ በር ላይ የሴት እና የወንድ ተብሎ በቋንቋ መለየት ከፋለስ ጋር ግንኙነት የለውም ማለት አይደለም። በወንድ ውስጥ ሴት በሴት ውስጥ ወንድ አለና። ከአንዱ ሌላው ሊገባም ይችላል። ፋለስ ቋሚ ማዕከል የሌለው ሚናው ያልተገደበ እና መቋጫ አልባ ነው። የሁለቱም ቦታ የት ነው? የምልዑነት ሕብረት ‹‹እጦት›› (lack) እና ‹‹እጦት›› (Lack)፤ተደራሽ ያልሆነው እኔ በቋንቋ ይቃረናል። የእኔ እጦት ከሥነ-ፍጥረት ይልቅ ከቋንቋ ሐሳብ እና ትርጓሜ ጋር ቁርኝት ያለው ነው። እጦት በሁለቱም ጾታ የሚስተዋል ሲሆን ምናባዊ ዓለምን በእጦት ማጀብ ለፈጠራ ሥራ ኪናዊነትን ያጎናጽፋል (Lacan,1977, 284; Rawson and Nisbet, 2008, 86)።

Saussure, (1857-1913) በቅደም-ተከተል ዛፍ *(T-R-E-E)* የሚለው ድምጽ ሲጠራ በአእምሯችን ብዙ ምሥል እንደሚቀረጸው ሁሉ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎችን ስናነብም የተለያየ ምሥል በአእምሮ ይከትማል። ‹‹የሥነ-ጽሑፍ ሥራው ሲጀምር ለነገሮቹ የነበረው ምልክት

በመቋጫው ሌላ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንም Derrida, ‹‹*differance and different*›› ይሉታል›› (Klarer, M.,1999, 85, 87)፡፡ *ሜታፈር* ከልዩ ልዩ ነገሮች ጋር የሚቆራኝ ሲሆን፣ *ሜታኖሚ* አንድ ሐሳብ (ቁስ) ከሌላ ጋር የሚተሳሰርበት ነው (Wolfreys et al., 2006, 65)፡፡ ለዚህም ፍቅርን ከቀይ አበባ *(My love is a red, red rose)*፣በማነጻጸር ምሣሌ ይሰጣሉ ነው (Klarer, M.,1999,138)፡፡ በሌላ መልኩ Klarer, M.(1999)፣*Imago (Picture)*፣የላቲን ቃል ሲሆን ትኩረቱን በቋንቋ ላይ በማድረግ ጥልቅ ምሥል የሚፈጥር ነው ይላሉ (ገጽ፣137)፡፡

እንደወረደ *(stream of consciousness)*፣የትረካውን ፍሰት የሚያስቀጥሉ ገጸ-ባህርያት ከሚመለከቱት ነገር በመነሳት የውስጥ ስሜታቸውን በቋንቋ የሚገልጹበት ነው፡፡ ከሚያወጡት ቃል እና ከሁኔታቸው በመነሳትም ገጸ-ባህርያቱ የገቡበትን ሁኔታ ማወቅ ይቻላል፡፡ ደራሲው መቼቱን እና ሐሳቡን ለሥነ-ጽሑፍ ሥራው ኪናዊነትን በሚያጎናጽፍ መልኩ ትእምርታዊ ቅርጽ አስይዞ ይቀርጻል፡፡ ሥምምነቶችን፣ባህላዊ፣ማሕበረሰባዊ ወይም ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በአርትፊሻል ዘዴ ይገልጻል፡፡ የእኔነት ስሜት አጻፋም በአንባቢያን ይስተዋላል፡፡ የሚቀረጹ ገጸ-ባህሪያት በእጦት የታጀቡ በመሆናቸው በንቃት ይፈልጋሉ፡፡ የፍላጎቶቻቸው ኃይልም በአባዊ ቁጥጥር ሥር የወደቀ ነው፡፡ በትኩረት መመልከት (*gaze*) ማሕበራዊ ውቅር ነው፡፡ የመስታወት ደረጃ (1977) ሕጻኑ ራሱን የሚያይበት ሁኔታ ሲሆን ገጸ-ባህርያቶች በአለባበስ፣ በአጋጊያጥ፣በውበት፣በገጽታ፣በአካላዊ ሁኔታ፣በፍላጎት፣በርእይ እና በሌላም ራሳቸውን የሚያዩበት ሁኔታ በኢ-ንቁ መዋቅር ይወሰናል፡፡ የገጸ-ባህርያቱ የእይታ ውስንነትም ከሚታየው በስተጀርባ ካለው እውነታ ያፋታቸዋል፡፡ እያለ የለም፤የሌለውን ደግሞ እንዳለ የሚያምኑ ገጸ-ባህርያት ለርስ በርስ የሕይወት ፍልሚያ ይዳረጋሉ፡፡ ይህም ለጥላቻ እና ለውድቀት ይዳርጋቸዋል፡፡ ለሚያጋጥሟቸው ችግሮችም ከሦስቱ የልቦና ውቅሮች ማለትም፡- (*ምናባዊ፣ ትእምርታዊ፣ እውናዊ)* ጋር በማቀናጀት መፍትሔ ይሰጣሉ (Wolfreys et al., 2001, 94, 96,102,105)፡፡

የመሠረታዊ ፍላጎት እጦት እሳቤ በሰው ልጆች ልቦና የሚከሰት ልምድ እና እጦት ሲሆን፣ ኢ-ንቁ የሆነው የፍላጎት ተግባር በንቁ የማንነት ዲስኩር ይንጸባረቃል (Lacan,1977a,191)፡፡ ማንነት መጨረሻ የሌለው ሕሊናን እረፍት የሚነሳ ጽንሰ-ሐሳብ ሲሆን ገጸ-ባህርያት ማንነታቸውን ለማግኘት ሲማስኑ ከሌሎች ገጸ-ባህርያት ጋር የከረረ ፍጥጫ ውስጥ የሚገቡ ሲሆን ይህም ‹‹የግጭት ሥርዓት›› *(Confilicting Order)* ይባላል፡፡ ሕይወት በፍላጎት የተሞላ እና ከራስ ጋር ትግል የሚደረግበት በመሆኑ ከግጭት (ከፍላጎት) ጋር እንኖራለን፡፡ በሌላ

ግጭት ካለ ፍላጎት፣ፍላጎት ካለ ግጭት ይኖራል፡፡ በመሆኑም ግጭት የፍላጎት ምንጭ ይሆናል (Lacan,1988b,210)፡፡ በልፋታቸው ልክ ካልተሳካላቸውም ራሳቸውን ከእድለ-ቢስነት ጎራ ያሰልፋሉ፡፡ የተጣባቸውን የተስፋ ቆራጭነት ስሜት በቋንቋ ገሃድ የሚያወጡ ሲሆን ይህም ‹‹ትእምርታዊ *ሥርዓት*›› ይባላል (Lacan,1988b,210)፡፡ *ሥነ-ልሳናዊ ሥምምነቶች*፣*ሕግጋት* እና ተግባቦት ደግሞ ‹‹*ማሕበራዊ ሥርዓት*›› የሚባል ሲሆን እውነታን በመፈለግ ሒደት ይንጸባረቃል (Lacan,1977b,245)፡፡ የራስ ልምድ እና የራስ የከልካይነት ጭንቀት *(ego defends)* እውናዊውን በመቃረን ሒደት ምናባዊ *ሥርዓት* ይዋቀራል (Lacan,1988b,177)፡፡

‹‹ራስን›› ምናባዊ በሆነ መዋቅር ማወቅ፣መፈለግ እና ማግኘት ይስተዋላል፡፡ ይህም የጋራ ተግባቦት እና ተመሳስሏዊ የማንነት ኃይል ትረካን ይገልጻል፡፡ እጦትን እና የስሜት አለመቋጨትንም ያስከትላል፡፡ ይህም በገጸ-ባህርያት የማንነት ታሪክ ላይ የሚደመጥ ሲሆን ወደ **ሌላ** *አሮንቃ* ያሰጥማል፡፡ የእኛ የአልችልም ስሜት ምኞት (ፍላጎት) ይሆናል፡፡ ክስተቱም አብዝቶ መጨነቅ፣መቃወም፣**ሌላ** ግልጽነት የሌለው ንግግር እና እረፍት አልባ ሐሳብን ይፈጠራል፡፡ የእኛ ምናባዊ መዋቅር እጦት ይሆናል፡፡ ገጸ-ባህርያት ፍላጎታቸውን ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ሳይሆን፣በተዘዋዋሪ እና በድግግሞሽ ይገልጻሉ፡፡ ይህንም ሌሎቹ ገጸ-ባህርያት ስለማይረዱት የባይተዋርነት እና ‹‹የ**ሌ**ላነት›› *(Otherness*) ምንጭ ይሆናል፡፡ የራስ ያልሆነ **ሌ**ላ እና **ሌ**ላ ፍላጎት እንዲከሰትም ያደርጋል (Lacan,1977b,214)፡፡ ፈልገው የደረሱበት *ምንም* ስለሚሆን **ሌ**ላ ይፈልጋሉ፡፡ *‹‹የምንምነት እና ምንም የሆነ ፍላጎት››* ይከሰታል (Lacan, 1988b, 211)፡፡ በፍላጎታችን ስለማንረካ፣የምንፈልገውን ስናገኝ **ሌላ** እንሻለን (Lacan,1977b, 268)፡፡

ገጸ-ባህርያት ለችግሮቻቸው ከሚወስዱት መፍትሔ ምናባዊ እና እውናዊ ፍለጋን ይማሩበታል፡፡ አንዳንዴም መፍትሔ የማይገኝለት እና መፍትሔ የተባለው በራሱ ውድቀትን ሊያስከትል ቢችልም ከሁለቱም *ዕውቀት* ያገኙበታል (Lacan,1977, 218)፡፡ የእኛ አለመቻል እና እውነታን መፈለግ፣ገፊ የሆነው ኃይልም ትግልን ይፈጥራል (Fink, 2004, 62)፡፡ የእጦት ልምድና ግፊት ስለራስ በግልጽ እድንገልጽ ያደርጋል፡፡ ‹‹ራስ›› ሁልጊዜ ከሐሳብ ነጻ የማይሆን ኃያልነት ያለው ፈጠራ ነው፡፡ የእኛ ስብዕና የተገደበ ስላልሆነ በየጊዜው የሚታይ ነው፡፡ ገጸ-ባህርያት ይዘውት ከነበረ ሐሳብ እና ድርጊት አላዋጣ ሲል ፈቀቅ ይላሉ፡፡ ፍጹም የሆነ **ሌ**ላነትም ይስተዋልባቸዋል፡፡ ይህም ‹‹የማንነት ለውጥ›› ይባላል፡፡ የማንነት ለውጡም ሠናይ ወይም

እኩይ በሆነ መልኩ ሊንጸባረቅ ይችላል›› (Parker,2014,198)፡፡ ያልሰከነ ምናባዊ ስሜት እይታን ያደበዝዛል፡፡ ባልተረጋጋ ስሜት የሚንጸባረቀው የእጦት ጥያቄ በምናባዊ እና በትእምርታዊ ሥርዓት መልስ ያገኛል›› (Fink, 2004,157)፡፡ በእኒህ እና በመሠል ጉዳዮች የLacan ፍካሬ-ልቦና በሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች ላይ በጉልህ ይስተዋላል፡፡

## 2.1. 3. ቋንቋ እና ኢ-ንቁ ልቦና

Lacan, ‹‹የኢ-ንቁ መዋቅር እንደ ቋንቋ ነው፡፡›› ሲሉ ያስረዳሉ፡፡ ቋንቋ የኢ-ንቁ መፈጠሪያ ሲሆን ከቋንቋ በፊት ኢ-ንቁ የሌለ በመሆኑ ኢ-ንቁ የሚዋቀረው በቋንቋ ነው፡፡ Lacan, ቋንቋን እና ኢ-ንቁን ከባህል፣ ከቋንቋ እና ከአእምሮ መዋቅር ጋር ባለው ግንኙነት እና ትርጓሜ ላይ ያተኩራሉ (Hill,1997, 25)፡፡ Lacan, ‹‹የሥነ-ልሳን ሕግጋትን እና ሥምምነቶችን ከድምጸት ጋር ያዛምዳሉ›› የሚሉት ደግሞ (Bowie,1990,108) ናቸው፡፡ እንዲሁም በቋንቋ እና በኢ-ንቁ ልቦና መካከል ያሉ ግንኙነቶችን በሁለት ይከፍላሉ፡፡ የመጀመሪያው፡- ‹‹ኢ-ንቁ ልቦና ቋንቋን ይፈጥራል፤እና ሁለተኛው፡- ቋንቋ ኢ-ንቁ ልቦናን ይፈጥራል›› ናቸው፡፡

ለመጀመሪያው በማመሳከሪያነት ተከታዩ ሐሳብ ቀርቧል፡- ‹‹የሰው ልጅ ቋንቋ በኢ-ንቁ መዋቅር የሚወሰን ሲሆን፣ከፊል ምሥልን ይፈጥራል፡፡ በኋላ የሚፈጠረው ተፈጥሯዊ ስሜትም ሁለቱን የሚያቆራኝ ይሆናል››፡፡ ለሁለተኛው ሐሳብ አስረጅ ይሆን ዘንድ ደግሞ፡- ‹‹ቋንቋ የፍካሬ ልቦና ነብስ እና የተግባቦት ማዕከል ነው፡፡ ታካሚ ሕልሙን እና ፋንታዚውን ለሐኪሙ ይገልጻል፡፡ ሐኪሙ በሥርዓት በመጠየቅ ዲስኩር ያዋቅራል፡፡ ኢ-ንቁ የሆነው ሥነ-ልሳናዊ ቅርጽ በመያዝ ይገለጻሉ›› (ዝኒ ከማሁ፣108-109)፡፡

Lacan, ቋንቋ ኢ-ንቁ ልቦናን ይፈጥራል በሚለው እሳቤ ይመሠረታሉ፡፡ ማመሳከሪያቸውም ኢ-ንቁ የሚገለጸው በቋንቋ መዋቅር ሲሆን የሰው ልጅ የሚወከለው በቋንቋ እና በሲግኒፋየር ነው፡፡ የእኔ ሲግኒፋየር የሚወከለው በሌላ ሲግኒፋየር እና በቃል ነው፡፡ ትክክል ከስሕተት፣ጥሩ ከመጥፎ ጋር ያለው የጥንድ ተቃርኖ ለዚህ አስረጂ ይሆናል፡፡ እኔ እና ሲግኒፋየር ለጥንድ ተቃርኖ መፈጠር አስፈላጊ ቢሆኑም የእኔነት ክልከላ ይስተዋላል፡፡ ይህም የጠፋ\ ሳናገኘው የቀረ ፍላጎት ሁሌም እንደሚኖር ጠቋሚ ነው (Bowie,1990, 110)፡፡

እኔነት በባህል የሚዋቀር እና ተለዋዋጭነት ያለው ነው፡፡ ‹‹*የቃላት አጠቃቀም እና ትርጓሜ በተጠቃሚዎች ታሪክ፣ባህል እና ቃላቱ ለሕይወት እና ለማሕበረሰብ በሚሰጡት አገልግሎት የሚወሰን ነው*›› (Hill,1997, 28)፡፡

Lacan, የJakobsonን ‹‹*ሜታፈር*›› *እና* ‹‹*ሜታኖሚ*›› የተባሉ ሁለት ምሶሶዎችን ከFreud, ‹‹*ኮንደንሴሽን*›› እና ‹‹*ዲስፕለስመንት*›› ጋር በማስተሳሰር አገልግሎት ላይ አውለዋል፡፡ ‹‹*ሜታፈር*›› አንድ ቃል በሌላ የሚተካበት ሲሆን፣‹‹*ሜታኖሚ*›› ቃል ከቃል ጋር ያለውን ግንኙነት አመላካች ነው፡፡ በLacan, እይታ የሲግኒፋየር መዋቅር ምልዑነት የጎደለው እና መቋጫ አልባ እኔነት እንዲፈጠር የሚያደርግ እና በቋንቋ የሚለይ በመሆኑ የአንድ ነገር እኔ የተለያየ ሲግኒፋየር ይፈጥራል፡፡ እኔነት ሁልጊዜ በተጓደለ እና በእጦት የሚዋቀር በመሆኑ እጦት ለእኔ ፍለጋ ምክንያት ሆኖ ይከሰታል (Green, K.,and Lebihan,J.,1996,169; Hill,1997,78)፡፡

የሰው ልጆች ለኢ-ንቁ ልቦናቸው ተገዥ ሲሆኑ የLacan, የሕልም ትንተና ከFreud, የሚለየው የኢ-ንቁ ትእምርታዊነትን ለታካሚዎች በመጠቀም በቃላት ጨዋታ አማካኝነት ለሁሉም ነገር ትርጓሜ መስጠታቸው ነው፡፡ Lacan, የSaussureን ሲግኒፋየር እና ሲግኒፋይድ የተባሉ ሁለት ዋልታዎችን ሲግኒፋየር እና ሲግኒፋይድ በሚል ተጠቅመዋል፡፡ የእንግሊዝኛው *‹‹S››* በትልቁ ፊደል ሲጻፍ ሲግኒፋየርን የሚወክል ሲሆን የእንግሊዝኛው *‹‹s››* በትንሹ ፊደል ሲጻፍ ሲግኒፋይድን ይወክላል፡፡ በሒሳብ ቀመር *S (Signifier over s (signified*) ነው (Bailly, 2009,1-27 ; Leitch, B. Vincent, 2001, 1299)፡፡

ኢ-ንቁ ፍላጎት እና ምሥል በሲግኒፋየር ይገለጻል፡፡ አንድ ሲግኒፋየር ብዙ ትርጉም የሚሰጥ ሲሆን *የሲግኒፋየር ሠንሠለት* ይባላል፡፡ አንድ ሲግኒፋየር ሌላ ሲግኒፋየር ስለሚተካ *ሲግኒፋይድ* ከሌለ ሲግኒፋየር *‹‹ምንም››* ነው፡፡ ወጥ የሆነ ትርጓሜ ስለማይሰጥ *ሲግኒፊኬሽን (የሲግኒፋየር እና የሲግኒፋይድ ድምር*) መኖር አለበት፡፡ ይህም ‹‹*ሲግኒፊኬሽን*›› ከሌለ ኢ-ንቁ ልቦና እንደማይኖር አመላካች ነው፡፡ Lacan, ኢ-ንቁ ልቦናን በሠንሠለት ይመስሉታል፡፡ ጎልማሳነት የራስ መረጋጋት ትርጓሜ ነው፡፡ እኔ አይደለሁም! እና እኛ አይደለንም! ከሚለው ስሜት ይወጣል (Rawson and Nisbet, 2008, 75-76)፡፡

### 2. 1. 4. የLacanian የዲስኩር ብያኔ

የአለቃ (ልሒቅ) እና ምንዝር ዲስኩር (*The Master-Slave Discourse*)፤የንጼት ዲስኩር (*The Hysterics Discourse*)፤የዩኒቨርሲቲ\ትምህርታዊ ዲስኩር (*The University\Academic Discourse*)፤የታካሚዎች ዲስኩር (*The Discourse of The Analyst*) ናቸው፡፡

ከአሠሪ ሠራተኛ እይታ አንጻር የአለቃና ምንዝር ዲስኩር ሲባል ከሌሎች ተግባራት አንጻር ግን *ዕውቀት (ልሒቅ)* የሚለው ትርጓሜ ይገልጸዋል፡፡ በጥንድ ተቃርኖ የሚገለጽ ሲሆን ዕውቀት የሌሎቹ ዲስኩሮች ማዕከል ነው፡፡ ምንዝር በአለቃው ዘንድ እንደ አላዋቂ፣ኃይል እና ደስታ የሌለው፣እንዲሁም ለችግሮች መፍትሔ መስጠት የማይችል ተደርጎ ሊሣል ቢችልም ምንዝር ግን ለራሱ አለቃ ነው፡፡ አለቃም ለራሱ አለቃ ተገዥ ስለሚሆን በመካከላቸው የጎላ ልዩነት የላቸውም፡፡ ሁለቱም ዕውቀት ለማግኘት ይጥራሉ (Lacan, 2007, 22)፡፡

*አለቃ እና ምንዝር* የነበረ እና አስፈላጊ የሆነ ማሕበራዊ ሥርዓት ነው፡፡ አንዱ የሌላውን ፍላጎት ሊፈቅድ ወይም ሊከለክል ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ የተከለከሉ ፍላጎቶች ወደ ኢ-ንቁ ልቦና ይመሽጋሉ፡፡ በሒደትም በትእምርታዊ ሥርዓት ይከሰታሉ፡፡ አለቃ እና ምንዝር ለማሕበራዊ ሥርዓት ወይም ለታዛዥ እና አዛዥ ባህል ተገዥ ይሆናል፡፡ የሰው ልጆች ግንኙነት በአለቃ እና ምንዝር ባህል ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ለምሣሌ፡-ባል እና ሚስት፣ቀጣሪ እና ተቀጣሪ፣አሣሪ እና እሥረኛ፣ተፈቃሪ እና አፍቃሪ፣መምህር እና ተማሪ፣አንዱ ለሌላው አስፈላጊ እና ታዛዥ ነው (Jafferson et al.,1986,153)፡፡

Fry, (2012)፣ Foucaultን ዋቢ በማድረግ ‹‹ዕውቀት እና ኃይል ተጣማሪ ናቸው፡፡ ዕውቀት ጉልበት በመሆኑ ኃይል ለዕውቀት ተገዥ ነው፡፡ ርዕዮተ ዓለማዊ ተጫኝነትም ይስተዋላል›› (291)፡፡ Hegel, ‹‹የራስ ንቁነት የሚወሰነው በሌላ ራስ ነው፡፡ የራስ እና የእኔ የመስታወት ምሥል ግንኙነት መጨረሻው የበታችነት ስሜትን ይፈጥራል፡፡ በሚል በአለቃ እና ምንዝር ዲስኩር ዙርያ መከራከሪያ ሐሳብ ያነሳሉ›› (Wolfreys, J.,2001,64)፡፡ Hegel, ደግሞ የአለቃ እና ምንዝር ዲስኩር አስፈላጊ እና የጋራ መዋቅር ያለው ነው በማለት ይበይናሉ፡፡ ምንዝር በሌለበት ምንም የሚሆን ነገር ስለሌለ አለቃ በራሱ አለቃ አይሆንም፡፡ መተባበር እና መሸናነፍ ያስፈልጋል፡፡ ምንዝር የሚፈልገው መሠረታዊ ፍላጎቱን እና መኖሩን ነው፡፡ የካበተ ዕውቀት እና ክሕሎት ባለቤት ስለሚሆን አለቃው የምንዝሩ ጥገኛ ይሆናል፡፡ አለቃ (ምንዝር) ሌላነትን አመላካች ነው (Fry,2012, 293-294)፡፡

*የንዴት ዲስኩር*- (*Hysteric)* ከአእምሮ መረበሽ ጋር ያዛምዱታል፡፡ የሚያስለቅስ (የሚያስቅ). ይሉታል፡፡ ድብቅ የሆነ ፍላጎት በቅጽበት እንዲታወቅ ያደርጋል፡፡ ግልፍተኛ ግለሰብ የራሱን ፍላጎት ዝቅ አድርጎ በማየት የሌላውን ፍላጎት ይመለከታል፡፡ ፍላጎቱን በግልጽ አይናገርም፡፡ ነገር ግን ከሁኔታው መረዳት ይቻላል፡፡ ፍላጎቱን የማይናገርበት ምክንያትም የሚያሣያቸውን ምልክቶች እና ከሚጠይቀው በመነሳት ሌሎች ይተረጉማሉ ብሎ ስለሚያሥብ ነው፡፡ የፍላጎት ምልክቶች የራስ ምታት፣ዐይንን መሸፈን እና አካላዊ ስቃይ ናቸው፡፡ ጥሩ ያልሆነ ስሜትን በመፍጠር ስቃይን ያስከትላል፡፡ ሠራተኞች ዕውቀትን እና ጥቅምን ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረት የንዴት ዲስኩር ያንጸባርቃሉ (Lacan, 2007,23,32)፡፡

በሰው ልጆች ዘንድ ራስን ከፍና ዝቅ አድርጎ መገመት ይስተዋላል፡፡ ለምሣሌ፡- አፍቃሪ ‹‹**እኔ ያላንች ምንም ነኝ**›› ቢል ፍቅረኛውን ከፍ ራሱን ዝቅ አድርጓል፡፡ በዚህም አፍቃሪ የተፈቃሪ ባሪያ ነው፡፡ የዩኒቨርስቲ ዲስኩር መምህሩ ልሒቅ ሲሆን፣ተማሪዎች ምንዝር ናቸው፡፡ የሕግ ባለሙያው ራሱን ልሒቅ፤ደንበኛውን እንዳላዋቂ ይቆጥራል (Basic Psychological Ideas, undated, Page. 22-46)፡፡

*የታካሚዎች ዲስኩር (የሕክምና ዲስኩር)*፡- መሠረቱ ዕውቀት በመሆኑ የሐኪም ታካሚ ግንኙነት ልዩነት አለው፡፡ ሐኪሙ ዕውቀቱን በመጠቀም ታካሚውን ይጠይቃል፡፡ ትእዛዝ ያስተላልፋል፡፡ ታካሚውም ፍላጎቱን ለማግኘት በተለሳለሰ መልኩ በመጠየቅ የተባለውን ይፈጽማል (Lacan,2007,32)፡፡ Althusser, የሕክምና ዲስኩርን ከርዕዮተ ዓለም ጋር አስተማስሎ ያለው ሲሆን ምናባዊ የሆነውን ከእውነታ ጋር በማስተሳሰር ታካሚውን አተኩሮ በማየት ያክማል (Bertens, 2001,151)፡፡ Foucault, ሐኪሙ በኃይል እና በተጫኝነት፣ ማንኛውንም ትእዛዝ እንዲቀበል በማድረግ ያክማል፡፡ በመሆኑም ኃይል ሁልጊዜ የተጫኝነት ባህሪ አለው (Bertens,2001,152-153)፡፡ ሐኪሙ ከታካሚዎቹ ከሚያገኘው መረጃ በመነሳት ዲስኩሩን ምናባዊ እና ትእምርታዊ ቅርጽ በማስያዝ (ዲ) ኮንስትራክት ያደርጋል (Fink,1997, 6-10)፡፡

## 2. 1. 5. ፍላጎት

‹‹*መሠረታዊ ፍላጎት*›› (*need*)፣‹‹መጠየቅ›› (*demand*)፣እና ‹‹ፍላጎት›› (*desire*) እንዲሁም ‹‹እውናዊ››፣ ‹‹ምናባዊ›› እና ‹‹ትእምርታዊ›› *ሥርዓቶች* ሦስቱ የሰው ልጅ የዕድገት ደረጃዎች ናቸው (Rawson and Nisbet, 2008,76)፡፡ ሦስቱ የLacan, የሰው ልጅ የልቦና መዋቅሮች

እና አስተምህሮዎች (‹‹ፍላጎት››፣‹‹የመስታወት ደረጃ (ባይተዋርነት)›› እና ‹‹ፋለስ››) ለትንተና ሲባል የከፋፈሏቸው እንጂ ተቆላላፊ በመሆናቸው አንደኛው በሌላኛው ውስጥ ይስተዋላል፡፡ ምናባዊ በውቅያኖስ ይመሰላል፡፡ እውናዊ ደግሞ ከሳይኪ-ልምድ እና ከቋንቋ ውጪ የሆነ ነው (Wolfreys,J., 2001,108)፡፡ ‹‹የLacan, ፍካሬ-ልቦና ረቂቅ የፍላጎት እጦት ሲሆን በመሠረታዊ ፍላጎት፣በመጠየቅ እና በፍላጎት መካከል ያለውን ልዩነት እና መስተጋብር የሚገልጽ ነው›› (Hill,1997,65)፡፡

‹‹መሠረታዊ ፍላጎት›› (*need*) ቁሳዊ (እውናዊ) ሲሆን፣የሕጻኑ መሠረታዊ ፍላጎት ምግብ እና ጡት በመሆኑ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ሕጻኑ ለመሠረታዊ ፍላጎቱ እና ለእናቱ (ሞግዚቱ) ጥገኛ እና ተገዥ ነው፡፡ እናቱ (ሞግዚቱ) የሕጻኑን ፍላጎት በማሟላት ክፍተቱን ትሞላለች፡፡ በዚህ ደረጃ የሕጻኑ መሠረታዊ ፍላጎት በደስታ፣በምቾት፣በጸጥታ (በደሕንነት) ይተካል፡፡ እናት ርሃቡን እና ድምጹን በመስማት አቅፋ ጡት (ጡጦ) ስትሰጠው፣በራሱ እና በእናቱ እንዲሁም በቁሱ መካከል ልዩነት መኖሩን ስለማያውቅ ወዲያውኑ ይረካል (Green, K., and Lebihan, J.,1996,176)፡፡

እናቱ ጊዜ የማትሰጠው እና የማትመግበው ከሆነ ውስብስብ ወደ ሆነው የቋንቋ መማር ደረጃ ይሸጋገራል፡፡ የቃላቱን ሲግኒፋየር በመገንዘብ ትመግበዋለች፡፡ የእናቱን ፍላጎት ከትእምርታዊ አባት ጋር በመመሰል የሚያገኝ ሲሆን፣ከመሠረታዊ ፍላጎት ወደ መጠየቅ እንዲሸጋገርም ምክንያት ይሆናል፡፡ ከመሠረታዊ ፍላጎት ደረጃ ወደ መጠየቅ ሲሸጋገርም ከእናቱ እና ከራሱ ይለያል፡፡ ሕጻኑ ቋንቋ መጠቀም ሲጀምር ከእናቱ ባይተዋር በመሆን ወደ ትእምርታዊ አባቱ ያመዝናል፡፡ ትእምርታዊ አባት፣አካላዊ አባት፣የእንጀራ አባት፣*sibling* ወይም ከእናት ተግባር ባይተዋርነትን ይፈጥራል፡፡ ሕጻኑ ከእናቱ ፍላጎት ባይተዋር በመሆን ሌላ ይመለከታል (Hill, 1997,60)፡፡ ‹‹ሐሳብ ጉድለት እንዳለበት ይሰማዋል፡፡ በውስጣዊው ስሜት እና በውጫዊው ዓለም እርካታ መካከል መሠረታዊ ፍላጎት ይፈጠርበታል፡፡ ግንዛቤውም ራሱ በፈጠረው ዓለም የሚዘወር ይሆናል›› (Rawson and Nisbet, 2008,75)፡፡

ሕጻኑ ከእናቱ ከተለየ እጦትን ያስተናግዳል፡፡ በራሱ እና በእናቱ መካከል ልዩነት እንዳለ ማወቅ ከጀመረ *Individuated,* ሕልው ይሆናል፡፡ ያለፈ ጊዜ የእጦት ስሜት፣ደሕንነት እና ምቾት ያሳጣል፡፡ ትራጀዲ እንዲዋቀርም ያደርጋል፡፡ ሕጻኑ መለየት ሳይችል በመሠረታዊ ፍላጎቱ ብቻ እርካታን ካገኘ በራሱ እና በቁሱ መካከል ልዩነት ስለሌለ በመሠረታዊ ፍላጎቱ እርካታን ያገኛል፡፡ ይህም የእውናዊ ግዛት ነው፡፡ እጦት ባለመኖሩ የእውናዊ ትክክለኛ ቦታው (ምንጩ)

ይታወቃል። ሕጻኑ የሚፈልገው ሁሉም እውናዊ ነገር ተሟልቶለታል። መሠረታዊ ፍላጎቱ ከሌለ ግን እጦት ስለሚከሰት አይረካም። በእውናዊ ቋንቋ የለም (Rawson and Nisbet, 2008 ,76-77)።

ሕጻኑ በዐሥራ ስምንት ወራት ዕድሜው ‹‹እማ (አባ)›› በማለት በራሱ የቋንቋ መዋቅር የቋንቋ ምልክቶችን ማሳየት ይጀምራል። ቋንቋ የእጦት መከሰቻ ሲሆን፣ሕጻኑ መሠረታዊ ፍልጎቱን የሚያሟሉ ቃላትን ብቻ ይጠቀማል። የሚጠቀማቸው ቃላትም የሚፈልገውን ሁሉ የሚያሟሉለት ስለሆኑ ቁሱን በመፈለግ ሒደት እጦት አይስተዋልም። በመሆኑም ባዶ (የለም) የሚባል ነገር ስለሌለ መሠረታዊ ፍላጎት ቋንቋ ነው ።

ሕጻኑ በመሠረታዊ ፍላጎቱ ሳይረካ ሲቀር ይጠይቃል። ሕጻናት **ሌላ** ለማወቅ፤**ሌላ** ለማፍቀር ደጋግመው ይጠይቃሉ። በዚህም ጊዜ ከእናቱ ውጪ ያሉ ነገሮችን ማወቅ ይጀምራል። የሚያየው የራሱ አካል እንዳልሆነ ስለሚያውቅ የ**ሌላ** ሐሳብ ይፈጠራል። የሕጻኑ የራስ ስሜት ተያያዥነት ስለማይኖረው ራስ (**ሌላ**) የሚለው የጥንድ ተቃርኖ የለም። መለየቱን ማወቁም **ሌላ** የጭንቀት እና የእጦት ስሜትን ይፈጥርበታል። በዚህን ጊዜ ወደ ቀደመው በመመለስ ይጠይቃል። ይህ ሐሳብ የ**ሌላ** መኖርን የሚያመላክት ሲሆን የሕጻኑ መጠየቅ በ**ሌላ** ይሟላል። ወደ ቀደመው የስሜት ሕብረት የሚመልስ ሲሆን የሕጻኑ መፈለግ የ**ሌላ** ሐሳብ  መጥፋትን የሚገልጽ ነው። መጠየቅ፣መጠየቅ መሟላት **ሌላ** የሕጻኑ እጦት በልምዱ ያበቃል (ገጽ፣78)።

እጦት የማይቻል እና *የሌላነት (other›ness)* ስሜት አለው። ሕጻኑ መጠየቅ እና **ሌላ** ማወቅ ስለሚስተዋልበት የራስ (የእኔ) እሳቤ በቋንቋ ባህል ሕልው እና ተግባራዊ ይሆናል። ከስድስት እስከ ዐሥራ ስምንት ወራት የሚፈልገውን ስለማይናገር በትክክል አለመርካት ይኖራል። ሕጻኑ ያለቅሣል፣እናቱ ጡት (ጡጦ) ትሰጠዋለች ወይም ዝም እንዲል የሆነ ነገር ታደርጋለች። ይሁን እንጂ ሕፃኑ በቁሳዊ መልስ ብቻ ስለማይረካ ደጋግሞ ይጠይቃል (ገጽ፣79) ።

*ሕጻኑ ‹‹እማ (አባ)››* እያለ መጫወቱ ቋንቋን በመጠቀም አፍራሽ እጦት እና የ**ሌ**ላነት ሐሳብ በመከፋፈል የማይቻል መዋቅራዊ ሒደትን የሚከተል ሲሆን Lacan, *‹‹ምትክ ፍላጎት›› (objet petit a or objet petit autre)* ይሉታል። ሕጻኑ የሚያውቀው **ሌላ** ሲጠፋው ወደ ቀደመው በመመለስ የሚያውቀውን **ሌላ** መልሶ ያመጣል። እንደ Lacan, ትንታኔ እጦቱን ለመተካት ሐሳቡን በመቀየር ወደ **ሌላ** ያመራል። እጦት እና ምትክ ፍላጎቶች በቋንቋ የሚፈጠሩ ናቸው። የሕጻኑ **ሌ**ላ እጦት ማጣት እና አለመኖር የማያልቅ እና የራስ ነው (ገጽ፣82)።

የLacan, የመስታወት ደረጃ እሳቤ በእኔ እና *‹‹ምትክ ፍላጎት››* (*the object a*) መካከል ያለውን የሚገልጽ ነው፡፡ ሕጻኑ እኔ ማን ነኝ? በመስታወቱ የምታየው እኔ ነኝ? በማለት ይጠይቃል፡፡ ራሱን ከ**ሌላ** ለመለየት ይሞክራል፡፡ ለጥያቄው እና ለፈለገው ነገር መልስ ስለማያገኝ ምናባዊነት ይስተዋልበታል፡፡ ከእናቱም ጋር ጥብቅ ቀረቤታን ይፈጥራል፡፡ ምናባዊ **ሌላ** እና ትእምርታዊ **ሌላ** ፍላጎትም ይኖረዋል፡፡ የፍላጎት አለመሳካት ሲኖር እና በሌላ ሲተካም ምትክ ፍላጎት ይባላል፡፡

> ‹‹ምትክ ፍላጎት›› *(objet petit a,or object Small a)* በ**ሌላ** እና **ሌላ** ዙርያ ልዩነት አለ፡፡ ሕጻኑ በመስታወት የሚያየው ምሥል የራሱ ሳይሆን **ሌላ** ነው፡፡ ራሱን ለ**ሌላ** ሐሳብ ይሰጣል፡፡ እውነተኛ እኔውን ማግኘት ስላልቻለ **ሌላ** ያውቃል፡፡ የራሱን ምሥል በመተው ሌላ ይከተላል፡፡ **ሌላ** ሰው እና ሌላነት የሚለውን የሚገነዘብበት ነው፡፡ **ሌላ** (*Other)* የሚያመላክተው የእሱ (የእሷ\እኔ) የሚሉት ነገር እንደራቀ እና ከትእምርታዊ እይታ አንጻር ብቻ የሚታይ ሲሆን ነው፡፡ እያንዳንዱ የምንናገረው ነገር በሌላ መንገድ ያልፋል፡፡ ቀጥተኛ በሆነ መንገድም ከአካል እጦት ጋር ግንኙነት አለው፡፡ የሆነ ነገር ከጠፋ (ከተዘነጋ) አካል ጋር ይያያዛል፡፡ ነገሮች የራሱ ባይሆኑም ከመኮላሸት ሐሳብ ጋር በማያያዝ ያጣውን አካል ያስታውሳል፡፡ ያጣው አካል በእሱ (እኔ) ውስጥ ትእምርታዊ በሆነ መልኩ ይተካል (ሕልው) ይሆናል፡፡ ይጻፋል፡፡ (Green,K.,and Lebihan,J.,1996,164 ; Lacan, 1977,6)

ሕጻኑ እጦቱን ይጠይቃል፡፡ መሠረታዊ ፍላጎት እና መጠየቅ ተነጻጻሪ ሲሆኑ ቁሳዊ እና ፍጆታዊ ብቻ አይደሉም፡፡ ሕጻኑ እያለ ያላገኘውን ለማግኘት ይጠይቃል፡፡ እናት ሕጻኑ ለሚጠይቀው ሁሉ መልስ መስጠት አትችልም፡፡ ፍላጎቱን ባለማሟላቷ እና ጥያቄውን ባለመመለሷ ይበሳጫል፡፡ ደስታን ይነፈጋል፡፡ መበሳጨቱ ለመጠየቅ እና ለፍላጎት ምክንያት ስለሚሆን ከመጠየቅ ወደ መፈለግ ይሸጋገራል፡፡ ፍላጎት ሕጻኑ የጠየቀውን በማጣቱ እና ተስፋ-በመቁረጡ ምክንያት የሚፈጠር ነው፡፡ የመጠየቅ እና የፍላጎት ተነጻጻሪነት፡- ‹‹መጠየቅ ሁሌም ያለ ነው፡፡ የሚነሱ ጥያቄዎች የማይሳኩ እና **ሌላ** የሚያስፈልጋቸው ይሆናሉ፡፡ የሆነ ነገር በ**ሌላ** ምንም ያልሆነ የእኔ ከሆነ፤የማይቻለው የእኔ ፍላጎት የሆነ ነገር ኃይል እና ውጤት ይሆናል›› (Hill,1997,67)፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት የአማርኛ መዝገበ ቃል (1999፣585) ‹‹ፈለገ ማለት፡- ወደደ፣ ፈቀደ፣የጠፋን ወይም አስፈላጊ የሆነን ነገር ለማግኘት ሞከረ፡፡ ጣረ፡፡ ማለት ሲሆን ፍላጎት ማለት ደግሞ አንድ ነገር ለማድረግ፣ለማግኘት፣ለመሆን የመሻት ስሜት ነው በማለት ትርጓሜ

ይሰጣል፡፡›› Klages, M., (2011) ደግሞ ‹‹ፍላጎት የሰውን ልጅ አንቀሳቃሽ ኃይል ሲሆን፣ የሰው ልጅ የሚንቀሳቀሰው የሚወጣ እና የሚወርደው፣የሚሄድ የሚመጣው በራሱ ሳይሆን ምንጩ የት እንደሆነ በማይታወቅ የልቦና ኃይል ነው›› (ገጽ፣76) በማለት ይተነትናሉ፡፡

*‹‹**ፍ**ላጐት›› (Desire*) ደመ-ነብሳዊ ሲሆን፣እናት ከሕጻኑ ቀድማ ትእምርታዊውን ዓለም ስለተዋወቀች የልጇን ፍላጐት በ**ሌ**ላ ለማሳካት ጥረት ታደርጋለች፡፡ መሠረታዊ ፍላጐትን በመጠየቅ እና በመመለስ ሒደት የተፈጠረው ፍቅርን መሻቱ ሳይረካ የሚቀርበት ፍላጐት ይባላል፡፡ በሌላ ፍላጎት ማለት በመሠረታዊ ፍላጎት እና በፍላጎት እጦት መካከል ያለውን ክፍተት በቋንቋ ግልጽ አድርጎ በመናገር እና በመጠየቅ የሚከሰተው ነው፡፡ ፍላጎት ከምናባዊ ወደ ትእምርታዊ ዓለም የሚደረግ ሽግግር ነው፡፡ *ሥነ*-ልሳን ውስጡ ባዶ የሆነ ሕልው የፍላጎት መገኛ ሲሆን፣የፍላጎት ምንጭ እጦት ነው (Green,K., and Lebihan, J.,1996,177; Tyson, 2006,28)፡፡

የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቱን እና ፍላጎቱን ከመፈለግ ባሻገር፤በልቦናው የላቀ መጠየቅ እና ፍላጎት ይንጸባረቃል›› (Wolfreys et al.,2006,31)፡፡ Bennett A, and Royle N, (2004, 180) እንደሚያስረዱት ደግሞ የሰው ልጅ ልቦና ‹‹የፍላጎት ከረጢት\የፍላጎት መፈልፈያ›› (*Desire Machine*) ስለሆነ፣በ*ሥነ*-ጽሑፍ *ሥራ*ዎች ላይ የገጸ-ባህርያት ፍላጎት ምን እንደሆነ ብቻ ሳይሆን፣ፍላጎት እንዴት እንደሚከሰትም ማወቅ ይገባል›› በማለት ይገልጻሉ፡፡

የፍላጎት ፍሰት መጨረሻ የሌለው እና ሁልጊዜ ‹‹*በራሪ*›› በመሆኑ የሰው ልጅ የሚፈልገውን ሲያገኝ ሌላ ይፈልጋል፡፡ ተሳካ ሲባል ወደ ሌላ ፍላጎት *መብረር*፤የፈለግነውን ማግኘት እንደገና ወደ ሌላ ፍላጎት *መብረር*፤ለመያዝ እንሞክራለን አሁንም ያመልጠናል፡፡ ሁልጊዜ መፈለግ፤ ሁልጊዜ *መብረር* ነው›› (Bennett A, and Royle N,2004,31-32*)፡፡ ‹‹ምትክ ፍላጎት* ውስብስብ እሳቤ ሲሆን፣ተፈላጊ ቁስ ሁልጊዜ ተለዋዋጭ በመሆኑ፣ፍላጎትን ለማሟላት ፈታኝ ሒደቶች ይታለፋሉ፡፡ ይሁን እንጂ ይኸም ሆኖ ላይሟላ ስለሚችል፣ፍላጎትን በ*ፋንታዚ* (ምናባዊ \ትእምርታዊ) ማሟላት ይስተዋላል፡፡ በዚህም ምክንያት Lacan እጦት ሁልጊዜ ሊደረስበት የማይችል እና ለእኔነት ተገዥ የሆነ ነው›› በማለት ያብራራሉ (Wolfreys, et al., 2006, 72-73)::

Bailly, (2009) Lacanን ዋቢ በማድረግ ‹‹ፍላጎት መጨረሻ አልባ የሰው ልጆች ደመ-ነብሳዊ ጉዳይ በመሆኑ፣የሰው ልጅ ዕድሜውን በሙሉ ይፈልጋል፡፡ ፈልጎ ሲያገኝ ያገኘው ነገር

*‹‹ምንም››* ይሆንበት እና እንደገና **ሌላ** ይፈልጋል፡፡ Lacan, **ለፍላጎት** ከJean Paul Sartre, የ*‹‹ምንምነት››* ፍልስፍና ጋር በማዋሃት ትንታኔ ይሰጣሉ፡፡ ተጨባጭ እና ሕልው የሆነ ምንምነት በማሕበራዊ መዋቅር ትእምርታዊ ሥርዓት ነው (Ellmann,1994,2)፡፡ የሰው ልጅ በዚህች ምድር ላይ በፍላጎት ለመባዘን የተፈጠረ ሲሆን፣የፈለገውን ለማግኘት በሚጥርበት ጊዜ በስቃይ እና ውጣ ውረድ እንዲሁም በጥንድ ተቃርኖ ይታጀባል፡፡ በመሆኑም የሰው ልጅ ፈልጎ አንዱን ሲይዘው ሌላው ይጎድላል፡፡ የጎደለውን ሲደርሱበት ደግሞ ያልተገመተ እና ያልተጠበቀ ሌላ ችግር አዘል ክስተት ይስተዋላል፡፡ አፈንጋጭነት፣ተለዋዋጭነት እና ረቂቅነት የፍላጎት መገለጫ ባህርያቶች ናቸው›› (Bailly,2009,16-27)፡፡

የአንዱ ፍላጎት የሌላው እጦት ስለሆነ፣የአባት ‹‹**ፍ**ላጎት›› *(Desire)* ሁልጊዜ **ሌላ** ነው፡፡ በመሆኑም የሰው ልጅ ፍላጎት ትርጉም የሚኖረው በሌላው ፍላጎት ነው፡፡ ‹‹**ፍ**ላጎት›› *(Desire)* የሚገለጸው በሲግኒፋየር ሲሆን፣ድብቅ ፍላጎት በሕልም (ቅዥት)፣በቀልድ፣በምላስ ወለምታ፣ በቁጣ፣በእንደወረደ እና በበሽታ ይገለጻል፡፡ ‹‹የ**ፍ**ላጎት›› *(Desire)* እና የእኔነ ውጤት በሚያጋጥሙን ሁኔታዎች ጫና ላይ የሚመሠረቱ ሲሆኑ፣ሕልው የሚሆኑትም ባመለጡን የመሠረታዊ ፍላጎት ዲስኩር እና በሲግኒፋየር ነው›› (Jafferson et al.,1986,153)፡፡

ርስ በርስ መተጋገዝ እንዲጎለብት ፍላጎት እና ሐሳብን ማካፈል ያስፈልጋል፡፡ Lacan፡- ‹‹**ፍ**ላጎት *(Desire)* የሚገልጸው ክፍተት በራሱ ውስጡ ባዶ እንደሆነ መጠይቅ ይቆጠራል፡፡ ስለዚህ ስለራስ በግልጽ መናገር *የሲግኒፋይንግ* ሠንሠለትን ይፈጥራል፡፡ አንዱ ለሌላው ፍላጎቱን እና እጦቱን ከገለጸ ፍላጎቱን ፍላጎቱ፣ጥያቄውን ጥያቄ በማድረግ ለስኬታማነቱ ሊተጋ ይችላል›› (Lacan,1980,263)፡፡

## 2. 1. 6. የመስታወት ደረጃ *(mirror stage)*

*‹‹ቅድመ-ኤዲፐስ››* የሕጻኑ ምናባዊ ደረጃ ሲሆን፣በራሱ እና በእናቱ *m(other)* እንዲሁም በአካሉ እና በውጫዊው ዓለም መካከል አንድነት እንጂ ልዩነት መኖርን ስለማይረዳ ራሱን በዙርያው ካለው ነጸብራቅ ጋር በተመሳስሎ ይመለከታል፡፡ ምናባዊ ሥርዓት ለሕጻኑ እውነታ እና የእሱን እና የእናቱን ሕብረት መረዳት የሚጀምርበት ሲሆን፣ከስድስት እስከ ዐሥራ ስምንት ወራት ሕልው ይሆናል፡፡ ይህም የራሱን ነጸብራቅ ለመጀመሪያ ጊዜ በመስታወት የሚመለከትበት እና ‹‹የኢጎ›› መፈጠሪያ ነው፡፡ የመስታወት ደረጃ ውጫዊው (መስታወቱ) እና

ውስጣዊው የስሜት ዓለም የሚንጸባረቅበት በመሆኑ፣የአእምሯዊ እና የአካላዊ ቅንጅት ውጤት ነው (Wolfreys et al., 2006, 66)፡፡

የLacan, *የመስታወት ደረጃ* ሕጻኑ ለራሱ አካል አዛዥ የማይሆንበት እና የራሱን እንቅስቃሴ መቆጣጠር የማይችልበት ስለሆነ ምልዑ ስሜቱን እና አካሉን አያገኝም፡፡ ‹‹አውራ እጣቱን›› *(thumb*) በአፉ ላይ ማንቀሳቀስ እና እጣቱን መምጠጥ ይጀምራል፡፡ የሕጻኑ ልምድ የተዘበራረቀ አካል ቅንጣት (*piece*) ነው፡፡ የሚያየው ሌላ ሰው ምልዑ እና ሕልው በመሆኑ ራሱን ምልዑ እንደሆነ አድርጎ ይሥላል፡፡ ሕጻኑ የሚመለከተው ሌላው ግለሰብ ሁሉ እንደ እሱ (እሷ) አንድ ስለሚመስለው ወጥ እና ምልዑ የሆነ የምሥል እይታ አይኖርም፡፡ ሕጻኑ የሚረዳው አካል ሁሉም የስሜት ክፍል የስሜት ችሎታው ቅንጣት የሆነ ሌላ ይሆናል፡፡ ሕጻኑ በመስታወት የሚመለከተው ነጸብራቅ፣ከኂላ የሚመለከተው እውናዊ ግለሰብ፣እናቱን (ሌላ) ሰው ሲሆን ይችላል፡፡ ይሁንና ሕጻኑ ምሥሉን ደጋግሞ ሲመለከተው ሁሌም የሚያውቀው ሌላ ሰው ሲሆንበት ‹‹የምመለከተው እኔን ነው? በሚል የስሜት ጡዘት ውስጥ በመግባት ይወራጫል፡፡ ይፈነድቃል፡፡

በኂላው እና በፊቱ ያለውን እውናዊ ሰው እና የመስታወቱን ምሥል እያፈራረቀ ይመለከታል፡፡ እኔ ማን ነኝ? በሚል ስሜት እንደገና ይነሳሳል፡፡ እኔ ነኝ? በሚል ሁሉም የሕጻኑ ስሜት ከማግኘት እና ከምልዑነት ጋር ይቀናጃል፡፡ በዚህም ጊዜ ሕጻኑ ሌላ እና ምልዑን ለይቶ ስለሚያውቅ ፣ከሌላ መለየቱን ይረዳል፡፡ በመስታወት ደረጃ የሕጻኑ ምልዑነት ለመጀመሪያ ጊዜ ሕልው ይሆናል ተብሎ የሚጠበቅበት ሲሆን፣ይህም ‹‹ወደ ተዘበራረቀ አካል›› እና ጥቅል ወደ ሆነ ትክክለኛ እይታ ያመራል፡፡›› የራሱ እይታ ምልዑ እና ከሌላ ጋር የተቆራኘ እንደሆነ በማሰብ ምናባዊውን በራሱ ምልዑ እንደሆነ መረዳት ይጀምራል (Rawson and Nisbet, 2008, 79)፡፡

Lacan, የመስታወት ደረጃን እና የምናባዊ ሥርዓት የልምድ እና የሳይኪ እንዲሁም ያለፈ ጊዜ መከፋፈል እና የጥንድ ተቃርኖ ውጤት ነው፡፡ ምክንያቱም በክፍተት እና ክልከላ ሁሉም የራሱን እና የሌላን መለየት በእሱ (በእሷ) ተገዥነት መካከል ተቃርኖ ያለበቂ ሳይኪ ይፈጠራል፡፡ ሕፃኑ 18 ወር ሲሞላው ‹‹*ሶሻላይዝድ*›› የሚሆን እና ‹‹እማ (አባ)›› በማለት ቋንቋ የሚጀምርበት ሲሆን ሒደቱም *Identification* ይባላል፡፡ በመሆኑም በእኔነት ሒደት ከምናባዊ ወደ ትእምርታዊ የሚደረግ ሽግግር ሲሆን ሒደቱም የመስታወት ደረጃ ይባላል፡፡ *Sym-biotic,* ከሕጻኑ ዓለም ጋር ግንኙነት አለው፡፡ ሕጻኑ ደመ-ነብሳዊ በሆነ መንገድ የአካል ወሰን መኖሩን

ሳያውቅ አካሉን ይመጣል (ይጠባል)፣ያለቅሣል። በLacanian,ዲስኩር ምናባዊ ከሳይኪ ተግባር ጋር የሚቆራኝ ሲሆን፣በቀላሉ የሚታይ (የሚፈጠር) አይደለም። እውናዊ አባት በሌለበት የአባት ሥም ተጫኝነት ያለው በመሆኑ፣ምናባዊ አባት የ‹‹**ፍ**ላጎት›› (*Desire*) አነሳሽ ይሆናል። ‹‹**ፍ**ላጎት›› (*Desire*) እንደማይሟላ ሲያውቁ ራሳቸውን እንደ እድሉ-ቢስ የሚቆጥሩ ሲሆን ይህም በኢ-ንቁ ልቦና ሕልው ይሆናል።

> ‹‹የመስታወት ደረጃ የፋለስ ‹‹**እ**ጦትን›› (*Lacking)* ይፈጥራል። በዚህም ጊዜ ምትክ (*ፋንታዚ*) የሆነውን ለይቶ ያውቃል። የተበታተነ ምስል ይስተዋላል። የእኔ የአእምሮ ዕድገት የማይለዋወጥ የባይተዋርነት መዋቅር ይኖረዋል›› (Lacan, 1977, 4)።

የእውነታ መከሠት *Identification* በተሳሳተ መንገድ ማወቅ፤ሕጻኑ በመስታወት የሚመለከተውን ምሥል ማሠብ፤‹‹እኔ ነኝ ወይስ እኔ አይደለሁም?›› በሚል ምሥሉን ይመለከታል። **ሌ**ላ ሰውን በተሳሳተ ግንዛቤ በማነሳሳት ‹‹እኔ ነኝ!›› ወደ ማለት ይሸጋገራል። **ሌ**ላ ሰውም ሥነ-ልሳናዊ ሥም ይሰጠዋል። **ሲ**ግኒፋየር ‹‹እኔ፣ ምሥሉ እና በመስታወት በሚታየው ምልዑ አካል መካከል የሕጻኑ የራሱ ስሜት ምልዑ እና ሕልው የሆነ ትስስር አለው።›› ሕጻኑ ምሥሉን ሕልው እና ‹‹የራሱ›› እንደሆነ ይደመድማል። ይህም የተሳሳተ የራስ የግንዛቤ ሒደት የመስታወቱ ምሥል *‹‹ኢጎ››* ይፈጥራል። በተሳሳተ ግንዛቤ የሚፈጠረው *‹‹armor››* እኔነትን በስሕተት ከምልዑነት ጋር በማስተሳሰር ይገልጻል። Lacan, ኢጎ (የራስ\የእኔ ማንነት)፤ውጫዊው ምሥል የውስጣዊው ስሜት አካል ሳይሆን *ፋንታዚ* ነው። በዚህ ሒደት ባይተዋርነት እና ምልዑነት የሚከሠት ሲሆን ይህምን Lacan *የመጠየቅ ደረጃ* ይሉታል (Rawson and Nisbet, 2008, 80)። *ፋንታዚ* በምናባዊ እና በትእምርታዊ የሚገለጽ የሰው ልጆች የሰርክ ቋንቋ ነው። በፍካሬ-ልቦና ሕልም የፍላጎት ማሟያ ሲሆን፣ያልተደሰተበትን ነገር በሕልሙ በደስታ (በፈለገው ነገር) ተተክቶ ሲያይ *በፋንታዚ* እውነታውን እንዳገኘ ይቆጥረዋል (Wolfreys et al., 2006, 40-41)።

የማንነት ጉዳይ አከራካሪ ነው። እውነተኛ ማንነት የቱ ነው? የሚታይን ሁሉ እውነተኛ ማንነት ማለት ይቻላል? ተቀያያሪ የሚሆንበት አጋጣሚስ የለም? ገጽታ፣አለባበስ፣የሰውነት ሁኔታ ተለዋዋጭ ነው፤ስለዚህ እውነተኛ እኔ የት ይገኛል? እንዲህ ነው ብሎ መደምደም ለስሕተት ይዳርጋል›› (Rawson and Nisbet,2008, 81)። ናርሲስት *በግሪክ ሚቶሎጂ* በውኃ ውስጥ የሚመለከተውን ምሥል ለማምለክ ጥቂት የቀረው ሆኖ ተሥሏል›› (ወዳጄነህ መሐረነ፤ክልሷ

*ሳይኪ*፤2011፣17)፡፡ በተሳሳተ የምናባዊ ስሜት ግንዛቤ ለማንነት ዕውቅና መስጠት እና ዓለምን በመስታውቱ መፈለግ ይስተዋላል፡፡ ይሁን እንጂ በመስታወት የሚታየው ምሥል ነጸብራቅ እንጂ እኔ አይደለም፡፡ የእኛ ማንነት የሚዋቀረውም ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት እና በትኩረት በማየት በ*(gaze*) ነው፡፡ እኛ እውናዊ የምንሆነው ራሳችንን ከሌላ ስንለይ በመሆኑ፣ራስን መምሠል ይገባል፡፡ በተጨማሪም ማንነት በቋንቋ እና በባህል ይዋቀራል፡፡ ኢ-ንቁ ልቦና ግዛቱ እና መዋቅሩ *በፋንታዚ* ለመተካት የሚያነሳሳ ነው (Bertens, 2001,160)፡፡ ‹‹ከምናባዊ በፊት በጫና እና በእምቢተኝነት ስሜት ትእምርታዊ ሥርዓት ይከሠታል›› (Lacan,1980,10)፡፡

‹‹ሐሳባዊ ኢጎ›› ውስጣዊ ሲሆን ‹‹የራስ›› ስሜት መገንቢያ ‹‹ራስ›› የእኔ ማንነት በስሕተት መለየት በሐሳባዊ ኢጎ እኛ ስለ ራስ የምናስበው የእጦት አስተያየት የሌለበት እና ያልተሟላ ነው፡፡ ሕጻኑ በመስታወት የሚያየው የተረጋጋ የራስ ሕብረት እና ምልዑነት የሚታይበት ነው፡፡ ከእናቱ አካል ጋር ያለው የእጦት ሕብረት፤እንደ Lacan, የራሳችን እጦት ሕብረት፣ የእናት አካል ተፈጥሯዊ ግዛት የሆነው ‹‹እውናዊ›› ወደ ‹‹*ባህላዊ እና የቋንቋ ሥርዓት*›› በሚሸጋገርበት ጊዜ በተሳሳተ መልኩ እጦት የለም በሚል ከመቋጨት ይልቅ የእኛን እጦት ማወቅ እና *መጠየቅ* ያስፈልጋል፡፡

Lacan, እንደሚገልጹት የሕጻኑ የራስ ጽንሰ-ሐሳብ ኢጎ የእኔ ማንነት ከእኛ ሕልው የመስታወት ምሥል ጋር የማይዛመድ ይሆናል፡፡ የሕጻኑ **ሌ**ላን በስሕተት ማወቅ፣የመስታወቱን ምሥል በማውሳት የራሱ አዛዥ ይሆናል፡፡ *በምናባዊ ሳይኪ ደረጃ* ሕጻኑ በመስታወት የሚያየው ምሥል የራስ ነጸብራቅ ነው፡፡ የመስታወት ደረጃ ራስ (**ሌ**ላ)፣*dichotomy,* በቀደመው ጊዜ ሕጻኑ የሚያውቀው ‹‹**ሌ**ላ›› ራስ አይደለም፡፡ Lacan, *Identification,* ሁልጊዜ ራስ እና **ሌ**ላ የሚሉትን ቃላቶች ከጥንድ ተቃርኖ ጋር ተመሳሳይ አይደሉም በማለት ያብራራሉ፡፡ *self defined what is not other; other defined what is not self* ፡፡ ራስ እና **ሌ**ላ፣ በLacan, እይታ የራስ ሐሳብ በውስጣዊ ሕልው የእኛ ‹‹እኔ›› የሚመሠረተው በምሥሉ **ሌ**ላ የራስ ጽንሰ-ሐሳብ ሲተካ በተሳሳተ መንገድ ምሥሉን እና **ሌ**ላን በመለየት ነው፡፡

Lacan, **ሌ**ላ የሚለውን ቃል የተጠቀሙት ለብዙ ነገር ነው፡፡ በ**ሌ**ላ እና ፍጹም **ሌ**ላ መካከል ያለውን ልዩነት ይገልጻል፡፡ ሕጻኑ በመስታወት የተመለከተው **ሌ**ላ እና ለሕጻኑ የሚሰጠው የ**ሌ**ላ ሐሳብ መዋቅራዊ የማይቻል እኔ\ራስ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ የሕጻኑ ፍጹም የሆነ **ሌ**ላ እና የ**ሌ**ላ ሰው የራስ ምሥል፤ ‹‹የ**ሌ**ላነት ሐሳብን ለመገንዘብ የሆነ ነገር እንጂ የራስ

አይደለም›››፡፡ እንደ Lacan, እይታ **ሌ**ላነት የሚቆጠረው እንደ *ምናባዊ ደረጃ\ከመጠየቅ ጋር* የሚቀናጅ ነው፡፡ ከራስ ስሜት በፊትም የ**ሌ**ላነት ሐሳብ ይዋቀራል (Rawson and Nisbet, 2008, 81)፡፡

የጤናማ ጎልማሳ ስኬታማነት *በትእምርታዊ ሥርዓት* የሚዋቀረው በቋንቋ ሲሆን፣ይህም በራሱ የእሱ\የእሷ  የቋንቋ ሕግ እንጂ ሐሳባዊ አይደለም፡፡ የSaussurean, *ሥምምነት* እና አስታራቂ የሆነ ቁሳዊ ግንኙነትን መግለጽ ቢሆንም፣በLacan, ትንታኔ ግን ቋንቋ  የሚገልጸው ይህንኑ አይደለም፡፡ ለዚህም ማመሳከሪያቸው ሕጻን ልጅ ቋንቋን መናገር እና መመለስ የሚማረው ተፈላጊው ቁስ በሌለበት (በእጦት) ነው፤(በእናቱ ጡት) እሱ የሚማረው ‹የእኔ መሠረታዊ ፍላጎት› እና ሐሳብ ማፍለቅ በመጀመሪያ የራሱ አስፈላጊ ቢሆንም የሚያም እና እረፍት የለሽ ያደርጋል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ከትእምርታዊ *ሥርዓት* ጋር የሚደረግ ግንኙነትም *‹‹በመስታወት ደረጃ››* ሕጻኑ ቋንቋ ማፍለቅ ሲጀምር የሚመለከተውን ይይዛል፡፡ በሌላ ነጸብራቅ ራሱን እና ሌላን በመስታወቱ የሚያውቅ ሲሆን፣የሕጻኑ ምሥል *ሲግኒፋየር* ነው፡፡ በዚህም ሁኔታ ሕጻኑ በመስታወቱ ላይ ያለውን ብቻ በማመን ምሥሉን በተሳሳተ መልኩ ከመረዳት ባሻገር፣የተሳሳተ ትእምርታዊ ቅርጽን ይይዛል፡፡ *‹‹እውናዊ››* ሦስተኛው *ሥርዓት* ሲሆን በሰርክ ከሚያጋጥሙን ተጨባጭ ክስተቶች ጋር ይያያዛል (Wolfreys, et al.,2006, 55)፡፡

በሕጻኑ ላይ በእናቱ እና በእሱ፣በወንድ እና በሴት፣በጎልማሳ እና በሕጻን መካከል የሥነ-ልሳናዊ (የባህላዊ *ሥርዓት*) ልምድ ልዩነት መኖሩን መለየት ይጀምራል፡፡ ይህም የኤዲፐልዜሽን ሒደት ሲሆን፣በእናት እና በልጅ መካከል ያለውን ግንኙነት በመነጣጠል እና የአዋኪነት ስሜትን በመፍጠር፣ሦስትዮሽ *(እናት-አባት-ሕጻን)* እንዲስተዋል ያደርጋል፡፡ የትእምርታዊ አባት ትእይንት ጣልቃ መግባት፣የፋለስ ተግባር እንዲረበሽ እና *ለSym-biosis,* በር በመክፈት በእናት እና በሕጻኑ መካከል ክፍተት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

Lacan, ‹‹ኢጎ››ን እኔ ወይም የራስ ምሥል በማለት የሚጠሩት ሲሆን፣ሕጻኑ በተሳሳተ መልኩ የራሱን ምሥል ከመስታወቱ ይለያል፡፡ ሕጻኑ የራሱን እና በመስታወት የሚያየውን ምሥል በተሳሳተ መንገድ መለየት ፋለስ *(m)other* እና ተከታታይነት ያለው **ሌ**ላ ምሥል እና ምሥሉ የሚያንጸባርቀው **ሌ**ላ በማኅበረ-ባህላዊ ሕጉ ላይ የሚመሠረት ነው (Green, K., and Lebihan, J.,1996, 164-165)፡፡

በሕጻኑ ላይ የ**ሌ**ላነት ሐሳብ ሲፈጠር የራሱን **ሌ**ላ በመለየት፣በራሱ የመስታወት ምሥል ወደ ትእምርታዊ ደረጃ መሸጋገር ይጀምራል፡፡ ይሁንና ትእምርታዊ እና ምናባዊ ሥርዓቶች ባንድ ላይ ሊከሠቱ ይችላሉ፡፡ በዚህም ጊዜ የእኛ ወደ መዋቅራዊ ሥርዓት መሸጋገር በእኔ*ኑ* ንግግር **ሲግኒፋየርን** ከሲግኒፋይድ ጋር በማያያዝ ይጠቀማል፡፡ የቃላት ትርጓሜ የእኛ የራስ ነጸብራቅን እኔ ብሎ መናገር፤በምናባዊ የራስ ምሥል ነጸብራቅ ነው፤በማለት ያብራራሉ (Rawson and Nisbet, 2008, 82)፡፡

## 2. 1. 7. ፋለስ (*Phallus)*

ፋለስ ከሃፍረተ-ሥጋ የሚለይ ሲሆን ‹‹ሃፍረተ-ሥጋ የአጥንት እና የደም ተቃይጦ ውጤት ነው›› (Green,K., and Lebihan, J.,1996,172-173)፡፡ በሌላ መልኩ ‹‹ሃፍረተ-ሥጋ እውናዊ የአካል ክፍል ሲሆን ፋለስ ግን ምትሃታዊ በምናባዊ እና ትእምርታዊ ሥርዓት የሚወከል ረቂቅ ኃይል ነው፡፡ ‹‹ምትሃታዊ የሆነ *ቀጭን በትር* (*Magical Wand)፣ቀጥ ያለ አካል (ቁስ)* ሲሆን ትርጓሜው ተለዋዋጭ እና በእሴቶች ላይ የሚመሠረት ነው›› ሲሉ ማብራሪያ የሚሰጡት ደግሞ (Ellmann,1994,20) ናቸው፡፡ Lacan ለኤዲፐስ ኮምፕሌክስ፣ለካስትሬሽን (መኮላሸት) ኮምፕሌክስ እና ለጾታዊ ልዩነት እንደገና የተረጎሙ ሲሆን *ፋለስ* የሚወክለው ኃይልን ነው ይላሉ፡፡ ፋለስ እና *መኮላሸት (Castration)* የጥንድ ተቃርኖ ሲሆኑ፣መኮላሸት የሚወክለው የኃይል እጦትን ነው፡፡ ‹‹ፋለስ ሞተር ነው፡፡ የሴት ሥራ ሕጻን መንከባከብ ሲሆን፣ሠራተኛ ወንድ ቤት በመገንባት፣በእርሻ እና ከበድ ባሉ ሥራዎች ይመሠላል›› የሚሉት ደግሞ (Hill, 1997,103) ናቸው፡፡

በትእምርታዊ ሥርዓት ቋንቋ በራሱ ‹‹የእጦት›› ሐሳብ **ሲግኒፋየርን** ያቀርባል፡፡ የእኔ ጠጣር ነገር፤የመስታወት ምሥል ሲግኒፋይድ፣ራስን በእጦት ለመካስ እና ለመግለጽ የቋንቋ ሚና የጎለበተ ነው፡፡ Lacan, የ**ሌ**ላ እና **ሌ**ላ እጦትና የእኔ ማንነትን በተሳሳተ ሁኔታ መለየት ራስ **ሌ**ላ (**ሌ**ላ) በትእምርታዊ ሥርዓት ከሕጻንነት እስከ ጎልማሳነት የሚስተዋል እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ **ሌ**ላነት ‹‹*በእማ (አባ)*›› ጨዋታ በመስታወት ደረጃ በራስ እና በ**ሌ**ላ መካከል ያለ መዋቅራዊ የሐሳብ ልዩነት ነው፡፡

Derrida, የሥልት (የትእምርታዊ) ማዕከል ከ**ሌ**ላ ጋር ግንኙነት ያለው እና የ**ሌ**ላ ማዕከል ምንም እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ሰው የሚፈልገው ሁሉም ነገር የ**ሌ**ላ ቦታ (መፈጠሪያ) ቀጣይነት

ያለው እጦት ሲሆን፣ይህንም Lacan, ፍላጎት ይሉታል፡፡ ፍላጎት በራሱ **ሌላ** ፍላጎት ሲሆን፣ ይህም ፍላጎት እንደማይሟላ አስረጅ ነው፡፡ ፍላጎት ከሌለ አካል (ከመሠረታዊ ፍላጎት) እና የት ነው? ከሚል መጠየቅ የሚመሠረት ነው፡፡ የፍላጎት ማዕከል የትእምርታዊ ሥርዓት ማዕከል በመሆኑ፣ የLacanian, **ሌላ** ጽንሰ-ሐሳብ **ፋለስ** ነው፡፡ ይህም የራስ መዋቅር ከሌላው ጋር ያለው ግንኙነት የሚገለጽበት ነው፡፡ የ**ሌ**ላ ሐሳብ እና የራስ ፍላጎት ከ**ሌ**ላ ጋር በመዋሃድ የሕጻኑ *መጠየቅ* የራስ (የ**ሌ**ላ) መከፋፈልን ያጠፋል፡፡ ከዚያም ሕጻኑ *(child)* መዋሃድን በማቋረጥ እናት የምትፈልገው ምንድን ነው? በማለት የእናቱን ፍላጎት ለማሟላት ይሞክራል፡፡ የእናት ፍላጎትም ወደ ትእምርታዊነት ይሸጋገራል፡፡ በጎልማሳነት ‹‹የራስ›› ‹‹**እ**ጦት**እ**ጦት›› *(lack\| Lack)* የእናት ፍላጎት **ሌ**ላ ነው፡፡ የ**እ**ጦት ቦታ ‹‹*ምንም*›› ነው (Rawson and Nisbet, 2008, 83)፡፡

በትእምርታዊ ሥርዓት እናት በአባት ሥም የምትተካ ከመሆኑ በተጨማሪ የማኅበረሰብ ክልከላ እና የአባዊ ሥልጣን የሚስተዋልበት ነው (Tyson,2006,30-31)፡፡ በLacan ለማኮላሸት መዛት ሜታፈር በ ‹‹**እ**ጦት›› *(Lack)* በመዋቅራዊ ጽንሰ-ሐሳብ የሚወከል ሲሆን፣እውናዊ አባት በሌለበት ለማኮላሸት መዛት ይኖራል፡፡ ምክንያቱም የ‹‹**እ**ጦት›› *(Lack)* ጽንሰ-ሐሳብ በቋንቋ መዋቅር ከእውናዊ አባት ይልቅ በ**ሌ**ላ የትእምርታዊ መዋቅር መርሆ ይከሠታል፡፡ የአባት ሥም (የአባት ሕግ) *(Name-of-the-Father\the Law-of-The-Father)*፣(Rawson and Nisbet, 2008,84)፡፡ የራስ በቋንቋ መገዛት እና መማረክ እንዲሁም በአባዊ ሕግ የመገዛት አስፈላጊነት ወደ ትእምርታዊ ሥርዓት ያሸጋገራል፡፡ Lacan, ለቋንቋ መዋቅራዊ ሕጉ ተገዥ መሆን የሚያስፈልግ ሲሆን፣የአባዊ ሥርዓት ከትእምርታዊ ጋር የሚቆራኝበት እንደሆነ ሰፋ ያለ ትንታኔ ይሰጣሉ፡፡ በቋንቋ መዋቅር የአባዊ ሕግ ማዕከሉ **ሌላ** ሲሆን፣የምልዑ መዋቅሩ ተገዥነት የሚወሰነው ደግሞ ከሥልት ጋር ባለው ግንኙነት ነው፡፡ ማዕከሉም ፋለስ *(Phallus)* ይባላል፡፡ የአባዊ ተፈጥሮ እና ትእምርታዊ ሥርዓት (*Order*) የፋለስ ማዕከሉ የተወሰነ መሆኑ የተረጋጋ መዋቅርን ይፈጥራል፡፡ የፋለስ ማዕከል የቋንቋ ሥርዓት *(Order)* እና ቃል በመሆኑ የፋለስ ጨዋታ ከሲግኒፋየር እና ከሲግኒፋይድ ጋር የተቀናጀ ነው፡፡

ፋለስ ረቂቅ እና *በሲግኒፊኬሽን* የሚከሠት በመሆኑ በአንድ ጾታ ብቻ የተገደበ አይደለም (Rawson and Nisbet,2008,186)፡፡ በሲግኒፋየር አማካኝነት ትእምርታዊ ሥርዓትን ይይዛል››

የሚሉት ደግሞ (Ellmann,1994,26) ናቸው። ሃፍረተ-ሥጋ የሚገናዘበው ከግለሰብ ጋር ሲሆን ፋለስ ግን ለቋንቋ መዋቅር ሕግ ተገዥ ነው። ፋለስ ማዕከል ነው። ለምንድን ነው በምልዑ መዋቅሩ መገዛት ሁሉም ሰው የሚፈልገው? Derrida, የሥልት ማዕከል የለም የሚሉትን Lacan, ‹‹ፍላጎት›› ይሉታል። ‹‹**ፍ**ላጎት›› (*Desire)*፣ ‹‹ፍላጎት›› (*desire*) ለየትኛው እርካታው ነው ማዕከሉ እና ዘዴው ፍጹም ተገዥ የሚሆነው? በማለትም ያብራራሉ (Rawson and Nisbet, 2008, 84) ።

ጾታዊ ማንነት ከቋንቋ ተዛማጅ በመሆኑ ሕጻኑ ከማንነቱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ወንድ (ሴት) ፣አባት (እናት) ወንድ ልጅ (ሴት) ልጅ የሚሉትን ይለያል። ተፈጥሯዊ ልዩነቱም አንዱ ሌላውን እንዲፈልግ ያደርጋል። ‹‹በማሕበረሰብ ሥምምነት መሠረት ፋለስ የአባዊ ሲግኒፋየር ሲሆን፣የአባት ሥም በቋንቋ ሲገለጽ ከፍተኛ ኃይል እና ሥልጣን አለው›› (Bertens, 2001, 161):: ቋንቋ ሲግኒፋየር በመሆኑ ሕጻኑን እውነታ ነው ከሚለው በመነጠል ያልሰከነ ስሜትን ይፈጥርበታል። ‹‹እውነታ ከሰው ልጅ ጋር ግንኙነት ሲኖረው የሚፈለግ አካል ሆኖ ይከሠታል። ምክንያቱም ሲግኒፋየርን በተጓደለ ሁኔታ የመግለጽ ዘዴ የሚፈለገውን አካል እንድናስብ እና ያደርጋል። ምናባዊ የአካል እጦት የእናቱ ያለፈ ጊዜ ሕብረት ነው›› (Jafferson et al., 1986, 153)።

Lacan, ኤዲፐስ ኮምፕሌክስን እውናዊ (አካላዊ) አባት በሌለበት በቋንቋ አማካኝነት ለአባት ሥም ተገዥነት እንዳለው (Ellmann,1994,5; Wolfreys et al., 2006,69) ይገልጻሉ። በጾታዊ ልዩነት ከእናቱ ወደ ሌላ ጾታ ያደርጋል። ሦስተኛው ቃል ትእምርታዊ እና ጨቋኝ ምሥልን ይፈጥራል። **ሌ**ላ፡- የአንስታይ ግዛት ሲሆን፣ **ሌ**ላ (ምትክ ፍላጎት) በእኔ እና በቁሱ መካከል ያለው ግንኙነት አመላካች ነው። ፋለስ ጾታዊ እና ትእምርታዊ ኃይል እና ሥልጣን እንዲሁም በጾታ መካከል የሚኖር ልዩነት *በሚታፈር* እና *በሚታኖሚ* ሲገለጽ ተመጣጣኝ የማይሆንበት ሁኔታ ፋለስ እንደሚባል (Green,K., and Lebihan, J.,1996,177-179) ይገልጻሉ።

የፋለስ ትርጓሜ ምልዑ ነው። የተጨቆኑ ስሜቶች ፍጹም በሆነ የመኮላሸት ፍርሃት ቤተሰብ ‹‹አካለ ሥንኩል›› (*mutilation*) እንዳደረጋቸው በማሠብ እንደ ባላንጣ ይቆጥሯቸዋል። በLacan, ፍካሬ-ልቦና ፋለስ ጠጣር አይደለም። የሳይኪ ቅርጽ ስሜታዊ በሆነ መልኩ በሰው ልጅ የማንነት ስሜት ውስጥ ይኖራል። የወንድ ሃፍረተ-ሥጋ መኖር እኮላሻለሁ ከሚል የስሜት ጭንቀት የሚያላቅቅ አይደለም። Lacan, የኤዲፐስ ሦስትዮሽ (*Oedipal triangle*) እናት-አባት-

ሕጻን፤ አባት ሊደረስበት የማይችል በመሆኑ እናት በሌላ ተፈላጊ ናት፡፡ የእሷ የተጨቆነ ፍላጎት በንቁ ልቦና ይጣራል፡፡ የአባት ቅጣትን በመፍራት እናት የኢ-ንቁ ልቦና ትእምርታዊ ሌላ የፍላጎት አካል ትሆናለች፡፡ በኮንደንሴሽን እና ዲስፕለስመንት ሒደት ሥነ-ልሳን ምትክ ፍላጎት ይሆናል (Ellmann, 1994, 22)፡፡

Lacan, ሕጻኑ የፋለስን ማዕከላዊ ቦታ በእድለኝነት ስሜት እንደሚይዝ ያስረዳሉ፡፡ ምክንያቱም ሃፍረተ-ሥጋ አለና፡፡ ‹‹ልጃገረድ›› *(Girls)* እሷ ለአንድ ተግባር እንደደረሰች ታምናለች፡፡ መኖርን በማጠናከር በተሳሳተ መልኩ ታስተውላለች፡፡ ምክንያቱም ፋለስ በFreud, ተገዥ እና እጦት ነው፡፡ የምእራባውያን  የጥንድ ተቃርኖ መዋቅራዊ ሐሳብ ከወንዱ ሃፍረተ-ሥጋ ጋር የሚቆራኝ ነው፡፡ ልጃገረዷ (*girls*) የሃፍረተ-ሥጋ እጦት፣አለመኖር እና አዋኪነት ጋር ታመሳስላለች፡፡ በፋለስ ቦታ ግን እጦት የለም፡፡ ልጇገረዷ (*girls*) በቃሉ ኃያልነት ፋለስ እንዳለ ታምናለች፡፡ Lacan, በሐሳብ መጽናት በራሱ ፋለስ ነው ይላሉ፡፡ የሁሉም ነገር ባለቤት ቋንቋ ነው፡፡ የትእምርታዊ ሥርዓት ባለቤትነት እና ተገዥነት ለእጦት ነው፡፡ የእኛ በቋንቋ የመኖር ምክንያት ‹‹ማጣት›› *(loss\lack)* ከእናት አካል ጋር ሕብረት አለው፡፡ ከጎልማሳነት ደረጃ ሲደርስም የባህሉ አካል ይሆናል፡፡ የቋንቋ ኃይል መኖር ሁሉም ሰው የሚተረጉመው አለመኖርን (*loss\Lack*) ነው፡፡ በምእራባውያን ፍልስፍና ከእሴት ጋር መኖር የሥልጣኔን ጭምብል አጥልቆ እጦት ይኖራል፡፡ *ውጤታማ የሆኑት (የሠለጠኑት) ያጡት ነገር ስላለ ቢሆንስ?*

በLacan, ትንታኔ ፋለስ ጠጣር (*Anatomical*) እንዳልሆነ ይገለጻል፡፡ በLacanian, እና በFreudian, ፍካሬ-ልቦና መካከል የጾታ ልዩነት ተመሳሳይ አይደለም (Rawson and  Nisbet, 2008,85)፡፡ ይህንንም ከSaussure, ጽንሰ-ሐሳብ አንጻር ሁለት ምሣሌዎችን በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡ የመጀመሪያው፡- ሲግኒፋይየር (ቃል)፣ ሲግኒፋይድ (ቁስ)፤‹‹ዛፍ›› የሚለው ቃል እና የዛፍ ምሥል፤ሁለተኛው ደግሞ፣ ሁለት ተመሳሳይ በሮችን በመሣል ለአንደኛው በር ‹‹ሴት›› (በቃል) ለሌላኛው ደግሞ ‹‹ወንድ›› በማለት በቃል ይሠይማሉ (Rawson and Nisbet, 2008 ,85)፡፡ ሴት እና ወንድ ትእምርታዊ ሥርዓት ሲሆኑ የቋንቋ መዋቅሩ ይለያያል፡፡ የLacan, እይታ ሕጻኑ (*child*) የሚመለከተው ከሌላው ጾታ ጋር ያለን ሲግኒፋየር ነው፡፡ ሕጻኑ የሚገነባው በዓለም እይታ ነው፡፡ በሲግኒፋየር እና በሲግኒፋይድ መካከል ያለውን ልዩነት የሚገነዘቡት ሌላ በማየት ውጤት ነው፡፡ ‹‹ሁለቱን ልጆች ሁለት የተለያየ አገር ቢኖሩ

ነብሳቸው ወደ ልዩ ልዩ አቅጣጫ ለመብረር ጥረት ያደርጋል፡፡›› የሕጻን ጾታ በማየት ሲግኒፋይ **ሌ**ላነት እና ሌላ ጾታ ነው (ገጽ፣86)፡፡

በFreud, እና በLacanን *‹‹የቅናት››* እሳቤ መካከል ልዩነት ያለ ሲሆን Freud, ወንዶች የመኮላሼት ጭንቀት ያለባቸው ሲሆን፣ሴቶች ደግሞ በወንዶች ሃፍረተ-ሥጋ ይቀናሉ *(Penis envy)* ይላሉ፡፡ Lacan, ደግሞ ሴቶች የመኮላሼት ጭንቀትም ሆነ የፋለስ እጦት ፍርሃት ይስተዋልባቸዋል፡፡ በወንዶች ላይ ሴትን ለማግኘት የሚስተዋልባቸው ቅናቶች ስኬታማነት፣ በገንዘብ፣ሞተር ሳይክል፣ አውቶ ሞቢል፣ቤት እና ሌሎች እንዲኖሩት ይፈልጋል፡፡ ከሌለው ግን የምፈልገውን አላገኝም በሚል በተሟላላቸው ይቀናት፡፡ እንደ ባላንጣም ይቆጥራል፡፡ Lacan, ‹‹**እ**ጦት›› *(Lack)* የሴት ብቻ ነው የሚለውን ይቃረናል፡፡ የሁሉም እኔነት የሚመሠረተው በ*Loss,* በአለመኖር እና በውድቀት ላይ ነው (Green, K., and Lebihan, J.,1996,164-165)፡፡ ከዚህ በታች ደግሞ ‹‹ጁዊሶንስ››፣‹‹ፋሎ-ሴንተሪዝም›› እና ‹‹ሳይኮ-ፓቶሎጂ›› የሚሉት ጭብጦች ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

## 2. 1. 7. 1. ጁዊሶንስ (*Jouissance*)

‹‹ጁዊሶንስ›› የፈረንሳይኛ ቃል ሲሆን ደስታ ከሚለው ቃል ጋር አቻ እና ከጾታዊ ግንኙነት ፍላጎት ጋር ተጣማሪ ነው (Wolfreys et al., 2006,59)፡፡ የሕጻኑ በእናቱ እና በትእምርታዊው ሕግ መካከል የጾታዊ ግንኙነት የደስታ ክልከላ ይኖራል፡፡ ሕጉን እና ክልከላውን በተዛባ መልኩ በመቃረን የደስታ ምልክት የሚስተዋልበት ሲሆን *‹‹ጁዊሶንስ››* ይባላል፡፡ ጁዊሶንስ በጾታዊ ግንኙነት የሚገኝ እርካታ ሲሆን ተለዋዋጭ እና ሕግን የሚተላለፍ ነው (Hill,1997,107)::

Bennett and Royle, (2004) Berthaን ዋቢ በማድረግ ‹‹ከምንም ነገር ተነስተን ብንስቅ ሣቁ ምንም ነው››፡፡ ሣቂታው የመሣቅ ፍላጎቱ መገለጫነቱ ለከፍተኛ ደስታ የዳረገው የመሣቅ ፍላጎት እና የሣቂታው ፍላጎት *‹‹ምንም››* ስሜት የማይፈጥር ሲሆን ይችላል፡፡ ትርጉም አልባ፣ በራሱ ምንም የሆነ ነው›› (ገጽ፣178-186)፡፡

Lacan, ደስታ እና ጁዊሶንስ የልቦናን ተግባር የሚያቀላጥፉ ቢሆኑም ልዩነት እንዳላቸው ያብራራሉ፡፡ ጁዊሶንስ አብዝቶ ነጻነትን በመስጠት ሕግን የሚጥስ፣ሌላ ነገር የሚያስረሳ፣ሌላ እና ሌላ የሚስተዋልበት፣እጦት የሚዘነጋበት፣ቅጽበታዊ ምልዑነት የሚስተዋልበት፣ከጭንቀት እና ከፍርሃት መደበቂያ፣በሰውነት ክፍል የሚገኝ ከፍተኛ ደስታ፣አስቸጋሪውን ዓለም አስረስቶ ሌላ

ዓለም የሚፈጥር፣ ከሴቷ ወደ ወንዱ የኃይል ሽግግር የሚታይ ሲሆን፤ *‹‹ደስታ››* ደግሞ ለሕግ ተገዥ ነው፡፡ (Green, K, and Lebihan, J,1996,178; Wolfreys et al, 2006, 78)፡፡ በጁዊሶንስ የሚገኘው ደስታ በሒደት የሚቀንስ ሲሆን ወንዶች (*Masturebatory*)፣ሴቶች (*Clitoris*) የአካል (የስሜት-መዋቅራቸውን) ምናባዊ እና ትእምርታዊ ምሥል በመሣል *ፋንታዚ* በሆነ መልኩ ጁዊሶንስ ሊያገኙ ይችላሉ (Leitch, B. Vincent, 2001, 303)፡፡

በእጦት ተገፊ መሆን በወንድ (በሴት) ሊስተዋል ይችላል፡፡ የእኔ ተንቀሳቃሽ ቦታ፣ግንኙነት ፋለስን መፍቀድ የሚከሠተው በጁዊሶንስ ነው፡፡ ሁሉንም አስተማስሷዊ በሆነ መልኩ አዋኪ ነው፡፡ ጁዊሶንስ ኢ-ንቁ በሆነ መልኩ በሴቷ ቦታ ይስተዋላል፡፡ የ**ሌ**ላ ቦታ፣የሴቷ ክፍል ነው፡፡ ጁዊሶንስ በመጀመሪያ ከፍተኛ ደስታ ቢያስገኝም እየቆየ ሲሄድ ለጸጸት፣ለሕሊና ሕመም፣ ለባይተዋርነት፣ራስን ለመጥላት፣ለብቀላ፣ለእጦት እና ስቃይ፣ለናፍቆት፣ ለ*Obsessional Fear,* ለሌላ መጥፎ ድርጊት ሊያነሳሳ እና አጣብቂኝ ውስጥ የሚያስገባ ሊሆን ይችላል (Green,K, and Lebihan, J, 1996,174)፡፡

## 2. 1. 7. 2. ፋሎ-ሴንተሪዝም *(Phallo-centrism)*

*‹‹ፋሎ-ሴንተሪዝም››* ፋለስ ከአባዊ *ሥርዓተ-ማሕበር ጋር* የሚቀናጅበት ነው፡፡ የፋለስ ማዕከል አባዊ ነው የሚል ሐሳብ የሚቀነቀንበት ነው፡፡ *‹‹ቅድመ-ኤዲፐስ የእማዊ ዘመን›› (Matriarchal epoch)* ነው፡፡ የእማዊ ዘመን በኤዲፐስ ኮምፕሌክስ *ኃያልነት* ይደፈቃል፡፡ የእናት ጡት የነበረውን ሚና ይነጠቃል፡፡ በዚህም ጊዜ እናት በቅድመ-ኤዲፐስ የነበራትን *ኃያልነት* በማስታወስ ትጨነቃለች፤እንዲሁም በፋለስ ናፍቆት ትማስናለች፡፡ በእናት ፍላጎት እና በፋለስ መካከል ያለው ግንኙነት ሲቃኝ የእናት ፍላጎት ፋለስ ነው፡፡ *‹‹ፋሎ-ሴንተሪዝም››* እና *አባዊ* በትይዩ የሚቃኙ ናቸው፡፡ የእናት ፍላጎቷ በዐይኗ ይመላለሳል፡፡ የፋለስ ሚና እና ተግባር የሚቃኝበት ሕግ፣ኮድ፣አድርጉ አታድርጉ (ክልከላ)፣ባህላዊ *ሥርዓት ‹‹ፋሎ-ሴንተሪዝም››* ይባላል፡፡ ሴቶች *ማኅበረ*-ባህላዊ *ሕግጋትን* በመፍራት ፍላጎታቸውን ይደብቃሉ፡፡ የፋሎ-ሴንተሪዝም መፍለቂያ እጦት ሲሆን ወደ ጥንድ ተቃርኖ የሚሸጋገር፣ከ**ሌ**ላ እና **ሌ**ላ እጦት *ጋር* ተጣማሪ ነው (Ellmann, 1994, 23-25)፡፡

Wolfreys et al, (2006) እንደሚገልጹት ደግሞ ፋለስ የኃይል ትእምርት እና የወንድነት የዕድገት ደረጃ ሲሆን *ፋሎ-ሴንተሪዝም* ለወንድ ሕብረት ልዩ መብት የሚሰጥ ነው በማለት ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡ ወንዶች ራሳቸውን እንደ አሸናፊ እና ጀብደኛ ይቆጥራሉ፡፡ በLacanian,

ፍካሬ-ልቦና ሌላ እና **ሌላ** ይስተዋላል፡፡ ሌላ የኢጎ ነጸብራቅ ሲሆን፣ሲግኒፋየር ሊስተካከል የማይችል ምናባዊ እኔነት ለይቶ ማወቅ፣ሴቶች ሁልጊዜ በአባዊ ባህል ቁጥጥር ሥር ናቸው፡፡ በአንስታይ የትችት አንጻር በሥነ-ጽሑፍ ሥራው ፋሎ-ሴንተሪዝም እንዴት ተንጸባረቀ የሚለውን በጥንድ ተቃርኖ ይተነትናሉ (ገጽ፣77)፡፡

Foucault, ኃይል (ዕውቀት) በወንዶች ይወከላል፡፡ የወንድ እና የሴት ግንኙነት በኃይል ዲስኩር፣የበላይ እና የበታች እሳቤ እንዲሁም በማሕበረሰብ ሕግ እንደሚወሰን ያብራራሉ፡፡ የኃይል ግንኙነት መዋቅር በሴት እይታ እጦት ነው፡፡ አባት የተቀባይነት እና የበላይነት ዲስኩርን ማዕከል በማድረግ ተጫኝነት ይስተዋልበታል፡፡ ኃይሉንም በንዴት ቀመስ ዲስኩር ያንጸባርቃል፡፡ የአካል ልዩነት በራስ ሥነ-ልሳናዊ አቅም እና በgaze, የባህል መዋቅር ሥምምነቶች ስለሚተረጎም ቋንቋ ለአካላዊ ልዩነት ጥገኛ ነው (Bertens, 2001, 155)፡፡

## 2. 1. 7. 3. ሳይኮ-ፓቶሎጂ (*Psycho-Pathology)*

Vaknin, (2006) ሳይኮ-ፓቶሎጂን ሲያብራሩ፡- ከሰው ልጆች የሰርክ ሕይወት ተነጥሎ የማይታይ በተገመተ እና ባልተጠበቀ ሁኔታ የአሁን እና የወደፊት ሕይወት ላይ ጥቁረት የሚያቀልም፣ በጽሑፍ፣በንግግር እና በሌላም ጭንቀት፣ድብርት እና ውድቀት ውስጥ በመዘፈቅ የሐዘን ስሜትን የሚፈጥር ነው፡፡ በፍላጎታችን የማንረካበት ያለፈን ኑሮ፣መልካም ተዝናኖት እና ጤንነት በመናፈቅ *በፋንታዚ* የምንቃኝበት ነው (unpaged)፡፡ ‹‹ማኅበረ-ባህላዊ ሥርዓት በሳይኮ-ፓቶሎጂ ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር እና ከባህል ባህል ልዩነት እንዳለው የሚገልጹት ደግሞ (Matsumoto,2001, 296) ናቸው፡፡

*ሁለንተናዊ የሆነ Pneurotic,* ናፍቆት፣ፓቶሎጂካል ኃያልነት የሳይኮቲክ ስብዕና ስቃይን እና *መሠረታዊ የሆነ ውድቀትን* ያስከትላሉ፡፡ *የትእምርተ-ሕይወት ናፍቆት (Sym-biotic Longings)* እና ግንኙነታቸውን ነጣጥሎ ማየት ከባድ ነው፡፡ ከፍተኛ የሆነ ናፍቆት የሚስተዋል ሲሆን ትዕግስት የለሽነት፣ፍርሃት፣የራስን ማጥፋት *(Self annihilation*) እና ከመሠረታዊ ፍላጎት ወደ ኋላ ማለት እና ፍጹም የሆነ የገለልተኝነት ስሜት ይስተዋላል (Lacan,1977, 201)፡፡

እናት መኮላሸትን በራሷ ላይ የደረሰ አድርጋ ትመለከታለች፡፡ በሳይኮቲክ ዕድገት መኮላሸት ከሕጻኑ ጋር ግንኙነት ያለው፣የሕጻኑ መንታ ጉዳዩች ማለትም፡- ትእምርታዊ እና ሥነ-

ፍጥረታዊ ሕብረት የሚስተዋልበት፣ሕጻኑ ከእናቱ የሚለየው ሕልው የሆነ የእናት የአካል ፍላጎት ነው፡፡ የእናት ፍላጎት ፋለስ ነው፡፡ በምናባዊ ፋለስ እናት የሕጻኑን መኮላሸት ትቃረናለች፡፡ ራሷን በጥፋተኝነት ትፈርጃለች፡፡ የትእምርታዊ አባትን እርዳታ እስከ መጠየቅ ይደረሳል (Miller and Richardson, 1982, 23-24)፡፡

በLacan, ተቀዳሚው የመምታታት ምንጭ በኢ-ንቁ ልቦና የኤዲፐላይዜሽን መሠረታዊ ውድቀት የሚስተዋለው የፋለስ ሲግኒፋየር በአባት ሥም መኮላሸት እና ሕጻኑ ከእናቱ በመነጠሉ ለትእምርታዊ ሥርዓት እድል ይሰጣል፡፡ የኢ-ንቁ ልቦና ፍጹም የሆነ ክፍተት እና የውድቀት ጉድጓድ (*hole)* በራሱ የእጦት ሲግኒፋየር ይሆናል፡፡ የትእምርተ-ሕይወት ናፍቆት እና የፍርሃት መስተዋል ውድቀት እና ልዩነት ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ውስጣዊ እጦት የተሸናፊነት እና የከልካይነት ስሜት እንዲስተዋል ያደርጋል፡፡ የመኮላሸት ስሜት ተሸናፊነትን፣ ተስፋ-ቆራጭነትን፣መከዳትን፣ የመመከት ኃይል መሟሸሽን ያስከትላል (Lacan, 1977, 214)፡፡

ኢጎ *(ego*) እና የራስ ፍካሬ-ልቦና እንደ Lacan, እይታ ትኩረት የሚያደርገው አስፈላጊ የሆነ የ‹‹ኢጎ›› ፓቶሎጂካል ተፈጥሮ ወይም ከራስ ይልቅ ለመሠረታዊ ፍላጎት ጥንካሬ ነው፡፡ /ይህም የዋና መሠናክሎች ተገዥነት ይስተዋልበታል፡፡ ‹‹እኔ›› የ‹‹ኢጎ ምሥሉን›› ማፍቀር እና ለዚሁ ምርኮኛ መሆን፡፡ ኢጎ ሕክምናዊ እና ተዝናኖታዊ በሆነ መንገድ *በፋንታዚ* ራስን በ *False Self,* መገንባት ነው፡፡ በድብቁ መሠረታዊ ፍላጎት እና በውጫዊ ቁጥጥር መካከል የሚፈጠር ተቃርኖ ይመጣል፡፡ የተመሠረተባቸው ቃላት አቻዊነት ትርጉምን ያዛባል፡፡ ሕጻኑ በቅድሚያ በራሱ እና በሌላ መካከል ያለውን እጦት እና ልዩነትን ያውቃል፡፡ ከኢጎ ምስል በመውጣትም ወደ ሌላ ማምራት ይጀምራል (Lacan, 1977, 215)፡፡

Foucault, (1962) ከ ‹‹አእምሮ ሕመም›› *(Madness)* ጋር በማስተሳሰር ትንታኔ ይሰጣሉ፡፡ በዚህ ጥናት የሚዳሰሰው ግን ከLacan, ሳይኮ-ፓቶሎጂ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ብቻ ነጥሎ በማውጣት ይሆናል፡፡ ገጸ-ባህርያት ከፍላጎት በመነጨ ‹‹ቅናት›› (*Jealousy*) ይጠናወታቸዋል፡፡ ቅናት፡- ፍቅርን፣ፍትሕን፣አካልን፣የራስ ብቻ ለማድረግ በመፈለግ የሚስተዋል ነው፡፡ ፍላጎታቸውን ለማሳካትም ረቂቅ የሆነ የበቀል እርምጃ ይወስዳሉ፡፡ የ*obsessional,* ቅናት ትእምርታዊ በሆነ መልኩ ሲተገበር እኔ (ሌላ) አቅጣጫ ይስታል፡፡ ያለፈ ጊዜ ምናባዊ ሥርዓት የፓቶሎጂካል ተጣብቆ ይስተዋልበታል፡፡ አንድን ነገር ሆን ብሎ በማሳየት ቅናት እና ጥላቻ እንዲያመረቅዝ ያደርጋል፡፡ ትራውማ፣መፈላለግ፣ባይተዋርነት እና ቁጣ *(hysteric*) እንዲያገረሽ ያደርጋል፡፡ በሒደትም ፍቅር በጥላቻ፣መዋደድ በመለያየት ይተካል፡፡ ሁሉም ነገር እንዳልነበር

ከንቱ ይሆናል፡፡ ሌላ ሰው ለመሆን ቢሞክርም ያለፈው ጊዜ ውል ስለሚለው ለመወሰን ይቸገራል፡፡ ውስጡ **ሌላ** ስላለች **ሌላ** አይፈልግም (Foucault,1962, p. 31,33, 36-37)፡፡

*Obesessional neurosis,* የግል እና የቡድን ፍላጎቶች ይኖራሉ፡፡ የቡድን ፍላጎት ተሟልቶ የግለሰብ ፍላጎት የማይሟላበት አጋጣሚም ይስተዋላል፡፡ በዚህን ጊዜ የእኔን እንጂ የሌሎችን ፍላጎት አልሆንም ማለት ስለማይቻል በሌላ ፍላጎት ተገዥ መሆን አማራጭ የሌለው ጉዳይ ይሆናል፡፡ በግለሰቡ ላይም ቁጣን የሚቀሰቅስ አእምሮን የሚያውክ ዲስኩር ይስተዋልበታል፡፡ ያልፈለገውን የፈለገ በመምሠል ስለሚኖር አእምሮው ከፍላጎት ወደ ፍላጎት ይማስናል፡፡ ‹‹ሕጻናት በሐሳብ እና በጨዋታ ይመሰጣሉ፡፡ ወደ ጎልማሳነት ሲሸጋገርም ራሱን በሐሳብ በማድከም ለሌላ ተግባር ራሱን ያዘጋጃል፡፡ የሌላ እጦት እና ፍላጎት፣ በአስቸጋሪ እና በሚያምታታ ሁኔታ ያልፋል፡፡ ከዚያም የነበረውን ነገር ለመርሳት ራሳቸውን ይደብቃሉ›› (Hill,1997, 99)፡፡

የመቅጣት ፍላጎት፣እጦት እና ግጭት ውስጥ ይሰነቀራል፡፡ በእንቅልፍ መረበሽ፣የመኝታ ክፍልን በየሰዓቱ ማየት፣የጾታዊ ግንኙነት እና እርካታን መቃረን፡፡ መንታነት ስለሚስተዋልበት ካለፈ ጊዜ ልምዱ ጋር ግጭት ይፈጥራል፡፡ በናፍቆት ከውጫዊ እና ከውስጣዊ ኃይል ጋር መጋጨት፣ፍርሃት፣ጭንቀት፣ከሕይወት እና ሞት ጋር መፋጠጥ ይስተዋላል፡፡ ጭንቀቱ በተበራከተ ጊዜ ድርጊት ያረካዋል፡፡ ከሌሎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ይሻክራል፡፡ በሒደትም ለከፍተኛ ስቃይ እና ለሞት ይዳርጋል፡፡ እጦት፣ባይተዋርነት፣መጠየቅ፣መበቃቀል ይስተዋላል፡፡ በእውናዊ ኑሮውም አደጋ ይጋረጣል፡፡ ሌላ ሰው አይቀርብም በራሱ ይሁንታ ብቻ ይመራል፡፡ የራሱን *ፋንታዚ* የሆነ ምናባዊ ዓለም ይገነባል፡፡ ከእውናዊው ጋርም ይጋጫል፡፡ ቃላት በሚፈጥሩት ጭንቀት ደስታን ይነጥቃል፡፡ ከመሠረታዊ ፍላጎቱ፣ከባህሉ እና ከእውነታው ነገር ይፈናቀላል፡፡ በቅዠት ዓለም ውስጥም ይመሽጋል፡፡ ማሕበራዊ ፍንገጣ ስለሚጠናወተው የተከለከሉ (ጸያፍ) የተባሉ ፍላጎቶችን ያንጸባርቃል (Foucault, 1962, p.40, 60, 80)፡፡

## 2. 2. የቀደምት ጥናቶች ክለሳ

ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተዛማጅነት ያላቸው አንድ በአማርኛ ረጅም ልቦለዶች የተሠራ የሦስተኛ ዲግሪ ጥናታዊ ጽሑፍ እና አምስት በውጭ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፎች ላይ የተሠሩ ጥናቶች ተዳሰዋል፡፡ እነዚህ ጥናቶች የተመረጡትም ከዚህ ጥናት ጋር ካላቸው ንድፈ-ሐሳባዊ እና የጭብጥ ግንኙነት (ተቀራራቢነት) አንፃር ነው፡፡

### 2. 2. 1. በአማርኛ ረጅም ልቦለዶች ላይ የተሠሩ ጥናቶች ክለሳ

በአማርኛ ከተገኙ የቀደምት ጥናት መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው በLacanian, የትችት አንጻር የተጠና ጥናት አንድ ብቻ ነው፡፡ ይኸም የሰብለ ወልደኪዳን (2009 ዓ.ም.) ሲሆን፣ ጥናቱም ‹‹የእኔነት ሐተታ በተመረጡ የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች›› በሚል ርእስ የሦስተኛ ዲግሪ ጥናት ጽፋለች፡፡ የበዓሉ ግርማ *ከአድማስ ባሻገር* (1962፣1999)፣ የአዳምረታ *ግራጭ ቃጭሎች* (1997)፣ የዓለማየሁ ገላጋይ *የብርሃን ፈለጎች* (2005) እና *በፍቅር ሥም* (2009) የተባሉ ልቦለዶችን በጥናቷ አካታለች፡፡ የሰብለ ጥናት ዋና ዓላማ በአራቱ ልቦለዶች ውስጥ የእኔነት መገኛ ምንጮች ምን ምን እንደሆኑ ማሳየት ነው፡፡ የሰብለ የእኔነት ሐተታ ትኩረቷ በLacanian, ፍካሬ-ልቦና ማናበቢያነት ‹‹ፋለስ››፣ ‹‹ፍላጎት›› እና ‹‹ባይተዋርነት›› የሚሉ ጽንሰ-ሐሳቦችን ተንትናለች፡፡ ሕልም እንደ ዋና የፋለስ እጦት የፍላጎት መሙያ መድረክ ሆኖ እንደቀረበም አመላክታለች፡፡ ማንነትን በመሥራት የ ‹‹**ሌላ\ሌላ**›› (*other|Other)* ሚና ደምቆ በአራቱም ልቦለዶች ታይቷል በማለት ገልጻለች፡፡ ገጸ-ባህርያቱ ለፍላጎታቸው ምትክ ሲፈልጉ እንደሚታዩ እና የፍላጎት ምትክ የሚሆነው አካል ግን በአገኙት ጊዜ በመተው ወይም ባለመተው ልቦለዶች ልዩነት እንደሚስተዋልባቸው ሐሳብ ትሰነዝራለች፡፡ በእኔነት እና በማንነት መካከል ያለውን ልዩነት እና ርስ በርስ ተጽእኖ አሳይተዋል ትላለች፡፡ በመጨረሻም የገጸ-ባህርያቱ የራስ ማንነት ምሥል እኔነት በማንነታቸው ላይ ትልቁን ሚና ሲጫወት ይታያል በማለት ጥናቷን አደማድማለች (ገጽ፣169-170)፡፡

### 2. 2. 2. በውጭ ቋንቋ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች የተሠሩ ጥናቶች ክለሳ

በLacanian, የትችት አንጻር ዙርያ በውጭ ቋንቋ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች ከተካሄዱ ጥናቶች መካከል፡- Lacan, et al, (1977)፣Vanheule s, and Paul V, (2009)፣Gokariksel,

Banu, and Secor, Anna, (2014)፣ Gardiner, Raleigh M, (2014) እና Komorowski, Jennifer, (2017) ጥናታዊ ጽሑፎች በዘመን ቅደም-ተከተል ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡

የመጀመሪያው፣Lacan, et al, (1977) ‹‹*Desire and the Interpretation of Desire in Hamlet*›› በሚል ርእስ በፈረንሳይ የተጠና ነው፡፡ በጥናታቸው ያካተቱት ‹‹Hamlet›› የተሰኘውን የሼክስፒርን ተውኔት ነው፡፡ የLacan et al, ጥናት ዋና ዓላማ በ ‹‹Hamlet›› ተውኔት ፍላጎት እና የፍላጎት ትርጎሜ ላይ የሚያተኩር ሲሆን የLacan, ፍካሬ-ልቦናን በማናበቢያነት ተጠቅመዋል፡፡ የሐምሌት ተውኔት ፍላጎት እና የፍላጎት ትርጎማ ከተውኔቱ ተዋንያን አንጻር ጊዜ፣ሁኔታ፣የመድረክ አወጣጥ እና አወራረድ አካላዊ ገለጻ፣ሙድ (ድባብ) እና ሌሎችንም ባማከለ መልኩ ከፍላጎት ጽንሰ-ሐሳብ አንጻር ተንትነዋል፡፡ ‹‹Hamlet›› ፍጹም **ሌላ** በሆነ መልኩ ከእናቱ ጋር ጥብቅ ቀረቤታ ያለው ሆኖ ተሥሏል፡፡ ያለፈ ጊዜ እኔነት አብዝቶ የሚጠይቅ እና የሚፈልግ ነው፡፡ ከፍተኛ ፍላጎት በተዋኒያን ዘንድ የሚስተዋል ሲሆን ይህን ለማሳካት የተለያዩ አማራጮችን ይጠቀማሉ፡፡ ሐምሌት በከፍተኛ ሁኔታ ወላዋይነት ስለተስተዋለበት እጦትን አስተናግዷል፡፡ ፍላጎትን *በፋንታዚ* መተካት፣**ሌላ** እና **ሌላ**፣ስሜትን የሚያውክ ንግግር፣ለፋለስ ፍላጎት ተገዥ መሆን እና በዚሁ ምክንያት ለበቀል መነሳሳት ተስተውሎበታል፡፡ ተውኔቱ በእጦት፣በባይተዋርነት፣በምንምነት፣በሐዘን እና በለቅሶ፣እንዲሁም በትራጀዲያዊ ገጽ የተሞላ እንደሆነ ትንታኔ እና ትርጓሜ ሰጥተዋል (ገጽ፣11-52)፡፡

ሁለተኛው፡- የVanheule s, and Paul V, (2009). *‹‹Identity through A Psychoanalytic Looking Glass››* በሚል ርእስ፣Freudian, (አእምሮን በመሳሪያነት), Lacanian, (የመስታወት ደረጃ), እና ጥንታዊ የሆነው Fonagy and Target, (*attachement theory*) በመጠቀም፣ ስለማንነት በየራሳቸው ንድፈ-ሐሳብ በሚያነሷቸው ጥያቄዎች እና በሚሰጧቸው መልሶች ዙርያ ያተኮረ ጥናት ነው፡፡

ሦስተኛው፣Gokariksel, Banu, and Secor, Anna, (2014) ‹‹*The Veil,Desire, and the Gaze: Turning the inside out*›› በሚል ርእስ በቱርክ የአለባበስ ፋሽን እና እስታይል ላይ ያተኮረ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ Lacan, ለመጀመሪያ ጊዜ በ1972 (እ.ኤ.አ) ሴሚናር ያቀረቡትን የአንስታይ ጾታዊ ግንኙነት የParakeet Picasso, የፍቅር ታሪክን መነሻ ያደረገ ነው፡፡ ጥናቱ ማንነትን በእይታ ከመወሰን እና ከመምረጥ ጋር የተያያዙ ሐሳቦችን በሠፊው ይተነትናል፡፡ አለባበስ፣አካል እና በአጋጣሚ የሚታዩ ነገሮችን አይቶ ማፍቀር እና ይህ ነው ማንነት ማለት

አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ልብስ፣ገጽታ እና አካል ተለዋዋጭ ናቸውና፡፡ የተመለከትነውን ሁሉ እውነት ነው ማለትም አንችልም፡፡ በመሆኑም ሃይማኖት፣ፖለቲካ፣ሞራል፣ፍላጎት እና ክልከላ፣ ውበት *(aesthetic)*፣ በአለባበስ፣በፋሽን፣በእይታ መማረክ እና የፍቅር ግንኙነት፣በእኔነት እና በማንነት ምሥል ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር መሆኑን ከንድፈ-ሐሳብ ጋር በማዋሃድ ድምዳሜ ሰጥተዋል (ገጽ፣195-196)፡፡

አራተኛው፣የGardiner, Raleigh M, (2014) ‹‹*Desire and Fantasy: The Condition of Reality between the Self and the Other*›› በሚል ርእስ የተካሄደ የማስተርስ ጥናታዊ ጽሑፍ ሲሆን፣ጥናቱም ፍላጎት እና *ፋንታዚ*፣በእኔ እና በ**ሌላ** መካከል ያለውን እውናዊ ሁኔታ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በሰው ልጆች ላይ የፍላጎት እና *የፋንታዚ* ተግባር፣ጉዞ እና ምናባዊ ሥርዓት፣ፋለስ (ኤዲፐስ ኮምፕሌክስ)፣በራስ እና በ**ሌላ** መፈጠር መካከል ያለ ልዩነት፣ፍላጎት እና **ሌላ**፣*የፋንታዚ* ተግባር (ምትክ ፍላጎት)፣*የፋንታዚ* ተግባር በሲኒማ፣ በሚሉት ርእሶች ላይ የተመሠረተ ጥናት ሲሆን የማናበቢያ የትችት አንጻሩ፣Lacanian, አንስታይ ነው፡፡

አምስተኛው፣Komorowski, Jennifer, (2017) ‹‹*The Voice as an Object of Desire in the work of* Ann Quin›› በሚል ርእስ የተካሄደ የማስተርስ ጥናታዊ ጽሑፍ ነው፡፡ በብሪታኒያዊቷ እውቅ ኤክስፐርመንታል ደራሲት (*Experimental Writer*)፣Quin Ann, *ሥራዎች* ዙርያ ማለትም፡- *The Silent Voice*, *Letters & Journals* እና *Women Writers* አተኩሯል፡፡ ንድፈ-ሐሳባዊ *መሠረቱም* Lacanian, አንስታይ ነው፡፡ በቋንቋ ሳይቀር ወንዶች በሴቶች ላይ የሚያሳድሩት ተጽእኖ ከባድ ነው በሚል፣ኤዲፐስ ኮምፕሌክስን በመቃረን፣ ኤሌክትራ ኮምፕሌክስን ይጠቀማሉ፡፡ የKristevaን ሐሳብም መሠረት አድርጎ ተንትኗል፡፡ በመጨረሻም Quin. አባዊ የሆነውን የቋንቋ አጠቃቀም በመቃረን ሴቶች ፍላጎታቸውን መግለጽ እና ፍካሬ-ልቦናዊ ስሜታቸውን የሚጎዱ ነገሮች እንደገና እንዲዋቀሩ በሚገልጽ መልኩ የተደረሱ ናቸው በሚል ጥናቱን ያጠናቅቃል፡፡

ከላይ በተገለጸው መሠረት ይህ ጥናት ክለሳ ከተደረገባቸው ቀደምት ጥናቶች የሚለየው፣ከሰብለ ጥናት አንጻር የመጀመሪያው ልዩነት ለጥናት በተመረጡ ልቦለዶች ሲሆን፤የዚህ ጥናት ትኩረት *በቃል ኪዳን ረጅም* ልቦለድ ነው፡፡ ሁለተኛው፡- ለጥናት ይዛው በተነሳችው ዋና ዓላማ እና በሚተነተኑ ጭብጦች ዙርያ ልዩነት አለው፡፡ የLacan et al., ጥናት ስለፍላጎት የተነተነ እና የተረጎመ ቢሆንም ከዚህ ጥናት ጋር የዘውግ ልዩነት አለው፡፡ የGokariksel, and Secor,

ጥናት በሥነ-ጽሑፍ ዘውግ ሳይሆን የቱርክ የፋሽን እስታይልን ከሃይማኖት እና መሠል ጉዳዮች ጋር በማዛመድ ያጠና መሆኑ ከዚህ ጥናት ይለያል። የVanheule, ጥናት ሦስቱ አራማጆች ንድፈ-ሐሳብ ላይ የሚያተኩር ነው። የGardiner, እና የKomorowski, Lacanian, አንስታይ ላይ በማተኮራቸው ይመሳሰላሉ። ልዩነታቸው ደግሞ Gardiner, ፋንታዚን ከፍላጎት ጋር በማዛመድ በሲኒማ ሲያተኩር፣Komorowski, በአን ኩዊን ሥራዎች ላይ ማተኮሩ ናቸው። ከዚህ በላይ የተከለሱት ጥናቶች ጠቅለል ተደርገው ሲወሰዱ በመጽሐፍ ምርጫ፣በሚተነተኑ ሐሳቦች፣በዘውግ እና መሠል ልዩነቶች ቢስተዋልም፤በሌላ መልኩ በጥናቶች ውስጥ ‹‹ፍላጎትን›› በቀጥታም ይሁን በተጓዳኝ የነኩ ናቸው። ይህ መሆኑም ለዚህ ጥናት ጠቃሚ ግብዓት ሊያስገኝ ችሏል።

# ምዕራፍ ሦስት፡- የፍላጎት ትንተና

ይህ ምዕራፍ በተመረጠው ረጅም ልቦለድ ማለትም፡- *ቃል ኪዳን* ላይ የተደረገውን የLacanian, የፍካሬ-ልቦና ትንተና እና ፍካሬ የያዘ ነው፡፡ የምዕራፉ የትንተና አደረጃጀት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የተደራጀ ነው፡፡ እነሱም፡- ‹‹ፍላጎት›› ፣‹‹የመስታወት ደረጃ (ባይተዋርነት)›› እና ‹‹ፋለስ›› የሚሉ ጭብጣዊ ርእሶች የተሰጣቸው ሲሆን፣ የጭብጦቹ ትንተናም በተጠቀሰው ቅደም ተከተል መሠረት የሚቀርብ ይሆናል፡፡

ወደ ትንተናው ከመግባታችን በፊት ግን በተጠቀሱት ሦስት የፍካሬ-ልቦና ጭብጦች (ጽንሰ-ሐሳቦች) መካከል ያለውን ተዋረዳዊ ደረጃ እና ግንኙነት በአጭሩ ማብራራቱ አስፈላጊ ነው፡፡ ይኸውም፡- የጥናታዊ ጽሑፉ የርእስ ሐረግ ውስጥ የመጀመሪያው ቃል ‹‹ፍላጎት›› መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ዐብይ ርእስ ጉዳይ (ጭብጥ) ይህ ‹‹ፍላጎት›› የሚለው ቃልና ቃሉ የሚወክለው የፍካሬ-ልቦና ጭብጥ (ጽንሰ-ሐሳብ) መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በተመረጠው ረጅም ልቦለድ ላይ የተካሄደውን የመረጃ ትንተና በሚይዘው ምዕራፍ ሦስት ውስጥም ‹‹ፍላጎት›› ሰፋ ያለ እና ጠቅላላ ርዕሰ ጉዳይ (ጭብጥ) ስለሚሆን፣ በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ የሚተነተኑት ሌሎች ባይተዋርነት እና ፋለስ የተባሉ የፍካሬ-ልቦና ጽንሰ-ሐሳቦች ‹‹የፍላጎት›› ገጽታዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን በተወሰኑት የፍካሬ ልቦና ጽንሰ-ሐሳቦች መካከል ያለውን ተዋረዳዊ የደረጃ ልዩነት መለየት አስቸጋሪ የሚሆንበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በተቃራኒው ጽንሰ-ሐሳቦቹ ከሚኖራቸው ልዩነት ይልቅ ከሚጋሩት ጥምረት አንጻር ሊጠኑ (ሊተነተኑ እና ሊፈከሩ) የሚችሉበት ሁኔታ የተለመደ ነው፡፡ ይህ አይነቱ ሁኔታ በዚህ ጥናት ውስጥ ለሚተነተኑት ዋና ዋና የፍካሬ-ልቦና ጽንሰ-ሐሳቦችም (ማለትም፡- ‹‹ፍላጎት››፣ የመስታወት ደረጃ [ባይተዋርነት]›› እና ‹‹ፋለስ›› ) መገለጫ የሚሆኑ ይመስላል፡፡

በተጨማሪም፣ ከሦስቱ ጽንሰ-ሐሳቦች ጋር የተቆራኙ፣የግድ አብረው የሚነሱ ሌሎች የፍካሬ-ልቦና ጽንሰ-ሐሳቦች ማለትም፡- ጁዊሶንስ፣ፋሎሴንተሪዝም እና ሳይኮ-ፓቶሎጂ የሚሉ ጭብጦች ራሳቸውን ችለው በርእስ ደረጃ ሳይሆን እንደ አስፈላጊነታቸው ‹‹በፋለስ ትንተና›› ውስጥ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ እንዲሁም ለትንተና ከተወሰዱ ቀጥተኛ ጥቅሶች ውስጥ ቃላት \ ሐረጋት\ዐ.ነገሮችን በመምረጥ ‹‹አጽንዖት›› ለመስጠት ሥልተ ኢታሊክ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

## 3. 1. ፍላጎት (*Desire*)

የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ የርእስ ሐረግ ውስጥ የመጀመሪያው ቃል ‹‹ፍላጎት›› የሚለውን ጽንሰ-ሐሳብ ለመተንተን (እታፈራሁ፣ድጋፌነህ፣መስፍን፣ፀሐይ እና ጥጉ)፣የተባሉ ዋና ገጸ-ባህርያትን ኢ-ንቁ ፍላጎቶች፣ዝንባሌዎች፣እጦቶች፣የቋንቋ አጠቃቀም፣የሚወዷቸው እና የሚጠሏቸው ነገሮች፣ለፍላጎታቸው ብለው የሚፈጽሟቸውን ድርጊቶች፣አስተዳደግ፣ጾታዊ ግንኙነት፣ፍላጎት እና ግላዊ ባህርይን፣ሕልሞች\ቅዥት ወ.ዘ.ተ. ይተነተናል፡፡ እንዲሁም ኢ-ንቁ ፍላጎትን ለማሟላት በሚደረገው ጥረት ገጸ-ባህርያት የሚያጋጥማቸው ፍርሃት፣ጭንቀት፣ስቃይ እና ወ.ዘተ ተተንትኗል፡፡ ልቦለዱ በእጦት የሚጀምር ሲሆን፣ራሄል እና ጥጉ የመስፍን የ**ሌ**ላ ፍላጎት ማሟያ ሆነው የድጋፌነህን እና የፀሐይን ፍቅር እንዴት እንደፈተኑት የጥናቱን ጥያቄዎች የሚመልሱ ሐሳቦችን ከልቦለዱ ነቅሶ በማውጣት ትንታኔ ተሰጥቷል፡፡

ምዕራፍ አንድ በመጠጥ ቤት ትርምስ ይጀምራል፡፡ ስለአባ ውቃው ማንነት የሚያውቅ የለም፡፡ ለነገሮቹ ደንታ የለውም፡፡ ጠጪ ነው፡፡ ሲሰክር ‹‹ምን ዋጋ አለው!›› ማለቱ የሰርክ ጩኸቱ እና ፉከራው ነው፡፡

> *‹‹ምን ዋጋ አለው...››* በማለት ድምጹን ከፍ አድርጎ ይጮኸል፡፡ ጉልበቱ ድረስ የተተረተረው ሱሪው ከእግሩ *ሥር* ደንቃራ እየሆነበት አላስኬድ በማለት ይጠልፈዋል፡፡ የሰፈሩ ሕጻናትም፤ ‹‹አባ ውቃው! አባ ውቃው›› በማለት ከኋላው እየተከተሉ ከመቆሸሹ የተነሳ ወደ ቡና አይነት መልክ የተቀየረውን እና መሬት ለመሬት የሚጎተተውን ጋቢውን በጭንቅላቱ ላይ እየጣሉበት ይጮኸሉ፡፡
> ‹‹አንተ *ዘረ-ቢስ*፣መድረሻ የሌለህ›› በማለት ከተቆጣ በኋላ ጋቢውን ከጭንቅላቱ ላይ ያወርዳል፡፡
> ‹‹...ምን ዋጋ አለው! ምን ዋጋ አለው!›› በማለት ይጮኽና እንደገና ወደ ሰማይ ይዞር እና ተንበርክኮ አንድ ዐይኑን ጨፍኖ እንደ ተኳሽ ያነጣጥራል፡፡ ይፎክራል... [አጽንዖት የእኔ]
>
> (ጌታቸው ፣1982፣4-5)

Lois Tyson, እንደሚሉት ‹‹የፍላጎት ምንጭ እጦት ሲሆን ‹‹እጦት›› በትእምርታዊ ሥርዓት ይገለጻል›› (2006፣28) ይላሉ፡፡ Ellmann, ደግሞ ‹‹Lacan, ለፍላጎት፣Sartre, ‹‹ለምንምነት›› (*being & Nothing-ness*) ጽንሰ-ሐሳብ ጋር በሚሠምር መልኩ ‹‹ምንምነት በማሕበራዊ ውቅር ትእምርታዊ ሥርዓትን ይይዛል›› (1994፣2) ይላሉ፡፡ አባ ውቃው *‹‹ምን ዋጋ አለው!››* እንዲል ያደረገው እና ደንቃራ የሆነበት እጦቱ ነው፡፡ ‹‹ምንም›› የሆነበት ፍላጎቱ የቱ ነው?

በምንምነት ውስጥ ሌላ ፍላጎት አለ፡፡ የአባ ውቃው ትእምርታዊ ዓለም የሌላ እጦትን ፈጥሮበት የሌላ ስሜቱ በእረፍት አልባ የምናባዊ ዓለም መዋቅር እንዲዋልል አድርጎታል፡፡ የሕጻናት ጩኸት እና ድርጊት ሲግኒፋየር ሆኖ ስለረበሸው ወደ ኢ-ንቁ ልቦናው በመመሸግ እጦት ፍላጎቱን *‹‹ዘረ-ቢስ››* በማለት ይገልጻል፡፡ ወደ ሰማይ ያንጋጠጠ ደግሞ የምናባዊ ዓለም እጦቱ የሆኑትን ዘመድ ልጆቹን *በፋንታዚ* ዓለም ለማየት እና ለእጦቱ ምክንያት የሆነውን ለመውቀስ ነው፡፡ በሌላም እሱ በሕይወት በመኖሩ ለማመስገን እና ዕድሜ እንዲሰጠው ተማጽኖ እያቀረበ ነው፡፡ ትእምርታዊ የሆነው አገላለጽ እጦት ፍላጎትን የሚያሣይ፣የታጨቀ ሐሳብ ያለበት እና የትረካውን ሠንሠለት አሻጋሪ ነው፡፡

ወ\ሮ እታፈራሁ በባላቸው ሞት አዝነዋል፡፡ ከዚያም ባላቸው የልጃቸው ክርስትና ዕለት የገለጹትን የራስ እረፍት የለሽ ‹‹ፍላጎት›› በትዝታ ተሻግረው ያስታውሳሉ፡፡

> *…እንደ ሕጻን ልጅ እየፈነደቀ፤‹‹የእኔ ልጅ ዶክተር መሆን አለበት…ዶክተር ሆኖ ወገኑን ከበሽታ የሚፈውስ እውቅ ዶክተር፣…የለም…የለም ልጄ ወታደር ነው መሆን ያለበት…ጀግና…ጀግና ወታደር አገሩን ወገኑን ጠባቂ…የለም…የለም ልጄ መሀንዲስ …መሀንዲስ መሆን ነው ያለበት…ኅበዝ መሀንዲስ ሕንጻ ሠሪ… ድልድይ ሠሪ…የለም ልጄ አሮፕላን ነጂ…ነው በማለት ጮቤ እየረገጡ በመፈንደቅ፣የለም እናቱ ትወስን ዘጠኝ ወር ተሰቃይታለች ‹‹እታፈርዬ አንቺስ ለዚህ ለተወዳጁ ልጃችን ምን እንዲሆን እንደምትፈልጊ ተናገሪ እስኪ የእኔ ዓለም…ብቻ ድኃ በሕልሙ ቅቤ ባይጠጣ እየተባለ…››*
> *…እኔ እውን አደርገዋለሁ፡፡…ደስታዬን፣ዓለሜ ሁሉ ይህን ልጅ ለቁም ነገር ማብቃት ብቻ ነው፡፡ ፍላጎትሽን ተናገሪ…፡፡*
> (ጌታቸው ፣1982፣6)

Lacan, *እንደሚሉት ‹‹የሰው ልጅ ልቦና የፍላጎት ከረጢት\መፈልፈያ ሲሆን መሠረታዊ ፍላጎቱን እና ፍላጎቱንም በራሱ እና በሌላ ለማሟላት ይጥራል››* (Bennett A. and Royle N,2004,180)፡፡ የይስማሸዋ ፍላጎት ከጽንሰ-ሐሳቡ ጋር የሚሠምር ነው፡፡ ወ\ሮ እታፈራሁ ባላቸው ለልጃቸው የገለጹትን ፍላጎት እንዲያስታውሱ ያደረጋቸው፣የልጃቸው ፍላጎት *‹‹ምንም››* ይሆናል የሚል ስጋት ስላደረባቸው ነው፡፡ ልጃቸው ድጋፌነህ የተባለው እና ‹‹ድጋፍነቱ›› ይህችን ምድር ሲቀላቀል የጀመረው፣ ቤተሰቦቹ የምናባዊ ዓለም ‹‹እጦት ፍላጎታቸው›› በበኩር ልጃቸው እውን እንዲሆን ፍላጎት ስለነበራቸው ነው፡፡ ይህም የትእምርታዊ ፍላጎት ማሚያነቱን የሚያሣይ ነው፡፡ ይስማሸዋ እናት ለልጇ ያላትን ፍላጎት ምን እንደሆነ ይጠይቅ እና መልሷን

ሳይጠብቅ የልጇን ፍላጎት ‹‹እኔ ብቻ›› አሟላዋለሁ ማለታቸው ‹‹አባዊነትን›› ጠቋሚ ነው፡፡ ‹‹ድኃ በሕልሙ ቅቤ ባይጠጣ…›› ያሉም ፍላጎታቸውን በሕልም ዓለም *ፋንታዚ* ስላሟሉ ነው፡፡

ወ\ሮ እታፈራሁ የባላቸውን ደስታ እና ልጃቸው እንዲሆንላቸው የሚሹትን ፍላጎት ባስታወሱ ጊዜ *‹‹የ ምን ነበር* ?›› ጥያቄዎች ያነሳሉ፡፡ ‹‹ምን ነበር እኔንም ብታስከትለኝ ?…ምን በደልኩህ አንተ ከዳተኛ…ምን ነበር የልጅህን መጨረሻ ብታየው›› በማለት ይንሰቀሰቃሉ፡፡ ‹‹አሁንስ አበዛሽው ጠዋት እና ማታ እያለቀስሽ ዐይንሽን ልታጠፊው ትፈልጊያለሽ እንዴ? ›› በለቅሶ ምንም የሚገኝ ነገር የለም…›› (ጌታቸው፣1982፣7)፡፡

ወ\ሮ እታፈራሁ *‹‹በየ› ምን ነበር ?››* የፍላጎት ጥያቄዎች ያነሱት የ**ሌ**ላ ፍላጎታቸውን ለመግለጽ ሲሆን፣ለጥያቄዎቻቸው ምክንያት የሆናቸው ባላቸው ለልጃቸው ያንጸባረቁት ፍላጎት ነው፡፡ የልጃቸውን ፍላጎት እንዴት እንደሚያሳኩ እና መጨረሻው ምን እንደሚሆን አሳስቧቸው ነው፡፡ የልጃቸውን ፍላጎት የማሟላት ኃላፊነታቸውን በሞተው ባላቸው ይሽፍናሉ፡፡ ይህም የልጃቸው ፍላጎት ካልተሟላ ‹‹ለሙት መንፈስ›› ቃል አባይ እሆናለሁ ከሚል ስጋት የመነጨ ሲሆን፣‹‹ምን በደልኩህ አንተ ከዳተኛ›› ማለታቸውም ለዚህ ነው፡፡ ድጋፌነህ *ዐይንሽን* ልታጠፊ ነው ማለቱ ደግሞ መተኪያ የሌለውን ዐይናኗን እንዳታጠፋ ስለፈለገ እና ፈርታ ለቅሶ እንድትተው ነው፡፡ በሌላም ‹‹እንደ ዐይኗ ብሌን›› የምታየውን ልጇን እንዳታጣ እያስጠነቀቃት ነው፡፡

ድጋፌነህ የእናቱ ለቅሶ አባቱ ሊሞት ሲል ያስገባውን ቃል እንዲያስታውስ አድርጎታል፡፡ ቃሉም እንዲህ የሚል ነበር፡፡ ‹‹…በብርድ በሽታ ተለክፈው ብዙ ከታመሙ በኋላ እንደማይድኑ በተረዱ ጊዜ ትምህርትህን ጨርሰህ እናትህን እርዳት፣መልካም ጸባይ ያለህ ምስጉን ሁን፣አገርህን በሐቅ አገልግል፣ለወግ ለማዕረግ ያብቃህ›› (ጌታቸው፣1982፣9-10) አሉት፡፡ የአባቱ ቃል የወደፊት ፍላጎት ማሳኪያ ማስጠንቀቂያ አከል ምክር ነው፡፡ ይስማሸዋ ቃል ማስገባቱ ከሞተ በኋላ ልጁ እንዲሆንለት የሚፈልገውን ለመግለጽ ነው፡፡ ይህም የሰው ልጅ ከሞት በኋላ የሚፈልገው እንዳለ ጠቋሚ ነው፡፡

ድጋፌነህ ከአባቱ ‹‹መንፈስ እና ከቃሉ›› ላይ አተኩሯል፡፡ ቃሉ በልጅነት አእምሮው ተቀርጾ ቀርቷል፡፡ የአባቱን ቃል እንዴት እውን እንደሚያደርግ አስጨንቆታል፡፡ ይህን የተመለከቱ እናቱ ወጣ ብሎ እንዲዝናና ብር ሰጡት፡፡ ከዚያም አምሽቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ አስደንጋጭ ክስተት ተፈጠረ፡፡

> *…ጓ…ጓጓጓ…*የሚል ድምጽ ሰማ ዐይኑን አፍጥጦ ሲመለከት አንድ መኪና ያገኘውን እየገጨ…በመዋለል ወደ እሱ ሲመጣ ተመለከተ፡፡…በድንጋጤ ተራወጠ ግን መሄጃ ሥፍራ አልነበረውም፡፡ የሆነ ሐሳብ ከፊቱ ድቅን አለ፡፡ *አስፈሪው ሞት ጥርሱን አግጦ* ወደ እሱ የመጣ መሰለው…አልቀረለትም መኪናው አሽቀንጥሮ ጣለው…[አጽንዖት የእኔ]
> (ጌታቸው፣1982፣11)፡፡

ወ\ሮ እታፈራሁ ለልጃቸው እንዲዝናና ብር የሰጡት አንድም ልጃቸው ከትካዜ እንዲወጣ ሲሆን፣በሌላ መልኩ ደግሞ በኢ-ንቁ ልቦናዋ ባሏን እያስታወሰች ያለምንም ከልካይ ማልቀስ ስለፈለገች ነው፡፡ ድጋፌነህ የሰማው *ጓ…ጓጓጓ* የሚል ድምጽ አስፈርቶታል፡፡ ይህም **ሲግኒፋየር** ሲሆን፣ ራሱን ማዳን ባለመቻሉ የምናባዊ አባት ፍላጎት እና ትእምርታዊ የሆነው ቃል የስሜት መረበሽ ፈጥሮበታል፡፡ በዚህም ሁኔታ ከትእምርታዊ ዓለም ወደ እውናዊ ዓለም በመሸጋገር የመኪና አደጋ ሲደርስበት በምናባዊ እና በትእምርታዊ ዓለም የሞትን አስፈሪነት ይገነባል፡፡ ይህም Hegel, ‹‹ክስተት (*Phenomenolog*) ከፍላጎት ያደናቅፋል›› (Fry,2012,293)፡፡ በማለት ከሚያስረዱት ጋር የሚገናኝ ሲሆን፣ድጋፌነህ የፍላጎቱ ማሳኪያ ይሆናል ካለው ፈተና በመኪና አደጋ ተደናቅፏል፡፡ የእናት ፍላጎትም **ሌ**ላ እጦት አስከተለ፡፡ ይህም እናቱን *ዐይንሽን ልታጠፊ ነው* ካላት ጋር የሚዛመድ ነው፡፡

እናት በልጃቸው ማምሸት ተጨነቁ፡፡ አዘኑ፡፡ ጮኹ፡፡ ከዚያም የመንደሩ ‹‹ወንዶች›› ተሰባስበው ፍለጋ ሄዱ፡፡ ከብዙ ፍለጋ በኋላ ሆስፒታል ገብቶ አገኙት፡፡ ከተኛበት ሆስፒታል ወሰዷቸው፡፡ ፀሐይ እና ሁሴን እየተመላለሱ ይጠይቁት ስለነበር ፀሐይ ባልመጣች ቀን ድጋፌነህ ፈተናዬ በማለት ‹‹ሲቃዥ›› አደረ፡፡ በጠዋቱ የጠፋውን ነገር በማማተር ፈለገ፡፡

> ጧት…ዐይኑን ገለጥ አደረገና…ክርተት…ክርተት ሲል፣ምን ተሻለህ ልጄ ብዬ ብጠይቀው…ውኃ ውኃ…አለኝ እንዴው አንጀቱ ተቃጥሎ…ውኃ ጥም ብዬ… ነርሲቱን…ውኃ…ውኃ ይላል›› ብላት ‹‹አይጠጣም›› አለችኝ…እኔ ለእሱ ተንገበገብኩ …እንደው ልጄ ላመል ጠብ አርጊለት ከንፈሩ እኮ ደርቋል ብላት ‹‹አይሆንም›› አለችኝ መጨረሻ ላይ ዐይኑን ዝብርቅርቅ…አንጄ ነጨን… ጥቁሩን…ሲያደርገው ውኃ ሆኘ ቀረሁ፡፡ ወይኔ ፈተናዬ አለ፡፡
> (ጌታቸው፣1982፣23-24)

ድጋፌነህን ያቃዠው የፀሐይ ፍቅር እና የአባቱ ‹‹ቃል›› ሲሆን፣ ይህም ፍላጎቱ ላይሳካ ነው የሚል ስጋት ፈጥሮበታል፡፡ ፀሐይን ሳያያት መዋል ማደር ስለማይችል የምናባዊ ዓለም የፍቅር ግንባታ እንቅልፍ ነስቶታል፡፡ ‹‹*ፈተናዬ*›› ያለ የአባቱን ቃል የሚያሳካበትን ትምህርቱን ሲሆን፣

በሌላ መልኩ ደግሞ በፀሐይ ‹‹ፍቅር እየተፈተነ›› መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ Foucault, ‹‹ፍላጎትን ለማሟላት ሲባል ለዕውቀት (ለኃይል) ተገዥ መሆን ይገባል›› (1980፣119)፡፡ የሚሉት ሃሳብ ነርሷ ውኃ እንዳይጠጣ የከለከለች ከእውቀት አንጻር ሲሆን፣የእናትዬው ዝም ማለት ደግሞ ልጄን ይሻለው እንጂ ግድ የለም ከሚል የመነጨ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ድጋፌነህ የተጠማው ፍላጎቱ የሆነውን የፍቅር ውኃ እንጂ እውናዊውን ውኃ አይደለም፡፡ የዐይን ነጩ እና ጥቁሩ ሌላ እና **ሌ**ላ ሲሆን ይህም የምናባዊ ዓለም ፍላጎት እና የ**ሌ**ላ ፍላጎት መዘበራረቅን ጠቋሚ ነው፡፡ እንደ ውኃ የተጠማት ፀሐይ ለመጠየቅ በመጣች ጊዜ የፍቅር መግለጫ የሚሆን ስጦታ አበረከተችለት፡፡

> ‹‹ድጋፍዬ ተሻለህ?›› አለችው አልጋው ላይ ቁጭ ብላ፤…
>
> ‹‹በጣም ደህና ነኝ ትናንት ምነው ቀረሽ?››
>
> ‹‹መጥቼ ነበር እኮ…አንድ የተረገመ ዘበኛ አትገቢም ብሎ ከለከለኝ››
>
> ‹‹ብዙ ቀን ያላየሁህ መሰለኝ››፣ ‹‹እኔም ናፍቀሽኝ ነው ስሮጥ የመጣሁት
> እናትህስ አወቁኝ እንዴ?››
> ‹‹አላወቀችም…ብቻ ትናንት ስትቀሪ…ያች ልጅስ አለችኝ››
> …‹‹ አሁን ደህና ነህ አይደል?››
> ‹‹ይህችን እንካ እኔ ሳልኖር አሽትታት››
> ‹‹ምንድን ናት?››
> ‹‹የፍቅር መግለጫ ጽጌረዳ፡፡››
> (ጌታቸው ፣1982፣25)

ፀሐይ ድጋፌነህን አከታትላ የምትጠይቀው በጥያቄዎቿ መሃል **ሌ**ላ ማወቅ የምትፈልገው ነገር ስላለ ነው፡፡ የ**ሌ**ላ ፍላጎቷን በሁለት መንገድ ትገልጻለች፡፡ የመጀመሪያው ‹‹ድጋፍዬ›› ብላ በማቆላመጥ የፍቅር ፍላጎቷን ትገልጻለች፡፡ በሌላ መሻል አለመሻሉን ትጠይቃለች፡፡ የድጋፌነህ ፍላጎት ፀሐይን ባለማየቱ እጦት ሆኖበታል፡፡ ‹‹ለምንድን ነው ትናንት ያልመጣሽ? ያላትም›› ለዚህ ነው፡፡ የጥበቃው ክልከላ ለሁለቱ እጦት ምክንያት ሲሆን፣ ይኸም በፍላጎት መካከል ክልከላ እና መሰናክል እንዳለ አመላካች ነው፡፡ ፀሐይ ‹‹እናትህስ አወቁኝ?›› በማለት የጠየቀችው በማወቃቸው ያሉት ነገር ካለ መስማት ስለፈለገች እና ከዘመኑ ማኅበረ-ባህላዊ ሕግ አንጻር አፍራ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁለተኛው የፍላጎት መግለጫ ደግሞ የጽጌረዳ አበባው አበርክቶ ነው፡፡ ይህም የፍቅር *ሜታፈር ነው፡፡* ፀሐይ ‹‹የፍቅር መግለጫ ጽጌረዳ›› ለድጋፌነህ ማበርከቷ፣ ከማኅበረ-ባሕላዊ ሕግ ክልከላ ተላቃ ፍላጎቷን እንደምትገልጽ ጠቋሚ ነው፡፡ የጽጌረዳው *ሜታፈር* ግን በልቦለዱ ታሪክ መቋጫ ላይ ወደ የሐዘን መግለጫ *ሜታፈር* የተለወጠ ሲሆን፣

ፀሐይ በመኪና ተገጭታ ሆስፒታል በገባች ጊዜ ድጋፌነህ ‹‹ከመቃብሯ ላይ ጽጌረዳ አበባ እንዲያስቀምጥላት ብትጠይቀውም እሱ ግን ፍላጎቷን አላሟላም፡፡ ፀሐይ በኢ-ንቁ ልቦናዋ ‹‹ይህችን እኔ ሳልኖር አሽትታት›› ማለቷም ቀድማው እንደምትሞት ያወቀች መሆኑን ጠቋሚ ነው፡፡ በመሆኑም የጽጌረዳው ትርጓሜ **ሌ**ላ እና **ሌ**ላ ነው፡፡

ለድጋፌነህ እና ፀሐይ መገናኘት ምክንያት የሆነው ወደ እሱ ትምህርት ቤት መምጣቷ እና ከእሱ ጋር በአንድ ወንበር መቀመጧ ነው፡፡ ደብተር እንዲያውሳት ጠየቀችው፡፡ ደብተሩን ስትመልስለት ደግሞ የስምንት ወራት ትዝብቷን እንዲህ በማለት ‹‹ጠየቀችው››፡-

‹‹ ለምን እንደሌሎች ልጆች አትጫወትም ?››
‹‹ በእረፍት ቀንህ ምን ትሰራለህ ?››
‹‹ አባትህ ምን ይሰራል ?››
‹‹ በእረፍት ቀናችሁስ ?››
‹‹ ክራር መምታት ትችላለህ ?››

ክራር መምታት *ትልቅ ስሆን በደንብ እችላለሁ፤*

ጊዜ ካገኘሁ ክራር እመታልሻለሁ *ግን የት* ?... [አጽንዖት የእኔ]

(ጌታቸው ፤1982፤27-28)፡፡

ድጋፌነህ እንደሌሎች ልጆች የማይጫወት መሆኑ ለጥያቄ እና ለፍላጎት መፈጠር ምክንያት ሆኗታል፡፡ የፀሐይ ጥያቄ የ**ሌ**ላ ፍላጎት ማሟያ እና ከጥያቄው በስተጀርባ የምትፈልገው **ሌ**ላ እንዳለ አመላካች ነው፡፡ ክራር እንዲመታላት የፈለገችም ቅኝቱን እና ዜማውን መስማት ስለፈለገች ነው፡፡ ድጋፌነህ ክራር ለመምታት፣ቤተሰብ ለማገዝ *ትልቅ* መሆንን እና ጊዜ ካገኘ ፀሐይን የሚያስደስታትን ሁሉ ማሟላት ይፈልጋል፡፡ *ግን የት?* በማለት የጠየቃት ክራር ከመታላት በኋላ የሚፈልገው **ሌ**ላ ስላለ ነው፡፡ ፀሐይ *በመጠየቅ* ያልተሟላላትን በ**ሌ**ላ እየፈለገች ነው፡፡

ወንዶች በፀሐይ ሰውነት ላይ ያተኩራሉ፡፡ ድጋፌነህ ግን ውበቷ አልታየውም፡፡ በፈላጊዎቿ ዘንድ ደንቃራ ስለሆነ ምኗ ነው? የሚል ጥያቄ እያስነሳ ነው፡፡ ‹‹…እንደ እህቱ ነበር የሚያያት ለመመኘትም ጊዜ አልነበረውም፡፡ ስለ ማይነጣጠሉ እሷን የሚፈልጉ ሁሉ ድጋፌነህን ጠሉት፡፡ ‹‹ከእግር እግሯ እየተከተለ ችግር ፈጠረብን፡፡ ምኗ ይሆን…ዘመዷ ወይንስ አሽከሯ?...›› ይሉ ነበር›› ([አጽንዖት የእኔ]፡፡ ጌታቸው፣1982፣30)፡፡

ድጋፌነህ ፀሐይን እንደ እህቱ እንዲያያት ያደረገው ምንድን ነው? ውበቷ እንዳይታየው ያደረገው ምንድን ነው? ጊዜ እንዳይኖረው ያደረገውስ ነገር ምንድን ነው? በምናባዊ ዓለም እየፈለጋት ያልፈለጋት የሚመስለው የትእምርታዊ ዓለም [የገንዘብ] እጦት ስላለበት ነው፡፡ በማፍቀሩ ምክንያት በምናባዊ ዓለም ያሟላው ፍላጎቱ በትምህርቱ መስተጓጎል እንዳይደናቀፍ ስለሰጋ ነው፡፡ የፀሐይ ፈላጊዎች ፍላጎታቸውን የሚያሳጣቸው መስሏቸዋል፡፡ ዘመዷ ነው ወይስ አሽከሯ…? እንዲሉ ያደረጋቸውም በአለባበስ፣በውበት እና በአካላዊ ሁኔታ ብቁ አይደለም በሚል ማንነቱን ስለገነቡ ነው፡፡

ፀሐይ ከተማሪ የፍቅር ደብዳቤ ተላከላት፡፡ ድጋፌነህ እንዲያነበው ሰጠችው፡፡ ቢያነበውም ምንም አልመሰለውም፡፡ በፀሐይ ላይ ግን ቁጣንና ስድብን ፈጥሮባታል፡፡

‹‹ከሰው ተጣልቼ ነው የመጣሁት ››
‹‹ለምን ?››
‹‹ያቺ *ቀልቃላዋን…ወንዳ ወንድ* የመሠለችውን ታውቃታለህ ?....
‹‹አዎን…*ሱሪ* ብቻ የምትለብሰውን ነው አይደል ?››…
‹‹አያስቅም…እኔም ሙልጭ አድርጌ ሰድቤ መልስ ጻፍኩለት፡፡››
‹‹ለምን ትሰድቢዋለሽ ? ክፉ ነገር አልጻፈ ››
…‹‹ በል ተወው ወንድሜ›› ብላ እየተቆናጠረች ወደ ክፍሏ ስትሄድ ግራ ገባው ድጋፌም ተከትሏት ሄደ፡፡ [አጽንዖት የእኔ]
(ጌታቸው ፣1982፣31-32)

ፀሐይ የማኅበረ-ባህላዊ ክልከላ እና አባዊነት ይስተዋልባታል፡፡ *ሥነ-ፍጥረታዊ* ከ*ሥነ-*ልሳናዊ ጋር በማዋደድ *‹‹ቀልቃላ፣ወንዳ ወንድ፣ሱሪ ለባሽ››* የሚሉትን የክልከላ *ቃላቶች* በቁጣ ትገልጻለች፡፡ እኒህ *ቃላቶች* ‹‹ክልከላንና አባዊን›› ጠቋሚ ከመሆናቸው ባሻገር ሴቶች ከወንዶች ጋር ያላቸውን የሲግኒፋየር እና የሲግኒፋይድ ሠንሠለትን አመላካች ናቸው፡፡ ፀሐይ የፍቅር ደብዳቤውን እንዲያነበው የሰጠችው በቁጣ ፍቅሩን ይገልጽልኛል በሚል ሲሆን፣ ይኸም Lacan, ‹‹ቁጣ (*hysterics*) ድብቅ ፍላጎት በቅጽበት ገሃድ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡ የሚናደደው ሰው ፍላጎቱን በግልጽ ባይናገርም ከሁኔታዎቹ እና ከሚያወጣቸው *ቃላት* ፍላጎቱን መረዳት ይቻላል›› (2007፣23፣32)፡፡ በማለት ከሚያስረዱት ጋር ግንኙነት ያለው ነው፡፡ ፀሐይ ፍላጎቷን ‹‹በቁጣ›› አንጸባርቃለች፡፡ ከዚያም ስለፍቅር እንዲያወራት ትፈልጋለች፡፡

‹‹ ስለምን እናውራ?››
‹‹ ሞልቷል ለምሣሌ ስለ *ሮሚዎ እና ጁልየት*፣ስለ ፀሐይ እና *መስፍን፣*…በቃ እንዲህ ዓይነት ››
‹‹ እሽ ትናንት ስለአነበብኩት የፍቅር ታሪክ ላውጋሽ ››

‹‹ *ግን…ግን…መጨረሻው የማያምር ከሆነ አልፈልግም…በፍቅር…ተጀምሮ… አምሮ ሲያልቅ ነው የሚያስደስተኝ…ወይንም አለ አይደል እንደ ፍቅር እስከ መቃብር›› ሁለቱም ግራ የተጋቡ ነበሩ፡፡ ምን እንደሚያስቡ ምን እንደሚፈልጉ የማያውቁ በልባቸው ግን የፍቅር ፋኖስ ይንቦገቦጋል፡፡* [አጽንዖት የእኔ]
(ጌታቸው ፣1982፣ 32)

ፀሐይ ድጋፌነህ *ስለሮሚዎ (Romeo) እና ጁልየት (Juliet)* እንዲያወራት የፈለገች የፍቅር ቃል እንዲያወጣ ስለፈለገች ነው፡፡ በሌላ ፀሐይ በኢ-ንቁ ልቦናዋ የምናባዊ ዓለም ፍላጎቷ መሟላቱን እንጂ እጦትን ያላሰበች ቢመስልም ቅሉ፣*ሮሚዎ እና ጁልየትን*፣ እንዲሁም *የፍቅር እስከ መቃብር* ዋና ገጸ-ባህርያትን በታሪኩ መጨረሻ የገጠማቸው ትራጀዲያዊ ገጽ ነው፡፡ ይህንንም ፀሐይ አውቃም ይሁን ሳታውቅ በኢ-ንቁ ልቦናዋ እንደ *ሮሚዎ* እና *ጁልየት* እንዲሁም እንደ *ፍቅር እስከ መቃብር* ያለ የፍቅር ታሪክ ማለቷ መጨረሻቸው እንደማያምር የሚያመላክት ነው፡፡ እንዳለችውም አልቀረም የፈለገችው ፍቅር መጨረሻው አላማረም፡፡ በፍቅራቸው ላይ ፈተና በመብዛቱ ፀሐይ የፈለገችውን ሳታገኝ በሞት የተለየች ሲሆን፣ድጋፌነህ ደግሞ ያለ ፍቅረኛ ቀርቷል፡፡ ስለሆነም የሁለቱ የፍቅር ታሪክ ልክ እንደ *ሮሚዎ* እና *ጁልየት*፣ እንዲሁም እንደ *ፍቅር እስከ መቃብር* ሁሉ በስቃይ፣በእጦት እና በሞት ተደምድሟል፡፡ *መስፍን* የተባለው በፍቅራቸው መሃል ጣልቃ በመግባት የሚነጣጥላቸው ሲሆን የፍላጎታቸው እንቅፋት የሚሆነውን በኢ-ንቁ ልቦናዋ (*በምላስ ወለምታ*) እያነሳች ነበር፡፡ ሁለቱም ግራ የተጋቡ መልሱ (መልሷ) ምን ይሆን? በሚል ስለሚያስቡ ነው፡፡

ድጋፌነህ ፀሐይን ስለፈተና ይጠይቃታል፡፡ እሷም **ሌ**ላ ፈተና እንዳጋጠማት ትነግረዋለች፡፡ ከዚያም ስለውበቷ እንዲነግራት ትፈልጋለች፡፡

‹‹ እባክህን ፈተናው አልቸገረኝም ግን በራሴ ላይ የደረሰብኝ ፈተና ነው ያስቸገረኝ ፡፡››
‹‹ የምን ፈተና ነው የደረሰብሽ ›› አላት እየተጨነቀ
‹‹ ጭንቅ ጥብብ ይለኛል ››…ህም! አለችና ትከሻዋን ነቅነቅ አደረገችው
‹‹ ምን ሆነሻል ፀሐይዬ ?››
‹‹ ምንም ብቻ *መጨረሻዬ ምን ይሆን ?››*
‹‹ እኔ ከሌሎቹ ሴቶች በምን እለያለሁ ?››
ድንግጥ አለና የሚናገረው ጠፋው አተኩሮ ከተመለከታት በኋላ ብዙ የምትለይበት ሁኔታ እንዳለ የሚሰማውን ስሜት በሙሉ ሊነግራት ፈለገ ግን ፈራ ‹‹ ት…ትለያለሽ…በብዙ ነገሮች ›› [አጽንዖት የእኔ]
(ጌታቸው ፣1982፣32)

በፀሐይ ላይ የደረሰው ሌላ ፈተና የፍቅር ፈተና ነው፡፡ ፀሐይ ብዙ ወንዶች በውበቷ ስለማለሉ መጨረሻዋ እንደማያምር ከመስጋቷ የመነጨ ‹‹መጨረሻዬ ምን ይሆን?›› እንድትል አድርጓታል፡፡ ይህ የፀሐይ የኢ-ንቁ ልቦና ስጋት በታሪኩ መጨረሻ ድጋፌነህን እንደፈለገች በመስፍን የበቀል እና እሷን የራሱ የማድረግ ፍላጎት ምክንያት እንደተሰቃየች ትሞታለች፡፡ ድጋፌነህን ከሌሎች ሴቶች የምትለይበትን እንዲነግራት የጠየቀችው ምናባዊ እና ትእምርታዊ ፍላጎቷን ለማሟላት ነው፡፡ ድጋፌነህን የሌላ ጥያቄው ለምን አስደነገጠው? ፍርሃትንስ ምን አመጣው? ‹‹ቆንጆ ነሽ›› ቢላት የምትኩራራበት ስለመሰለው እና ማፍቀሩን እንዳታውቅበት ስለፈለገ ነው፡፡ አተኩሮ የተመለከታት (*gaze*) ለጥያቄዋ መልስ ሲሰጣት ከፊቷ ላይ የሚነበበውን ምናባዊ ሥርዓት ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ ፈልጎ ነው፡፡ ከዚያም ምናባዊ ምሥልን ከትእምርታዊ ሥርዓት ጋር በማቀናጀት ‹‹ቆንጆ›› ስለመሆኗ ነገራት፡፡

በድጋፌነህ ላይ እንደገና ሌላ ፍላጎት ተሥተዋለ፡፡ ከመምህሯ የተላከላትን የፍቅር ደብዳቤ በቁጣ ነጥቆ አነበበው፡፡ ‹‹ፍቅርሽ ሐሳብ እና ሰቀቀን ሆኖብኛል፡፡ የእኔ እመቤት፣የእኔ ንግስት ስለዚህ እሺ በይኝ እሽ ካላልሽኝ ማበዴ ነው፣እባክሽን ቁርጡን ንገሪኝ የሚል ጭብጥ ያለው ነው›› (ጌታቸው፣1982፣33)፡፡ *በዚህ ጊዜ* ድጋፌነህ ያልተለመደ ስሜት እና ከቁጥጥር ውጪ የሆነ ቁጣ ተስተዋለበት፡፡ ለምን ተቆጣ? ውጤቱስ ምንድን ነው? በቁጣ ኢ-ንቁ ፍላጎቱ ገንፍሏል፡፡ ይህም ፀሐይ የናፈቀችውን ፍላጎት እንድትመለከት ምክንያት ሆኗል፡፡ የድጋፌነህ ቁጣ እንዳፈቀራት እና እንደቀና (*envy|Jealousy*) የሚያመላክት ነው፡፡

ድጋፌነህ ከስድስት ሳምንት የሆስፒታል ቆይታ በኋላ ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡ ፀሐይ እጮኛው እንደሆነች ለእናቱ ባስተዋወቃት ጊዜ ‹‹እስኪ መጨረሻውን ያሳምረው›› አሉ በሆዳቸው (ጌታቸው፣1982፣50)፡፡ ለዚህ የውስጥ ድምጽ ምክንያቱ ከትምህርቱ ተስተጓጉሎ ፍላጎታቸው ሳይሟላ እንዳይቀር፤እንዲሁም በኑሮ እና በውበት ስለማይመጣጠኑ አይዛለቁም ከሚል ስጋት የመነጨ ነው፡፡ ጎረቤት ዘመድ አዝማድ ተሰብስቦ በእልልታ ተቀበሏቸው፡፡ እንግዶችን በደስታ አስተናገዱ፡፡ ‹‹…ዘመድ አዝማድን በፈገግታ ይጋብዛሉ፡፡…ጠላ የሞላበትን ማንቆርቆሪያ ይዘው *‹‹ጠጡልኝ ዛሬ እኮ የልጄ ሠርግ ነው፡፡››* እያሉ ይቀዳሉ፡፡ ሁሴን ግማሽ የተጠጣለትን ብርጭቆ እንዲሞሉለት ብርጭቆውን የያዘውን እጁን ዘረጋው›› ([አጽንዖት የእኔ]፡፡ጌታቸው፣1982፣ 52)፡፡

የወ\ሮ እታፈራሁ የደስታ ምንጭ ልጃቸው ከሞት መትረፉ እና የልጃቸውን የወደፊት ሚስት ማወቃቸው ነው፡፡ *‹‹የልጄ ሠርግ ነው››* ያሉ ለዚህ ነው፡፡ የብርጭቆው ግማሽ ጎደሎ መሆን

የፍላጎት አለመሳካትን ጠቋሚ ነው፡፡ ከዚያም ወደ እነፀሐይ እና ድጋፌነህ ዞር በማለት ፀሐይን እንዲህ አሏት፡-

‹‹እታለም አንቺሳ? ጠጪው እንጂ›› አሏት የፀሐይን *ያልተቀመሰለትን*
ብርጭቆ እያዩ
‹‹እሽ እማማ›› አለች ፀሐይ የተከፋባት ስለመሰላት ብርጭቆውን አንስታ አንድ
ጊዜ ጎንጨት አደረገችው፡፡
‹‹ ብቻችሁን ስትሆኑ በደንብ ታወራላችሁ ዛሬ ጨዋታው የጋራ ቢሆንስ?››
አሏቸው ሁሴን እና ዓይናለም፡፡ [አጽንዖት የእኔ]
(ጌታቸው ፣1982፣53)

ወ\ሮ እታፈራሁ በመጠጡ አሳበው የተመለከቱ የፀሐይን ውበት ሲሆን፣*ያልተቀመሰለት* ብርጭቆ እያዩ የተባለውም የፀሐይን ‹‹ልጅነት›› ለመግለጽ ነው፡፡ ፀሐይና ድጋፌነህ ማኅበረ-ባህላዊ ሕጉን ዘንግተው ለራሳቸው እንጂ ለሌሎች ጊዜ አልሰጡም፡፡ ሁሴን እና ዓይናለም ‹‹ብቻችሁን ስትሆኑ በደንብ ታወራላችው አሁን በጋራ እንጫወት ያሏቸው›› ለዚህ ነው፡፡ ጨዋታው ደርቶ አመሸ፡፡ ፀሐይ እንደዚያን ዕለት ተደስታ አታውቅም ነበር፡፡ ድጋፌነህ ግን ቢደሰትም ሌላ የሚያሳስበው ነገር ነበር፡፡ አንድ ዓመት ያለ *ሥራ* እንዴት እንደሚያሳልፍ አስጨንቆታል፡፡ ከዚያም ከሁለት ቀን እረፍት በኋላ *ሥራ* ፍለጋ ተነሳ፡፡ የባለ*ሥ*ልጣኑ ንግግር *ያ*ቃጭልበታል፡፡ ‹‹…ጠዋት ቁርሱን የቀመሠ በመሆኑ ረሃቡን ለመላቀቅ አንዱ ቡና ቤት ገብቶ ሻይ ያዛል፣*‹‹ማን ላከህ አሉኝ…ማን ልበል›› ማን የሚጠራ ዘመድ አለኝ* በማለት ራሱን በራሱ ይጠይቅ እና የውሸት ፈገግታ ይፈጋል…›› ([አጽንዖት የእኔ] ፡፡ ጌታቸው፣1982፣55)፡፡

በድጋፌነህ ኢ-ንቁ ልቦና የሚነሱ ጥያቄዎች *ማን ልበል? ማን የሚጠራ ዘመድ አለኝ?* በሚል የራሱን ማንነት ከሌላ ፍላጎት እጦቱ ጋር በማዛመድ ይጠይቃል፡፡ የራስ ማንነቱን ‹‹ማንም የለኝም !››፣ ‹‹ብቸኛ ነኝ!›› በማለት ይገልጻል፡፡ ከዚያም እጦት ፍላጎቱን በምናባዊ ዓለም ፋንታዚ የሆነ ፈገግታ ይሸፍናል፡፡ የባለሥልጣኑ ንግግር ማንም የለኝም! በሚል *ሥራ* የማግኘት ተስፋው እንዲመናመን አድርጓታል፡፡

ድጋፌነህ *ሥራ* በመፈለግ ብዙ ውጣ ውረድ አሳለፈ፡፡ ከዚያም ተስፋ በመቁረጥ ለአንድ ሀብታም የእርሻ *ሥራ* የሒሳብ ሠራተኛ ሆኖ ወደ አርሲ ሊሄድ መሆኑን ለፀሐይ ሲነግራት ደነገጠች፡፡ እንዳይሄድ ፈለገች፡፡ ገንዘብ ሰጠችው፡፡ ወደፊት ልታግዘው ቃል ገባችለት፡፡

…*መቅረት እንዳለበት ወተወተችው፡፡ግራ የገባ ነገር…ዓመት ሙሉ*
*ሥራ መፍታት…ወይስ…ፀሐይን ማስከፋት…ለጊዜው አርእስት*

*ቀይረው ሲጫወቱ ቆዩ ምሣ ከጋበዘችው በኋላ እጁ ላይ ቁጥሩ ያልታወቀ ብር አስቀመጠችለት፡፡*
*‹‹የማገኘውን ደመወዝ ሦስት አራተኛውን እጅ ሥራ እስከምትይዝ በየወሩ ልሰጥህ ቃል ገብቻለሁ፡፡*
*‹‹ ይህ ሁሉ ምን ያደርግልኛል ?›› አላት በሁኔታው እየተገረመ*
*‹‹እናትህን ትረዳታለህ ››*
*‹‹ታዲያ ሠርቼ ባገኘው ነዋ!›› [አጽንዖት የእኔ]*
(ጌታቸው ፤1982፤57)፡፡

ፀሐይ ድጋፌነህን ማጣት ስለማትፈልግ እንዲሄድ አልፈለገችም፡፡ ብር የሰጠችው እና ቃል የገባችለትም ለዚህ ነው፡፡ ድጋፌነህ የሚናገረው የጠፋው እና የተምታታ ፀሐይን ማጣት ስላልፈለገ ነው፡፡ አርሲ ለሥራ ከሄደ የፈለገውን ሥራ እና ደመወዝ ያገኛል፡፡ ፀሐይ እና እናቱ ደግሞ እጦቱ ይሆናሉ፡፡ ከቀረ ደግሞ ፀሐይ እና እናቱን ያገኛል፡፡ ሥራ እጦቱ ይሆናል፡፡ ይህም ፍላጎት እና እጦት የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ያስገነዝባል፡፡ ገንዘብ ስትሰጠው *‹‹ይህ ሁሉ ምን ያደርግልኛል እና ሠርቼ ባገኘው ነዋ !››* ማለቱ እንደ ማኅበረ-ባህላዊ ሕጉ የሴት ጥገኛ መሆን ስላልፈለገ እና የአባቱን ቃል በኢ-ንቁ ልቦናው አስታውሶ ነው፡፡

ድጋፌነህ በፀሐይ ሐሳብ እና በአባቱ ቃል እየተመናታ ቤቱ ደረሰ፡፡ ከዚያም እናት እና አባቱ ፍላጎታቸው በልጃቸው እንዲሟላ የገዙለትን መጽሐፍት እንደ ከንቱ አያቸው፡፡ ‹‹…በከንቱ ኑሯል ለካ እስከዛሬ ድረስ ጓደኞቼ ሆናችሁ የኖራችሁት፡፡ …በከንቱ ኖሯልና በውስጣችሁ የተደበቀውን ሚሥጢር ለማወቅ ከጧት እስከ ማታ ከእናንተ ጋር ስዳረቅ… ዕድሜዬን የገፋሁት፡፡…አዬ ከንቱ ጊዜ አለ…›› (ጌታቸው፤1982፤59)፡፡

ድጋፌነህ መጽሐፍትን እንደ ከንቱ ያያቸው ተስፋ ያደረገው ፍላጎቱ ስላልተሟላ ነው፡፡ ድጋፌነህ *‹‹ምን ዋጋ አለው!››* የሚለው የአባ ውቃው ንግግር ሚሥጢሩ ስላልገባው ከቁብም አይቆጥረውም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ሥራ እጦቱ ሲሆን ሚሥጢሩ ገብቶታል፡፡ የመጽሐፍት ጓደኝነት ፍላጎቱን ስላላሟላለት ‹‹*ምንም*›› ሆኖበታል፡፡ ከዚያም አዲስ ከተከፈተ ድርጅት ለቅጥር እንደተመዘገበ ከንቱ ያላቸውን መጽሐፍት ፈለገ፡፡ ‹‹ልጠየቅ እችል ይሆናል ብሎ የሚያስበውን ጥያቄ መጻሕፍት በማገላበጥ ማንበብ ጀመረ፡፡ በትምህርት ዓለም በቆየበት ወቅት ምንጊዜም ፈተና ፈርቶ አያውቅም አሁን ግን ፍርሃት ፍርሃት አለው›› (ጌታቸው፤1982፤62)፡፡ ድጋፌነህ አይፈለጉም ያላቸውን መጽሐፍት ጊዜያቸው ሆኖ መፈለጉ፤የአንድ ነገር ትርጉም በጊዜ የሚወሰን መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ ለፍርሃቱ ምክንያት የሆነው የባለሥልጣኑን ንግግር በኢ-ንቁ ልቦናው ስላስታወሰ እና ካላለፈ ወደ አርሲ እንደሚሄድ አስቦ ነው፡፡

ድጋፌነህ ማለፍ መውደቁን ለማረጋገጥ ሄደ። ፀሐፊዋ ማለፉን ከነገረችው በኂላ እንዲህ አለችው ፡- ‹‹ጥሩ *መሥሪያ* ቤት ነው። አለሁ አለሁ ካላልክ አለቆችህን ካከበርክ›› የምትታዘዘውን ከፈጸምክ ምንም ችግር አይገጥምህም የደመወዝ ጭማሪ እንደልብ ነው…ግን ልታይ ልታይ ከጀመርክ አጉል ነው (ጌታቸው፣1982፣68)። ከዚያም ወደ ኃላፊው ክፍል ገባ። ጥጉ ከተባለው የቅርብ ኃላፊው ጋር በማስተዋወቅ የፀሐፊዋን ምክር ተጋራ። Bennett A, and Royle N, እንደሚሉት ‹‹የሰው ልጅ ሁልጊዜ ፈላጊ እና ሁልጊዜ ፍላጎቱን ለማግኘት የሚበር ነው›› (2004፣31-32*)። ድጋፌነህ ማለፉን ማወቅ ፈለገ።* ዐወቀ። ከዚያም ሌላ ምናባዊ ዓለም ገነባ። ደስታውን ለማጋራት ፈለገ። ሮጠ። ‹‹እየሮጠ…ወዴት እንደሚሄድ አላወቀም በረረ… በረረ… (ጌታቸው፣1982፣71)። ድጋፌነህ **ሌ**ላ ዓለምን ሣለ። እንደገና **ሌ**ላ ፍላጎት በቅድሚያ ለፀሐይ ቀጥሎ ለእናቱ አበሠራት። እንደገና **ሌ**ላ ፍላጎት መገባበዝ እና መዝናናት መፈለግ። ተዝናኑ። ጋበዛት።

ከላይ በተገለጹት ታሪኮች የፀሐይ እና የድጋፌነህ ፍቅር የሚያስቀና፤የእናቱ ኑሮም ደስተኛ ሆኖ ነበር። ከዚያም በፀሐይ እና በድጋፌነህ ፍቅር መካከል ሦስተኛ ወገን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ገብቷል። አንዱ ሌላውን ለማሳጣት እና ፍላጎቱን ለማሳካት በየራሱ መንገድ ጥረት አድርጓል። በመሆኑም የታሪኩ አቅጣጫ ወደ ፍርሃት እና ስጋት፣ስቃይ እና እጦት እንዴት እንደሚሸጋገር በአቶ ሞልቶለት (የመስፍን አባት) ሐሳብ መነሻነት እንመልከት።

አቶ ሞልቶለት በልፋት ያገኙትን ሀብት ልጃቸው ከሴት ጋር ‹‹እየተዳራ›› እንዲያባክንባቸው አይፈልጉም። ስለሆነም *ፋንታዚ (ምናባዊ እና ትእምርታዊ)* ሐሳብ በመፍጠር እንዲህ አሉት። ‹‹…ንብረቴን በሙሉ በሥምህ አዙሬ ሳበቃ እፎይ ብዬ እየተጦርኩኝ መኖር ነው የምመኘው ይህ ደግሞ ከተባረከ ልጅ የሚጠበቅ ግዴታ ነው (ጌታቸው ፣1982፣85) አሉት። መስፍን ደስተኛ በመሆን፡- ‹‹ልክ ነህ…የምትፈልገውን ሁሉ ለመፈጸም ዝግጁ ነኝ አለ እየተቅለሰለሰ›› (ጌታቸው፣1982፣85)።

አቶ ሞልቶለት ይህን የሚፈጽሙት ‹‹ሲያገባ›› እንደሆነ ነገሩት። ‹‹…ትዳር መያዝን የመሠለ ዓለም ፈጽሞ አይገኝም።…ስለዚህ ትዳር መመሥረት ይኖርብሃል (ጌታቸው፣1982፣85-86) አሉት። ይህም የሴትን ለዋጭነት ጠቋሚ ነው። *በቅድመ-ኤዲፐስ* ከነበረው *የእማዊ ሥርዓት* ጋር የሚዛመድ ነው። ለዚህ ሁሉ ምክንያቱ ገንዘባቸው እንዳይባክን ስለፈለጉ ነው። የልጅ ልጅ አቅፈው የመሣም ፍላጎታቸው እውን እንዲሆን ነው። *ከዕቁባቶቻቸው (በዘመናችን ልሳን*

*ከውሽሞቻቸው)* መካከል አንዷን ወደ ቤታቸው ማስገባት ስለፈለጉ ነው፡፡ መስፍን ሀብት ንብረቴን ትወርሳለህ ሲባል ደስ ብሎት ነበር፡፡ ‹‹ትዳር›› *መያዝ* ሲነሳበት ግን ደስተኛ አልሆነም፡፡ ስለሆነም የአባቱን ሐሳብ ላለመቀበል ሰበብ ይፈጥራል፡፡

> ‹‹…*መች* ሳላስብበት ቀረሁኝ ብለህ ነው፡፡ ችግሩ ለትዳር የሚስማማ ሴት ፈልጌ አጣሁ፡፡›› የአሁን ሴቶች እንብላ እንጠጣ እንዲህ ይደረግልን የሚሉ እንጂ *ጨዋ ሴቶች ለትዳራቸው ሙቶች ባለቤቴ ልጆቼ* የሚሉት በእናንተ በተባረከው ጊዜ ቀረ ይህ በመሆኑ ነው እኔም ችላ ያልኩ፡፡ [አጽንዖት የእኔ]
> (ጌታቸው ፤1982፤86)

መስፍን *መዳራትን* የሚከለክል እና እጦት የሚያስከትል በመሆኑ ትዳር *መያዝ* አልፈለገም፡፡ በዚህም ምክንያት የምናባዊ ዓለም ፍላጎቱን *በፋንታዚ* በመሸፈን፤ትእምርታዊ የሆነውን የአባቱን ሀብት ለመውረስ ይፈልጋል፡፡ መስፍን *ፋንታዚ* የሆነ ማኅበረ-ባህላዊ ሕግ ይስተዋልበታል፡፡ *‹‹ጨዋ ሴቶች ለትዳራቸው ሙቶች›* የሚለው አገላለጽ ለዚህ ጠቋሚ ነው፡፡ ሞልቶለት መስፍን የወዳጁን ልጅ እንዲያገባ ይፈልጋሉ፡፡ *‹‹…ብትወድም ባትወድም* በፈጣሪ ትእዛዝ *ቃል* ኪዳን ከጓደኛዬ *ጋር* ልጅህን ለልጄ ተባብለን ጥንት ተፈጣጥመናል›› ([አጽንዖት የእኔ]፡፡ ጌታቸው፣ 1982፣86) አሉት፡፡ *‹‹ብትወድም ባትወድም››* ያሉት የአባት ወግ ትርጓሜ አለው፡፡ ይህን ማለታቸው *ቃል* አባይ እንዳይባሉ ፈልገው ነው፡፡ ከዚያም ፀሐይ እንደታጨችለት ነገሩት፡፡

መስፍን ‹‹ደስ ይለኛል አባዬ በመጀመሪያ ግን እኔ ቀርቤ ፀባዩዋን ላጥናት ከዛ በኋላ መልሱን ብነግርህ አለ እሱም በደስታ ልቡ እየተፍለቀለቀ›› (ጌታቸው፣1982፣89)፡፡ መስፍን ይህን ማለቱ ከፀሐይ *ጋር* ቀድሞ በመዳራት የአባቱን ሐሳብ ውድቅ ማድረግ ስለፈለገ ነው፡፡

መስፍን በምናባዊ ዓለም እየዋተተ ፍላጎቱ እንቅልፍ ነስቶታል፡፡ ከዚያም ፀሐይን ለማየት ወደ *መሥሪያ* ቤቷ ያመራል፡፡ ከድጋፌነህ *ጋር* ሲጨባበጡ እና ሲሳሳቁ አየ፡፡ ጥንዶቹ የሚነጋገሩት ስለሰርጋቸው ነበር፡፡

> ‹‹አንተ…ልብስ፣ወርቅ፣ሻንጣ …ሌሎችም ነገሮች መግዛት እንዳለብህ ታውቅ የለ?››
> ‹‹…ለዚህ አይደል ሆዴን አስሬ ገንዘብ እማጠራቅመው አለ በቅሬታ፡፡››
> ‹‹አይዞህ ሁሉንም እኔ አሟላለሁ ለዚሁ ብዬ ነው ዕቁብ የገባሁት ›› አለች እና ፈገግ ብላ ተመለከተችው፡፡
> ‹‹ አንቺ እኮ ለእኔ የተለየሽ ፍጡር ነሽ ሕይወቴ አንቺን በማግኘቴ ሁሌ ደስተኛ እንደሆነች ናት ፡፡›› (ጌታቸው፣1982፣93)

ፀሐይ **ሌላ** የሆነ የሠርግ ፍላጎት ያላት ሲሆን ድጋፌነህ ግን የ**ሌላ** ፍላጎት የለውም፡፡ ‹‹ለዚህ አይደል ሆዴን አስሬ ገንዘብ እማጠራቅመው አለ በቅሬታ›› የሚለው ለዚህ ነው፡፡ እንደገና የድጋፌነህን ዝግጅት መጠየቅ፤እንደገና አንዳቸው ሌላኛቸውን ስላገኙ ሁሌም ደስተኛ ሕይወት መምራትን ይፈልጋሉ፡፡ ፀሐይ የድጋፌነህን የኑሮ ሁኔታ አምና እንደተቀበለች ትረካው ያስገነዝባል፡፡

ከዚህ በታች ያሉትን የበቀል ፍላጎቶች አከዋወን ለመረዳት ይመች ዘንድ በቀጣዮቹ ጽንሰ-ሐሳቦች ማዕቀፍነት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ Bennett; Girard (1965፣14-16) በLacan, 1977a, መነሻነት የሰጡትን ትንታኔ ዋቢ በማድረግ ‹‹ለፍላጎት የባለ ሦስት ጎን ምሣሌ ይሰጣሉ፡፡ በ ‹‹ኤ›› ፣ ‹‹ቢ›› እና ‹‹ሲ›› በመወከል፡፡ የአንዱ ፍላጎት የሌላው ነው፡፡ ‹‹ቢ›› በ ‹‹ኤ›› እና በ ‹‹ሲ›› ተፈላጊ ስለሚሆን በሁለቱ መካከል ግጭት ይስተዋላል፡፡ የ ‹‹ኤ›› ፍላጎት የ ‹‹ቢ›› ነው፡፡ Sedgwick, (1985፣25) የGirard, ሐሳብ በመውሰድ ከጾታ አንጻር እንዲህ ያብራራሉ፡፡ ‹‹ቢ›› በሴት ትወከላለች፡፡ ‹‹ኤ›› እና ‹‹ሲ›› ደግሞ ወንዶች ናቸው፡፡ ሴቷ በሁለቱ ወንዶች ተፈላጊ (ተፈቃሪ) ስለምትሆን ርስ በርስ የግላቸው ለማድረግ ይጥላላሉ፡፡ የየራሳቸውን አማራጭ ይወስዳሉ (Bennett, 2006,178-186)፡፡ በመሆኑም ድጋፌነህ (ኤ)፣ፀሐይ (ቢ) እና መስፍን በ (ሲ) ይወከላሉ፡፡ ፀሐይ በድጋፌነህ እና በመስፍን ተፈላጊ መሆኗ ከዚሁ ጽንሰ-ሐሳብ ጋር የሚሠምር በመሆኑ እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

መስፍን ያየው ነገር ረብሾታል፡፡ ከዚያም ወደ መጠጥ ቤት አመራ፡፡ በቅናት በገነ፡፡ ጾታዊ ፍላጎት እና ውጫዊ ጠላት መታየት የሚጀምረው እዚህ ላይ ነው፡፡ መስፍን ፍላጎቱን እንዴት ለማግኘት አስቧል? ፈልጎ ያጣው ነገር ምንድን ነው? ፍላጎቱን ለማሟላት የሚከተለው መንገድ ሞራላዊ ነው? ወይስ አይደለም? መስፍን የፍላጎት ማሟያ የጥፋት ተባባሪ ይሆኑት ዘንድ ራሄል ከምትባል ሴት ጋር ተዋወቀ፡፡ ከጥጉ ጋር ደግሞ ቀረቤታውን በሌላ አደረገ፡፡

በቅድሚያ እሾህን በእሾህ እንደሚባለው ራሄል ከምትባል የሥራ ባልደረባዋ ጋር ተዋወቀ፡፡ ለምን እንደሚፈልጋት ነገራት፡፡ ራሄል በቀለኛ እና ቅናተኛ ሴት ስለሆነች የብዙዎችን ትዳር አፍርሳለች፡፡ ራሄል ፀሐይ ድጋፌነህን እንድትጠላው ፋንታዚ የሆነ ምክር መከረቻት፡፡ ‹‹ስለምታሳዝኝኝ...በመጽሐፍት ያነበብኩት...በተግባር በሰዎች ላይ ያየሁት እና...ሌላው ቀርቶ በራሴ ላይ የደረሰው ነገር በአንቺ በእህቴ ላይ እንዳይደርስ እየፈራሁኝ ነው እንጂ ምንገዶኝ ብቻ መጠንቀቅ ነው ደረብ ደረብረብ ማድረጉ ይበጃል...›› (ጌታቸው፣1982፣96)፡፡ Lacan,

እንደሚያስረዱት ‹‹ልቦና ቴክስት ነው፤ቴክስትም ልቦና ነው›› (Rawson & Nisbet, 2008, 185) ይላሉ፡፡ በመሆኑም የራሄል ምክር *በፋንታዚ* ዓለም የተሸፈነ የራሷ የልቦና ቴክስት ነው፡፡ ይህን ማለቷም እንዲለያዩ ስለፈለገች ነው፡፡

ራሄል የድጋፌነህን ማንነት ዝቅ አድርጋ በማዋቀር ለመስፍን ነገረችው፡፡ ‹‹…ወደድኩት የምትለውን ሰው ብታየው እኮ ይገርምሀል ቅሽምድምድ፣ሽፋፋ ሰው እኮ ነው፣ከመልክ መልክ የለው፣ከሀብት ሀብት የለው ይገርማል…ፍቅር እውር ያደርጋል የሚባለው እውነት ነው›› (ጌታቸው ፣1982፣97)፡፡ ራሄል ድጋፌነህን ‹‹ቅሽምድምድ!››፣‹‹ሽፋፋ!››፣‹‹መልክ የለሽ!››፣ ‹‹ሀብት የሌለው!›› በማለት ድጋፌነህ የሚያውቀውን እና የማያውቀውን ማንነት በመገንባት ለመስፍን የነገረችው ለበቀል እንዲነሳሳ ሲሆን፣ይኸም መስፍንን ስለረበሸው ወደ መጠጥ ቤት እንዲያመራ አድርጎታል፡፡ ‹‹…የጠጣው አልኮል ናላውን አዙሮ የበለጠ ፀሐይን ውብ አድርጎ ፊቱ ላይ ያሳየዋል፡፡ መኝታ ክፍሉ ገብቶ *መስኮቱን* ከፈተና ሲጋራውን ሁለት ሦስት ጊዜ በመሳብ እታባ ትሙት…ሥራ እንኳን ከያዘ ስምንት ዘጠኝ ወር ግፋ ቢል ዓመት ቢሆነው ነው…›› (ጌታቸው፣1982፣98)፡፡ መስፍን በመጠጥ ኃይል የፀሐይን ውብት *በፋንታዚ* ዓለም እንዲመለከት እና እንዲያደንቅ አድርጎታል፡፡ እንዲሁም በራሄል ንግግር ፍላጎቱ ከፍ ስላለ *በመስኮት* አሻግሮ ፍላጎቱን ሊመለከት ችሏል፡፡

መስፍን ጥጉን ላግኝህ ብሎ ቀጠረው፡፡ ጥጉ ብድር ስለነበረበት ጭንቀት ተጋረጠበት፡፡ ይሁን እንጂ መስፍን የፈለገው ለሌላ ነበር፡፡

> …ውለታህን…እንዴት አድርጌ እንደምከፍለው አላውቅም…አለ
> የደስታ ሲቃ እያነቀው፡፡
> ‹‹ብዙ አትቸገር ይህን ገንዘብ ስሰጥህ…መበደርህን የሚያረጋግጥ
> ማስረጃ *ትፈርምልኛለህ*
> …እና…ብሎ የጀመረውን ሳይጨርስ ››
> ‹‹በሚገባ…በሚገባ እፈርማለሁ፡፡…መቼም ሰው እና እንጨት
> ተሰባሪ ነው ››
> አለ ጥጉ በመጨረሻ ሐሳቡን የሚቀይር እየመሰለው፡፡
> [አጽንዖት የእኔ]
> (ጌታቸው ፣1982፣106-107)

መስፍን ጥጉን ቀድሞ ቃል የሚያስገባው ሐሳቡን እንደሚቀበለው ለማረጋገጥ ነው፡፡ ጥጉ ጉዳዩን ሳያውቅ ይሁንታ የሰጠበት ምክንያት የቁስ ዓለም [ገንዘብ] እጦቱ ስለተሟላለት ነው፡፡ ለምን *አስፈረመው?* የሚፈልገውን ካሳካለት ሥጦታ፣ካላሳካለት ባለዕዳ ለማድረግ እና በትጋት

ሰርቶ ፍላጎቱን እንዲያሟላለት ነው፡፡ ከዚያም ጉዳዩን እንደሚቀበለው ካረጋገጠ በኋላ ድጋፌነህን ፡- ‹‹…አበሳጭቶ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሥራ ማባረር የሚጠበቅበት መሆኑን ነገረው፡፡ ‹‹ታዛዥ ነኝ እንኳን ይህችን ሌላም ለመታዘዝ ዝግጁ ነኝ›› አለ ከት ብሎ በመሣቅ (ጌታቸው፣1982፣109)፡፡ ጥጉ የምናባዊ ዓለም እጦቱ ድጋፌነህን በመበቀል እንደሚሟላ አመነ፡፡ በዚህም የሌላ ፍላጎት ማሟያ ሆነ፡፡ ይህን ያደረገም ገንዘብ እና የቤተሰብ ፍቅር ለማግኘት ነው፡፡

ጥጉ መስፍን ብር ስለሰጠው ድጋፌነህን በሥራ ፋታ ነስቶታል፡፡ አምሽቶ እንዲሠራ ያደርጋል፡፡ በዚህም ፀሐይን እንዳያገኛት ተደርጓል፡፡ ፀሐይ የድጋፌነህን መምጣት ትጠባበቃለች፡፡ ከዚያም ባለ ቀይ ማርቼዲስ ይጠራታል፡፡ ከመኪናው ውስጥ ገባችና ወደ ‹‹ራስ ሆቴል›› አመሩ፡፡

> ‹‹…ውብ መልኳ ያስደነግጠዋል፡፡ ቢወድም ባይወድም ማዋራት አለበት፡፡…ግን ምን ያረጋል የስንቱን ሴት ልብ የሰቀለው… የስንቱን እድል ያኮላሸ ምላሱ ተሳሰረበት መስማት እንጂ መናገር ተሳነው፡፡…ሁለት ቢራ አዘዘ ላለመጠጣት ብትግደረደርም አጥብቆ ስለለመናት እሽ አለችው››
> (ጌታቸው ፣1982፣111)፡፡

ፀሐይ ከመስፍን ጋር የሄደች ድጋፌነህ ስለቀረ እና መስፍንን ዘመድ ነው ብላ ስላሰበች ነው፡፡ መስፍን ማናገር የከበደው የአባቱን ሐሳብ ስላስታወሰ እና በምናባዊ ዓለም *ፋንታዚ* ስለተሸፈነ ነው፡፡ በውበቷ ፈዞ ፍቅር ቋንቋ አሳጥቶት ነው፡፡ አብዝቶ በመለመን ሳትፈልግ እንድትጠጣ ያደረገ በአልኮል ኃይል ሌላ ስትሆን የሚፈልገውን ለማግኘት ነው፡፡ ፀሐይ ላለመጠጣት የተግደረደረች የሴትነት ወጉ ስለያዛት እና ራሷን እንዳትስት ነው፡፡

ድጋፌነህ ፀሐይን ለሦስት ቀናት ስላላገኛት የተሰጠውን ሥራ በፍጥነት ሠርቶ ሄደ፡፡ ከዚያም ሊስትሮዎች ባለ ቀይ ማርቼዲስ እንደወሰዳት ነገሩት፡፡ ማን ይሆን? የሚል ጥያቄ ራሱን ጠየቀ፡፡ ከፀሐይ ጋር ከከተማ ውጪ መዝናናት ፈለገ፡፡

> ‹‹ ዛሬስ የእኔ ምርጫ መሆን አለበት ›› አላት፡፡
> ‹‹ ምርጫህ ምንድን ነው ?››
> ‹‹ ምርጫዬ ከከተማ ውጪ ወጥቶ ተፈጥሮን ማድነቅ ?›› ነው
> ‹‹ ደስ ይለኛል ከከተማ ግርግር…ጫጫታ ሰልችቶኛል›› አለችው››
> (ጌታቸው ፣1982፣114)፡፡

ለድጋፌነህ ‹‹ቀይ ማርቼዲስ›› አደገኛ ትእምርት አለው፡፡ ድጋፌነህ ‹‹ዛሬስ›› ማለቱ ከዚህ በፊት ያለ ምርጫው ይዝናና እንደነበር ለመግለጽ እና የባለ ቀዩ ማርቼዲስ ማንነት ስለረበሸው ነው፡፡

ከከተማ ውጪ ለመዝናናት ለምን ፈለገ? ስለፍቅራቸው ለማውራት እንዲመቼው፣በሥራ የተወጠረ አእምሮውን ለማዝናናት፣ተፈጥሮን ለማድነቅ፣በአለቃው የሚደርስበትን የሥራ ጫና ለመንገር ብቻ አይደለም። የባለ ቀዩን ማርቼዲስ ማንነት ማወቅ ስለፈለገ ነው። ተጨንቆ ነው። ቀንቶ ነው። ፍላጎቱን እንደሚነጠቅ አስቦ ነው። ከዚያም ድጋፌነህ ድንገተኛ ጥያቄ ይጠይቃታል። ‹‹ለመሆኑ ቤተሰቦችሽ እንዴት ናቸው? ይስማማሉ *በደም በአጥንት* ማለቴ በሀብት የሚያምኑ ናቸውን?›› አላት። ‹‹በእሱ ኩራ›› ቤተሰቦቼ ከእኔ ምርጫ ውጪ አይሆኑም ሙሉ ለሙሉ ዝግጁ ስንሆን ሽማግሌ መላክ ብቻ ነው ([አጽንዖት የእኔ]። ጌታቸው፣1982፣ 116)። ድጋፌነህ ቤተሰቦችሽ *በደም በአጥንት* ይስማማሉ፤ማለቱ ከዘመኑ አንጻር ከጋብቻ የሚያስከለክል ነገር እንዳለበት በኢ-ንቁ ልቦናው ያለው *በምላስ ወለምታ* አፈትልኮት ወጥቶ ሲሆን፣ወዲያውኑ ማለቴ በሀብት የሚያምኑ ናቸው ማለቱ አምልጦት በወጣው ነገር ስለደነገጠ ለማረሳሳት እና ሐሳብ ለማስቀየር ነው። ከዚህም ባሻገር ድጋፌነህ ስጋት አከል ጥያቄ እንዲጠይቅ ምክንያት የሆነው *‹‹የባለ ቀዩ ማርቼዲስ››* ማንነትን በኢ-ንቁ ልቦናው አስታውሶ ነው።

ጥጉ ከሥራ ለማባረር ሞክሮ ስላልተሳካለት ወደ በረሃ እንዲሄድ አቀነባበረ። ከዚያም አዲስ ለሚቋቋመው ፋብሪካ ለጥናት እንዲሄድ የሚል የትእዛዝ ደብዳቤ ደረሰው። ድጋፌነህ በጉዳዩ ቢያዝንም ወደኋላ አላለም። ‹‹...ደጋግሞ አነበበው። እንባው ዱብ ዱብ እያለ ደብዳቤው ላይ አረፈ። ‹‹ወንድ ሁን! አባትህ ደኃም ቢሆን ኩሩ ነበር፣አንተም ኩሩ ሁን፣ ለጠላትህ አትሸነፍ፣ ከዓመት በኋላ ዲግሪህን ታገኛለህ›› (ጌታቸው፣1982፣118)። ደብዳቤ የፍላጎት ማሳኪያ ሆኗል። Bertens, Lacanን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት ‹‹የቴክስቱን መዋቅር በወጉ ለመረዳት እና ተግባቦት ለመፍጠር ደጋግሞ ማንበብን ይጠይቃል›› (2001፣163)። በመሆኑም ድጋፌነህ ደብዳቤውን ደጋግሞ ማንበቡ ከዚሁ ሐሳብ ጋር የሚቆራኝ ነው። እንባው የውስጡን **ሌላ** ብሶት ፍላጎት በማውጣት ኃይል ሆኖታል። በሥራ ትእዛዙ ምክንያት ሥራውን ይለቃል፣ከትምህርቱ ይደናቀፋል እና ሥራ-አጥ ከሆነ ከፀሐይ ይለያል በሚል ነበር። ይሁን እንጂ ድጋፌነህ ወንድ ሆነ። የአባቱን ማንነት እና ቃል በኢ-ንቁ ልቦናው ማስታወሱም ብርታት እና ጽናት ሆነው።

ድጋፌነህ ለሥራ ሌላ ቦታ እንደተመደበ እና እንደሚሄድ ለፀሐይ ደውሎ ነገራት። ጥጉ የሰማውን ነገር ለመስፍን ነገረው። መስፍን በቁጣ፡- ‹‹...አንድ ዘመድ አልባ መናጢ ሰው ከሥራ መንግሎ ማስወጣት ከበደኝ ብትለኝማመን ነው የሚያቅተኝ›› (ጌታቸው፣1982፣119) አለው። መስፍን ጥጉን የተቆጣው ፍላጎቱ እንደማይሟላለት ስላሰበ ነው።

መስፍን ጥጉ እና ራሄል ለጥፋት ቅንብር ተገናኙ። ሲጠጡ አመሹ። መስፍን ልቡ በጭካኔ ተሞላ። ራሄልን ምን ታግዥኛለሽ አላት። *‹‹በእኔ እንኳን አትተማመን አለችው››* (ጌታቸው 1982፣123)። ራሄል ይኽን ማለቷ ፀሐይ እሽ እንደማትል ስለተረዳች እና ሁኔታቸው ስላላማራት መራቅ ፈልጋ ነው። መስፍን መረር ያለ በደል በድጋፌነህ ላይ ለመፈጸም አሰበ። ድጋፌነህን መግደል። ይህንንም ጥጉ እንዲፈጽም ትእዛዝ ሰጠው። ጥጉ የመንፈስ ደስታ ቢሰማውም ያገኘውን ደስታ የመነጠቅ ስጋት ስላደረበት ፈራ።

> ‹‹…ፍርሃት አስጨንቆታል። የድጋፌነህ ሞት ታወሰው እና ሚሥጢሩ ሲገለጥ እጁ በእግር ብረት ታስሮ ለፍርድ ሲቀርብ ሚስቱ…ልጆቹ…ሲያለቅሱ የፍርዱን ውጤት ለመስማት ሲመጡ።…የሥቅላት ሞት ሲፈረድበት…ሚስቱ እሪታዋን ስታቀልጠው፣ልጆቹ በእሱ ሞት ምክንያት በችግር ሲቆራመዱ ታወሰውና መስፍን ያወጣውን የጭካኔ ሐሳብ ጭራሽ ሊዋጥለት አልቻለም›› (ጌታቸው ፣1982፣124)።

z'iz'ek, Lacanን ጠቅሰው እንደሚሉት ‹‹የምናባዊ ዓለም **ሌላ** እጦት የማይሸሹት ፍላጎት ይሆናል። የአንዱ የበቀል ፍላጎት ሲሳካ የሌላው ምናባዊ **ሌላ** እጦት ይሆናል። ፍላጎቱ የተሟላለት ወዲያውኑ በበቀሉ በመደሰት ወደ **ሌላ** በቀል ይሸጋገራል (Ellmann,1994,104)። ጥጉ በበቀሉ የሚደርስበትን የምናባዊ ዓለም **ሌላ** እጦትን ያንጸባርቃል። እጦቱ የሚገለጸውም ድጋፌነህን በመበቀል ገንዘብ ማግኘት እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል። ይሁን እንጂ የጥጉ የምናባዊ ዓለም ፍላጎቱ አልተሟላም። ደስተኛም አልሆነም። ጥጉ ለራሱ ፍላጎት ሲል የመስፍንን **ሌላ** ፍላጎት ማሟያ መሆኑ ወደ አሮንቋ እንደሚያስገባውም አስቧል። ይህም **ሌላ**ነት የሚንጸባረቅበት ጭንቀት እና የምናባዊ ዓለም እጦትን ይጋርጥበታል። ጥጉ ድጋፌነህን ሲጎዳ ምንም አልመሰለውም ነበር። እየቆየ ግን ድጋፌነህን መጉዳቱ ረብሾታል። ጉዳዩ ይገላለጣል ብሎ ስጋት አድሮበታል። በኢ-ንቁ ልቦናው ያስፈረመውን እያስታወሰ የመስፍንን ድርጊት ስላልወደደው ነው። ይህም የምናባዊ ዓለም *ፋንታዚ* እንዲያዋቅር አድርጎታል። ድጋፌነህ ቢሞት ሊፈጠር የሚችለው ነገር የተዘበራረቀ ምናባዊ ዓለም ፈጥሮበታል። ጥጉ ድጋፌነህን ለመግደል የፈራ ውጤታማ መሆን እንደማይችል ስለተገነዘበ ነው። በሌላም ሰዋዊ ሐዘኔታ ስላለው ሲሆን፣በዋናነት ግን መስፍን ባለዕዳ እና ወንጀለኛ ሊያደርገው ስለሆነ ለራሱ እና ለቤተሰቦቹ አስቦ እና ተጨንቆ ነው።

አቶ ሞልቶለት የተግባቡትን ቃል ለመፈጸም ወደ አቶ አሰፋ ቤት ሄዱ። ተግባቡ። አቶ አሰፋ ተደሰቱ። ፀሐይ የመደሰቱን ምክንያት ጠየቀችው። እጮኛ እንዳላት ነገራት። ተበሳጨች።

> ‹‹ ምንድን ነው?›› ስትመኘው የነበረውስ ምንድን ነው?
> ‹‹ ጉዳዩ እንኳን ስለአንቺ ነው ››
> ‹‹ ምን? ›› ስትል በድንጋጤ ፊቷ ሁሉ ተለዋወጠ።
> ‹‹ የአንቺን ዓለም የማይበት ጊዜ ደርሷል ››
> በረጅሙ ተነፈሱና ዐይናቸውን በድንጋጤ ፊቷ ወደ ገረጣው ልጃቸው ላይ በመትከል
> ታሪኩን ተረኩላት፤በሕጻንነቷ መታጨቷን ስትሰማ ሕሊናዋን ልትስት ምንም ያህል አልቀራትም።...አልተቀበለችውም።
> (ጌታቸው ፣1982፣125-126)

የፍላጎት ኃይል በአባዊ ቁጥጥር ሥር ነው (Lacan,1977a,190)። አቶ አሰፋ ልጃቸውንም ሆነ ሚስታቸውን ሳያማክሩ የወሰኑ ለዚህ ነው። አቶ አሰፋ የተደሰቱ ፍላጎታቸው በምናባዊ ዓለም *ፋንታዚ* ስለተሟላ ሲሆን ፀሐይ ግን በውስጧ **ሌላ** ፍላጎት ስላለ ፈቃደኛ አልሆነችም። በምናባዊ ዓለም ፍላጎት እጦቷ በመዋተት ስሜቷ ተረብሿል። ፀሐይ ከድጋፌነህ ጋር የያዘችው የሽርሽር ቀጠሮ መሠረዙ እና ስለጋብቻ እና ስለቤተሰቦቿ ፈቃደኝነት ሲጠይቃት ምንም ችግር የለውም በማለት የመለሰችለትን በኢ-ንቁ ልቦናዋ ማስታወሷ፣ በምናባዊ ዓለም ፍላጎት እጦቷ በመዋለል እንድትረበሽ አድርጓታል።

## 3. 2. የመስታወት ደረጃ (ባይተዋርነት)

በዚህ ርእስ ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ የድጋፌነህ፣የሠናይት፣የፀሐይ እና የመስፍን ታሪክ ተነጥሎ የቀረበ ሲሆን፣ለባይተዋርነት የሚዳርጉ ድርጊቶች፣እንግዳ ኢ-ንቁ ፍላጎቶች፣ባይተዋርነት፣ የቋንቋ አጠቃቀም እና ወ.ዘ.ተ የተተነተነበት ነው። መስፍን ፀሐይን የራሱ የማድረግ ሙከራው ተጠናክሮ ቀጥሏል። ይህም በፀሐይ እና በድጋፌነህ መካከል ቅራኔን በመፍጠር እንግዳ ባህርይ እንዲጣባቸው ከማድረጉ ባሻገር መወጣት ወደማይችሉት አሮንቋ ሲዘፈቁ እና እነሱን ለመታደግ በሌሎች ገጸ-ባህርያት የሚደረጉ ጥረቶች ተብራርተዋል። ድጋፌነህ ሰካራም ሆነ። በዚህም እናቱ ራሳቸውን ለማጥፋት ሞከሩ። የሁለቱ የፍቅር ግንኙነት ጠላትን በማፍራቱ በእጅጉ የሚፈተን ከመሆኑ በተጨማሪ ፍርሃት፣ጭንቀት፣ስጋት እና ስቃይ ተስተውሎባቸዋል።

ድጋፌነህ በራሱ ሐሳብ የሚኖር፣ሌሎች ስለእሱ ስለሚናገሩት ትኩረት የማይሰጥ እና በራሱ የሚተማመን ገጸ-ባህርይ ነው። ለእናቱ አሳቢ፣ታጋሽ፣መልካም ጠባይ የነበረው ሲሆን፣በሒደት

ግን ግብታዊነት እና ባይተዋርነት ታይቶበታል። ፀሐይ እና ድጋፌነህ ሊረሳሱ አልቻሉም። በዚህም ነብስ ያለው ይመስል አንዳቸው የሌላቸውን ፎቶ-ግራፍ በማውጣት ይመለከታሉ። ይወቅሳሉ። ልዩ ክብር ሰጥተው ያስቀምጡታል። ባይተዋርነታቸው ሲያይልም መስታወቱን ወርውረው ይሰባብሩታል። በፍቅራቸው መካከል የተፈጠረውን ሴራ ለፎቶ-ግራፉ ያወያዩታል። በኢ-ንቁ ልቦናቸው ምሥል እየተፈራረቀ ፍርሃትን፣ስጋትን፣ጭንቀትን፣እጦትን፣የተሸናፊነት ስሜትን ይፈጥርባቸዋል። እነዚህም በምናባዊ እና በትእምርታዊ ሥርዓቶች ይገለጻሉ።

መስፍን በሲጋራ ጢስ ቀለበት ፀሐይ የእሱ እንደምትሆን አለመ። ከዚያም አንዱን ሲጋራ በሌላ ተካ። ‹‹በሲጋራ ጢስ ቀለበቶችን ይሰራ ጀመር። አንዷት ቀለበት አንደኛውን ቀለበት እያፈረሰች ብቻዋን ስትምዘገዘግ ይመለከታል። በጢሱ ቀለበት ውስጥ ድጋፌነህ እና ፀሐይን አያቸው። በንዴት እንደገና ሲጋራውን ስቦ ቀለበቶቹን አጠፋቸው። …ያለቀውን ሲጋራ አጥፍቶ ሌላ ለኮሰ …›› (ጌታቸው ፣1982፣99)። መስፍን ሲጋራ እንዲያጤስ ያደረገው የጥጉ እና የራሄል ንግግር እንዲሁም የድጋፌነህ ብርታት ስላበሳጨው እና ተስፋ ስላስቆረጠው ወደ ሌላ ምናባዊ በቀል በመሸጋገር የፀሐይ እና የድጋፌነህን ቃል ኪዳን ማቋረጥ ስለፈለገ ነው። በሲጋራው ጢስ ቀለበት የሚስለው ለዚህ ሲሆን፣በሌላ መልኩ ደግሞ ድጋፌነህን እንደ ጢሱ አበነዋለሁ ለማለት ነው። መስፍን በሲጋራ ጢስ አንደኛውን ቀለበት በማፍረስ ሌላውን የተካ በድጋፌነህ ቦታ ራሱን መተካቱን ለመግለጽ ነው። ያለቀውን ሲጋራ አጥፍቶ ሌላ የለኮሰም ለዚህ ነው።

መስፍን ከሽማግሌዎቹ ጋር ከእነ-ፀሐይ ቤት ደርሶ መጣ። በዚህም ስለተደሰተ ከአልኮል መጠጥ ላይ በረዶ እየጨመረ ሲጠጣ አመሸ። ሰከረ። አስመለሰው።

> ከት ብሎ ሳቀና ሎሚውን በምላሱ ላስ ላስ አድርጎ ብርጭቆው ውስጥ ጨመረው። በማንኪያ አንዱን በረዶ ለማንሳት ሲል *በረዶው ወደቀ። ሌላ በረዶ አንስቶ ብርጭቆው ውስጥ ጨመረ*።… ልቤ… ልቤን ያኘኘ አላት ሰራተኛዋን።…ግቢ ነብስ ውጭ ነብስ …ወይኔ እናቴ›› አለ ለሀጩ ተዝረከረከ ሊተፋው ፈለገ፣ ለሀጩ ግን እንደቀጭን ክር ከአፋ ሰሆኑ ድረስ ደረሰ። *የማይበጠስ ክር መሰለ።* እንደምንም አፋን ጠራርጎ እስከ ነጫማው አልጋው ላይ በጀርባው ተንጋሎ ማንኮራፋት ጀመረ። [አጽንዖት የእኔ]
> (ጌታቸው ፣1982፣135)

መስፍን መጠጥ አብዝቶ የጠጣ ፀሐይን የራሱ ማድረግ እንደቻለ ምናባዊ ዓለም ስለገነባ ነው። የበረዶው ትእምርት ጋብቻ ሲሆን፣ይህም በታሪኩ ተመላክቷል። *የበረዶው መውደቅ* ደግሞ የድጋፌነህ ፍቅር እንዳለቀለት አመላካች ነው። *ሌላ በረዶ አንስቶ ከብርጭቆው መጨመሩ*

ደግሞ በድጋፌነህ ቦታ ራሱን መተካቱን ጠቋሚ ነው፡፡ *የማይበጠስ ክር መሰለ* ማለቱ ሁለቱን ለመለያየት እንደከበደው እና ስጋት እንደፈጠረበት የሚያመላክት ነው፡፡

ፀሐይ የድጋፌነህን ፎቶ-ግራፍ ተመለከተች፡፡ ቀዳደደችው፡፡ ከዚያም ሌላውን የድጋፌነህ ፎቶ በልዩ ፍሬም አስቀመጠችው፡፡ እንደምትወደው ገልጻም አለቀሰች፡፡

> ‹‹ምን ይጠቅመኛል?›› አለች እና ለማስታወሻ የሰጣትን ፎቶ-ግራፍ አውጥታ ትኩር ብላ ተመለከተች፤
> ‹‹አንተ ጨካኝ አለች በምሬት እጆቿ ምን እንዳዘዛቸው ሳታውቀው ፎቶውን መቅደድ ጀመረች ከሐሳቧ ስትነቃ ቀዳዋለች *በመቀደዱ አዘነች፡፡* ሌላ የሰጣትን ፎቶ አወጣች…የሚች አያቷን ፎቶ ደስ ከሚል ፍሬም ውስጥ አውጥታ በምትኩ የድጋፌነህን ፎቶ-ግራፍ ከተተችው ፡፡››
> ‹‹እኔ እድሜ ልኬን እወድሃለሁ መልካሙንም እመኝልሃለሁ፡፡ አለችና በሁለት እጆቿ ይዛ *ራቅ አድርጋ ተመለከተችው* እንባዋ በአራት መንታ ይወርድ ጀመር፡፡ ፎቶውን እንቅ አድርጋ ወደ *ደረቷ አስጠጋች እና ትንሡቀሡቅ* ጀመር፡፡ [አጽንዖት የእኔ]
> (ጌታቸው ፣1982፣152-153)

የፋለስ እጦት ባይተዋርነት እንዲፈጠር እና *በፋንታዚ* ዓለም የተዘበራረቀ ምሥል እንዲታይ ያደርጋል (Lacan,1977a,4)፡፡ ፀሐይ በፎቶው አልፋ የምትመለከት የራሷን ፍላጎት እና ምናባዊ እጦቷን ነው፡፡ ፀሐይ የድጋፌነህን ‹‹ፎቶ ወደ ደረቷ የለጠፈች›› በምናባዊ የፋለስ ናፍቆት እየዋለለች ስለሆነ ነው፡፡ ከየት እንደመጣ በማይታወቅ ኃይል ፎቶ-ግራፉን መቀዳደዷም የፍላጎት ምንጭ የማይታወቅ መሆኑን ጠቋሚ ነው፡፡ *ፎቶውን በመቅደዷ* ያዘነች በድርጊቷ ስለተጸጸተች፣ድጋፌነህን ስለምትወደው እና መለየት ስለማትፈልግ ነው፡፡ የሚች አያቷን ፎቶ አውጥታ የድጋፌነህን መተካቷም ለድጋፌነህ ያላት ፍቅር ከፍ ያለ መሆኑን ማሳያ ነው፡፡

ድጋፌነህ ፀሐይ ተለይታኛለች ብሎ ማሠቡ ስለረበሸው ቤት እና መንደር መቀየር ፈለገ፡፡ ከዚያም ለእናቱ ነገራት፡፡ ካቅማሙ በኋላ ሳይፈልጉ ፈቃደኛ ሆኑ፡፡ ከጎረቤቶቻቸው ጋር በእንባ ተሸኛኙ፡፡

> ‹‹…*ፈቃድህ* ቢሆን *የአባትህ ሬሳ* የወጣበት ቤት የእኔም ሬሳ ቢወጣ ደስ ይለኝ ነበር፣አንተ የምትወዳት ጋር አሻህ ሥፍራ ብትኖር ጥሩ ነበር›› አሉት፡፡
> ‹‹እማዬ ብቸኛ ነኝ ከእንግዲህ ከአንቺ ከእናቴ በስተቀር ማንንም አላምንም ይልቅስ አታመንቺብኝ›› ሲላቸው ደነገጡ ጭንቅላቱ ምን እንደሆነ ወዲያው ገባቸው *‹‹ጥንቱኑ ያለአቅምህ››* አሉ ቀስ ብለው፣ *ዕቃቸውን* ተከራይቶ ባመጣው *የዕቃ መጫኛ* መኪና ላይ

ማስጫን ጀመሩ። አያስፈልግም የሚለውን ዕቃ ለጎረቤቶቹ ሰጣቸው እናቱ ከሚወዷቸው ጎረቤቶቻቸው ጋር መላቀስ ጀመሩ።
[አጽንዖት የእኔ]
(ጌታቸው ፣1982፣155)

ወ\ሮ እታፈራሁ ለሙት መንፈስ ተገዥ ናቸው። *የአባትህ ሬሳ* ከወጣበት የእኔ ሬሳም ይውጣ የሚሉት ለዚህ ነው። አልሄድም ያሉት በስተርጅና ለሰው ባዕዳ ለመንደሩ እንግዳ መሆን ስላልፈለጉ እና አግብቶ ትቶኝ ይሄዳል በሚል ስለሰጉ ነው። *‹‹ጥንቱኑ ያለአቅምህ››* ማለታቸው እንደማይዛለቁ የገለጹትን በኢ-ንቁ ልቦናቸው አስታውሰው ነው። (እዚህ ላይ፣‹‹በፍላጎት ትንተና›› እስኪ መጨረሻውን ያሳምረው ያሉትን ማስታወስ ይገባል)። ድጋፌነህ ቤት እና መንደር መቀየር የፈለገ ለምንድን ነው? ብቸኛ ስለሆነ፣ተከድቻለሁ ብሎ ስላሠበ፣የተሻለ ቤት ለመኖር፣ፀሐይ እየመጣች እንዳትጨቀጭቀው፣የበፊቱን ላለማስታወስ ብቻ አይደለም። የመንደሩን ሰው ሐሜት ስለፈራ እና እንግዳ ባህርይ ማምጣት ስለፈለገ ነው። በመሆኑም የድጋፌነህ እጦት **ሌ**ላ መሠረታዊ ፍላጎት እንዲሟላ አድርጓል።

ድጋፌነህ ቤት እና መንደር ቢቀይርም የፀሐይ ትዝታ አብሮት ዘልቋል። ‹‹ቃል ኪዳን እና ፎቶ-ግራፍ›› ከልቦናው እና ከቤቱ አልጠፉም። ከዚያም ፎቶዋን የእኔ ነበርሽ፣አሁን ግን ከድተሽኛል በማለት ይመለከታል። ቃሌን አክብራለሁ በማለት በልዩ ክብር ያስቀምጠዋል።

> ‹‹ፈገግታሽ ደስ ሲል! ጥርሶችሽ ማማራቸው አሁን ግን የእኔ ንብረት አይደሉም። በየዋህነት ዘመኔ የእኔ የግሌ ይመስሉኝ ነበር። ይህን ውበት ይህን ፈገግታ በገንዘብ ለወጥሽው በማለት ፎቶዋን የሚያምር ፍሬም ውስጥ ካስገባው በኋላ፣‹‹ፀሐይ ሳሎን አላስቀምጥሽም *ስተኛ ተሳልሜሽ፣* ቃሌን አከብራለሁ፣ብዬ ስሜሽ ! ተመልክቼሽ ደህና እንቅልፍ እተኛ ዘንድ ከአልጋዬ ጎን ካለው ኮመዲኖ ላይ አስቀመጠና ራቅ ብሎ ከመቼውም የበለጠ ዐይኑን አፍጦ ተመለከተ›› ፎቶዬን ከጎንሽ አጠገብ እንኳን የማስቀመጥ መብት የለኝም። አንቺ የእኔ ሳትሆኚ አንቺ አንቺነትሽን በገንዘብ ለውጠሻልና በማለት አንዴ ወደ አንዱ ሌላ ጊዜ ወደ ሌላው ክፍል በመንቆራጠጥ ቤቱን ማዘጋጀት ጀመረ። [አጽንዖት የእኔ ]
> (ጌታቸው ፣1982፣156)

እንደ Lacan, አባባል ‹‹እኔ በትእምርታዊ ሥርዓት በቋንቋ የእጦት ሲግኒፋየር የሚዋቀር እንጂ ጠጣር አይደለም።›› (Rawson and Nisbet, 2008, 83)። ድጋፌነህ ፀሐይን እና ውበቷን የእኔ የግሌ ትመስይኝ ነበር፤አሁን ግን የእኔ አይደለሽም ማለቱ ማንነት በሌለ ነገር ላይ የሚዋቀር መሆኑን የሚገልጽ ነው። ‹‹የእኔ የግሌ›› የሚለው ምኗን ነው? ውበቷን፣

ፈገግታዋን፣ እሷነቷን ምኗም የእሱ አይደለም፡፡ እኔ ተጨባጭ ስላልሆነ እንኳን ፀሐይ ድጋፌነህ ለራሱ አይደለም፡፡ ራሱ ለራሱ ባይተዋር ነው፡፡ ይህም በሚያፈልቀው ተለዋዋጭ ሐሳብ ይገለጻል፡፡ ምኗ ነው የ**ሌ**ላ የሆነ? ምኗስ ነው በገንዘብ የተለወጠ? ‹‹ምኗም›› ነው፡፡ ምክንያቱም የ‹‹እኔነት›› (*Subjectivism*) ቅርጽ እና ድጋፌነህ በምናባዊ እና በትእምርታዊ ዓለም የቀረጸው ቅርጸት ተጨባጭነት እና ምልዑነት የጎደለው ነው፡፡ ፎቶ-ግራፏ ከባይተዋርነት የሚያላቅቀው ምትክ ፍላጎቱ ሆኗል፡፡ እሷን ያገኘ እየመሠለው *በፋንታዚ* ዓለም ምትሃታዊ ለሆነው ፎቶ-ግራፍ ልዩ ክብር መስጠቱም የጠላት ቢመስልም፣ፍላጎቱ እንደሆነች አመላካች ነው፡፡ ምናባዊ ከሆነ **ሌ**ላ ጎራ ያሰለፋት የፍቅሩን ኃያልነት ለመግለጽ ሲሆን፣*‹‹ስተኛ ተሳልሜሽ››* የሚል ለዚህ ነው፡፡ እሱ(እሷ)፣ **ሌ**ላ (ፎቶ-ግራፋቸው) እና **ሌ**ላ (ፍሬሙ) ናቸው፡፡ ሁለቱም በሚያምር ፍሬም ፎቶውን ማስቀመጣቸው ለዚህ አስረጂ ነው፡፡

ድጋፌነህ በተጋበዘው *መሠረት* መስፍን እና ፀሐይ ከሚዝናኑበት *ሥፍራ* ባለፈ ጊዜ ትዝታ እና በመምታታት ታጅቦ አመራ፡፡

> የእኔዋ ፀሐይ ሰበታ ትመጣ ይሆን? ወይስ ኧረ ባልመጣች›› ይላል፡፡ በመጣችና እርሜን ባወጣሁ በዐይኔ ባረጋገጥኩ ምንም አልፈልግም ከዐይን ወዲያ የሚታመን ነገር የለም ካልሆነ ግን ሐሳቧን ትለውጥ ዘንድ አላምናትም፡፡ የለም! የለም! አልለምናትም *ድኃ ነኝ ግን ኩሩ ድኃ ማንንም የማልለምን? የማልለማመጥ ኩሩ ነኝ፣* ከአባቴ የወረስኩት ነው፡፡…እናቴ ብቻ ደህና ትሁንልኝ›› በማለት ያስባል ወዲያው ግን ከፀሐይ ጋር ያሳለፈው የደስታ ጊዜ ይታየዋል፡፡
> ‹‹ፀሐይ እኮ ለእኔ ልዩ ነበረች…ደግነቷን መርሳት የለብኝም›› ወይኔ ምን ያደርጋል ያን ሁሉ ደግነቷን ገደል ከተተችው፡፡በማለት የፊት ለፊቱን ብረት ገጨት ገጨት አደረገ፡፡ [አጽንዖት የእኔ]
> (ጌታቸው ፣1982፣162-163)

ድጋፌነህ *‹‹ድኃ ነኝ!››፣‹‹ኩሩ ነኝ!››፣‹‹ማንንም አልለምንም፣አልለማመጥም››* በሚል ራሱን እንዲገልጽ ያደረገው የአባቱ ቃል ሲሆን፣ይኸንም የተጠቀመ ራሱን ለማጽናናት፣ይቅርታ ላለመጠየቅ እና ለመወሰን ፈልጎ ቢሆንም፣የሦስትዮሽ መምታታት ይፈጠርበታል፡፡ አንዴ የአባቱን ማንነት፣ በሌላ ጊዜ ስለእናቱ፣አለፍ ሲልም ስለፀሐይ መልካምነት በኢ-ንቁ ልቦናው በማስታወስ፣ለመወሰን ሲቸገር ይታያል፡፡ ይህም ፀሐይን ማጣት እንደማይፈልግ ጠቋሚ ነው፡፡

ድጋፌነህ ከውስጥ ድምጹ ጋር እየተጋጨ ወደ ቀጠሮ *ሥፍራው* ሲያመራ ቀይ ማርቼዲስ ሲያልፍ አየ፡፡ ፀሐይን በመስኮቱ *ሥላያት* ተደናገጠ፡፡

ቀይ ማርቼዲስ እንደ ውኃ እየፈሰሰች በአጠገባቸው አለፈች ፀሐይ እጇን በመስኮት አውጥታ የለበሰችው *ቀይ ልብስ ያ* የሚያውቀው ያ ዘወትር ይህን ልብስ ስትለብሺ ደስ ይለኛል ይላት የነበረው ነው፡፡ በመስኮት የሚገባው ነፋስ ፀጉሯን ብትንትን ያደርገዋል፡፡ ‹‹እነሱ ናቸው! አዎ! አለ…እንባው በዐይኑ ሙሉ ግጥም አለበት፡፡

[አጽንዖት የእኔ]

(ጌታቸው ፣1982፣163-164)

Lacan, እንደሚሉት ‹‹የገጸ-ባህርያት የእይታ ውስንነት ከሚታየው በስተጀርባ ካለው እውነት ያፋታቸዋል›› (1977a,191)፡፡ ድጋፌነህ ቀዩ ማርቼዲስ በትእምርታዊ ዓለም እየተሰነቀረ እረፍት ነስቶታል፡፡ ድጋፌነህ የደነገጠ የኑሮ ልዩነት ንጽረተ-ዓለም ውስጥ ገብቶ እና ፀሐይ እጇን በመኪናው መስኮት አውጥታ ሥላየ ነው፡፡ ያለፈ ጊዜ ናፍቆት ውስጥ ስለገባ እና እሱ የሚወድላትን ቀይ ልብስ ለብሳ ሥላያት ነው፡፡ ፀሐይ ግን እጇን በመስኮት ያወጣች የመስፍን ድርጊት ስላስጠላት እና የሌላ ፍላጎቷን እየተመለከተች ስለሆነ ነው፡፡ ድጋፌነህ የሚያውቀውን እና ስትለብሰው የሚወድላትን ቀይ ልብስ እንድትለብስ የተደረገም ሆን ተብሎ ድጋፌነህ እንዲበሳጭ ስለተፈለገ ነው፡፡ በመሆኑም በድጋፌነህ ኢ-ንቁ ልቦና ‹‹ቀይ መኪና እና ቀይ ልብስ›› ለምናባዊ እና ትእምርታዊ ዓለም ባይተዋርነቱ ምክንያት ናቸው፡፡ የድጋፌነህ ዐይኑ እንባ ያቀረረ ደግሞ ከፀሐይ ጋር ያሳለፉትን ጊዜ አስታውሶ እና ለምን ተከዳሁ? በሚል ቁጭት ነው፡፡ እንዲሁም ድኃ በመሆኑ ፀሐይን እንዳጣት እና ስለጋብቻው አታስብ ዝግጁ ስትሆን ብቻ ሽማግሌ መላክ ነው ያለችውን በኢ-ንቁ ልቦናው አስታውሶ ለባይተዋርነት ስለተዳረገ ነው፡፡

የፀሐይ እናት ወ\ሮ ዘለቃ አቶ አሰፋ ወ\ሰንበትን ያገቡ ከቤተሰቦቻቸው ፍቃድ ውጪ በራሳቸው ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ልጃቸው የፈለገችውን እንድታገባ መከሯት፡፡ ወደ ሸርሸሩ ሥፍራ እንደምትሄድም ተግባቡ፡፡ ይሁን እንጂ ፀሐይ፡- ‹‹የሸርሸሩ ቦታ ሰበታ መሆኑን ሲነግራት የሆነ ስሜት ተሰማት ሌላ ቦታ ቢሆን ይሻላል ብላው ነበር ግን መስፍን ፈቃደኛ አልነበረም›› (ጌታቸው፣1982፣164)፡፡ መስፍን የሸርሸሩን ቦታ ሰበታ እንዲሆን የፈለገ ትዝታ ለመቀስቀስ ነው፡፡

ድጋፌነህ ከተቀጠረበት ሥፍራ ደረሰ፡፡ ከዚያም ጋቢውን ተጎናንቦ ሲያማትር ከድንጋይ ላይ ተቀምጠው አያቸው፡፡ በዚህም ጊዜ ፀሐይ ይበልጥ ውብ ሆና ታየችው፡፡ ‹‹…ጋቢውን ተከናንቦ ማንነቱን ሳያሳውቅ በዐይኑ ይፈልጋቸው ጀመር በሩቅ ከአንድ ድንጋይ ከተሠራ መቀመጫ ላይ እንደተቀመጡ አያቸው፡፡ የእሱ ስላልሆነች ነው መሠል የበለጠ ያማረች የደመቀች መሠለው›› (ጌታቸው፣1982፣165)፡፡ ድጋፌነህ ጋቢ ተጎናንቦ በቦታው የተገኘ ፀሐይ እንዳትለየው ሲሆን፣

ያማረች የመሠለው ደግሞ ስለቀና ነው፡፡ ከዚያም መስፍን ወደ ፏፏቴው እንዲሄዱ ጠየቃት፡፡ ፀሐይ ግን ትዝታ ስላለባት ፈቃደኛ አልሆነችም ነበር፡፡ በኋላ ግን ተቀበለችው፡፡

> ‹‹የዛሬን ብቻ ያውጣኝ›› አለች ሰውነቷ በቀዝቃዛ ላብ ተነከረ፡፡ ድጋፌነህ በዐይኑ ተከተላቸው መስፍን እጇን በትከሻዋ ላይ ሲያሳርፍ ተመልክቶ ሰውነቱ አንዳች ነገር የወረረው ይመስል ሰቀጠጠው ››
> ‹‹ይህን ጉድ ከማይ ወደ ቤቴ መመለስ ይሻለኛል ››
> (ጌታቸው ፤1982፤165)፡፡

መስፍን ወደ ፏፏቴው እንዲሄዱ የፈለገ ትውስታ ለመቀስቀስ እና ድጋፌነህን ለማበሳጨት ነው፡፡ የመስፍን እጅ ትከሻዋ ላይ ሲያርፍ የወረራት ጥላቻ እና የሌላ እጦት ትውስታ ነው፡፡ ድጋፌነህ ያየውን ማመኑ ራሱን እና ፀሐይን በተሳሳተ መልኩ እንዲረዳ፤ተስፋ እንዲቆርጥ እና ወደ ቤቱ ለመመለስ እንዲያስብ አድርጎታል፡፡

ድጋፌነህ ፀሐይን ለመርሳት እና ከልቡ ለማውጣት ማሠቡ መምታታትን ፈጥሮበታል፡፡ ‹‹ከእንግዲህ ወዲያ *የምችል ከሆንክ* ከልቤ አውጥቼሻለሁ፤ለእኔ ከእንግዲህ ሞት ነሽ›› ለእኔ ከእንግዲህ ፀሐይ የምትባል ሴት *ሞታ የተቀበረች ሬሳ* ናት›› በማለት ለመሄድ አቅማማ›› ([አጽንዖት የእኔ]፡፡ ጌታቸው፤1982፤166)፡፡ Lacan, ‹‹ገጸ-ባህርያት ያለውን የለም፤ የሌለውን አለ፤በሚል ርስ በርስ የሚጋጩ ሲሆን፤ ይህም ለጥላቻ እና ውድቀት እንደሚዳርጋቸው ይገልጻሉ›› (1977a,191):: ድጋፌነህ በምናባዊ ዓለም የሌለ እንዳለ፤ያለ እንደሌለ አድርጎ ይገነባል፡፡ ፀሐይ ሳትሞት እንደሞተች አድርጎ ማንነቷን ያዋቀረ ባየው ነገር ስለጠላት እና መርሳት ስለፈለገ ነው፡፡ ‹‹ለእኔ ከእንግዲህ ሞት ነሽ›› ያላት መስፍን ያስገድለኛል ብሎ ስለፈራ ነው፡፡ ድጋፌነህ በቃላት ኃይል ፀሐይ ‹‹ሞታለች›› ቢልም ከውስጡ ግን አልወጣችም፡፡ ለመሄድ አለመሄድ ያቅማማ ለዚህ ነው፡፡ አስፋው ድጋፌነህ ፀሐይን እንዲረሳት መከረው፡፡ ድጋፌነህ ራስ ወዳድ በሆነ መልኩ አልችልም አለው፡፡

> የእኔ እና የአንተ ፍቅር የተለያየ ነው እኔ ለፀሐይ ሞቸላታለሁ *በድን ሬሳ እንደ አባቴ አፈር ትቢያ...እሷ ግን...እኔን* አሳልፋ ለሀብታም ገንዘብ ስትል ከድታኛለች፡፡ ድንቅና ብርቅ የሆነ *ገላዋን አሳልፋ* ሰጠችው፡፡ ይህ ነው እኔን ናላየን እያዞረ ሰካራም ያደረገኝ...አንተ ምን አልባት ፍቅር ሊኖርብህ ይችል ይሆናል... እንደእኔ ዘልቆ የሚገባ አይመስለኝም...፡፡ [አጽንዖት የእኔ]
> (ጌታቸው ፤1982፤227)

ድጋፌነህን ሰካራም ያደረገው ስለፀሐይ መጨነቁ እንደሆነ ከትረካው ተመላክቷል። መርሳት አልችልም ማለቱም **ሌላ** እጦት ሆኖበታል። *Basic Psychological ideas*, (undated)፡- ‹‹አፍቃሪ ተፈቃሪን እኔ ያላንቺ ምንም ነኝ! ካለ አፍቃሪ የተፈቃሪ ተገዥ ነው›› (ገጽ፣38)። ድጋፌነህ ራሱን እንደ ሙት የቆጠረ ስለተከዳ እና ከፀሐይ ውጪ ሞቱን እንደሚመርጥ ለመግለጽ ነው። እንዲሁም የትእምርታዊ አባቱን ቃል በኢ-ንቁ ልቦናው አስታውሶ እና ገላዋን ለሌላ አሳልፋ የሰጠች ስለመሰለው ቀንቶ ነው።

ፀሐይ በአካል ከመስፍን ጋር ብትሆንም በመንፈስ ከድጋፌነህ ጋር ናት። ከድጋፌነህ ጋር ያሳለፉት ተዝናኖት በምናቧ ተቀርጿል። ከዚያም መስፍን ‹‹ለስላሳ ይዤ ልምጣ›› ብሏት ሲሄድ ተደሰተች። ‹‹...እዚህች ሥፍራ ከድጋፌነህ ጋር ያሳለፈችው ጊዜ ትዝ አላት እና ሥቅሥቅ ብላ ታለቅሥ ጀመር። ከቦርሳዋ ውስጥ ቀይ መልክ ያላት መሐረብ አውጥታ እንባዋን ጠረገች›› (ጌታቸው፣1982፣166)። Lacan, ‹‹የሰው ልጅ ለኢ-ንቁ ልቦናው ተገዥ ሲሆን፣ ያለፈን ጊዜ ባስታወሱ ጊዜም ያልተረጋጋ ስሜትን ይፈጥርባቸዋል›› (Bailly,2009,18)። ፀሐይ ያለፈን ጊዜ አስታውሳ ያለቀሠች ያልተረጋጋ ስሜትን ስለፈጠረባት ነው። መሐረቡ እንባን ብቻ የሚጠርግ ሳይሆን የድጋፌነህ ምትክ እና ማስታወሻ ነው። የምናባዊ ዓለም እጦቷን ትእምርታዊ በሆኑ ቃላት እና በሥፍራው ታሟላለች። በዚህም ምክንያት በአካል ካለው መስፍን ይልቅ *‹‹በቃል እና በመንፈስ››* ከውስጧ ካለው ድጋፌነህ ላይ አተኩራለች።

ድጋፌነህ በመዝናኛ ቦታው ምን ምን አጋጠመው? መስፍንስ ፀሐይን ለስላሳ ላምጣ ብሎ ሄዶ ድጋፌነህን፡- ‹‹...ምን ልትሠራ መጣህ? እዚህ ቦታ እኮ ብቸኛ ሆኖ መምጣት ያስጨንቃል እንጂ አያስደስትም›› በማለት የፌዝ ሣቅ መሣቅ ጀመረ። ...አንጀቱ እየተቃጠለ›› (ጌታቸው ፣ 1982፣166)። የመስፍን ንግግር ኢ-ንቁ ልቦናን በመቀስቀስ ለብቸኝነት እና ለብስጭት የሚዳርግ ነው። *ፋንታዚ* የሆነ ሣቅ የሣቀ ብስጭቱን ለመጨመር ሲሆን፣የድጋፌነህ አንጀቱ በብስጭት የተቃጠለም ያለፈን ጊዜ ስላስታወሰ እና በመስፍን ንግግር ስለተበሳጨ ነው።

ድጋፌነህ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ከዚያም ከአልጋው አጠገብ ኮመዲኖ ላይ ያለውን የፀሐይን ፎቶ አንስቶ ሲመለከት እንቅልፍ የሚነሳ የተዘበራረቀ ስሜት ፈጠረበት። ‹‹በፎቶው ላይ ቀይ ማርቼዲስ ታየው...እንደ ገና ፀሐይ...ትንሽ ቆይቶ መስፍን በፀሐይ ትከሻ ላይ እጆቹን ጣል አድርጎ አቅሙን አያውቄ በአጠቃላይ የመስፍን ፋከራ ታየው። ...*መረታቱን* አመነ። ያደገ ጺሙን እያከከ አልጋው ላይ ይገላበጥ ጀመር›› ([አጽንዖት የእኔ]። ጌታቸው፣1982፣167)።

Lacan, ‹‹ገጸ-ባህርያት በልፋታቸው ልክ ካልተሳካላቸው ራሳቸውን ከእድለ-ቢስነት ጎራ ያሰልፋሉ፡፡ የተጣባቸውን የተስፋ-ቆራጭነት ስሜትም በቋንቋ ይገልጻሉ›› (1988b,210) ይላሉ፡፡ ድጋፌነህ መረታቱን የሚገልጽ ከጽንሰ-ሐሳቡ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ *መረታቱን እንዲያምን ያደረገው ነገር ምንድን ነው? የድጋፌነህ የመረታቱ ምክንያት መኪና የሌለው መሆኑ ሲሆን፣* ይኸም በትእምርታዊ የተገለጸ የተስፋ-መቁረጥ እና የእጦት ምልክት ነው፡፡ ይህም የተዘበራረቀ የምናባዊ ዓለም ምሥል እና ትእምርታዊነትን ፈጥሮበት እንቅልፍ ነስቶታል፡፡

ፀሐይ ከሰበታ እንደተመለሰች በእንባ ያበጠ ፊቷን ታጥባ ማሰላሰል ጀመረች፡፡ ለድጋፌነህ እናት የተፈጠረውን ሁሉ መናገር ፈለገች፡፡ ከዚያም ራሷን ለውጣ ወደ እነ-ድጋፌነህ ቤት አመራች፡፡ ይሁን እንጂ የእነ-ድጋፌነህ ቤት ተቆልፏል፡፡ ‹‹...ደስ አላት በችኮላ ልብሷን ቀይራ *ጋቢ ደርባ* ተጓዘች፡፡ ከእነ-ድጋፌነህ ቤት ስትደርስ *ቤቱ ተቆልፏል* ልቧ ሊቆም ደረሰ፡፡ በድንገት ወሬኛዋን አሮጊት አገኘች እና ሰላምታ ሰጠቻት›› ([አጽንዖት የእኔ]፡፡ ጌታቸው፣1982፣168)፡፡ ፀሐይ ወደ እነ-ድጋፌነህ ቤት የሄደች ብቸኝነት ስላስጨነቃት ይቅርታ ለመጠየቅ ሲሆን፣*ጋቢ ደርባ* የሄደች ደግሞ የመንደሩ ሰዎች ወሬውን ሰምተው ከሆነ ማንነቷን አውቀው እንዳያሟት ስለፈለገች ነው፡፡ ከዚህም ልብስ ማንነትን እንደሚለውጥ እንገነዘባለን፡፡ *የቤቱ መቆለፍ* የልብ መቆለፍን፣ የማግኘት ተስፋ መመናመንን ጠቋሚ ነው፡፡ ከዚያም አሮጊቷ ምሬት በተሞላበት መልኩ እንዲህ አሏት፡-

> ‹‹አየሽ ልጄ ልጇ ከበርቴ ሞጆ፣ቱጃር ሆነና የድሮውን ጭራሽ ረስቶ ፍርፋሪ በልቶ ማደጉን ዘንግቶ አሮጌ ዕቃውን ጥሎልን እንኮኮ ብለን ሽንቱን እየሸናብን አሳድገን ደህና ሰንብቱ ሳይለን ከአዲስ አበባ ውጭ ሄደዋል...ውይ...ውይ...ጭካኔ እግዜሩስ አድባሩስ አይወቅሳቸውምን? እኛ ገንዘብ ስጠን አንለው! ውይ! ውይ! አሉ እጃቸውን ወደ ሰማይ ዘርግተው አንገታቸውን በማንጋጠጥ-ተንገሸገሹ፡፡ (ጌታቸው፣1982፣169)

ለአሮጊቷ ድጋፌነህ ቱጃር ማግባቱን ማን ነገራቸው? የልጅነት አስተዳደጉን ስበው የሚያመጡት በንጽረተ-ዓለም መኩራራቱን ለመጠቆም ነው፡፡ አሮጊቷ እንዲህ የሚሉት ብቸኛ ስለሆኑ እና ቡና አጣጫቸውን ስላጡ ነው፡፡ ሌላው ልጅ ስለሌላቸው በራሳቸው ላይ አዝነው ሲሆን፣የተንገሸገሹት ደግሞ ‹‹ለመርገም›› ነው፡፡ ፀሐይ የአሮጊቷን ንግግር ጥጉ ከነገራት ጋር በማዛመድ ስሜቷ ተረበሸ፡፡ ሁሉም ነገር ‹‹ምንም›› ሆነባት፡፡ ብቻዋን እየተናገረች ከዳተኛ! ወንዶች አረመኔዎች በማለት እያማረረች ወደ ቤቷ ሄደች፡፡

ድጋፌነህ እረፍቱን ጨርሶ ወደ ሥራ ገበታው ተመለሠ። የሥራ ትእዛዝ አክባሪ በመሆኑ ሹመትና ሽልማት አገኘ። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ መጠጥ ቤት ሄደ። ጠጥቶ የማያውቀውን አልኮል ጠጣ።አመሸ።ሰከረ።እናቱ ያለወትሮው በማምሸቱ ተጨነቁ። በኋላ ግን እየዘፈነ መጣ።

> ‹‹…ብቻቸውን ሲጨነቁ…እየዘፈነ የሚመጣ ሰው ተመለከቱ ልጄ ይሆናል የሚል ግምት ጭራሹኑ አላሰቡም ግን ልጃቸው ነበር። ድጋፌነህ *እየተኮላተፈ ‹‹ሴትን…*ሴትን *ያመነ…ጉ*ም የጨበጠ… አንድ ነው…›› ይል ነበር።
> እየዘፈነ ገብቶ አልጋው ላይ ቁጭ አለ። እናቱም ትኩር ብለው ተመለከቱት፡- እናቱን *ማሪኝ የሚልበት ቋንቋ አጥቶ ዲዳ ሆነ*።… *ያያቸዋል ሊያናግራቸውና ማሪኝ…*እማዬ ሊላቸው ይፈልጋል ግን *አፉ ስለተሳሰረ* ከመመልከት በስተቀር ምንም ሊላቸው አልቻለም። ጫማውን ለማውለቅ ሞከረ ግን አልቻለም። [አጽንዖት የእኔ]
> (ጌታቸው ፣1982፣173-174)

Hill, እንደሚሉት ‹‹ሕጻኑ ቋንቋ መጠቀም ሲጀምር ከራሱ እና ከእናቱ ባይተዋር በመሆን ወደ ትእምርታዊ አባቱ ስለሚያመዝን ከእናቱ ውጭ ሌላ ይመለከታል (1997፣ 60)። Lacan, ደግሞ ‹‹ተፈላጊ ነገር ሲሟላ ሌላ ባይተዋር ነገር ይዞ እንደሚመጣ ይገልጻሉ። በመሆኑም የድጋፌነህ ሹመት እንግዳ ነገር አስከትሎበታል። በሌላ መልኩ ድጋፌነህ የጠጣ በኢ-ንቁ ልቦናው እየታወሰ እረፍት የነሳውን የፀሐይን ፍቅር ለመርሳት ነው። ድጋፌነህ በስካር መንፈስ ኢ-ንቁ ፍላጎት እጦቱን ‹‹አደረች አራዳ እና ሴትን ያመነ›› በማለት ያዜመ ሲሆን፣‹‹ሴት›› የተባለችውም ፀሐይ ናት። በተጨማሪም ፀሐይ እንደማትታመን እና እንደማትጨበጥ ለመግለፅ ‹‹ከጉም›› ጋር አነጻጽሯታል። ድጋፌነህ አልኮል በጠጣ ጊዜ የተሰማውን ባይተዋር ስሜት እሱ ብቻ የሚያውቀው ሲሆን፣አልኮል በመጠጣቱ በፊቱ ላይ የሚስተዋለውን ደግሞ የሚያውቁለት ሌሎች ናቸው። ድጋፌነህ በአልኮል ከቋንቋ ለመዳ በሬት ሕጻኑ እንደሚያሳየው ባህርይ አሳየ። ሁሉም ነገር በእናቱ እርዳታ የሚፈጸም ሆነ። የሚናገርበት ቋንቋ ያጣ እና ጫማውን ማውለቅ ያልቻለም የእናቱን እርዳታ ስለፈለገ ነው።

ድጋፌነህ ማታ በስካር መንፈስ ስለነበር ምን እንዳደረገ አያውቅም። በመሆኑም በጠዋቱ እናቱ የሆነውን ሁሉ እንዲነግሩት ጠየቃቸው።

> ‹‹እማዬ ›› አላቸው ዝም አሉት
> ‹‹እማዬ ››፣‹‹አንቺ እኮ ለእኔ የተለየሽ ሰው ነሽ እባክሽ የሆነውን ልንገርሽ›› አላቸው።

‹‹ምን ሆነህ ነው አሉት ከአንገት በላይ በሆነ ቅያሜ አነጋገር ታሪኩን በሙሉ ሲነግራቸው በመሸሙ በጣም ተደሰቱና ሁለተኛ የትናንቱን ሁኔታ እንዳይደገም ተስማምተው ተለያዩ...››
(ጌታቸው ፣1982፣174)፡፡

ድጋፌነህ እናቱን ሲጠይቃቸው ዝም ያሉት እንግዳ ባህሪውን ስላልወደዱለት፣ስለተበሳጩ እና የብቻቸውን ስላስመሻቸው ነው፡፡ ወ\ሮ እታፈራሁ ድጋፌነህ መሸሙን ሲነግራቸው ደስተኛ የሆኑ እና ሁለተኛ እንዳይደገም ያሉት፣የልጃቸውን ከፍተኛ ደረጃ መድረስ እንደሚፈልጉ ጠቋሚ ነው፡፡ ድጋፌነህ አልኮል ላይጠጣ ለእናቱ ቃል ገብቶ ከቤቱ የወጣ ቢሆንም፣ በሚቀጥለው ቀን ለጓደኛው ሹመት የደስ ደስ በመጠራቱ ሲጠጣ አምሽቶ እየተወላገደ እና እያዜመ ከቤቱ ደረሰ፡፡ ከዚያም የፀሐይን ፎቶ-ግራፍ ከከሰከሰ በኂላ ተኛ፡፡

...እናቱ ብርድ ላይ ቁጭ ብለው ይጠብቁታል አላናገራትም፡፡ መኝታ ክፍሉ ገባ፤የፀሀይ ፎቶ-ግራፍ ታየው ፀሐይ የበለጠ ፈገግ ብላ አያት ‹‹አንቺ የተረገምሽ ዲያብሎስ! በማነው የምታላግጭው ? አለና ፎቶውን አንስቶ ከመሬት ላይ ወረወረው መስታወቱ ተሰባበረ፡፡ ስብርባሪው የፀሐይን ፈገግታ ሸፈነው ያን ጊዜ ቁጭቱ በረደለት፡፡ እፎይ አለና ተኛ በሰላም ያለምንም ጭንቀት አደረ፡፡
(ጌታቸው ፣1982፣175)

ሕጻኑ በመስታውት የሚያየው ምሥል የራስ ምሥል ነጸብራቅ እንጂ እውነት አይደለም፡፡ የሕጻኑ ምሥል ሲግኒፋየር ነው፡፡ ይህም ምሥሉን በተሳሳተ መልኩ እንዲረዳ ያደርገዋል›› (Wolfreys,et al.,2006, 65)፡፡ ድጋፌነህ እናቱን ሰላም ሳይላቸው የገባ የገባውን ቃል ስላላከበረ እና የፀሐይ ነጸብራቅ የሆነውን የፎቶ-ፍሬም ለመስበር ተቻኩሎ ነው፡፡ ድጋፌነህ በፀሐይ የፎቶ-ፈገግታ አልፎ ጥላቻውን ይገልጻል፡፡ ‹‹አንቺ የተረገምሽ!››፣‹‹አንቺ ዲያብሎስ!›› በማለት ማንነቷን ከሌላ እና **ሌ**ላ ጋር በማዛመድ ይገነባል፡፡ የተረገመ ምኗ ነው? ዲያብሎስ ምንድን ነው? የፀሐይ ዲያብሎስ ምኗ ነው? ያላገጠበት ምኗ ነው? የራሱን የተዘበራረቀ ምናባዊ ዓለም በመገንባት ከመዋተት ውጪ ተጨባጭ ማስረጃ የለውም፡፡ ስለዚህ የፀሐይ ‹‹ምኗም›› የ**ሌ**ላ አልሆነም፡፡ ፎቶ-ግራፏን የከሰከሰው የጥላቻ እና የጭንቀት መወጫ ለማድረግ ነው፡፡ የተሰበረ \የተሰነጠቀ መስታወት ምትሃታዊ የስበት ኃይሉ ስለሚቀንስ፣ውበቷ አልታየው በማለቱ ቁጭቱ በርዶለት ተኛ፡፡ አልኮል ድጋፌነህን ከራሱ፣ከፀሐይ እና ከእናቱ በመነጠል **ሌ**ላ እንዲሆን ምክንያት ሆኖታል፡፡ ትልቅና ትንሽ፣የተሰነጠቀ እና ያልተሰነጠቀ ፍሬም የእይታን ምትሃታዊ ኃይል ስለሚያጎላ እና ስለሚያደበዝዝ ምናባዊ እይታችን ከፍ እና ዝቅ እንዲል ያደርጋል፡፡ ከዚያም ድጋፌነህ በፍራቻ ተውጦ እናቱን ይቅርታ ጠየቀ፡፡

‹‹እማዬ...እማ መልስ የለም ተይ እንጂ እማ አትጨክኚብኝ ! ያላንቺ ማን አለኝ? አሁንም መልስ የለም እማዬ! ስሚ እባክሽ የእኔ ብቸኛ እናቴ እንዳስከፋሁሽ ይታወቃል በማለት ምክንያቱን በዝርዝር ተናገረ...››
(ጌታቸው ፣1982፣175)።

Lacan, እንደሚሉት ልጆች አብዝተው ይጠይቃሉ። ለምን? የት? ምንድን? ትልቅ ሲሆኑ ግን በራሳቸው መንገድ መልስ ስለሚሰጡ ጥያቄ ይቀንሳሉ። ድጋፌነህ እናቱን የሚጠይቅ ጀማሪ ጠጪ ስለሆነ ነው። ድጋፌነህ የራስ ማንነቱን ‹‹እኔ ብቸኛ ነኝ!››፣‹‹ያለ አንቺ ማን አለኝ?›› በሚል ይገልጻል። ድጋፌነህ ማታ ማታ **ሌላ** በመሆን ከራሱ እና ከእናቱ የሚነጠል ሲሆን፣ በጠዋት ደግሞ **ሌላ** በመሆን ከእናቱ የሚፈልገውን ለማግኘት ‹‹እማዬ... እማ›› ይላታል። ድጋፌነህ የራሱን ምናባዊ ዓለም በማዋቀር ከፍ ያለ ሥልጣን እና ደመወዝ ስለሚፈልግ፤ ሥራውን በትጋት ይከውናል። ከመጠጥ ቤት መልስ ደግሞ **ሌላ** ናፍቆት ውስጥ ይገባል።

ድጋፌነህ ፀሐይ ስለናፈቀችው እየፈራ ወደ ቢሮዋ ሄደ። ከዚያም ባለቀዩ ማርቼዲስን አየ። ራሄል ታለቅሳለች። ፀሐይ ወደ መኪናው ውስጥ ስትገባ እጇን አውለበለበች።

> ...ፍርሃት ፍርሃት ይለው ጀመር፤የአካባቢው ሰው በሙሉ ስለእሱ እና ፀሐይ የሚያውቁ መስሎ ተሰማው ሊስትሮዎቹ... ቦታቸውን እንደያዙ ናቸው›› ብዙ ሳይጠብቅ ያ የሚፈራው ቀይ ማርቼዲስ ከመሥሪያ ቤቱ አጠገብ ቆመ። እግሩም እጁም ይንቀጠቀጥ ጀመር መስፍን ከመኪናው ወጥቶ ወደ መሥሪያ ቤቱ ሲገባ ቀዝቃዛ ላብ በድጋፌነህ ጀርባ እንደ ውኃ ተንቆረቆረ። ብዙም ሳይቆዩ ፀሐይ ከራሄል ጋር በመሆን ከመሥሪያ ቤቱ ግቢ ወጡ ራሄል ታለቅሳለች መስፍን ሁለቱንም ያባብላቸዋል። ተሰናብታ ወደ መኪናው አመራች *እጇን አውለበለበችላት* ። [አጽንዖት የእኔ]
> (ጌታቸው ፣1982፣176)

ድጋፌነህን ያስፈራው ነገር ምንድን ነው? ምኑን ነው ሁሉም ሰው የሚያውቅበት የመሠለው? የድጋፌነህ የፍርሃት ምንጭ በኢ-ንቁ ልቦናው ልዩ ቦታ ያለው ባለማርቼዲሱ ይመጣል በሚል እና ሊስትሮዎች **ሌላ** ነገር ይነግሩኛል ብሎ ስለሰጋ ነው። ‹‹የአካባቢው ሰው በሙሉ ስለእሱ እና ፀሐይ የሚያውቁ መሥሎ ተሰማው›› የሚለው አገላለጽ ድጋፌነህ ለስሙ እና ለክብሩ እንደሚጨነቅ የሚያመላክት ነው። ራሄል ፋንታዚ በሆነ መልኩ ያለቀሰች ድጋፌነህ እንዲበሳጭ ሲሆን፣እጅ ማውለብለብ የሰላምታ እና የስንብት ሜታፈር ነው። ይሁን እንጅ

ድጋፌነህ ከውስጣዊ ስሜቱ አንጻር ‹‹የተሰናበተችው›› *መሥሎት* **ሌላ** ምናባዊ ስሜት ፈጥሮበታል፡፡

ድጋፌነህ ለሦስተኛ ጊዜ፣ለእናቱ የገባውን ቃል ወደ ጎን በመተው መጠጥ ቤት ገባ፡፡ ወደ ቤቱ ሲመለስ ግን እናቱን ጠላቸው፡፡ ‹‹…እናቱን ጠላቸው ‹‹ምን ነበር ብቸኛ ብሆን ለማንም የማላስብ የማልጨነቅ›› ማለት ጀመረ›› (ጌታቸው፣1982፣177)፡፡ ድጋፌነህ እናቱን እና ሴቶችን ከጠላትነት ጎራ አሰለፈ፡፡ በምትኩ **ሌ**ላ *ፋንታዚ* የራስ ዓለም ገነባ፡፡ እናቱን የጠላቸው አልኮል አትጠጣ ስላሉት ብቻ አይደለም፡፡ *ፋንታዚ* በሆነ መልኩ ከእናቱ ይልቅ የጠላ ራሱን ነው፡፡ ራሱን የጠላም ጠጪ ስለሆነ ነው፡፡ ፀሐይ ከድታኛለች ብሎ ስላሰበ ነው፡፡ በፊት ያደረገውን ነገር በማስታወስ ነው፡፡ ሀብት የሌለው በመሆኑ ነው፡፡ የአባቱን ቃል ስለሻረ ነው፡፡ እናቱን ግን እየወደደ ጠልቷቸው ነው፡፡ ይህም የሆነው እሱን ለማሳደግ የከፈሉትን ዋጋ በማሠብ ነው፡፡ ጥፋት ሲያጠፋ ከመቆጣት ይልቅ በዝምታ ሲለሚያልፋት መልካምነታቸው አስጨንቆት እና እናቱ በፊት ይሆኑለት የነበረውን ስላስታወሰ ነው፡፡

ድጋፌነህ እናቱን ገፍትሯቸው ገባ፡፡ የፀሐይ ፎቶ ያለበትን ፍሬም ሰባበረው፡፡ አዳልጦት ወደቀ፡፡

> ‹‹…በፈገግታ የተሞላ የፀሐይ ፎቶ በተሰበረው መስታወት ፊንታ ተተክቶ ነበር ትኩር ብሎ ‹‹ይህን ጊዜ…አንቺነትሽን ስጥተሽ ሁለመናሽን አስረክበሽ የእኔ የነበረውን ገላሽን…ለሌላው ሰው… አስረክበሽ…እሱ በአንቺ…አንቺ በእሱ ሆናችሁ ረካችሁ… እኔ ግን …አበድኩ…በመጠጥ ተቃጠልኩ አለና ፎቶዋን አንስቶ ከመሬት …ደባለቀው፡፡…*በእግሩ ይዘልበት ጀመር፡፡ ፎቶው እንደመሽከርከር አለ… አዳለጠውና ወደቀ*…እናቱ ቆመው የሚያደርገውን ድርጊት ተመለከቱት እና ትክዝ አሉ ፡፡ [አጽንዖት የእኔ]
> (ጌታቸው ፣1982፣179)

ድጋፌነህ ፀሐይ ለእንግዳ ባህሪው ምክንያት እንደሆነች ይገልጻል፡፡ ምናባዊ በሆነው ምሥል የፀሐይን *ፋንታዚ* ፈገግታ ይመለከታል፡፡ ፀሐይ የመስፍን ሆናለች ብሎ ባሠበ ጊዜ በምናባዊ እና ትእምርታዊ ፋለስ ናፍቆት ይማስናል፡፡ ይቀናል፡፡ *የፎቶ-ግራፉ መሽከርከር* ፀሐይ የ**ሌ**ላ መሆኗን ለመግለጽ ሲሆን፣መሽከርከር ደግሞ **ሌ**ላ እና **ሌ**ላ ገጽን የሚያሳይ ነው፡፡ ፎቶው *አዳልጦት መውደቁ* በመስፍን ውድቀቱ መፋጠኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ‹‹የእኔ እና የሌላ›› የሚለውን ቃል ደጋግሞ የሚጠቀምም የእሱ የነበረው ገላዋ የ**ሌ**ላ በመሆኑ ተቆጭቶ ነው፡፡ ፎቶዋን ከመሬት መደባለቁም ለመስበር እና እንደሞተች ቆጥሮ ለመርሳት ነው፡፡ እናትዬው ትክዝ ያሉት በልጃቸው የበፊት እና እንግዳ ማንነት ዙርያ ንጽረተ-ዓለም ውስጥ ገብተው ነው፡፡

ድጋፌነህ ሠናይት ከምትባለው የሥራ ባልደረባው ጋር ቀረቤታውን ስላጠናከረ፣ወደ ቤቱ መጣች፡፡ ከዚያም የሌላ ድርጊት ስታሳይ ‹‹ልወድሽ አልችልም›› ሲላት፣ተናዳ ‹‹በልክ ነኝ አይደለሁም›› ሐሳብ ውስጥ ገባች፡፡

> ‹‹እማማዬ ድረሽልኝ! ወይ! ወይኔ፡፡ *እኔ ነኝ፣ጋለሞታ ነኝ፣ የማልረባ ልክስክስ ወራዳ፣ሸርሙጣ ነኝ፣*ወይኔ እማማዬ የአንቺን ሞት ለእኔ ባደረገው፣ወይኔ ሞቴን ባደረገው›› አለችና ትንሠቀሠቅ ጀመር፡፡…እልህ ይዟት ሰውነቷን እንደምንም ተቆጣጥራ እንባዋን ከጠራረገች በኋላ፣ ለመሆኑ *ምን ይወጣልኛል፡፡* ወራዳ እኔ ነኝ ክብሬን እንደጠበቅሁ *መኖር* ስችል ፍቅርህ አስገድዶኝ ደጅ ጠኝ አደረገኝ፡፡ ኧረ ለመሆኑ የወንዶች ጸባይ አንድ *መሆኑ ያስደንቀኛል* ጥላ ናችሁ፡፡ [አጽንዖት የእኔ]
> (ጌታቸው ፣1982፣200)

ሠናይት *‹‹እኔ ነኝ ጥፋተኛ!››፣ ‹‹ጋለሞታ ነኝ!››፣ ‹‹እኔ የማልረባ ልክስክስ ወራዳ ነኝ !››፣‹‹ ሸርሙጣ ነኝ!* ››፣በሚል ራሷን የገለጸች የፋለስ እጦት ለባይተዋርነት ስለዳረጋ ነው፡፡ ድጋፌነህ ከጎኑ ያለችውን ሠናይትን ችላ ብሎ ‹‹ከናፍቆት እና ከቃል›› ላይ አተኩሯል፡፡ ይህም ‹‹እኔ ነኝ! ›› በሚል ራሷን እንደጥፋተኛ እንድትቆጥር አድርጓታል፡፡ ስሜቷ ተቀያይሯል፡፡ ይህንም ዐይኖቿ ያሳብቃሉ፡፡ ሠናይት ‹‹ልክ ነኝ አይደለሁም!›› በሚል የሐሳብ አዙሪት ውስጥ ገብታ በራስ ውንጀላ መዋለል አልነበረባትም፡፡ ምክንያቱም ድጋፌነህ ‹‹መላፋት›› ያልፈለገው **ሌ**ላ ከውስጡ ስላለች ነው፡፡ ከዚያም በእንባ ኃይል ብስጭቷን ካስተነፈሰች በኋላ ለዘብ ያለ ንግግር ተስተዋለባት፡፡ ሠናይት ራሷን ከሙቶች ጎራ ያሰለፈች እና ሞቼ ቢሆን ማለቷ ክብሯ እንደወረደ ስለቆጠረች፣አልፈለግም የሚል ስሜት ስለፈጠረባት እና እሷ ጠይቃው እምቢ ስላላት አፍራ ነው፡፡

ድጋፌነህ ሠናይትን በክብር እና የሙገሳ ቃላት ብስጭቷን አረገበ፡፡ ከዚያም በፀሐይ መከዳቱን ነገራት፡፡

> አልወድሽም ያልኩሽ *አንቺ ለእኔ አንሰሽ* አይደለም፡፡ እንዴውም *ትበዥብኛለሽ* ግን የራሴ የሆነ ምክንያት አለኝ ፡፡››
> ‹‹ሠንዬ…እንደ እህቴ ስላየሁሽ ጭንቀቴን አዋየሁሽ፤
> ፀሐይ ብትከዳኝም *እኔ ግን በምንም አይነት ከዳተኛ* ላልሆን ቃል ገብቻለሁ፤አንቺ ምንም እንከን የሚወጣልሽ ልጅ አይደለሽም፣ *ታዲያ ቃሌን* አጥፌ *ሌላ ሴት* ልወድ እንደማልችል ሕሊናዬ እያወቀ እንዴት ብዬ *ንፁህ ገላሽን ላርክሰው ? [አጽንዖት የእኔ]*
> (ጌታቸው፣1982፣201-202)

ድጋፌነህ በፀሐይ ስለመከዳቱ ለሠናይት የነገራት በምክንያት ነው። ‹‹ከዳተኛ ሴት ናት!››፣ ‹‹ ጠጪ እንድሆን ምክንያት ሆነች!››፣ ‹‹እናቴን እንድጎዳ አደረገችኝ!››፣ ‹‹አዋረደችኝ!››፣ ‹‹አሳበደችኝ!››፣ ‹‹ብቸኛ አደረገችኝ!››፣ ‹‹ገንዘብ ወዳድ ናት!›› በሚል የፀሐይን ራስ (እኔ) ይገነባል። ራሱን ደግሞ ‹‹እኔ ከዳተኛ አይደለሁም!›› በሚል ይገልጻል። ሠናይትን እንደ እህቱ እንደሚያያት ገልጾላታል። (እዚህ ላይ፣‹‹በፍላጎት ትንተና›› ፀሐይን እንደ እህቴ ነው የማይሽ ሲላት እንደነበር ማስታወስ ይገባል)። ድጋፌነህ ሠናይትን የብቸኝነት መታደጊያ ‹‹ምትክ ፍላጎቱ›› እንድትሆን ፈልጓል። በሌላ ፀሐይን መርሳት እንደማይችል እና ናፍቆቷ እንዳስቸገረው ይገልጻል። ‹‹**ሌ**ላ ሴት ልወድ አልችልም፣*ንጹህ ገላሽን ላርክሰው››* የሚለው አገላለጽ ለዚህ ጠቋሚ ነው። **ሌ**ላ ሴት የተባለችው ማን ናት? ሕሊናዬ እያወቀ እንዴት *ንጹህ ገላሽን ላርክሰው* ያለው ሠናይትን ሳይሆን በፀሐይ ላይ **ሌ**ላ ሴት መልመድ ስላልፈለገ ነው።

ድጋፌነህ የአባቱን ክራሩ አንስቶ የናፍቆት ስንኝና ዜማ መደርደር ጀመረ። እናቱ ግን በልጃቸው ሁኔታ አዝነዋል። በድንገት በሩ ሲንኳኳ ከገባበት ሐሳብ ይወጣል። የመጣው አስፋው ነበር። ከዚያም እንዲህ ብሎ ዘምር አለው። ‹‹አንቺ ብትሄጅ *ሌላ ሴት* ይተካል፤አንቺ የሸጥሽው ፍቅር ከሌላም ይገኛል›› ([አጽንዖት የእኔ]። ጌታቸው፣1982፣223)። አስፋው ድጋፌነህ ፀሐይን እንዲረሳት ይፈልጋል። ድጋፌነህ ‹‹*ከሐንጎበር*›› እየተላቀቀ በመሆኑ አስፋው የገጠመው ግጥም አንጀቱን አላወሰው ክራሩን አስቀምጦ በደፈረሰ ዐይኑ ጓደኛውን ትኩር ብሎ በተመለከተው ጊዜ አስፋው በእይታው ተደናግጦ ‹‹ምን ታየኛለህ *ሰው አተኩሮ ቢያዩት ዝንጀሮ* ነው›› አለው ([አጽንዖት የእኔ]። ጌታቸው፣1982፣223)። አስፋው አተኩሮ ሲያየው የፈራ ለምንድን ነው? አተኩሮ ሲያየው ማንነቱ ይታወቅ ይሆን? *ሰው አተኩሮ ቢያዩት ዝንጀሮ* ነው ማለቱ ሰውን አተኩረው ሲያዩት **ሌ**ላ እንደሚሆን ለመግለጽ እና ቁጣው አገርሽቶ እንዳይደበድበኝ በሚል ነው።

ድጋፌነህ እናቱ ራሷን የማጥፋት ሙከራ በማድረጓ ተጸጽቶ መጠጥ ተወ። ይህንም ለሠናይት ነገራት። በማመን አለማመን ከተመናታች በኋላ ቃል አስገባችው። ‹‹…ቃል ግባልኝ››፣ ‹‹ከእንግዲህ ወዲያ *የድሮው ድጋፌነህ ነኝ* እጅሽ ይጣለኝ ቃል ቃል ነው›› አላት›› ([አጽንዖት የእኔ]። ጌታቸው፣1982፣248)። Parker, እንደሚሉት፣‹‹ገጸ-ባህርያት ይዘውት ከነበረው ሐሳብ (ድርጊት) አላዋጣቸው ሲል **ሌ**ላነት ይስተዋልባቸዋል። ይህም ‹‹የማንነት ለውጥ›› ይባላል (2014፣198)። ድጋፌነህ መጠጥ በሴት ጀምሮ፤በሴት (በእናቱ) በመተው የማንነት ለውጥ

ታይቶበታል፡፡ ከዚህ በኋላ *‹‹የድሮው ድጋፌነህ ነኝ!››* ማለት ምን ማለት ነው? የድሮው ማንነት እንዴት ነው የሚመጣው? ማምጣትስ ይቻላል ወይ?

ፀሐይ ራሷን ለማጥፋት ባደረገችው ሙከራ በመኪና ተገጭታ ወደ ሆስፒታል ገባች፡፡ ድጋፌነህ ሊጠይቃት ሄደ፡፡ ለዚህ ሁሉ ምክንያት እነ-ጥጉ እንደሆኑ ነገረችው፡፡ ለበቀል ተነሳስቶ ሄደ፡፡ ሊበቀለው የፈለገውን ጥጉን የአእምሮ ሕመምተኛ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ድጋፌነህ አዘነ፡፡ ከዚያም የድሮ ማንነቱን ከአሁኑ ጋር በማነጻጸር እንደ ሙት ቆጠረው፡፡ *‹‹ያ የጥንቱ አለቃው! ያ ግርማ ሞገሱ የሚያስፈራው! ያ* በተንጣለለ ቪላ ቤት ይኖር የነበረው ዛሬ ግን እንዳልሆነ ሆኗል፡፡ …ከዚህ በላይ ቅጣት ሊኖር አይችልም፡፡ ሙት ነው…ሬሳ ነው…ሞት ይሻላል…ይህ ግን በቁሙ የሞተ ሰው ነው አለና ጠጋ ብሎ ቆመ›› ([አጽንዖት የእኔ]፡፡ ጌታቸው፣1982፣272)፡፡ ወዳጄነህ መሐረነ እንደሚሉት *‹‹ናርሲስት በግሪክ ሚቶሎጂ በውኃ* ውስጥ የሚመለከተውን ምሥል ለማምለክ ጥቂት የቀረው ሆኖ ተሥሏል (2011፣17)፡፡ ድጋፌነህ የጥጉን የድሮ ማንነት ያስታወሰ ማንነት ተለዋዋጭ እንደሆነ ለመግለጽ ነው፡፡ ማንነት ምንም እንደሆነ እና በሌለ ነገር የሚገነባ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ የምናየው እና አለን የምንለው ነገር ምንም ስለሆነ መመጻደቅ አይገባም ለማለት ነው፡፡ ‹‹በቁሙ የሞተ›› ማለቱ ላለመቅጣት ስለፈለገ ነው፡፡ የሰው ልጅ ሞቶ እንዳለ፤እያለ እንደሞተ የሚታሰብበት እሳቤም የተንጸባረቀበት ነው፡፡ ይህም የቃላትን ኃይል ይገልጻል፡፡

ጥጉ ድጋፌነህን ከእግሩ ሥር ወድቆ ምሕረቱን ጠየቀ፡፡ ጥፋቱ የእሱ ሳይሆን የመስፍን እንደሆነ ነገረው፡፡ ከዚያም ድጋፌነህ ሙት ነህ በማለት መስፍንን ለመፈለግ ወጣ፡፡ ‹‹ሙት ነኝ…ልጆቼ ይኑሩ ይሙቱ አላውቅም እኔ ሙት ነኝ… ለዚህ ሁሉ ጥፋት የዳረገኝ መስፍን የሚባል አረመኔ ሰው ነው፡፡ ብቀላን ከፈለግህ ተበቀለው እኔ ግን ዋጋ የለኝም…እጅህን በእኔ ላይ አታንሳ…ሲለው አንተማ ሙት ነህ ብሎ…ሄደ…›› (ጌታቸው፣1982፣273)፡፡ ‹‹ገጸ-ባህርያት ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች ምናባዊ መፍትሔ የሚወስዱ ሲሆን መፍትሔ የተባለው ነገር ውድቀትን ሊያስከትል ቢችልም ከሁለቱም ዕውቀትን ያገኙበታል›› (Lacan,1977a, 218)፡፡ ጥጉ ገንዘብ ማግኛ ዘዴ ብሎ የወሰደው መፍትሔ ወደ ችግር ዘፍቆታል፡፡ ቤቱን፣ሚስቱን፣መኪናውን፣ሥራውን፣ ልጆቹን፣ እንዲሁም ጤናውን ለማጣቱ ምክንያት የሆነ ቢሆንም ጥጉ ከውድቀቱ ተምሯል፡፡ ጥጉ ድጋፌነህን ይቅርታ የጠየቀው ከጥፋቱ ስለተማረ ሲሆን፣በሌላ መልኩ ደግሞ መስፍንን እንዲበቀልለት ስለፈለገ እና እንዳይገድለው ስለፈራ ነው፡፡ በትረካው እንደተመላከተው ጥጉ

በጥፋቱ በእጅጉ ተጸጽቷል፡፡ በየመጠጥ ቤቱ እየዞረ *‹‹ሥራ ለሠሪው››* (ጌታቸው፣1982፣272) የሚል እና መጠሪያው የሆነም ለዚህ ነው፡፡

### 3. 3. ፋለስ (*Phallus)*

በዚህ ጽንሰ-ሐሳብ *ሥር* ፋለስ (ጁዊሶንስ፣ፋሎ-ሴንተሪዝም እና ሳይኮ-ፓቶሎጂ) በሚሉት ነጥቦች ላይ አተኩሮ ትንተና ተሰጥቷል፡፡ የቋንቋ አጠቃቀም፣*ቃላት* ገንቢ እና አፍራሽ ናቸው፡፡ *ቃላት* ጁዊሶንስ *ያስገኛሉ፡፡* ፋለስ *ያስገኛሉ፤ያሳጣሉ፡፡ ያሳዝናሉ፡፡ ያስደስታሉ፡፡* ስሜትን *ያሚሸሻሉ፡፡* በመሆኑም የ*ቃላት* ልእለ ኃይል በፋለስ እንዴት እንደሚገለጽ ተብራርቷል፡፡ ድጋፌነህ በስካር መንፈስ ከፀሐይ *ጋር* የገባውን *ቃል* ወደ ጎን በመተው ከተለያዩ ሴቶች *ጋር* አድሯል፡፡ በዚህም በሴቶች ዘንድ ስድብ ደርሶበታል፡፡ Lacan, ‹‹ጁዊሶንስ በጾታዊ ግንኙነት የሚገኝ ነው ቢሉም ቅሉ፤አልፎ አልፎ ግን የማይገኝበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ *ፋንታዚ* (ምናባዊ እና ትእምርታዊ) የሆነ ጁዊሶንስ ይኖራል፡፡ ጾታዊ ግንኙነት ስለተደረገ ብቻ ጁዊሶንስ ይገኛልን? የጁዊሶንስ ክብደቱስ ምን ያህል ነው? በጾታዊ ግንኙነት ጁዊሶንስ መገኘቱ እንዴት ይታወቃል? ከወንዱ ወይስ ከሴቷ? በጾታዊ ግንኙነት ሁልጊዜ ጁዊሶንስ ማግኘት ይቻላል? የሚሉት ጥያቄዎች ይተነተናሉ፡፡ እንዲሁም ስለፋሎ-ሴንተሪዝም እና ፓቶሎጂዎች ከፋለስ *ጋር* በማዛመድ እንደ አስፈላጊነቱ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

ወ\ሮ እታፈራሁ ከባላቸው *ጋር* ያሳለፉትን ጊዜ መሬቱን በስንጥር ጫር ጫር በማድረግ ያስታውሳሉ፡፡ ‹‹...ከቤታቸው ደጃፍ ላይ ተቀምጠው *መሬቱን በስንጥር ጫር ጫር* በማድረግ ይተክዛሉ፡፡...ውዱ ባለቤታቸው ለእሳቸው ባል፣አባት፣ወንድም ነበሩ፡፡ ትንሽ ሕመም ሲሰማቸው፡፡ ‹‹እምዬ አመመሽ እንዴ? እስኪ *ድንገተኛውን እንኪበት*፤ይተውሻል በማለት ይጨነቁላቸዋል›› ([አጽንዖት የእኔ] ፡፡ ጌታቸው፣1982፣5-6)፡፡

*ድንገተኛውን እንኪበት* የተባለው ምንድን ነው? አትገልጸውም፡፡ *‹‹ድንገተኛ››* የተባለው ፋለስ መሆኑ ነው፡፡ ወ\ሮ እታፈራሁ በፋለስ ናፍቆት ይዋትታሉ፡፡ የLacanን የፋለስ ጽንሰ-ሐሳብ እንደሚያስረዳው ‹‹ፋለስ ምትሃታዊ የሆነ ቀጭን በትር፣ቀጥ ያለ ነገር፣አካል\ቁስ ነው›› (Ellmann,1994, 20) ሲሉ Green, K and Lebihan, J., (1996) ደግሞ ‹‹የሴቶች የጡት ራስ፣እግር፣እጣት እና...የፋለስ ወኪል ናቸው ይላሉ›› (ገጽ፣164-165)፡፡ በመሆኑም የላይኛውን እና ከዚህ በታች የተገለጹትን ታሪኮች ከሁለቱ ጽንሰ-ሐሳቦች *ጋር* አዛምደን እንመልከት፡፡ የወ\ሮ እታፈራሁ የፋለስ ናፍቆት መግለጫ ከጽንሰ-ሐሳቡ *ጋር* ግንኙነት አለው፡፡ የፋለስ ናፍቆት

መወጫቸው *በስንጥር መሬቱን ጫር ጫር ማድረግ* ነው፡፡ *ስንጥር* የፋለስ ተምሳሌት ሲሆን *‹‹መሬት››* በሴት ይወከላል፡፡ Bertens, ‹‹በማሕበረሰብ *ሥምምነት መሠረት* ፋለስ የአባዊ ሲግኒፋየር ነው›› (2001፣161)፡፡ ወ\ሮ *እታፈራሁ* ‹‹ባለቤታቸው ለእሳቸው ባል፣አባት፣ ወንድም›› እንደነበሩ የሚገልጹ ለዚህ ነው፡፡

ፀሐይ ከእነ-ድጋፌነህ ቤት መጣች፡፡ ወ\ሮ *እታፈራሁ ሥጋ* ልግዛ ብለው ሄዱ፡፡ ከዚያም ድጋፌነህ ስለቤተሰቦቹ ፎቶ-ግራፍ ገለጻ እያደረገላት እያለ አንዲት ሕጻን እየተንደረደረች ገባች፡፡

> እማማ እታፈራሁ…እያለች እየሮጠች ወደ ቤት እንደገባች ፀሐይን
> አይታ ደንግጣ *እንደተገተረች* ቀረች፡፡ ሁኔታውን ያየው ድጋፌነህ
> ‹‹ሚጢ… ምንድን ነው አላት? ሕጻኗ እየተሽኮረመመች፡-
> ‹‹ተልኬ ነው›› አለች፡፡
> ‹‹ንፍጥሽ ምንድን ነው?›› ሁለተኛ እንዳላይ አላልኩሽም? ሲል
> ዐይኑን አፈጠጠባት ደንግጣ *የቀሚሷን ጫፍ ወደ አፍንጫዋ*
> አስጠጋችው፡፡
> ‹‹እንዴ በልብስሽ በይ ዞር ብለሽ ተናፍጠሽ ነይ›› አላት
> አፍንጫዋን አጽድታ ከተመለሰች በኋላ
> ‹‹እማዬ ምነው! ምነው! *ጀበናው* ከወጣ ቆየ፣መጥተው ለምን ቡና
> አይጠጡም ፡፡›› [አጽንዖት የእኔ]
> *(ጌታቸው ፣1982፣64-65)*

ድጋፌነህ በሕጻኗ ላይ ዐይኑን ያጎረጠባት በጁዊሶንሱ መካከል ጣልቃ ስለገባች ነው፡፡ ‹‹ዞር ብለሽ ተናፍጠሽ ነይ!›› ማለቱ ያናቀፈችውን ጁዊሶንስ ለመቀጠል ነው፡፡ ለምንድን ነው ሕጻኗ የደነገጠች? ለምንስ ተሽኮረመመች? ፀሐይን *ሥታያት* ለምን *እንደተገተረች* ቀረች? *መገተርስ* ምንድን ነው? የሕጻኗ መቆም ወይስ **ሌላ** *የተገተረ* ነገር ይሆን? የተገተረው ትእምርታዊ ፋለስ ነው፡፡ ሕጻኗ ደንግጣ *‹‹የቀሚሷን ጫፍ ወደ አፍንጫዋ* ማስጠጋቷ›› የምናባዊ እና ትእምርታዊ ፋለስ ጠቋሚ ነው፡፡ *የአፍንጫ* ትእምርት ምንድን ነው? ካጤንነው **ሌላ** ነው፡፡ ሕጻኗ ስላየችው ነገር ለእናቷ ተናግራለች፡፡ ተመልሳ በመጣች ጊዜ *‹‹ጀበናው››* ከወጣ ቆይቷል ያለች ለዚህ ነው፡፡ የጀበና ማንዶልዶያው ትእምርታዊ ፋለስ ነው፡፡

ሠናይት የምትባለው የድጋፌነህ የሥራ ባልደረባው ስትሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ከቢሮ አምሽተው ሠሩ፡፡ ከዚያም በመሥሪያ ቤት መኪና እስከ ቤቷ ሸኛት፡፡ ተሳሳሙ፡፡ ‹‹ነገም አምሽተን እንሠራለን›› ስትል ጠየቀችው፡፡ አዎን አላት፡፡

… *ሹል ጫማዋ* እያደናቀፋት ይሁን ወይንም ሳያደናቅፋት… ስትንገዳገድ ደገፍ *ያደርጋትና* ይይዛታል፣እጇን ይዞ ሲጓዙ በድንገት ‹‹እማምዬ›› አለችና ትክሻው ላይ ተለጠፈችበት ታኮ *ጫማ ያደረገችበትን* ቀን *ረግማ ወገቡን ያዘችው፡፡…*
‹‹በል ቤቴ ይሄ…ነው›› አለችው ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ… ለመሆኑ ነገ እናመሻለን ስትል ጠየቀችው፡፡…
‹‹አዎን እናመሻለን አላት፡፡…የበለጠ ውብ መሆኗን ከበሩ አጠገብ የሚበራው *አምፑል* አሣየው ለእሷም እንዲሁ…

‹‹በይ ደህና እደሪ›› አላት፡፡

‹‹ደህና እደር›› አለችውና ጨብጧት ሲለይ *የጨበጠችበትን እጇን ሳም* አደረገችው (ጌታቸው፣1982፣67)፡፡

*ሠናይት ሹል ጫማ የተጫማች ለምንድን ነው? የምን ትእምርት አለው? ለምንስ ተንገዳገደች?* *ሠናይት* ሹል (ሄል *ያለው*) *ጫማ የተጫማች* **ለሌላ** ፍላጎቷ *ማሚያ* ነው፡፡ ይህንም አናቀፈኝ በሚል *ፋንታዚ* አሟልታለች፡፡ ፍላጎቷ እንዳይታወቅባት *ፋንታዚ* በሆነ *መርገም* ትሸፍናለች፡፡ ሹል *ጫማ የተጫማችበትን ቀን* በመርገም፡፡ *የድጋፌነህ መሸኘት* **የሌላ** ፍላጎትን *የሚገልጽ* ሲሆን፣*አምፑሉ* የፋለስ ተግባራቸውን እንዲመለከቱ *ያደረገ* ነው፡፡ በሌላ *መብራት* ከፋለስ *የሚያደናቅፍ* ነው፡፡ የአምፑል ጭንቅላት ብዙ ትእምርት *ያለው* ሲሆን፣*ጫፉ* ላይ የሚቀመጠውም ትእምርታዊ ፋለስ ነው፡፡

*መስፍን ዮዲትን* በመኪና ሲወስዳት፡- ‹‹*የመኪናውን ማርሽ ደጋግሞ* እፍን እፍን *ያደርጋል*›› (ጌታቸው ፣1982፣41)፡፡ *የመኪና ማርሽ ጫፉ* ላይ *ያለን* ምልክት አጢነን ከተመለከትነው **ሌላ** (ትእምርታዊ) ፋለስ ነው፡፡ *በመሆኑም መኪናውን የሚያሽከረክረው መስፍን ሳይሆን* የፋለስ ፍላጎቱ ነው፡፡ ቶሎ ቶሎ እፍን እፍን *ማድረጉም* ለጁዊሶንስ *መቻኮሉን አመላካች* ነው፡፡

*ድጋፌነህ* በሦስት ሴቶች (በፀሐይ፣በሠናይት እና በምሽት በመጣችው ሴት) ስድብ ደርሶበታል፡፡ የሦስቱ ሴቶች የስድብ *ቃላቶች* ‹‹ወንድነትን *የሚፈታተኑ* እና *ራሱን* እንዲጠላ›› *የሚያደርጉ* ናቸው፡፡ *በመጀመሪያ*፡- በፀሐይ የደረሰበትን የስድብ *ቃል* እንመልከት፡፡ ፀሐይ *ድጋፌነህን ታፈቅረዋለች*፡፡ እሱ ግን ፍቅሩን ሊገልጽላት አልቻለም፡፡ ከዚ*ያም ድንጋይ ነህ!* በማለት ሰደበችው፡፡ *ድጋፌነህ* ፀሐይ የሰደበችው ስድብ በአእምሮው ተቀርጾ እንቅልፍ ቢነሳውም በሂደት *ራሱን* እንዲለውጥ አድርጎታል፡፡

‹‹ለምን ድንጋይ ነህ አለችኝ?›› አለ ሌሊት ተኝቶ…የድጋፌነህ ጸባይ ተለወጠ፡፡ ፀሐይ አማረች፡፡ ደመቀች፡፡…እንደ ጥንቱ በሙሉ

> ዐይኑ ማየት ተቸገረ። እያቀፈ ማስጠናቱን እና ማስረዳቱን አቆመ። ሰውነቱ ከሰውነቷ ሲነካካ የማያውቀው ስሜት አደረበት። የሆነ ሙቀት በሰውነቱ ውስጥ ይሰማው ጀመር። ትኩር ብለው ሲመለከቷት ይበሳጫል። ጡቶቿን ሲመለከት ይሽበራል።
> (ጌታቸው ፣1982፣31)

‹‹ድንጋይ ነህ!›› ከፀሐይ የተደመጠ የስድብ ሲግኒፋየር ሲሆን የድጋፌነህን ‹‹የወንድነት ስሜት የተፈታተነ›› ቃል ነው። ፀሐይ ይህን ማለቷ ትእምርታዊ የፋለስ ፍላጎቷን ለማሟላት ነው። ድጋፌነህ የስድብ ቃሉ በመጀመሪያ ምንም አልመሰለውም ነበር። እየቆየ ግን እንቅልፍ ነስቶታል። በዚህም ምክንያት የወንድነት ስሜቱ ሞቋል። ‹‹እንደ እህቱ ሳይሆን እንደ ሌላ፤ ሰውነቱን ከሰውነቷ ሲያነካካ ሌላ ስሜት እና ፍላጎት የፈጠረበት ለዚህ ነው። በመሆኑም የፀሐይ የስድብ ቃል ድጋፌነህ ‹‹ወንድ›› እንዲሆን ምክንያት ሆኖታል።

ፀሐይ ድጋፌነህን ‹‹አንበሳ ግቢ›› ለማዝናናት ወሰደችው። ድጋፌነህ የፍቅር ቃል አላወጣ በማለቱ ፀሐይ ተማረረች። ‹‹በምን ቀን ለከፈኝ ድንጋይ ልብ ነው ያለው። አንድ ቃል ለመተንፈስ ምን ያቅታል...አንድ ቃል...ወደድኩሽ...ማለት›› (ጌታቸው፣1982፣36)። ፀሐይ ድጋፌነህን አንበሳ ግቢ ለመውሰዷ ምክንያት የሆናት የፍቅር ቃል አላወጣ ማለቱ ነው። ከዚህም የቃልን ኃይል እንገነዘባለን። ይህም Lacan, ‹‹የፋለስ ማዕከሉ የቋንቋ ሥርዓት እና ቃል በመሆኑ የፋለስ ጨዋታ ከሲግኒፋየር እና ሲግኒፋይድ ጋር የሚቀናኟ ነው›› (Rawson and Nisbet, 2008, 186)። የቃሉ መኖር እና መነገር በራሱ የፋለስ መኖርን ጠቋሚ ነው። ድጋፌነህ ፍቅሩን በድርጊት እንጂ በቃል መግለጽ አልቻለም። ከዚያም ፀሐይ ‹‹እወድሃለሁ›› በማለት ‹‹በለሆሳስ›› ነገረችው።

> ‹‹...ከንፈሯን ከከንፈሩ አጋጠመች...እሱ ወደ እሷ...እሷ ወደ እሱ...እየተንፏቀቁ ተጠጋጉ...አዲስ ሕይወት...የፍቅር አማልእክት ...ከሰማየ ሰማያት ወርደው እምቢልታ ነፉላቸው...የዘላለም ፍቅር ያሳድርባችሁ በማለት ከበሮ እየደለቁ አሸበሸቡላቸው...ጆሮው ሥር ተለጥፋ በሹክሹክታ ‹‹እወድሃለሁ›› አለቺው። ‹‹ እኔም›› አላት››
> [አጽንዖት የእኔ]
> (ጌታቸው ፣1982፣37)።

ፀሐይ ድጋፌነህን መዝናኛ ቦታ መውሰዷ ምናባዊ እና ትእምርታዊ ጁዊሶንስ እንድታገኝ ያደረጋት ቢሆንም፣ከድርጊቱ በታካይነት ‹‹የቃል›› ናፍቆት አለባት። ‹‹በለሆሳስ እወድሃለሁ ያለቺው ለዚህ ነው። ‹‹ቀድማ መሳሟም›› የፋለስ ፍላጎቷ ከፍ ያለ መሆኑን ጠቋሚ ነው። ድጋፌነህ እጦት እና ፍላጎቱን በምናባዊ ዓለም ያንጸባርቃል። ‹‹ሰማየ ሰማያት እና የፍቅር

*አማልእክት*›› በማለት፡፡ *መንፏቀቃቸው ፍቅርን አሐዱ ማለታቸው ሲሆን፣ከሕጻን ዳዴ ማለት መጀመር ጋር የሚዛመድ ነው፡፡*

*ድጋፌነህ ከፀሐይ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ አብረው ለማደር ወደ ሶደሬ ጉዞ ሲያደርጉ የስሜት መምታታት እና ጭንቀት ተፈጥሮበታል፡፡ ‹‹ጭንቅ ጭንቅ ይለው ጀመር ልጃገረድ እንደሆነች እርግጠኛ ነው ስሜቱን እንዴት እንደሚቆጣጠረው ግራ ይገባዋል…››* ([አጽንዖት የእኔ]፡፡ ጌታቸው፣1982፣77)፡፡ *ድጋፌነህን ጭንቅ ጭንቅ ያለው ነገር ፀሐይ ልጃገረድ ስለሆነች እሽነፍ ይሆን የሚል ስጋት አሳድሮበት ነው፡፡ ፀሐይ ሶደሬ በሄዱበት ጊዜ ከማኅበረ*-ባህላዊ ሕግ ጋር ተዛምዶ ያለው ተግባር ፈጸመች፡፡ ‹‹…ከደመወዝ የምትከፍለኝ ነው ወንድ ልጅ ሲከፍል ደስ ይላል፡፡ አለች እና ሁለት መቶ ብር ኪሱ ውስጥ ከተተችለት›› (ጌታቸው፣ 1982፣77)፡፡

*ድጋፌነህ* እና ፀሐይ ምግብ ከተመገቡ በኋላ አልኮል ጠጥተው ወደ አልጋ ክፍላቸው ገቡ፡፡ ከዚያ በኋላ ያለውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

> እየፈሩ…በደመ-ነብስ ልብስ ማውለቅ ጀመሩ፣ከጥቂት ደቂቃ በኋላ የሁለቱም ምኞት ፍላጎት ነውና…ሳያውቁት…*እሷ ከሥር እሱ ከላይ ሆኑ* ቀስ በል ድጋፌ አለችው ድጋፌ መልስ አልሰጣትም *ስሜቱ ገንፍሎ ወጣ…ሊጎዳት* አልፈለገም ግን ምን ያደርጋል …በስሜት ወደ ታች ይገፋት ጀመር ትንሽ ስትቆይ *ጮኸችና…* ሕሊናዋን ሳተች፡፡…አንሶላው በእምነት ማረጋገጫ ደም ተለውሶ *ድጋፌነህ* የተመኘውን አገኘ፡፡ [አጽንዖት የእኔ]
> *(ጌታቸው ፣1982፣ 78)*

Lacan, ‹‹*ሴቶችም ሆኑ ወንዶች የመኮላሸት ጭንቀት፣የፋለስ እጦት ፍርሃት እና ቅናት* አለባቸው›› (Green K, and Lebihan,J.,1996,165)፡፡ *የሁለቱ የፍርሃት ምንጭ እና ጭንቀት ‹‹ደናግልነታቸው››* ነው፡፡ *የፍርሃታቸው ምንጭ እውን ሆነ*፡፡ *‹‹ልጅነቷን፣ልጅነቱን››* ተበረካከቱ፡፡ በዚህም ኃይላቸውን አጡ፡፡ ፀሐይ ‹‹ከልጃገረድነት›› ወደ **ሌላ** የትእምርት (*የሥም*) ሽግግር አደረገች፡፡ እርቃናቸውን *መሆናቸው* **ሌላ** ነው፡፡ *እሷ ከሥር እሱ ከላይ* ሆነ የሚለው *ፋሎ-ሴንተሪዝምን* ጠቋሚ ነው፡፡ የልጃገረድ የፋለስ ጅማሬ ደም ጁዊሶንስ ብቻ አይደለም፡፡ ክብር ፣*መስዋዕትነት* እና **ሌላ** ነው፡፡ የፀሐይ ጩኸቷ የጁዊሶንስ እና የስቃይ ተዛምዶን ገላጭ ነው፡፡

*ሁለተኛዋ ድጋፌነህን የሰደበችው ሠናይት ናት፡፡ በቀለኛ ሴት ናት፡፡ ድጋፌነህን* የቀረበችው ለበቀል ነበር፡፡ በኋላ ግን ተቀየረ፡፡ *ድጋፌነህ ለሁለተኛ ጊዜ ከሠናይት ጋር* ከቢሮ በማምሸት ሠሩ፡፡ ከሸኛት በኋላ ለመሄድ ተጣደፈ፡፡ ሠናይት ግን እንዲስማት ፈልጋ ስለነበር፡- ‹‹ምን

አይነት *ደመ-ቀዝቃዛ* የሆነ ሰው ገጠመኝ አለች›› ([አጽንዖት የእኔ]።ጌታቸው፣1982፣197-198)። ለመሳደቧ ምክንያት ስላልሳማት ሲሆን፣ድጋፌነህ ለመሄድ የተጣደፈው ስለመሸበት ነው።

ሠናይት ድጋፌነህ ፀሐይን እንዲረሳት አበክራ ትመክረዋለች። እሱ ግን ሊረሳት አልቻለም። በዚህም ጊዜ ሠናይት ‹‹ወንድ ሁን፣ኮስታራ ሁን›› ትለዋለች። ‹‹እንጃ…ግን እችላለሁ ይሆን ? ›› በደከመ ድምጽ ኧረ ዲያ *ወንድ ልጅ ለሴት* እንዲህ ሲሆንስ አይቼም አላውቅ ልንገርህ ድጋፌ እኛ እኮ *ወንድ ኮስተር* ሲልብን ነው የምንወደው ገባህ›› አለችው እና አስካካች…ሣቋን ጨርሳ የተቀዳላትን ለመጎንጨት ብርጭቆውን እንዳነሳች በሩ ተንኳኳ እናቱ ነበሩ›› (ጌታቸው ፣1982፣219)። Foucault, ‹‹የወንድ እና የሴት የኃይል ግንኙነት በቋንቋ እና በማሕበረሰባዊ ሕግ ይወሰናል›› (1972፣155) ይላሉ። *ሠናይት ድጋፌነህን* ‹‹ወንድ *ሁን*›› በማለት የምትመክረው መወሰን ወንድነትን የሚጠይቅ መሆኑን ጠቋሚ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ኃይል (*ፋሎ ሴንተሪዝም*) በወንዶች ዘንድ ብቻ እንዳለ እየገለጸች ነው። ሴት ኮስታራ እንዳትሆን ያደረጋት ምንድን ነው? ወንድ ብቻ ኮስታራ ይሁን ያለ ማን ነው? ሴት ልጅ እንድታስብ እንድትቆዝም እንድታለቅስ ያለ ማን ነው? ካልን ከማሕበረሰባዊ ሕጉ ጋር ጥምረት ያለው ነው። ብስጭቷን *በፋንታዚ* ዓለም ፈገግታ ትሸፍናለች። ለዚህ ምክንያቷ ፍላጎቷ ባለመሟላቱ እና ‹‹ወንድ›› ሊሆን ባለመቻሉ ነው።

ሠናይት ድጋፌነህን ከመምከር ወደኋላ አላለችም። እናቱን እንዲወዳት፣እሱ የሚያደርገውን ሁሉ የምትወድለት ሌላ ሴት እንዳለች መከረችው።

> …እናትህን ከመጥላት እየወደድክ መውደድ ይኖርብሃል *ገባህ ክራር ስትመታ* ደስ ይላታል…*ሌላዋም* ደስ ይላታል ይሆናል ድርሰት ስትጽፍ ደስ ይላታል… *ሌላዋም* ደስ ይላታል…ስለዚህ እርሳት ለእናትህ ስትል… ይቅርታ…ስለምወድህ …ወንድሜ… ዐይንህ ስለተጋረደ የዚህን ዓለም ውበነት ልታውቅ አልቻልክም ግን እንደምንም ተንጠራርተህ የተጋረደብህን ግርዶሽ…ብትመለከት በዚህ ምድር ከፀሐይ የሚበልጡ ሚሊዮን ፀሐዮችን ታያለህ አለች። [አጽንዖት የእኔ]
>
> (ጌታቸው ፣1982፣219)

ሠናይት እናቱን እንዲወድ የምትመክረው ለእናቱ አስባ ሳይሆን ለራሷ ነው። የፋለስ እጦቷን ከድጋፌነህ ማግኘት ትፈልጋለች። ድጋፌነህ የ**ሌ**ላ እጦት አለበት። **ሌ**ላ የምትባል ማን ናት? **ሌ**ላ**ሌ**ላዋም በሚል የምትገባዋ ራሷ ናት። ስትጽፍ፣ክራር ስትመታ እኔም አደንቅሃለሁ፣እሷን እርሳት ማለቷ ነው። በዚህም የድጋፌነህ የ**ሌ**ላ እጦቱ ምትክ መሆን እንደምትችል

እያረጋገጠችለት ነው፡፡ ‹‹ዐይንህን ተጋርዶብህ የዚህን ዓለም ውብነት ልታየው አልቻልክም›› ማለቷም እሷን እንዲያያት ስለፈለገች ነው፡፡

ሦስተኛዋ ድጋፌነህን የሰደበችው ሴት ስሟ አልተገለፀም፡፡ ድጋፌነህ አስፋው ከተባለው ጓደኛው ቤት ሲጠጣ አመሸ፡፡ ከዚያም ማንነቷን ከማያውቃት ሴት ጋር አደረ፡፡ ይህች ሴት ቆንጆ እና ከእኔ በላይ ቆንጆ በአዲስ አበባ የለም የምትል ናት፡፡ ተቻኮለች፡፡ ሰክሮ ስለነበር እሷ ሱሪ እና ጫማውን አወለቀችለት፡፡ እሱ ግን ምንም ማድረግ አልቻለም፡፡ ከዚያም ‹‹ወራዳ ነህ! ፣ብስብስ ነህ!፣ የማትረባ ነህ!...›› በማለት ሰድባው ሄደች፡፡

> ...የእኔ ጌታ ቶሎ አውልቅ...*ጉልበት ከዳው ...ስካር*...ጫማውን ለመፍታት ሲታገል ከመቅጽበት *ከአልጋው ወርዳ አወላለቀችለት፡፡* ብርድ ልብስ ለብሰው በሞቀ ስሜት *ከላይ ሆና* ትስመው ጀመር፡፡ እሷ ላብ በላብ *ሆነች*...እሱ ግን *ማንኮራፋት ጀመረ ዋ!* አለች...ወሽመጧ ቁርጥ አለባት፡፡ የእሷም ስሜት ቀስ በቀስ ቀዘቀዘ...እንዳነባች አደረች...በገነች... እንዴት ቢንቀኝ ነው አለች፡፡ *ሱሪውን እንዴት እዳወለቀችለት ታወሳት* ‹‹ይህ ወራዳ›› አለች በየደቂቃው ሰዓቷን ስትመለከት ቆይታ 11፡30 ሲሆን ልብሷን ለባበሰች...ቀሰቀሰችው፡፡ ትኩር ብሎ ተመለከታት *ብስብስ ነህ! የማትረባ ነህ!...* አለችው አልተናገረም ሊናገራት ሞከረ ጂኑ ግን *አፉን አኮላሽቶታል ጥላው ምራቋን ጢቅ* ብላበት ሄደች፡፡
>
> [አጽንዖት የእኔ]
>
> (ጌታቸው ፣1982፣ 220-221)

ይህች ሴት በድጋፌነህ ላይ የስድብ ውርጅብኝ የማውረዷ ምክንያት ‹‹ወንድ›› *መሆን* ስላልቻለ እና በምናባዊ ዓለም የገነባችውን ጁዊሶንስ ገቢራዊ ስላላደረገላት ፋለስ የለውም በሚል ንቃው ነው፡፡ በሌላ ‹*‹የምትመጻደቅበት*›› ውበት ምንም እንደሆነ ስላሳያት የተናቀች *መሥሏት* ነው፡፡ እንደ ልጅነቱ ‹‹ሱሪውን እና ጫማውን አውልቃለታለች፣እንደ ልጅነቱ ጡት አጥብታዋለች፣ ተቆጥታዋለች፡፡ ይህም ድጋፌነህ *ንጥቀ-ፋለስ* እንደተካሄደበት አመላካች ሲሆን፣ሲያንኮራፋ ያደረም ለዚህ ነው፡፡ ስለሆነም የድጋፌነህ የተኮላሸበት አፋ ሳይሆን ‹‹ፋለሱ›› ነው፡፡

ድጋፌነህ በስካር መንፈስ ስለነበር ስድቧ ምንም አልመሰለውም ነበር፡፡ እየቆየ ግን ረብሾታል፡፡ ይቅርታ መጠየቅ ፈልጓል፡፡ ከዚያም ወደ ፀሐይ ትዝታ እና ወደ አባቱ ክራር አምርቷል፡፡

> ...አንገበገበው ሊያገኛት አልቻለም ትዝታ መአዛዋ፣ጠረኗ፤ ጥላው ከሄደች በኋላ *ማሪኝ አይላት ነገር ሄዳለች፤ቁጭት* ቆንጆ ነበረች ቅብዝብዝ ምን ዋጋ አለው! አለ እየተንገዳገደ በረጅሙ ተነፈሰ...፡፡ ድርሰቱን አወጣና አነበበ ፀሐይ ድቅን አለችበት፡፡ የእኔ ጌታ እራስህ ነህ የጻፍከው ስትለው ቻው የለም! የለም! አለና በስካር አንጎሉ ቀዳደደው...ደስ አለው...ፈገግ ብሎ ቀና ሲል የአባቱ ክራር

> *በሩቅ የሽረሪት ድር አድርቶበት ታየው፡፡… አትፍራኝ… ና … ምታኝ… አንጎራጉርብኝ…መተከዣ ልሁንህ እያለ ጠራው … ሊያነሳው ሲሞክር ወንበር አደናቀፈው፣…ከሁሉም ዘፋኞች የበለጠ የአንተ ዘፈን ደስ ይለኛል የሚል ድምጽ ተሰማው… እንደምንም ተንጠራርቶ አነሳው ጥቀርሻው ቢጃማው ላይ ወደቀበት አንስቶ ከመሬት ጣለው…፡፡ [አጽንዖት የእኔ]*
> (ጌታቸው ፣1982፣221)

*ድጋፌነህ የማታዋን ሴት ይቅርታ መጠየቅ የፈለገው እንዳታዋርደው ፈርቶ ነው፡፡ የትእምርታዊ አባት ጣልቃ ገብነት እና የአባቱን ክራር ለማንሳት የፈራበት ምክንያት ደግሞ የአባቱን ቃል የሻረ እና ወንድነቱን የተነጠቀ ስለመሰለው ነው፡፡ ድጋፌነህ ይህች ሴት ንጥቀ-ፋለስ ያካሄደችበት ቢመስለውም፣ለፀሐይ ፋለስ እንዳለው አስመስክሯል፡፡ ወደ ፀሐይ ትውስታ የሚዘልቀው ለዚህ ነው፡፡ በሌላ ፀሐይ ይህን ጉዳይ እንዳትሰማበት ፈርቶ ነው፡፡*

ሌላው ከዚህ ጋር አብሮ ሊታይ የሚችለው አረጋሽ የምትተርከው እና ከድጋፌነህ ጋር ያሳለፈችው ሌሊት ነው፡፡ ከአረጋሽ ጋር አብሮ ማደር የፈለገ ወንድ ሲጋብዛት አመሸ፡፡ አብረው አደሩ፡፡ ያደረችበትን ገንዘብ ስትጠይቀው እምቢ አላት፡፡ ሰደባት፡፡ ከዚያም ቀስ ብላ በመነሳት ለባበሰች እና እሷን ሊያቅፍ የፈታውን ሱሪ እና የአንድ እግር ጫማውን ይዛበት ሄደች፡፡

> …ስካሩ እንዳልለቀቀው ሳውቅ *ሱሪውን እና የአንድ እግር ጫማውን* ይዤው ሄድኩኝ፡፡ ጧት 2፡00 ሰዓት ላይ የእኛ ሀብታም፣የእኛ ጌታ 10፡00 ብሩን፣ሰው *መሣይ* በሽንጎ አትሁን ብዬ ሊስትሮ ላኩበት ሰድቦ አባረራቸው፡፡ እንግዲሁ *ሱሪህን እና ጫማህን የእኔ ወንድም የእገሌ ሱሪ ገኸ* እያልኩ አደባባይ ወጥቼ እንዳታፍር ብዬ በድጋሚ ላኩበት፡፡ ሊስትሮዎቹን ለምኖ ለእነሱ ገንዘብ ሰጥቶ 10 ብሩን 20 ብር አድርጎ ላከልኝ፡፡ ከት ብላ ስቃ ስታበቃ እጇ ላይ ያለውን *የመስቀል ንቅሳት በጣቷ ምራቋን አስነክታ ጠረግ* አደረገችው፡፡ [አጽንዖት የእኔ]፡፡ ጌታቸው፣234)

አረጋሽ *ሱሪህን እሸጠዋለሁ* ስትለው ለምን ፈራ? ለምንስ ከተጠየቀው በላይ ብር ላከ? ሱሪ የወንድነት ኃይል እና *ሱሪው* ከወለቀ *ፋለሱን እንደተነጠቀ* ስለሚቆጠር ነው፡፡ በማሕበራዊ ሕጉም ሱሪ ከወለቀ እንደ ወንድ አይቆጠርም፡፡ አረጋሽ ባደረገችው ድርጊት ተጸጽታለች፡፡ እንዲደመሰስላት ትፈልጋለች፡፡ ወይም በመስቀል ቅርጽ የተቀረጸውን ንቅሳት አልፈለገችውም፡፡ ‹‹የመስቀል ንቅሳቷን በጣቷ ምራቋን አስነክታ የጠራረገች›› ለዚህ ነው፡፡

ድጋፌነህ ፀሐይን ለመርሳት ሲጠጣ አመሸ፡፡ ከዚያም ከአረጋሽ ጋር አደረ፡፡ ድጋፌነህ ሰክሮ ስለነበር እሷ ኃያል ሆነች፡፡ ሁሉም ነገር በእሷ ቁጥጥር ሆነ፡፡ በኋላም ወደ መረታት ደረጃ ስለደረሰ ገልብጧት ሄደ፡፡

*…የድጋፌነህን እጅ እየደባበሰች፣በምሬት ስትራገም ስታጉረመርም* ብንን አለ፡፡ የተኛበት ክፍል ሁኔታን ተመለከተ፡፡
*‹‹ምነው ተኛ እንዲ የእኔ ገላ ገና እኮ ነው፡፡ እምቢ አለህ እንዴ እንቅልፍ ››* አለችው
*…እግሮቿን አንስታ በእግሮቹ መሀል አሳልፋ አስገባችው ትንሽ ቆይታ መላ ሰውነቷን ሰውነቱ ላይ አውጥታ እሱ ከሥር እሷ ከላይ* ግንባሩን ጉንጩን ትስመው ጀመር፣ሰውነቱን ነዘረው ከስሜቱ *ጋር* ትግል ጀመረ፡፡ ትንፋሽ እየበዛ ዳሰሳዋ እየጨመረ ሄዶ እሱም *ወደ መረታቱ ደረጃ* ደረሰ፡፡…እንዴት እንደገለበጣት አያውቅም ገልብጧት ተነስቶ ልብሱን ለባበሰ፣ደነገጠች፡፡…ሃያ ብር አውጥቶ ሰጣት፡፡ ‹‹ምነው ሌሊት ነው እኮ›› አለችው የሰጣት ገንዘብ *ንዴቷን ሁሉ አበረደው…፡፡* [አጽንዖት የእኔ]
(ጌታቸው ፣1982፣240- 241)

*አረጋሽ* በምሬት የተራገመች እና *ያጉረመረመች* ከድ*ጋ*ፌነህ ፋለስ ስላጣች ነው፡፡ *አረጋሽ ‹‹የእኔ ገላ ገና እኮ ነው››* ያለች ስሜቷን ነው፡፡ *‹‹እምቢ አለህ እንዴ›› ያለችውም* እንቅልፉን ሳይሆን ፋለሱን ነው፡፡ ‹‹እግሮቿን አንስታ በእግሮቹ *መሃል አሳልፋ ያስገባችም››* ፋለሱ *መኖር* አለመኖሩን ለማረጋገጥ እና በራሷ *መንገድ* ጁዊሶንስ *ለማግኘት ሙከራ እያደረገች* ነው፡፡ *‹‹እሷ ከላይ እሱ ከሥር መሆኑም›› ኃይሉን መነጠቁን* እና *ፋሎ-ሴንተሪዝም* በአረጋሽ በኩል *መሆኑን* የሚገልጽ ነው፡፡ ድ*ጋ*ፌነህ ‹‹ከስሜቱ *ጋር* ትግል›› *ያደረገ* አሸንፋለሁ ወይስ እሸነፋለሁ በሚል *ራሱን* እየፈተነ ነው፡፡ ፀሐይን *እያስታወሰ* ልፈጽም፣ አልፈጽም በሚል *እየተምታታ* ነው፡፡ *ከመረታት ደረጃ ያደረሰው* ምንድን ነው? *መረታትንስ* ምን አመጣው? በፍጥነት ገልብጧት እንዲነሳ *ያደረገው* ነገር ምንድን ነው? የአረ*ጋ*ሽ አሳሳም እና ሌላው ተግባሯ *ኃያል* ስለሆነበት ነው፡፡ በምሽት *የመጣችው* ሴትን ስድብ አስታውሶ ነው፡፡ በቅጽበት ገልብጧት የተነሳ ተሸናፊ እንደሚሆን ስለተረዳ ነው፡፡ አረ*ጋ*ሽ የነገረችውን *ታሪክ* ከዚሁ *ጋር* አያይዞ ሳልዋረድ ላምልጥ በሚል ነው፡፡ ወጥቶ አድሮ ስለማያውቅ የሚያስጨንቅ ምናባዊ ስሜት ተፈጥሮበት ይሆናል፡፡ የአረ*ጋ*ሽ ፍላጎት ከፋለስ በተጓዳኝ ገንዘብ ነው፡፡ ‹‹ገንዘብ ሲሰጣት ንዴቷ የበረደላት›› ለዚህ ነው፡፡

ዮዲት በውሸት ዶ\ር ነኝ ብሎ በተዋወቃት *መ*ስፍን ውበት እና አለባበስ ተማርካለች፡፡ በሁለተኛው ቀን ስልክ ደወለችለት፡፡ ተቀጣጠሩ፡፡ ከዚያም ዮዲት ‹‹እንዴት እድለኛ ነኝ›› አለች ስለባሻ ማሰብ ተወች ክፋታቸው ብቻ ወለል ብሎ *ታያት*…የኑሮ ትርጉም የማይገባው›› አለች (ጌታቸው፣1982፣41)፡፡ ዮዲት *ራሷን* እንደ እድለኛ የቆጠረች የፋለስ ፍላጎቷን በምናባዊ ዓለም

ስላሟላች ነው። ለዮዲት ኑሮ ማለት ፋለስ ነው። በአባቷ የሚደርስባትን የፋለስ ክልከላ አልወደደችውም።

ዮዲትና መስፍን በቀጠሯቸው መሠረት ብሔራዊ ቴኣትር ተገናኙ። ወደሚፈልገው ሥፍራ ወሰዳት። ወደ አንድ ክፍል ይዟት ሲገባ ተደናገጠች። ካለፍላጎቷ መጠጥ እንድትጠጣ አደረገ። የቅድመ ወሲብ ዝግጅት አደረጉ። ከዚያም የሚፈለገው ሆነ፣እሷ ወደ አክስቷ ቤት፣እሱ ወደ ውቤ በረሃ ሰፈር ሄደ።

> ‹‹እኔ እኮ ›› ብላ ያሠበችውን ሳትጨርስ ንግግሯን ዋጠችው ።…
> ‹‹…ሰውነቷ እየተፍታታ እየሞቃት ሄደ ስትናገር *አፏን ያዝ ያደርጋ* ጀመር።
> …ገላው ከገላዋ ሲነካካ ይብሱኑ የት? እንዳለች ማወቅ ተሳናት…የውስጥ ሱሪዋን አውልቆ ጣለው። ከዛ በኋላ የሆነውን እሷም አታውቅ…ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነብሷን እያወቀች መጣች።
> …በቀጥታ የሄደችው ሽሮ ሜዳ አክስቷ ጋር ነው። እሷን አድርሶ *ስሜቱ በሚገባ ስላልበረደለት ስሜቱን ለማብረድ ወደ ውቤ በረሃ* ሲከንፍ ሄደ። [አጽንዖት የእኔ]
> (ጌታቸው ፣1982፣45)

ዮዲት *‹‹እኔ እኮ››* ብላ በጅምር የተወችው ‹‹ድንግል ነኝ!›› ለማለት ፈልጋ ነው። ይሁን እንጂ ዮዲት ኃይሏን አጣች። ‹‹ልጅነቷን›› ተነጠቀች። ‹‹ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነብሷን እያወቀች መጣች›› የሚለው ጁዊሶንስ አቅልን እንደሚያሳጣ የሚገልጽ ነው። Lacan, እንደሚሉት ‹‹የኤዲፐስ ሦስትዮሽ የትእምርታዊ አባት ጣልቃ ገብነት ይስተዋላል። በዚህም ጊዜ የትእምርታዊ አባት ቅጣትን በመፍራት እናት የኢ-ንቁ ልቦና ትእምርታዊ ሌላ የፍላጎት አካል ትሆናለች›› (Ellmann,1994, 22)። ዮዲት ወደ ቤቷ መሄድ ያልፈለገች አረማመዷን አይተው አባቷ እንዳይደበድቧት ስለፈራች ነው። አክስቷ በእናት ቦታ የምትገባ ከጥቃት የምትታደግ ምትክ ፍላጎቷ ናት። Lacan, እንደሚሉት ‹‹በጁዊሶንስ የሚገኝ እርካታ ለጊዜው ከፍተኛ ቢሆንም በሒደት ይቀንሳል›› (Leitch, B. Vincent, 2001, 303)። መስፍን ወደ ውቤ በረሃ ሰፈር የሄደ እየቆየ ሲሄድ እርካታው ስለቀነሰበት ሌላ ‹‹ጁዊሶንስ›› ፈልጎ ነው። ከጀማሪ እና ልምድ ካላቸው ሴቶች የሚገኝ ጁዊሶንስ ስለሚለያይ ነው። ሳይሄድ ከቀረ የምትቀየመው ሴት ስላለች እና ስላደረገው ነገር የሚነግራቸው ስላሉ ነው።

ዮዲት ከመስፍን ጋር ከተደሰተች ወዲህ ጸባይ ነስቷታል። የአባቷን ቁጥጥር አልወደደችም። ትቆጣለች። እናቷ ሲመክሯት፡- ‹‹…አያገባሽም ዕድሜዬ ነው›› ትላቸዋለች (ጌታቸው ፣1982፣

46)፡፡ Lacan, እንደሚሉት ‹‹የፋለስ ትርጓሜ ምልዑ ነው፡፡ የተጨቆኑ ስሜቶች ፍጹም በሆነ የመኮላሼት ፍርሃት ቤተሰብ አካል ጉዳተኛ እንዳደረጋቸው በማሠብ እንደ ባላንጣ ይቆጥራሉ›› (Ellmann,1994, 22)፡፡ ዮዲት የምትበሳጨው በመጠጥ ኃይል ድንግልናዋን በመስጠቷ ተቆጭታ እና ድንግልናዋን መስጠቷ ምልዑ ያልሆነ ምሥል ፈጥሮባት ነው፡፡ ድንግልናዋን መስጠቷን ቤተሰቦቿ የሚያውቁባት መሥኂት ነው፡፡ ምክራቸውን እና ቁጥጥራቸውን ባለመቀበሏ ተጸጽታ ነው፡፡ ዮዲት ዕድሜዬ ነው ማለቷ ለአቅመ-ፋለስ መድረሷን ለመግለጽ ነው፡፡

ዮዲት መስፍን ዶክተር እንዳልሆነ ብታውቅም ምንም አልመሰላትም፡፡ የእሷ ፍቅር ከፍ ሲል፣ የእሱ ግን ቀንሷል፡፡ ስትደውልለት ጥሩ ነገር አያናግራትም፡፡ ዮዲት እውነቱን ተናግራ ራሷን እንደምታጠፋ ስትነግረው ፈራ፡፡ ከዚያም ተቀጣጥረው ተገናኙ፡፡

> …አሮጌ ኦፔል መኪና ይዞ ቀድሞ ይጠብቃት ነበር፡፡ ሲገናኙ …በፈገግታ ነበር የተቀበላት፡፡…ልቧም የተስፋ ብርሃን ፈነጠቀበት፡፡ ወጣት…ተምራ ትምህርቷን ጨርሳ ቢቻል ቤተሰቦቿን ለመርዳት ያም ባይሆን ራሷን ችላ ልትኖር የምትችል ለግላጋ ወጣት *እድሏ ተኮላሼ*…ለስላሳ አዘዘች፡፡…መስፍን ግን ውስኪውን ይጠጣል ከተወያዩና ከተጨቃጨቁ በኋላ እንባዋን ጠራርጋ ስሜቷን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ሥር አውላ ስታበቃ…፡፡ (ጌታቸው ፣1982፣47-48)

ዮዲት ፍላጎቴ ይሳካል የሚል ተስፋ ስለነበራት *ፋንታዚ* በሆነ ፈገግታው ተደስታለች፡፡ መኪናውን ለምን ቀየረ? ከቀጠሮ ሥፍራውስ ለምን ቀድሞ ተገኘ? አሮጌ መኪና የያዘ የተቀጠፈች አበባ ስለሆነች ነው፡፡ ቀደሞ የተገኘ ደግሞ ለማባበል እና ሚስጢሩ እንዳይዘረገፍበት ስለፈለገ ነው፡፡ እድሏን አኮላሼባት የተባለውም *ድንግልናዋን* ነው፡፡ ለስላሳ መጠጣቷ ቀድሞውን ለስላሳ ጠጥቼ ቢሆን ኖሮ ከዚህ አሮንቋ አልዘፈቅም ነበር በሚል ጸጸት ነው፡፡ መስፍን ውስኪ የጠጣ ያቺን ቀን እንድታስታውስ እና እንድትበሳጭ ፈልጎ ነው፡፡

ዮዲት እንደጸነሰች በመግለጽ እንዲያገባት ጠየቀችው፡፡ መስፍን ባለዕዳ እንደሆነ እና እንደሚታሠር ነገራት፡፡ ተቆጣች፡፡ ተጸጸተች፡፡ ከዚያም ብር እና የታሸገ ፖስታ ሰጥቶ ወደ ናዝሬት ሸኛት፡፡

‹‹*ታዲያ ምን ሁኝ ነው የምትለኝ፡፡ እንደ ጓደኞቼ ሳልሆን ትምህርቴን አቋርጬ ባለዲቃላ ሆኜ እንድኖር ነው የምትፈልገው፡፡ …አንቺ ገንዘብ የምታገኝ ከሆንሽ ተማርሽ አልተማርሽ ምን ሊበጅሽ ነው? ይልቅ ናዝሬት ትሄጅና አንድ ቡና ቤት ትቀጠሪያለሽ ዓመት ሳይሞላሽ ባለመኪና ነው የምትሆኚ፡፡*
‹‹*ምን ሽርሙጥና! እኔ! ዛሬውኑ ብሞት ይሻለኛል! ››*
‹‹*ሽርሙጥና አይደለም! አንቺ አንቺነትሽን ታውቂዋለሽ…፡፡አንቺ እኔን ሆነሽ ትቀመጭያለሽ ራስሽን ትጠብቂያለሽ ችግሬ እስኪቃለል ድረስ ነው፡፡ በየጊዜው እየመጣሁ እጠይቅሻለሁ ነጻ ከሆንኩ እንጋባለን እስኪሆን ግን መደበቂያሽ እዚያው ይሆናል፡፡ ወ\ሮ ማንያህልሻል ቤት ይህን ደብዳቤ ይዘሽ ትሄጅያለሽ እንዳይቸግርሽ ሁለት ሺህ ብር ያውልሽ ›› ብሎ አንድ ፖስታ እና የታሰረ ብር እጇ ላይ አስቀመጠላት፡፡ አመነችው ‹‹ገንዘብ በገንዘብ ሆነሽ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ከብረሽ እኔና አንቺ የሞቀ ትዳራችንን እንደምንመሠርት አትጠራጠሪ፡፡*
*ገንዘቡን እና ፖስታውን እንደያዘች ተከዘች፡ አፍንጫው ላይ ልትወረውርለት ፈለገች ዝምታዋን ሲመለከት ጨነቀው፡፡ ‹‹እኔ እኮ እንደምወድሽ ለምን አትረጅኝም እንደሌላ ወንድ እኮ አላውቅሽም ብዬ መሄድ እችላለሁ፡፡ ግን እወድሻለሁ ልተውሽ አልችልም ለዚህ ነው›› ሲላት አመነቺው አውቶቢስ ተራ ድረስ ወስዶ አሳፈራት፡፡* [አጽንዖት የእኔ]
(ጌታቸው ፤1982፤48-49)

Lacan, እንደሚሉት ‹‹ጁዊሶንስ ለጊዜው ከፍተኛ ደስታ ቢያስገኝም እየቆየ ሲሄድ ለጸጸት፣ ለባይተዋርነት፣ለበሽታ፣ራስን ለማጥፋት፣ለበቀል፣ለእጦት፣ለስቃይ እና ለናፍቆት ይዳርጋል›› (Green,K, and Lebihan,J,1996,174)፡፡ የዮዲት *ታሪክ*ም ከዚህ ጽንሰ-ሐሳብ *ጋ*ር የሚሠምር ነው፡፡ ዮዲት ማኅበረ-ባህላዊ ሕግ ይስተዋልባታል፡፡ ‹‹ሽርሙጥና እና ዲቃላ›› የሚሉ ቃላትን ደጋግማ መጠቀሟ ለዚህ ነው፡፡ ዮዲት ወደ ናዝሬት የሄደች በቤተሰቦቿ እና በእሷ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ነቀፌታ ለመሸሽ ነው፡፡ ስሕተት ስትፈጽም መቆየቷን ተረድታለች፡፡ ‹‹እንደ ጓደኞቼ ሳልሆን ትምህርቴን አቋርጬ›› ማለቷም ለዚህ ነው፡፡ መስፍን እንደሌላ ወንድ ያለ በኢ-ንቁ ልቦናው የሚያስበው ሐሳብ *በምላስ ወለምታ* በገሃድ ወጥቶበት ነው፡፡ ፖስታው ስለዮዲት ማንነት የሚገልጽ ሲሆን፣ወ\ሮ ማንያህሎት ተቀባዮዋ ናት፡፡ በመሆኑም ዮዲትን የፋለስ ፍላጎቷ ከቤት ገፍትሮ አስወጥቶ በሌላ ንጽረተ ዓለም እና ከቤተሰቦቿ ተለይታ እንድትኖር እንዲሁም በታሪኩ መጨረሻ ላይ ለአእምሮ ሕመም ለመዳረግ ምክንያት ሆኗል፡፡

# ምዕራፍ አራት፡- ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ‹‹ፍላጎት *በቃል ኪዳን ረጅም* ልቦለድ ውስጥ፤ከLacanian, የፍካሬ-ልቦና ትችት አንጻር›› በሚል ርእስ የተካሄደ ነው፡፡ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች የቀደምት ጥናቶች ሂሳዊ ክፍተት መኖሩ እና በአገራችን የሥነ-ጽሑፋዊ ትችት አንጻር የLacanian, የፍካሬ-ልቦና ትችትን በመፈከሪያነት በማዋል ረገድ ክፍተት መኖሩ የሚሉት ናቸው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ *ቃል ኪዳን* (1982 ዓ.ም.) በተባለው ረጅም ልቦለድ ውስጥ የዋና ገጸ-ባህርያትን ፍላጎቶችን እና የፍላጎት ምንጮችን ማሳየት የሚል ነበር፡፡ የጥናቱ ትኩረት የተመረጠውን ልቦለድ ከLacanian, የፍላጎት ጽንሰ-ሃሳብ ፍላጎት፣የመስታወት ደረጃ (ባይተዋርነት) እና ፋለስ አንጻር መተንተን ሲሆን፣እነዚህም ከፍላጎት ጋር ያላቸው ተዛምዶ ተብራርቷል፡፡

በምዕራፍ ሦስት ሥር ከቀረበው ትንተና መረዳት እንደሚቻለው ከፍላጎት ትንተና አንጻር የልቦለዱ ዋና ገጸ-ባህርያት የማደግ እና ቤተሰብ የመርዳት፣በትጋት የመማር፣የማፍቀር፣የመጠጥ፣ሥራ የመያዝ፣የገንዘብ፣የበቀል፣የመደሰት፣የተሻለ ኑሮ የመኖር፣የእኔነት፣ያለፈን አሁን ላይ የመፈለግ፣የዝና፣የጁዊሶንስ፣የመሞት፣ትዳር የመመስረት እና ልጅ የመውለድ ወ.ዘ.ተ ኢ-ንቁ ፍላጎቶች እና ተያያዥነት ያላቸው የLacanian, ፍካሬ-ልቦናዊ ጽንሰ-ሐሳቦች ተተንትነዋል፡፡ ሌላው የገጸ-ባህርያት ኢ-ንቁ ፍላጎቶች አለመሟላት ፍርሃትን፣ጭንቀትን እና ስቃይን እንደሚያስከትሉ ተብራርቷል፡፡

‹‹በመስታወት ደረጃ (ባይተዋርነት)›› ጽንሰ-ሐሳብ ፍላጎት እንዴት ወደ ባይተዋርነት እንደሚያመራ የተተነተነበት ነው፡፡ ‹‹በፋለስ›› ጽንሰ-ሐሳብ ውስጥ ጁዊሶንስ፣ፋሎ-ሴንተሪዝም እና ሳይኮ-ፓቶሎጂ የሚሉ ጭብጦች ራሳቸውን ችለው ሳይሆን እንደ አስፈላጊነቱ ከፋለስ ጋር በተዛመደ መልኩ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ፋለስ በምናባዊ እና በትእምርታዊ፣ጁዊሶንስ ደግሞ በፋንታዚ፣በምናባዊ እና በትእምርታዊ ሥርዓቶች ተገልጿል፡፡ ፋሎ-ሴንተሪዝም ለማኅበረ-ባህላዊ ሕግ ተገዥ ሲሆን፣ማእከሉን ሲቀያይር ይታያል፡፡ የገጸ-ባህርያት እጦት ለፓቶሎጂ እንደዳረጋቸውም በትንተናው ተመላክቷል፡፡

በልቦለዱ ዋና ገጸ-ባህርያቶች ወ\ሮ እታፈራሁ፣ድጋፌነህ ይስማሸዋ፣ፀሐይ አሰፋ፣መስፍን ሞልቶለት፣ጥጉ ይልማ እና ሠናይት ናቸው፡፡ ወ\ሮ እታፈራሁ የድጋፌነህ እናት ያልተማሩ፣ሩህሩህ፣ዐይናቸው የሞጨሞጨ፣ፊታቸው የተጨማደደ፣አዛውንት፣የቀን ሥራ በመሥራት የሚተዳደሩ፣ልጃቸው ጥሩ ደረጃ እንዲደርስላቸው የሚጥሩ፣መልካም ባህርይ እና ከጎረቤት ጋር

ጥሩ ቀረቤታ ያላቸው፣በታሪኩ ሒደት ልጃቸው ኑሯቸውን የለወጠላቸው ናቸው። ሆኖም በኋላ ላይ ልጃቸው ባሳየው የመጥፎ ስሜት ለውጥ ሥነ-ልቦናዊ እና አካላዊ ስቃይ የደረሰባቸው፣ እንዲሁም ራሳቸውን የማጥፋት ሙከራ እንዳደረጉ ተተንትኗል።

ድጋፌነህ ይስማሸዋ በልቦለዱ ታሪክ ውስጥ ያለው ሚና አቀንቃኝ እና ሠናይ ገጸ-ባህርይ ሲሆን የፍቅር ታሪኩ በዋናነት የሚያጠነጥነው በእሱ ዙርያ ነው። አባቱ ያስገቡትን ቃል ለመተግበር ትምህርቱን በትጋት የሚማር፣ጓደኝነቱ ከመጽሐፍ እና ደብተር ጋር የሆነ፣እንደ ልጆች መጫዎት የማይወድ፣እናቱን አድጎ መርዳት የሚፈልግ፣ወጣት፣የተከበረ፣የተማረ፣ፍቅረኛ ያለው፣ከተራ ሠራተኝነት የድርጅቱ ኃላፊ ለመሆን የበቃ፣መጀመሪያ መልካም ሰብእና፣ቀጥሎ መጥፎ ባህርይ የተጣባው፣ከዚያም ወደ ቀደመ ማንነቱ ሲለወጥ ይታያል። ፀሐይን በማጣቱ ሥነ-ልቦናዊ ጭንቀት፣ፍርሃት፣ስቃይ ታይቶበታል። ይህም ገጸ-ባህርያት ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት እንዲለዋወጥ አድርጓል። ለዚህም ድጋፌነህ በቅድሚያ ስለራሱ አብዝቶ የሚናገረው እኔ ጀግና ነኝ!፣እኔ ኩሩ ነኝ!፣እኔ ማንንም አልለማመጥም!፣እኔ አፍቃሪ እና ተፈቃሪ ነኝ! በማለት በራሱ ይመጻደቃል። ከዚያም እኔ ምንም አይደለሁም!፣እኔ ምንም አላውቅም!፣እኔ ምንም የለኝም!፣እኔ ማንም የለኝም!፣እኔ አልፈቀርም!፣እኔ ምንም አይገባኝም!፣እኔ ማንንም አላሸንፍም! ፣እኔ ማንንም አልፈልግም!፣በሚል ራሱን ምንም (ባዶ) ያደርጋል። ይህም በSarterian, ‹‹ምንም›› (*nothing*) ይባላል።

ድጋፌነህ በሦስት ሴቶች የደረሰበት የስድብ ውርጅብኝ ፋለሱን እንደተነጠቀ እንዲያስብ አድርጎታል። ለመሰደቡ ዋና ምክንያት የሆነው ፍላጎታቸውን ማሟላት አለመቻሉ ነው። በዚህም ኢ-ንቁ ፍላጎታቸው ያልተሳካላቸው ሴቶች ማለትም፡- ‹‹ድንጋይ ነህ!›› በፀሐይ፣‹‹ደመ-ቀዝቃዛ ነህ!›› በሠናይት፣‹‹ወንድ ነህ! ፣ብስብስ ነህ!›› በምሽት በመጣችው ሴት የደረሱበት የስድብ ቃላቶች ሲሆኑ ‹‹ወንድነትን የሚፈታተኑ›› እና በኢ-ንቁ ልቦናው እያስታወሰ እንቅልፍ የነሱት ቃላቶች ናቸው።

ፀሐይ አሰፋ ወጣት፣መልከኛ፣የስለት ልጅ፣በብዙ ወንዶች ተፈላጊ፣የሴት ጓደኛ የሌላት፣ የሀብታም ልጅ፣መልካም አሳቢ፣ባልሆነ ሁኔታ ለሚመጣባት ቁጡ፣በሀሳቧ የጸናች፣መልካም ባህርይ ያላት፣በፀሐፊነት ሙያ የተሰማራች፣ድንግልናዋን ለድጋፌነህ ያበረከተችለት፣ከድጋፌነህ ጋር ተጋብታ መኖር የምትፈልግ ናት። ፀሐይ መጀመሪያ በኢ-ንቁ ልቦናዋ ድጋፌነህ የፍቅር ቃል ማውጣት ባለመቻሉ የፍቅር መግለጫ ጽጌረዳ አበባ ያበረከተችለት፣ ሲሆን በታሪኩ ሒደት ግን የአበባው ትርጓሜው ተለውጧል። ፀሐይ መጀመሪያ ፍቅራቸው ‹‹እንደ ሮሚዎ እና

ጁልየት እንዲሁም እንደ ፍቅር እስከ መቃብር›› እንዲሆን እንደፈለገችው ሁሉ የሁለቱ ፍቅር ትራጀዲያዊ በሆነ መልኩ፣በሞት፣በእጦት እና በስቃይ ይቋጫል፡፡ እነዚህን ጉዳዮችንም በትንተናው ለማየት ተሞክሯል፡፡

መስፍን ሞልቶለት ወጣት፣በቁንጅናው የሚመጻደቅ፣ለትምህርት ሁለት ጊዜ ውጭ አገር ተልኮ ውጤታማ ባለመሆኑ የተመለሰ፣የሀብታም ልጅ፣የውበት መጨመሪያ ጌጣጌጥ የሚጠቀም፣ከብዙ ሴቶች ጋር የሚዳራ፣ሁሉን ነገር በገንዘብ ለማሟላት የሚሞክር ሲሆን መስፍን የአባቱን ሀብት ንብረት ለመውረስ እና ፀሐይን ለራሱ ለማድረግ መፈለጉ ከማይወጣበት ስቃይ ጨምሮታል፡፡ ሠናይት ወጣት፣መልከኛ፣በአስተዳደጓ ከደረሰባት በደል የተነሳ ወንዶችን የምትበቀል ስትሆን በታሪኩ መጨረሻ የሰብእና ለውጥ በማድረግ ድጋፌነህን ታፈቅረዋለች፡፡

ጥጉ ይልማ መልከ ጥፉ፣ጎልማሳ፣ባለትዳር እና ልጆች ያሉት፣ጠጪ፣አጫሽ፣ቆማሪ፣ገንዘብ ለማግኘት ሲል የመስፍን ፍላጎት ማስፈፀሚያ የሆነ፣ለገንዘብ ብሎ ሰዎችን የሚበቀል፣ቅንነት የጎደለው፣ክፉ፣ቀብቃባ በመሆኑ ማህበራዊ መገለል የደረሰበት ነው፡፡ ጥጉ እና ዮዲት የተባሉት ገጸ-ባህርያቶች የአእምሮ ሕመም የደረሰባቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ለሁለቱም የአእምሮ ሕመም ምክንያት መስፍን ነው፡፡ ዮዲትን በመስፍን መከዳቷ እና ከቤተሰብ መለየቷ ምክንያት ሲሆን፣ ጥጉ ደግሞ ፍላጎቱን ለማሟላት እየፈረመ ከመስፍን የተቀበለው ብር ባለዕዳ ሆኖ፣ከሥራ መፈናቀሉ፣መኪና እና ቤቱ በሐራጅ መሸጡ፣ሚስቱን እና ልጆቹን በማጣቱ ነው፡፡

የልቦለዱ ገጸ-ባህርያት በፍላጎታቸው አለመርካት ይስተዋልባቸዋል፡፡ ለዚህም ድጋፌነህን እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል፡፡ በቅድሚያ ትልቅ መሆንን እና ቤተሰብ ማገዝን ይፈልጋል፡፡ ካደገ በኋላ ሥራ ይፈልጋል፡፡ ፈልጎ የተሳካለትን እንደምንም ይቆጥርና ሌላ ይፈልጋል፡፡ ፍላጎቱ በትጋት መማር ነበር፡፡ ከዚያም በፀሐይ ፍቅር ተነደፈ፡፡ እንደገና ሌላ ፍላጎት ከፀሐይ ጋር በስቃይ መካከል ሆነው ‹‹ልጅነታቸውን›› ተለጋገሱ፡፡ እንደገና ሌላ ፍላጎት ፍቅራቸውን በቃል ኪዳን አሰሩ፡፡ እንደገና ሌላ ፍላጎት ትዳር መስርተው ልጅ ወልደው መሳም ፈለጉ፡፡ እንደገና ሌላ ፍላጎት ሦስት ጉልቻ ለመመስረት የቤት ዕቃ ማሟላት እና ጥሩ ቤት መከራየት ፈለገ፡፡ ፀሐይ ሰርጋን እውን ለማድረግ እቁብ መግባት ፈለገች፡፡ እንደገና ሌላ ፍላጎት ያቋረጠውን ትምህርት መቀጠል ፈለገ እንዳሰበው ሳይሆን ቀረ መሆኑ በትንተናው ተመላክቷል፡፡

ከLacanian, የፍላጎት እና እጦት ሐሳብ ጋር በተያያዘ የቋንቋ አጠቃቀም ለፍላጎት መሟላት እና ለእጦት ምክንያት ሲሆን በጉልህ ተስተውሏል፡፡ ይኸም ልቦለዱ ከLacanian, ምናባዊ፣

ትእምርታዊ እና እውናዊ ሥርዓቶች፣እንዲሁም በሲግኒፋየር እና ሲግኒፋይድ፣በሜታፊር እና ሜታኖሚን ከማሳየት አንጻር ጉልህ ሚና ያለው ነው። ፍላጎት የሚሟላ ሳይሆን በእጦት የሚስተዋል መሆኑን ከገጸ-ባህርያቱ መረዳት ይቻላል። ገጸ-ባህርያት ራስ-ወዳድነት የተጠናወታቸው በመሆናቸው፣የእኔ ይሟላ እንጂ የሌላው ግድ የለኝም በሚል ስሜት በሌሎች ላይ ይረማመዳሉ። ይበቀላሉ። በዚህም ሴላነት ይስተዋላል። ገጸ-ባህርያት ፍላጎታቸውን ለማሟላት የመረጡት መንገድ አላዋጣቸው ሲል እና ውድቀት ሲያጋጥማቸው የማንነት ለውጥ ሲያደርጉ ይስተዋላሉ። ለዚህም የእነ-ጥጉ፣ሠናይት፣ድጋፌነህ እና ፀሐይ የማንነት ለውጥ ታሪክ ምሳሌ ይሆናል። የፍላጎት አለመሟላት ‹‹ፓቶሎጂ›› ያስከትላል። ይህንም የጥጉ፣ የመስፍን፣የድጋፌነህ፣የእናቱ፣የፀሐይ እና የዮዲት ታሪክ ይጠቁማል። የሴቶች ፍላጎት በአባዊነት ማኅበረ-ባህላዊ ሕግ ተጽእኖ ሥር የወደቀ መሆኑን የጥናቱ ግኝት ያመላክታል።

Rawson and Nisbet, (2008) ኢ-ንቁ የሆነ ፍላጎት እጦት በሕልም\በቅዥት፣በትረካ፣በምላስ ወለምት፣በቀልድ እና በቁጣ ገሃድ ይወጣል (175):: እንደሚሉት ሁሉ ድጋፌነህ፣ፀሐይ፣ጥጉ እና ዮዲት የተባሉ ገጸ-ባህርያቶች ኢ-ንቁ እጦት ፍላጎታቸውን በሕልም፤በቅዥት፣በምላስ ወለምታ፤ በጽሑፍ (በስድስት ግጥም፣በስምንት ደብዳቤ) በቁጣና ወ.ዘ.ተ.ሲገልጹ እና ሲያሚሉ ተመልክቷል።

Lacan, ቴክስት የፋለስ ፍላጎት እና እጦት ውጤት ሲሆን፣የቴክስት የመጨረሻ ውጤት ውድቀት ነው ይላሉ (Rawson and Nisbet,2008, 187)። በመሆኑም የልቦለዱ ገጸ-ባህርያት የመጨረሻ ዕጣ ፈንታቸው ውድቀት እና እጦት ሆኗል። የልቦለዱ ታሪክ ‹‹በምን ዋጋ አለው!›› ጀምሮ ‹‹በምን ዋጋ አለው!›› እንደተቋጨ ትንተናው ያሳያል። በሁሉም ገጸ-ባህርያት ፍላጎት ላይ ‹‹ባዶነት›› የተስተዋለ ሲሆን፣ይህም የሰው ልጆች በዕለት ከዕለት ሕይወታቸው ፍላጎትን ለማሟላት የሚያደርጉት ጥረት በስቃይ፣በእጦት እና በውድቀት የተሞላ መሆኑን የሚያመላክት ነው። ስለሆነም የጌታቸው አያልቄ ቃል ኪዳን ረጅም ልቦለድ፣በላቀ የገጸ-ባህርያት ፍላጎት፣ ማንነትና ድርጊት፣እንዲሁም በአሳዛኝ ሁኔታዎች የተዋቀረ የአንባቢያንን ስሜት የመግዛት አቅሙ ከፍ ያለ ልቦለድ ቢሆንም፣በተደጋጋሚ የመታተሙን ያህል የሥነ-ጽሑፋዊ ትችት ብርሃንን የተነፈገ ነው። ይህም ለተለያዩ የሥነ-ጽሑፋዊ የትችት አንጻሮች ክፍት እንደሆነ አመላካች ነው። ሆኖም ይህ ልቦለድ ወደፊት በLacanian-አንስታይ እና ዲ-ኮንስትራክሽን ፣ እንዲሁም በሌሎች የትችት አንጻሮች ሊጠና ቢችል የተለያዩ ግኝቶች ሊገኙ እንደሚችሉ ይታመናል።

## ዋቢ ጽሑፎች

### ፩) ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች

ወዳጄነህ መሐረነ፡፡ (2011 ዓ.ም.)፡፡ *ክልሷ ሳይኪ*፡፡ *www.africaprinting.com.*

ጌታቸው አያልቄ፡፡(2006 ዓ.ም.)፡፡*ቃል-ኪዳን* (6ኛ እትም)፡፡አዲስ አበባ፣ማንኩሳ ማተሚያ ቤት፡፡

### ፪) ካልዓይ የመረጃ ምንጮች

ሰብለ ወልደኪዳን፡፡ (2009ዓ.ም)፡፡ ‹‹የእኔነት ሐተታ በተመረጡ የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች›› የሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ፣የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ቴዎድሮስ አለበል፡፡ (2006)፡፡ ‹‹ልጅነት *በማሕሌትና በአለንጋና ምስር* ፡ *ሥነ*-ልቦናዊ ንባብ›› የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ፣የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

እዮኤል እንደሻው፡፡ (2010)፡፡ ‹‹ድብቅ ባህሪያትና የተጨቆኑ ፍላጎቶች *ሥነ*-ልቦናዊ ንባብ *በቅበላ* ረጅም ልቦለድ›› የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፤ባሕር ዳር፣ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡(1993)፡፡ *አማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

American Psychological Association. (2015). A Guide to the APA Referencing Style: Publication manual of the American Psychological Association (6th ed.). Washington, Dc: Author.

Bailly,Lionel. (2009). Lacan A Beginner‘s Guide. Great Britain: Publications, One World Oxford Print.

Barry, P. (2002). *Beginning Theory: An Introduction to Literary and Cultural Theory (2nd ed.*). Chennai : Manchester University Press.

Bennett, Andrew., & Nicholas, Royle. (2004). *An Introduction to Literature, Criticism and Theory* (3rd ed.). London: Longman.

Bertens, H. (2001). *Literary Theory: The Basics*. London: Routledge.

Bowie, M.(1990). *Freud,Proust and Lacan:Theory as Fiction.* London:Cambridge University Press.

Castle, G. (2007). *The Blackwell Guide to Literary Theory.* USA: Black well publishing Ltd Print.

Childs,P.,& Roger, F.(2006).*The Routledge Dictionary of Literary Terms(3 rd ed.).* London and New York: Routledge and Kegan Paul Ltd.

Ellmann,M. (Ed.).(1994).*Psycho-Analytic Literary Criticism*. London and New York: Longman Singapore Publishers (pte) Ltd Print.

Fink, B. (1997). *A Clinical Introduction to Lacanian Psycho-analysis: Theory and Technique*. Harvard University Press.

Foucault, M. (1976). *Mental illness and Psychology.* Alan, Sherida, (Trans.), University of California Press.

Fry, Paul. H.,(2012).*Theory of Literature*. New Haven and London:Yale University Press.

Gardiner, Raleigh M., (2014).‹‹Desire and Fantasy: The Conditions of Reality Between the Self and the Other.›› Master of Fine Arts Thesis,Sam Fox School of Art and Design,Washington University in Saint Louis.

Gokariksel, Banu., & Anna, Secor.,(2014).*The Veil, Desire,and the Gaze: Turning The Inside Out*. Geography Faculty Publication, 3,http:// Unknowledge. uky.edu\geography Fac pub\3,V,40,no.1,177-200.http\\dx.doi.org\10.1086\676897.University of Chicago.

Green, K., & Jill, L.(1996).*Critical Theory and Practice* : *A Course Book.London* and New York: Routledge, Tayler and Francis Group.

Guerin,W, et al., (1999). *A Hand book of Critical Approaches to Literature*. New York: Oxford University Press, Print.

Hill, P.(1997). *Lacan for Beginners.*Chennai: Orient Longman Pvt. Lyd Print.

Jafferson et al.,(1986). *Modern Literary Theory: A Comparative Introduction.* London: Batsford Print.

Klages, M.(2011). *Literary Theory: A Guide for the Perplexed* (3rd ed.). Great Britain: Manchester Printed, Continuum International Publishing Group.

Klarer, M.(1999). An *Introduction to Literary Studies*. London and New York: Routledge,Taylor and Francis Group.

Komorowski, Jennifer., (2017).‹‹The Voice as an Object of Desire in the work of Ann Quin›› Master of Arts Thesis, The University of Western Ontain.

Lacan, J.,Jacques, A., James, H.,(1977). *Desire and The Interpretation of Desire in Hamlet.*Yale French Studies, No.55\56. Literature and Psychoanalysis. The Question of Reading: Otherwise.PP.11-52. Yale University Press.http \\www.Jstor.org Thu Feb 1 07:22 2oo7.

Lacan,J.(1977a). *Ecrits:A Selection*. A,Sheridan, (Trans.),New York: W.W.Norton.

-------------(1977b).*The Four Fundamental Concepts of Psychoanalysis*. Allan, Sheridan, (Trans.), New York: W.W. Norton.

-----------(1988 a). *The Seminar of Jacques Lacan, Book I : Freud's Papers. On Technique 1953-1954*. J. A. Miller & J. Forrester, (Eds. and Trans.), New York and London: W.W. Norton.

-----------(1988 b). *The Seminar of Jacques Lacan, Book II : The ego in Freud' s Theory and in the Technique of Psychoanalysis 1954-1955.* J.A. Miller and S.Tomaselli,(Eds.and Trans.),New York And London: W.W. Norton.

----------(2007).*The Seminar of Jacques, Lacan Book XVII Psychoanalysis, 1969-1970*. Du Seuil, Paris (Ed.). (1991).English Translation (2007).by W.W. Noton and Company, Inc.

Leitch, B. Vincent., (Ed.). (2001).*The Norton Anthology of Theory and Criticism.* University of Oklahama, USA: W.W. Norton and Company, Inc.

Lewis, J., & Ritchie,J. (Eds.). (2003).*Qualitative Research Practice*. London: Sage Publications.

Matsumoto, D. (Ed.). (2001). *The Hand Book of Culture and Psychology*. London and New York: Oxford University Press Inc.

Miller, J. P., & Richardson, W. J. (1982).*Lacan and Language A Reader's Guide to Ecrits*. New York, NY: International Universities Press.

Parker, I.(2014). *Psychology after the Unconscious*. New York and London: Routledge.

Rawson,C.,& Nisbet, H.B.(Ed.).(2008).*The Cambridge History of Literary Criticism Volume 9: Twentieth Century Historical, Philosophical and Psychological Perspectives.* USA: New York, Cambridge University Press.

Sarup, M.(1993). *Introductory Guide to Post-Structuralism and Post-Modernism* (2nd ed.). New York, London: Harvester WheastSheaf, Simon and Schuster International Group.

Singh, C, Sheel.(1998).*Theory of Literature*. New Delhi:Anomol Publications Print.

Tyson, L. (2006). *Critical Theory Today: A User-Friendly Guide* (2nd ed.). USA: Routledge,Taylor and Francis Group.

Vanheule S and Paul Verhaeghe.,(2009). ‹‹Identity Through A Psychoanalytic Looking Glass.›› *Theory & Psychology* Vol.19 (3) :391-411. http:\\ tap. Sagepub.Com.Uk\Journals.

Wellek, R and Austin, Warren., (1949).*Theory of Literature*. New York: Harcourt, Brace and Company Inc.

Wolfreys,J.,(2001).*Introducing Literary Theories: A Guide and Glossary*.Edinburgh: Edinburgh University Press Ltd Print.

Wolfreys,et al., (2006). *Key Concepts in Literary Theory* (2nd ed.). Edinburgh: Edinburgh University Press Ltd Print.

## አባሪ ፡- የልቦለዱ አጽመ ታሪክ

የጌታቸው አያልቄ *ቃል ኪዳን* (1982 [2006] ዓ.ም.) ረጅም ልቦለድ የጊዜ እና የቦታ መቼቱን በ1960ዎቹ ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ የመሠረተ ልቦለድ ነው፡፡ ልቦለዱ ከሮማንስ ንኡስ ዘውግ የሚቦደን ሲሆን፣መቋጫው ትራጀዲ ነው፡፡ የልቦለዱ ታሪክ በዋናነት ድጋፌነህ እና ፀሐይ በተባሉት ገጸ-ባህርያቶች የፍቅር ታሪክ ዙርያ የሚያጠነጥን ነው፡፡ ይህ ልቦለድ በጥብቅ ሴራ የተዋቀረ ሲሆን፣አቀንቃኝና ተቀናቃኝ ገጸ-ባህርያት በዋናነት በውስጣዊ (ከራስ ጋር በመጋጨት) የተጠመዱ ናቸው፡፡ ይህ ረጅም ልቦለድ ተውኔታዊ ነው፡፡ የልቦለዱ ዋና ገጸ-ባህርያት ስድስት ሲሆኑ፣እነሱም፡- ድጋፌነህ ይስማሸዋ፣ ወ\ሮ እታፈራሁ፣ፀሐይ አሰፋ፣ መስፍን ሞልቶለት፣ ሠናይት እና ጥጉ ይልማ ናቸው፡፡ ከንኡሳን ገጸ-ባህርያት መካከል ደግሞ አባ ውቃው፣ዮዲት፣ ወ\ሮ ዘለቃ፣አቶ አሰፋ ወ\ሰንበት፣መምሬ ዘነበ፣አቶ ሞልቶለት፣ባንቺዳሩ፣ የእነ-መስፍን ሠራተኛ ፣የፀሐይ አክስት፣አስፋው፣ራሄል፣አረጋሽ፣ሁሴን እና ዓይናለም ይጠቀሳሉ፡፡

ወ\ሮ እታፈራሁ የድጋፌነህ እናት፣ዓይናለም እና ሁሴን ባልና ሚስት ሲሆኑ፣የድጋፌነህ መልካም ጓደኞቹ ናቸው፡፡ ድጋፌነህ እና ፀሐይ በቅድሚያ በክፍል ጓደኝነት፣ከዚያም የአፍቃሪ ተፈቃሪ ግንኙነትን ፈጥረዋል፡፡ ሠናይት የሥራ ባልደረባው ስትሆን በታሪኩ ሒደት ከጠላትነት ወደ አፍቃሪነት ትሸጋገራለች፡፡ ወ\ሮ ዘለቃ የፀሐይ እናት ሲሆኑ፣በዘመኑ ማኅበረ-ባህላዊ ሕግ ላይ በማመጽ በራሳቸው ምርጫ ያገቡ ናቸው፡፡ አቶ ሞልቶለት እና አቶ አሰፋ ወ\ሰንበት ለጓደኝነታቸው ማሰሪያ ገና በሕጻንነት ዕድሜያቸው ፀሐይን ለመስፍን ልጅህን ለልጄ በሚል ቃል የተግባቡ ናቸው፡፡ ዮዲት በመስፍን ተታላ ድንግልናዋን የሰጠች እና ራሷን አደጋ ላይ የጣለች ናት፡፡ ጥጉ ይልማ የድጋፌነህ ኃላፊ ሲሆን፣ለገንዘብ እና ኑሮውን ለመቀየር፣ ራሄል የፀሐይ የሥራ ባልደረባ ስትሆን የአፍቃሪ ተፈቃሪ ግንኙነትን ጠል በመሆኗ፣ ድጋፌነህን ከፀሐይ በመለየት ለመስፍን በረከትነት ለማዋል ያለመ እኩይ ተግባር ያገናኛቸው ናቸው፡፡

ልቦለዱ በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡ ክፍል አንድ (ከገጽ 1-151)፣የገጸ-ባህርያት ግንኙነት፣ ድርጊት፣ባህርይ፣ኢ-ንቁ ፍላጎቶች በአወንታ የተስተዋለበት ሲሆን፣በክፍል ሁለት (152-280)፣ ሴራው የጎለበተበት፣መለየት፣ፍርሃት፣ጭንቀት፣ስጋት፣በቀል፣የግንኙነት እና የድርጊት ለውጥ (በአሉታ)፣የአእምሮ ሕመም እና ሞት የተስተዋለበት ነው፡፡ የታሪኩ መጀመሪያ፣መካከለኛ እና መጨረሻ ክፍልም ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

አባ ውቃው ግርግር እና ጩኸት በማይለየው መንደር አዳፋ ድሪቶ ለብሶ፣የነተበ ጋቢውን መሬት ለመሬት እየጎተተ ‹‹ምን ዋጋ አለው!›› በማለት ዘራፍ እያለ ይወጣል፡፡ የመንደሩ ሕጻናትም እየጮኹ እና ልብሱን ወደ ጭንቅላቱ እየወረወሩ ሲከተሉት፣ራሱን ‹‹ዘረ-ቢስ›› በማለት ወደ ሰማይ አንጋጦ መፈከሩን ይቀጥላል፡፡

አቶ ይስማሸዋ በሞት ስለተለዩ ወ\ሮ እታፈራሁ ባላቸው የልጃቸው ክርስትና እለት ልጃቸው እንዲሆንላቸው ሲመኙት የነበረውን አስታውሰው ያለቅሳሉ፡፡ ድጋፌነህ እንዳያለቅሱ ሲቆጣቸው ፣እንዲዝናና ብር ይሰጡት እና ከቤቱ ይወጣል፡፡ ከሦስት ቀን በኋላ ስለሚወስደው የዩኒቨርሲቲ መመረቂያ ፈተና እያሰበ ወደ ቤቱ ሲመለስ በድንገት የመኪና አደጋ ደርሶበት ወደ ሆስፒታል ይገባል፡፡ እናቱ በመቅረቱ ተጨንቀው ሲያለቅሱ እና ሲጮኹ፣የመንደሩ ወንዶች ለመፈለግ ይሄዳሉ፡፡ ከብዙ ፍለጋ በኋላ ሆስፒታል ገብቶ ስላገኙት፣እናቱን በጠዋቱ ይወስዷቸዋል፡፡ ፀሐይ፣ሁሴን እና ዓይናለም እየተመላለሱ ይጠይቁታል፡፡ ከስድስት ሳምንት በኋላ ወደ ቤቱ እንደተመለሰም ሥራ አፈላልጎ ይይዛል፡፡ ከዚያም በፀሐይ ግፊት ለሰርጋቸው ቅድመ-ዝግጅት እያደረጉ እያለ አንድ አስደንጋጭ ክስተት ይፈጠራል፡፡

ወ\ሮ ዘለቃ እና አቶ አሰፋ በትዳር ሲኖሩ፣በተደጋጋሚ ሴት ልጅ ወልደው ሁለት ዓመት ሲሆናቸው ይሞቱባቸዋል፡፡ ከዚያም በስለት እና በፀሎት ሴት ልጅ ወለዱ፣ስሟንም ፀሐይ አሏት፡፡ አቶ አሰፋ ከአቶ ሞልቶለት ጋር ላላቸው ጓደኝነት ማሰሪያ ያለ እናቷ ፈቃድ ፀሐይ በሕጻንነቷ ለመስፍን ታጨች፡፡ በኋላም አቶ ሞልቶለት ልጃቸው ሀብታቸውን ከሴቶች ጋር እየተዳራ በማባከኑ፣በተግባቡት ቃል ኪዳን መሠረት እጮኛማቾችን ለማስተዋወቅ ቀን ይቆርጣሉ፡፡ ይህንም ለፀሐይ ሲነግሯት ራሷን ትስታለች፡፡ ሌላ እጮኛ እንዳላት በመናገር አላገባም ትላለች፡፡ አባቷ ተበሳጭተው እመነኩሳለሁ ይላሉ፡፡ እናቷ ግን በብልሃት ይመክሯት እና ከመስፍን ጋር በማስመሰል እንድትቀጥል  ያደርጓታል፡፡

መስፍን ድጋፌነህን በጥጉ፣ፀሐይን በራሄል አማካኝነት ለማለያየት ብዙ ሙከራ አድርገዋል፡፡ ፀሐይ ለድጋፌነህ ስትደውልለት ጥጉ አንስቶ፣ድጋፌነህ እንደጠላት እና ሀብታም ሴት እንዳገባ ነገራት፡፡ ራሄል ደግሞ ድጋፌነህ ሲደውል አንስታ ፀሐይ ከመስፍን ጋር እየተቃበጠች እንደሆነ ነገረችው፡፡ የውሸት ደብዳቤም ላኩላቸው፡፡ በዚህም የስሜት ለውጥ ተስተዋለባቸው፡፡

ወ\ሮ እታፈራሁ ልጃቸው ወጥቶ ስላደረ፣እየጮኹ ሲፈልጉት፣እግራቸው ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ ስለተጎዱ የሁሴን ሚስት ልትወልድ ከገባችበት ሆስፒታል ይገባሉ፡፡ ከዚያም ሁሴን ከቤታቸው

አድርሷቸው ይመስሳል። የልጃቸው አለመምጣት ጭንቀት እና ፍርሃትን ስለፈጠረባቸው ራሳቸውን በቢላዋ ለማጥፋት ኑዛዜ እያደረጉ እያሉ፤ድጋፌነህ በሌሊት ወደ ቤቱ ሲመጣ፣በሩ ተከፍቶ እና ቤቱ ጭር ብሎ በማየቱ ስለተደናገጠ፣ራሱን ለማነቅ ገመድ በአንገቱ አስሮ ለፀሐይ ፎቶ-ግራፍ፣ለእናቱ እና ለሠናይት ይቅርታ እና ወቀሴታ በማቅረብ ላይ እያለ፣‹‹እናቱ ድምጽ›› ሰምተው ሲሄዱ ልጃቸው ታንቆ ያገኙታል። ከዚያም ወደ ላይ ከፍ በማድረግ ገመዱን በቢላዋ ለመቁረጥ እየተፍተረተሩ እያለ፣ሁሴን ደርሶ ገመዱን በቢላዋው ቆርጦ ከሞት ይታደገዋል። ድጋፌነህ የተፈጠረውን ሁሉ ነገር ለሁሴን ከነገረው በኋላም ራሱን እንደጥፋተኛ በመቁጠር አልኮል መጠጣት እና ማምሸቱን ይተዋል።

ፀሐይ አዘውትራ ታለቅሳለች። ሁሴን እና ዓይናለምን አግኝታ ስለተፈጠረው ሁሉ ነገር መናገር ብትፈልግም፣ ሁሴን ምራቁን ጢቅ ብሎባት ይሄዳል። ከዚያም እውነታውን የሚገልጽ ደብዳቤ ጽፋ ለድጋፌነህ እና ለዓይናለም ከላከች በኋላ፣የድጋፌነህን ፎቶ-ግራፍ ወቅሳ እና ቤተሰቦቿን ተሰናብታ በመኪና ትገጫለች። ድጋፌነህ እና ዓይናለም ደብዳቤውን እንዳነበቡ ተደናግጠው ወደ ሆስፒታል ያመራሉ። ፀሐይ ለመናገር ተስኗት እያቃተተች ድጋፌነህን ስታየው፣በአንድ በኩል አለመሞትን፣በሌላ መልኩ ‹‹ከመቃብሬ ላይ አበባ አስቀምጥልኝ›› አለችው። ከዚያም ለዚህ የዳረጓቸው ጥጉ እና መስፍን እንደሆኑ ስትነግረው፣ ለበቀል ይፈልጋቸዋል።

መስፍን የጥጉ ቤት እና መኪና በሐራጅ እንዲሸጥ ካደረገ በኋላ ወደ ሌላ አካባቢ ይጠፋል። በዚህም ጥጉ ለአእምሮ ሕመም ተዳርጎ በየመጠጥ ቤቱ እየተዘዋወረ ‹‹ሥራ ለሠሪው›› በማለት ራሱን ይጠላል። ከብዙ ፍለጋ በኋላ ድጋፌነህ ወደ አንድ ጠጅ ቤት ይገባል። ከዚያም ጥጉ ድጋፌነህን እንዳየው እየፈራ ተጠግቶ ጥፋተኛ እሱ ሳይሆን መስፍን መሆኑን በመንገር ይቅርታ ይጠይቀዋል። ድጋፌነህ ‹‹አንተማ ሳትሞት የሞትህ ነህ›› በማለት መስፍንን መፈለግ ይወጣል። በኋላም ከእነ-መስፍን ቤት ሲደርስ፣ፀጉሯን ያንጨበረረች አንድ የአእምሮ ሕመምተኛ (ዮዲት) በር እየደበደበች ልጄን በማለት ትጮኸለች። አቶ ሞልቶለት ልጃቸው ውርደት አከናንቧቸው እንደጠፋ ይነግሯቸዋል።

ድጋፌነህ ወደ ሆስፒታል ሲመለስ ፀሐይ ሞታለች። አባቷም በድንጋጤ ይሞታል። ድጋፌነህ የመቃብር አፈር ጨብጦ እያለቀሰ መስፍንን ለመበቀል ቃል ሲገባ፣ሁሴን፣ሠናይት እና እናቱ ይመጣሉ። እናቱ እግሩ ሥር ወድቀው ማንም እንደሌላቸው እያለቀሱ ሲማጸኑት፣‹‹ምን ዋጋ አለው! የተወጋ ልብ ይገኝ›› መስፍንን ሳልበቀልላት አልመለስም፤ቢልም ደግፈው ይዘውት ሲሄዱ ታሪኩ ይደመደማል።